# አ

**አ ከ"ኘ "** ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**አረ** 1.ለማጋነን የሚባል። *አረ ጉድ ፈላ!* 2.መገረምን ለመግለፅ የሚባል። *አረ! የሚገርም ነው።* 3.ለመጠየቅ ወይም ለማረጋገጥ የሚባል። *አረ? እውነትህን ነው?* 4.ለመለመን፥ እባክህ ለማለት ከሌላ ቃል ጋር በመጣመር የሚባል። *አረ እባክህ ስጠኝ።* 5.ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ወይም አንድን ነገር በርትተህ፥ ጠንክረህ አድርግ ለማለት ከሌላ ቃል ጋር ተጣምሮ የሚባል። *አረ ተው ሂድ/ አረ አጥና።*

**ኡ** የ"አ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ኡሁ**

**ኡሁ አለ** ግ ባለ።

**ኡኡ**

**ኡኡታ** ስ ጩሀት፥ እሪታ።

**ኡኡ አለ** ግ እሪ አለ፥ ጮሀ።

**ኡደት "አወደ$^{2}$"** ስር ተመ.

**ኢ** የ"አ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ኢ—** የአፍራሽነት ትርጉም ይዞ ከሌላ ቃል ጋር የሚገባ እስር ምእላድ። *ኢሳይንሳዊ /ኢሰብአዊ*፡

**ኢላማ "አለመ$^{2}$"** ስር ተመ.

**ኢማማ** ስ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚያደርጉት የራስ ጥምጥም።

**ኢማም** ስ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር፤ የፀሎት መሪ።

**ኢምንት** ስ 1.በጣም ትንሽ፥ ቅንጣት። 2. የተናቀ፥ ከቁጥር የማይገባ።

**ኢምፔሪያሊዝም** ስ ግዛት በማስፋፋትና በሌላው አገር ላይ ተፅእኖ በማድረግ ወይም አገሮችን በቅኝ ግዛትነት በመያዝ መርሆ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ እምነት።

**ኢርቱእ ተሳቢ "ርቱእ"** ስር ተመ.

**ኢሰብአዊ "ሰብ (ሰብእ)"** ስር ተመ.

**ኢሳይንሳዊ "ሳይንስ"** ስር ተመ.

**ኢንሱሊን** ስ ከእንስሳት ቆሽት የሚዘጋጅና ለስኳር ህሙማን የሚሰጥ መድሃኒት።

**ኢንሳይክሎፒዲያ** ስ በሁሉም የእውቀት ዘርፎች ወይም በአንድ በተወሰነ የሙያ መስክ ያሉ ፅንሰ ሃሳቦችን በፊደል ተራ መዝግቦ ሰፋ ባለ ሁኔታ አብራርቶ የሚገልፅ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ጥራዞች ያሉት መፅሃፍ።

**ኢንስቲትዩት** ስ ተቋም።

**ኢንሹ** ስ መልኩ ከወደላይ ጠቆር ያለ ግራጫ ሆኖ ከወደሆዱ ነጭ የሆነ፥ ረጅምና ከወደጫፉ ቀልመም ያለ አፍንጫና ቀጭን አንገት ያለው፥ እሾሃማ ቁጥቋጦዎች ባሉበት ቆላማ ስፍራዎች የሚገኝ፥ ሳርና ቅጠላ ቅጠል የሚመገብ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ኢንሹራንስ** ስ 1.መድን፤ በቋሚነት በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ በማስከፈል ደንበኞቹ የሞት፥ የአካል መጉደል፥ የቤት ንብረት መዘረፍ፥ መቃጠል፥... ሲያጋጥማቸው በደንቡ መሰረት ገንዘብ በመክፈል ወይም የጠፋውን፥ የተበላሸውን ንብረት በመተካት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት። 2. ከላይ በተራ ቁጥር አንድ በተጠቀሰው መሰረት ለደንበኛው ድርጅቱ የሚሰጠው ዋስትና ወይም አደጋው በአጋጠመው ጊዜ የሚሰጠው የገንዘብ ወይም የንብረት ክፍያ።

**ኢንሹራንስ አለው** ከኢንሹራንስ ወይም ከመድን ድርጅት የሚሰጠው ዋስትና አለው።

**ኢንሹራንስ ገባ** የኢንሹራንስ ወይም የመድን ድርጅት በሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን በየወሩ ክፍያ እየከፈለ ደንበኛ ሆነ።

**ኢንቶ (እንቶ)** ስ እንጉዳይ የሚመስልና ቁመቱ ከእንጉዳይ ከፍ የሚል፥ መልኩ ነጣ ያለና ተጠብሶ የሚበላ ተክል።

**ኢንዱስትሪ** ስ 1.የፋብሪካዎችና ትላልቅ የምርት ድርጅቶች አጠቃላይ መጠሪያ። 2. በአንድ አይነት ዘርፍ ብዙውን ጊዜ በርካታ ሰዎችን በማሳተፍና የማሽን መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚካሄድ ስራ።

**የኢንዱስትሪ ውጤት** ስ ከኢንዱስትሪ የተገኘ ምርት።

**ኢንጂነር** ስ መሃንዲስ።

**ኢኮኖሚ** ስ 1.የአንድ ሃገር የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ስርአት። 2.ቁጠባ። *ኑሮውን በኢኮኖሚ መምራት መቻል አለበት።*

**የኢኮኖሚ ቀውስ** ስ የስርአተ ኢኮኖሚ መዛባት።

**ኢኮኖሚስት** ስ በኢኮኖሚክስ ሳይንስ የሰለጠነ ባለሙያ።

**ኢኮኖሚክስ** ስ የአንድን አገር ሃብት አመራረትና አጠቃቀም የሚያጠና የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ።

**ኢኳቶር** ስ በምድር ወገብ ላይ ያለ የሃሳብ መስመር፤ የምድር ሰቅ።

**ኢየሱስ [ክርስቶስ]** ስ መድሃኒት፥ አዳኝ፤ ከሶስቱ ስላሴዎች አንዱ የሆነው እግዚአብሄር ወልድ።

**—ኢያ "—ያ"ን** ተመ.

**ኢዮቤልዩ** ስ አንድን ትልቅ ድርጊት ወይም ሁኔታ ለማስታወስ በየሃያ አምስት አመት የሚከበር በአል። *የወርቅ ኢዮቤልዩ /የብር ኢዮቤልዩ።*

**ኢዮሃ አበባዬ (እዮሃ አበባዬ)** ስ የመስቀል ዋዜማ እለት ችቦ ሲያበሩ ወይም ችቦውን ይዘው ደመራውን ሲዞሩ የሚዘፍኑት ዘፈን።

**ኢድ አል አድሃ** ስ ነቢዩ ኢብራሂም ከአላህ በታዘዘው መሰረት ልጁን እስማኤልን ለመሰዋት ሲዘጋጅ በምትኩ አላህ ከሰማይ በግ ያወረደበትንና በጉ ^ታረደበትን ቀን ለማዘከር ሙስሊሞች በየአመቱ የሚያከብሩት የበአል ቀን፤ አረፋ።

**ኢድ አልፈጥር** ስ በሙስሊሞች ዘንድ የሚከበር የፆም ፍቺ በአል።

**አ¹ የ"አ"** ፊደል ራብእ ዘር።

**አ²**

**አ በል** አፍህን ክፈት።

**አ አለ** አፉን ከፈተ።

**አ-** 1.አድራጊነትንና አደራራጊነትን ለመግለፅ ከሌላ ግስ ጋር የሚገባ እስር ምእላድ። *አበላ/ አጠጣ/ አመጣ*። 2. በ"አ" ለማይጀምሩ ግሶች የባቢ ዘር መነሻ። *አበላል/ አጠጣጥ።*

**አሁን** ተው.ግ. 1.በዚሁ ቅፅበት። 2.በዚህ ሰአት፥ ጊዜ፥ ወቅት፤ ዘንድሮ። 3.ከጥቂት ጊዜ በፊት። *ሲጠብቅህ ቆይቶ አሁን ነው የሄደው*። 4.ከጥቂት ጊዜ በሗላ። *ትንሽ ጠብቃት፤ አሁን ትመጣለች*። 5.እስኪ። *አሁን እንዲህ ማድረጉ ለምንድን ነው?*

**በአሁን ጊዜ** ተው.ግ. በዛሬው ጊዜ፥ ዘመን፥ ወቅት።

**አሁኑኑ** ተው.ግ. በዚሁ ሰአት ውስጥ፥ ቶሎ፥ ወዲያው። *አሁኑኑ እመለሳለሁ።*

**አሁን በአሁን** ተው.ግ በዚሁ ሰአት ውስጥ፥ በፍጥነት፥ ወዲያውኑ። *አሁን በአሁን ሰረቀው።*

**አሁንለት (አሁን ለታ)** ተው.ግ ከጥቂት ቀናት በፊት።

**አሁንም** እንደገና፥ በድጋሚ።

**አሁንም ቢሆን** በዚህ ጊዜም፥ ወቅትም፥ ሁኔታም፥ ምክንያትም ቢሆን።

**ከአሁን ቀደም** ተው.ግ. ከዚህ ቀደም፥ ከአሁን በፊት።

**ከአሁን [ከ] አሁን** ተው.ግ. በቅርብ ጊዜ፥ ትንሽ ቆይቶ፥ አሁን። *ከአሁን አሁን ይመጣል ብሎ ሲጠብቀው ቀረ።*

**የአሁን ጊዜ** ስ (ሰዋ.) ድርጊቱ አሁን እየተከናወነ ያለ መሆኑን የሚገልፅ የግስ ቅርፅ።

**አሂዶ "ሄደ"** ስር ተመ.

**አሃ!** 1.አንድ ነገር ጠፍቶ ወይም ተረስቶ ቆይቶ በሗላ ሲገኝ ወይም ትዝ ሲል የሚባል። 2.አንድን ነገር አሁን ተረዳሁት፥ ገባኝ ለማለት የሚያገለግል አባባል። *አሃ! ለዚህ ነው ፊቱን ያጠቆረብኝ።*

**አሃዝ** ስ ቁጥር፥ የቁጥር ምልክት (1፥ 2፥ ወይም ፩፥ ፪፥... )።

**አሃዱ** ስ አንድ። *አሃዱ ብሎ ስራውን የጀመረው በዚህ ወር ነው።*

**አሄሄ (ሄሄ)!** መገረምን፥ መደነቅን፥ ማዘንን፥ መቆጨትን፥ ዛቻን ለመግለፅ የሚነገር አባባል።

**አህዛብ** ስ ሃይማኖት የለሽ፥ በጣኦት የሚያመልክ ህዝብ።

**አህያ** ስ 1.በአቋም ከፈረስና ከበቅሎ የሚያንስ፥ ለጭነት የሚያገለግል የጋማ ከብት። ቅ 2.(ስድብ) ደደብ፥ የማይገባው(ስእሉን የቤት እንሳስ ስር ተመ.)።

**የአህያ ሆድ ሲመስል (ሰማይ)** ሊነጋ አካባቢ።

**የአህያ ኪንታሮት** ስ 1.በፊንጢጣ ላይ የሚወጣ ቁስል። 2. በውስጥ እግር ላይ የሚወጣና ለመርገጥ የሚያውክ ቁስል።

**የአህያ ውሃ ጠጪ** የፈለገውን ነገር ቀስ ብሎ ሳይታወቅበት የሚያደርግ።

**አህጉር** ስ ክፍለ አለም።

**አሆ** ስ በሆታ ጊዜ አውራጁን ተከትለው ተቀባዮች የሚሉት የሆታ ዜማ።

**አሆሌ "አኮሌ"** ን ተመ.

**አሆማ (ሆማ)** ስ የዛፍ አይነት።

**አለ** ግ 1.ተናገረ። 2.መልእክቱን፥ ሃሳቡን አስተላለፈ። 3. መታ። *በጥፊና በእርግጫ አለው።*

**ማለት** ስ የአንድን ነገር ትርጉም፥ ምንነት ለማስረዳት ወይም ነገሩን ሲገልፁ ቆይቶ ሃሳብ ለመጨመርና ይበልጥ ለማብራራት ሲፈለግ የሚባል ቃል። *አገር ማለት ህዝብ ነው/ለመወያየት ማለት ሃሳብ ለሃሳብ ለመለዋወጥ ...።*

**ስትለው** ለሶስተኛ ሰው እንዲተላለፍ የተፈለገን ነገር ለመልክተኛው እንዲህ ብለህ ንገረው ለማለት የሚባል ቃል። *በቀለን ስትለው ነገ ከቤትህ እመጣለሁና ጠብቀኝ በለው።*

**እንደምትለው** ስትለው።

**እንዳለ** እንደፈለገ፥ እንዳዘዘ። *እሱ እንዳለ ይደረጋል።*

**በል** (የ "አለ" ትእዛዝ አንቀፅ) 1.ተናገር። 2.አድርግ፥ ፈፅም። *በል ብላ / በል ሂድ።*

**በለው** 1.ንገረው፥ አሰማው። 2.ምታው፥ ደብድበው።

**በል ሲለው** ሲያሰኘው።

**በል በል አለው** አሰኘው፥ ገፋፋው፥ አድርግ አድርግ የሚል ስሜት አነሳሳው።
**ቢልልኝ** ቢሆንልኝ፥ ቢሳካልኝ ኖሮ።
**አልኩ ባይ** የማይፈፅመውን ነገር ለመወደድ ሲል የሚያወራ።
**ይሉታል** ይጠራል፥ ይሰኛል፥ ይባላል። *ዝዝዝ ነው ይሉታል።*
**ምን ይሉታል** 1.ምን ተብሎ ይጠራል። 2.ስለ እሱ ምን እያሉ ያወራሉ።
**ይሉኝታ** ትዝብት፥ የሰው አስተያየት ፍራቻ፣ ምን ይሉኝ፣ ሰዎች ይተቹኛል፥ ይታዘቡኛል ብሎ ያለእውነተኛ ፍላጎት አንድን ነገር ከማድረግ መቆጠብ ወይም ለማድረግ መገደድ።
**ይሉኝ አይል** ይሉኝታ ቢስ።
**ይሉኝታ ቢስ** ቅ ትዝብትን፥ ሃሜትን የማይፈራ፣ ይሉኝታ የሌለው።
**ይበል** ግሩም፥ ድንቅ ለማለት የሚባል ቃል (ብዙውን ጊዜ ለጥሩ ቅኔ ማወደሻ የሚሰነዘር ቃል)።
**ተባለ** ግ 1.ተነገረ፥ ተወራ። 2.ተሰየመ፥ ስም ተሰጠ። *የት/ቤቱ ስም የእውቀት ጮራ ተባለ።*
**— በመባል —** በመሰኘት ወይም —በሚል ስም። *ት/ቤቱ የእውቀት ጮራ በመባል የሚታወቅ ነው።*
**የማይባል** የማይነገር፥ መባል የማይገባው።
**ይባላል** ተብሎ ይጠራል።
**አባባል** ስ 1.አነጋገር። 2.የአነጋገር ፈሊጥ፥ ዘዬ።
**አለ** ግ 1.በህይወት ነው። *አልሞተም አለ።* 2.ይገኛል። *ምግብ አለ።* 3.ተገኘ፥ ኖረ። *ገንዘቢ አባለቀም አለ/መብራቱ ጠፍቷል? አይ አለ።* 4.የአንድ ነገር ባለቤት ወይም ባለ ይዞታ መሆንን ለማመልከት የሚያገለግል። *መፅሃፍ አለኝ።*
**አለሁ አለሁ ባይ** (ስድብ) 1.እዩኝ እዩኝ፥ ልታወቅ ልታወቅ ባይ። 2.አጎብዳጊ።
**አለበት** አንድ ነገር እንዲደረግ፥ እንዲፈፀም የግዴታ አስፈላጊ መሆኑን የሚገልፅ ቃል። *ወንጀለኛው ለፍርድ መቅረብ አለበት።*
**ያለ የሌለ** 1.እያሌ፥ ብዙ። 2.በሙሉ። *ያለ የሌለ ንብረቱን ፀጠ።*
**አለኝታ** ስ መመኪያ።
**እንዳለ** 1.በሙሉ፥ በጠቅላላ፥ ምንም ሳይቀር። 2.ምንም ሳይነካለት፥ ቀደም ሲል የነበረበት ሁኔታ ሳይጓደል።
**አለ—(ያለ—)** 1.ሳይኖር፣ ከ-በስተቀር። *ለለገንዘብ እቃውን ማግኘት አይቻልም/ያለእሱ አይሆንም።* 2.አፍራሽ ምእላድ። *አለመስራት ድህነትን ሊያስከትል ይችላል።*

**አለበለዚያ** (ያለበለዚያ፥ አለዚያ፥ ያለዚያ፥ አሊያ) ቀድሞ የተነገረው ነገር ካልሆነ (ይህ ካልሆነ) ለማለትና አማራጭ ለመስጠት የሚነገር። *ስራህን አክብር! አለበለዚያ ትቸገራለህ።*
**አለለ**[1] ግ አለሌ ሆነ።
**አለል ዘለል አለ** ስራ ፈታ፥ አውደለደለ፥ ዋልጌ ሆነ።
**አለሌ** ስ 1.ከፈረስ በቅሎን የሚያስወልድ፥ በቁመናውና በጥንካሬው ተመርጦ እየተቀለበ የሚቀመጥ አህያ። ቅ 2.(ስድብ) ቅንዝረኛ።
**አለለ**[2] ግ አቀለመ፥ ቀለም ነከረ።
**አለላ** ስ ቀለም የተነከረ ስንደዶ ወይም አክርማ።
**አለላ ሙዳይ** ስ ከአለላ የተሰራ ትንሽ አገልግል ወይም ሙዳይ።
**አለሌ** "አለለ[1]" ስር ተመ.
**አለሎ** "አሎሎ"ን ተመ.
**አለመ**[1] ግ ህልም አየ።
**እልም** "ህልም" ን ተመ.
**አለመ**[2] ግ 1.ተኩስ ወይም ወርውሮ ለመምታት አነጣጠረ። 2.አቀደ፥ ተለመ፥ ነደፈ።
**ኢላማ** ስ በማነጣጠር ወርውሮ ወይም ተኩሶ የሚመታበት የተወሰነ ቦታ ወይም ምልክት።
**አላማ** ስ 1.ኢላማ። 2.እቅድ፥ ትልም። 3.ስንደቅ አላማ።
**አለመኛ** "አለም" ስር ተመ.
**አለመጠ** ግ ለገመ፥ ቀለደ፥ አሾፈ፥ አላገጠ (በስራ ላይ)።
**አልምጥ (አልማጭ)** ቅ ልግመኛ፣ በስራ ላይ የሚያሾፍ።
**አለም** ስ መሬትና በመሬት ላይ ያሉ ህዝቦችና አገሮች በሙሉ።
**አለሙን አየ** 1.አገባ፥ ተዳረ፥ ትዳር መሰረተ። 2.በደስታ፥ በድሎት ኖረ።
**አለም በቃኝ** ስ 1.የእድሜ ልክ እስራት። 2.የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው ሰዎች የሚታሰሩበት ቦታ።
**አለም በቃኝ አለ** መነነ።
**አለም አቀፍ** ቅ መላውን አለም ወይም በርካታ አገሮችን የሚመለከት፥ የሚያካትት፥ የሚያጠቃልል (ድርጅት፥ ስብሰባ፥ ...)።
**የአለም ስም** ስ የአንድ ሰው የክርስትና ስም ሳይሆን ዘወትር የሚጠራበት ስም።
**የአለም ጦርነት** ስ ብዙ የአለም አገሮች የተሳተፉበት ጦርነት ( ለምሳሌ 1ኛና 2ኛ

የአለም ጦርነት)::

**አለመኛ** ቅ የደላው፥ የተመቸው::

**አለማዊ** ቅ 1.በምድር ላይ በህይወት ለሚቆይበት ጊዜ ብቻ የሚጨነቅ፥ ከሞት በሂላ ላለው ህይወት ግድ የሌለው:: 2.መንፈሳዊ ያልሆነ፤ ስጋዊ::

**አለቀ** ግ 1.ተፈፀመ፥ ተጨረሰ:: 2-ሞተ:: *በአደጋው ብዙ ሰው አለቀ::* 3.አረጀ (ልብስ፥ ጨርቅ፥ ...)::

**ማለቂያ** ስ መጨረሻ፥ ማብቂያ::

**አላቂ** ቅ ለብዙ ጊዜ የማይቆይ ወይም የማያገለግል፥ በአጭር ጊዜ የሚያልቅ::

**እላቂ** ቅ 1.አገልግሎቱን የጨረሰ፥ ያረጀ (ልብስ):: 2.አገልግሎት ሰጥቶ ሊያልቅ ትንሽ የቀረው:: *እላቂ ሳሙና::*

**እልቂት (እልቀት)** ስ በብዛት መሞት፥ ማለቅ::

**ተላለቀ** ግ ተጋደለ፥ ተፋጀ::

**አለቃ** ስ 1.ሹም፥ የበላይ፥ አዛዥ፥ ዋና:: 2.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) የአንድ ቤተ ክርስቲያን ሹም ወይም አስተዳዳሪ::

**አለቃና ምንዝር** ሹምና ጭፍራ::

**እልቅና (ልቅና)** ስ አለቅነት::

**አለቅት** "እልቅት"ን ተመ.

**አለበ**[1] ግ 1.ጡትን በመሳብ ወተት አወጣ:: 2.(ዘይ) በዘበዘ፥ በጠበጠ:: *ገንዘቡን አለበው::*

**አለበ**[2] ግ 1.አነጣጠረ፥ አለመ፥ አዘገበ:: 2.ምልክት፥ እልባት አደረገ::

**እልባት** ስ 1.አንባቢ የሚፈልገውን ወይም ያቆመበትን ገፅ ለማወቅ እንዲረዳው በመፅሃፍ ውስጥ የሚያስቀምጠው ምልክት:: 2.የነገር ማብቂያ፥ መደምደሚያ፥ መጨረሻ:: *ጉዳዩ እልባት አገኘ::*

**እልባት አደረገ** ግ 1. አንባቢው የሚፈልገውን ወይም ያቆመበትን ገፅ ለማወቅ በመፅሃፍ ውስጥ ምልክት (ክር፥ ሳር፥...) አስቀመጠ:: 2.ነገርን ወይም ጉዳይን ደመደመ፥ ፈፀመ፥ ቋጨ::

**አለበለዚያ (አለዚያ፥ ያለበለዚያ፥ ያለዚያ)** መ. ሊከተል የሚችል ውጤትን የሚገልፅ ሃሳብን ለማያያዝ የሚያገለግል አያያዥ ቃል:: *መከላከያውን ውሰድ አለበለዚያ ትታመማለህ::*

**አለብላቢት** "ለበለበ" ስር ተመ.

**አለተለተ** ግ በጣም ወፈረ (ሰውነት)::

**አለት** ስ በመሬት ላይ ወይም በወንዝ ውስጥ በተፈጥሮ ተነጥፎ የሚገኝ ጠንካራ ድንጋይ::

**አለታም** ቅ አለት የሚበዛበት ስፍራ::

**አለንጋ** ስ ከጠፍር ወይም ከጉማሬ ቆዳ፥... የሚሰራ መግረፊያ::

**አለንጋ ጣት** ስ ቀጠንና ረዘም ያለ የሚያምር የእጅ ጣት::

**አለኝታ "አለ"** ስር ተመ.

**አለዚያ "አለበለዚያ"**ን ተመ.

**አለፈ** ግ 1.ሄደ:: 2.ሞተ:: *በመኪና አደጋ ህይወቱ አለፈ::* 3.ተወ፥ ዘለለ:: *እኔን አልፎ አጠገቤ ላለው ሰው ሰጠ::* 4.ዋስ፥ ዋቢ ሆነ:: *የጠየቀሁን ገንዘብ አበድረው እኔ አልፍለታለሁ::* 5.ቀረ፥ ተተወ:: *በአለፈ ነገር መናደድ አይጠቅምም::* 6.ከልኩ፥ ከወሰኑ፥ ከመጠኑ በለጠ ወይም ጨመረ:: *ወሰን አለፈ::* 7.ከአለበት ክፍልና ደረጃ ወደሚቀጥለው ክፍል ተዛወረ:: *ወደ 5ኛ ክፍል አለፈ::* 8.ሾለከ፥ ወጣ:: *ብርሃኑ በቀዳዳው አልፎ ገባ::* 9.ቀደመ፥ ወደ ሂላ ተወ:: *እሱ ሲንቀረፈፍ እኔ አልፈው ሄድኩ::*

**አለፈለት** ከችግሩ ተላቀቀ፥ ቀን ወጣለት::

**አለፈበት** 1. ሂላ ቀር ሆነ፥ፋሽኑ አበቃ:: 2.ጊዜው ሄደበት፥ ሳይጠቀምበት ቀረ::

**ያለፈበት** ዘመናዊ ያልሆነ፤ ሂላቀር የሆነ:: *ያለፈበት አለባበስ::*

**ይለፍ (የይለፍ ወረቀት)** ስ ወደ አንድ ቦታ ለመግባት ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ወይም ለመዘዋወር የሚሰጥ የፈቃድ ወረቀት::

**ማለፊያ** ስ 1.ጥሩ፥ ውብ፥ ደህና:: ቅ 2.መተላለፊያ::

**ሃላፊ (አላፊ)** ቅ 1.ቋሚ ያልሆነ፥ ለዘላለም የማይኖር:: *ገንዘብ ሃላፊ ጠፊ ነው::* ስ 2.ዋና፥ ባለቤት፥ አዛዥ:: *የቢሮ ሃላፊው ማን ነው::*

**አላፊ አግዳሚ** ወጪ ወራጅ፥ ተመላላሽ መንገደኛ::

**ሃላፊ ጊዜ** ስ (ሰዋ.) ድርጊቱ የተከናወነ ወይም የተፈፀመ መሆኑን የሚገልፅ የግስ ቅርፅ (ለምሳሌ *ሞተ፥ ሄደ፥ ...)::*

**ሃላፊነት (አላፊነት)** ስ 1.ተያዥነት፥ ዋቢነት፥ ተጠያቂነት:: *እቃው ቢጠፋ ሃላፊነቱን አልወስድም::* 2.ስልጣን:: *ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር::*

**ሃላፊነቱን አወረደ** ዋቢነቱን፥ ተያዥነቱን አነሳ፥ ሰረዘ::

**ሃላፊነቱን ወሰደ** 1.አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመፈፀም ግዴታ ውስጥ ገባ:: 2.ስለ ጉዳዩ ተጠያቂው እኔ ነኝ አለ:: *በድብቅ ጥቃት ያደረሰው ወገን ማንነቱን ገልፆ ስለድርጊቱ ሃላፊነቱን ወሰደ::*

**ሃላፊነት የሚሰማው** 1.ሃላፊነትን ወይም ግዴታን መወጣት ይችላል ተብሎ እምነት የሚጣልበት:: 2.ግዴታውን የተገነዘበና በተግባር የሚተረጉም (ሰው)::

**አለፌታ** ስ 1.ትርፍ ነገር፣ አፍ እላፊ:: 2.ከተገቢው መጠን በላይ፤ እላፊ::

**እላፊ** ቅ 1.አፍ እላፊ:: 2.ከተወሰነው ልክ ወይም ገደብ በላይ የሆነ::

**እልፈት (ህልፈት)** ስ መሞት፣ ከዚህ አለም በሞት መለየት::

**ህልፈተ አለም** ስ የአለም ፍፃሜ ወይም መጨረሻ::

**ተላለፈ** ግ 1.ከአንዱ ወደ ሌላ ተራመደ፣ ተዛመተ፣ ተጋባ (በሽታ):: 2.ጣሰ፣ አፈረሰ (ህግን):: 3.ተዛወረ፣ ተሸጋገረ፣ለሌላ ጊዜ እንዲሆን ተወሰነ:: 4.ሄደ፣ አለፈ:: *በዚያ በኩል ሲተላለፍ አየው ነበር::* 5.ከአንዱ ወደ ሌላው ተሻገረ፣ አለፈ፣ ሲወርድ ሲዋረድ መጣ፣ ተወረሰ:: *ከትውልድ ትውልድ ተላለፈ::* 6.እያንዳንዱ ወደየተቃራኒው አቅጣጫ ሄደ፣ ተጠላለፈ:: *ተላልፎ ተቆለፈ::* 7.ተሰራጨ፣ ተነገረ:: *አዲስ መመሪያ ተላለፈ::* 8.ሳይገናኝ ቀረ::

**መተላለፊያ** ስ መሄጃ፣ መሹለኪያ፣ ማለፊያ (በር፣ መንገድ፣ ...)::

**ተላላፊ** ቅ 1.ወጭ ወራጅ፣ መንገደኛ:: 2.በግራና በቀኝ ያለውን የልብሱን ክፍል፣ አንዱን በአንዱ ላይ በማሳለፍ የሚቆለፍ (ኮት፣ ቀሚስ፣ ...)::

**ተላላፊ በሽታ** ስ በንክኪ፣ በትንፋሽ፣ በዝንብ ወዘተ. ምክንያት ከአንዱ ወደሌላ የሚጋባ ወይም የሚዛመት በሽታ::

**አሳለፈ** ግ 1.በጊዜው ወይም በወቅቱ ሳይደርስ ቀረ፣ ዘገየ:: *የስራ ሰአት አሳለፈ::* 2.አደለ፣ አስተናገደ፣ አቀረበ:: *ጠጅ ያሳልፋል::* 3.ተወ፣ ማረ፣ ታገሰ፣ ይቅርታ አደረገ:: *የዛሬውን አሳልፌሃለሁ::* 4.ከችግር አላቀቀ፣ ቀን አወጣ:: *ወንድሙ ነው ያሳለፈለት::* 5.መንገድ ለቀቀ:: *አሳልፈው! ሊሄድ ቸኩሏል::* 6.ነፍስ አጠፋ፣ ገደለ:: *ህይወቱን በገዛ እጁ አሳለፈ::* 7.አሾለከ፣ አስገባ:: *እግሩን በወንበር ስር አሳልፎ ረገጠኝ::*

**አሳልፎ ሰጠ** ለባለጋራ ወይም ለጥቃት ዳረገ፣ አጋለጠ::

**አሳላፊ** ስ በድግስ ወይም በግብዣ ላይ የሚያስተናግድ፤ ቋሚ::

**አስተላለፈ** ግ 1.አዘዋወረ፣ ለሌላ ጊዜ ቀየረ:: *ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ አስተላለፉት::* 2.አዛመተ፣ አጋባ (ተላላፊ በሽታን):: 3.አወሳሰበ፣ አመሳቀለ:: 4.አሰራጨ፣ ነገረ (በዜና ማሰራጫ፣ በፅሁፍ፣...):: 5.በውስጡ እንዲያልፍ አደረገ (ኮረንቲን፣ ድምፅን፣ ብርሃንን፣ ...):: 6.ላከ፣ ሰጠ፣ ወሰደ:: *ወደ ወህኒ ቤት አስተላለፉት::* 7.አወረሰ::

**አሉባልታ** ስ ያልተረጋገጠ ወሬ፣ ሃሜት::

**አሉባልተኛ** ቅ (ስድብ) የአሉባልታ ወሬን የሚያዛምት ወይም የሚያወራ::

**አሉታ** ስ አሌ ማለት ወይም እብለት፤ የአወንታ ተቃራኒ::

**አሉተኛ** ዋሾ::

**አላህ** ስ (እስል.) ፈጣሪ፣ አምላክ፣ እግዚአብሄር::

**አላል** ስ በጋማ ከብት ጭንት ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚደረብ ትንሽ ጭንት::

**አላማ "አለመ²"** ስር ተመ.

**አላቂ "አለቀ"** ስር ተመ.

**አላባ** ስ 1.የእህል ወይም ከመሬት የሚገኝ የማንኛውም ነገር ምርት:: 2.የስራ ውጤት ወይም ፍሬ::

**አላዘነ** ግ 1.ለቅሶ በሚመስል ድምፅ ጮሀ፣ አንቋረረ (በተለይ ውሻ):: 2.ስለአንድ ጉዳይ ደግሞ ደጋግሞ አወራ፤ ችክ አለ::

**አላድ** ስ የብር እኩሌታ የነበረ ገንዘብ፤ ሃምሳ ሳንቲም::

**አሌ**

**አሌ አለ** ግ አበለ፣ ካደ::

**አሌጠ** ግ አፈዘ፣ አላገጠ::

**አል—** (በሚያስር ጊዜ "-ም"ን ይጨምራል) አፍራሽ ሃሳብ መመስረቻ ምእላድ:: (ለምሳሌ ሰራ→አልሰራም/ በላ→አልበላም)::

**አልሚ ምግብ "ለማ"** ስር ተመ.

**አልማዝ** ስ 1.ከንፁህ ካርቦን የሚገኝና በጥንካሬው የሚታወቅ ብሩህ የሆነ የከበረ ድንጋይ:: 2.ከአልማዝ የተሰራ ጌጥ::

**አልምጥ "አለመጠ"** ስር ተመ.

**አልቃሽ** ስ አልሄድ ያለን በሬ፣ አህያ፣... እንዲሄድ ወይም ፍጥነት እንዲጨምር የሚያደርግ ሹልነት ያለው መጎነጫ፤ መጎንተያ እንጨት ወይም ብረት::

**አልቅት (አለቅት)** ስ በውሃ ውስጥ የሚኖርና ከብቶች ውሃ ሲጠጡ በአፋቸው ገብቶ ጉሮሮአቸው ውስጥ በመቆመጥ ደም የሚመጥ ትል መሳይ ነፍሳት::

**አልቢትር "አርቢትር"**ን ተመ.

**—አልባ** ቅ —የሌለው:: *ስርአት አልባ::*

**አልባሌ** ቅ 1.የማይረባ፣ የማይታወቅ:: *አልባሌ ቦታ አትዋል::* 2. ተራ፣ ተርታ:: *ምስጢሩን ያወጣው አንድ አልባሌ ሰው ነው::*

**አልባብ** ስ ሲጨስ ጥሩ ሽታ ያለው የጭስ

እንጨት።

**አልቤርጎ (ቤርጎ)** ስ እንግዶች ለማረፊያነት የሚከራዩት የሆቴል ቤት ክፍል ወይም መኝታ ቤት።

**አልቤን** ስ የጠመንጃ አይነት።

**— አልቦ** ቅ — የሌለው።

**አልቦ** ስ ከወርቅ ወይም ከብር የሚሰራና ሴቶች በእግራቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ።

**አልቴት** ስ እንደ ራስ ምታት ያለን በሽታ ያድናል ተብሎ የሚሸተት እንደ ሙጫ ያለ ነገር።

**አልኮል** ስ 1.እንደ ቢራ፣ ጂን፣ ውስኪ፣ ... ባሉ መጠጦች ውስጥ የሚገኝ አስካሪ ንጥረ ነገር። 2.በቀላሉ ተኖ ወደ ጋዝነት ሊቀየርና በቀላሉ በእሳት ሊቀጣጠል የሚችል፣ በሆስፒታል ውስጥ ለቁስል መጥረጊያና ለተለያዩ ተግባራት የሚያገለግል ፈሳሽነት ያለው ንጥረ ነገር።

**አልኮል መጠጥ** ስ በውስጡ ያለው የአልኮል መጠን ከፍተኛ የሆነ እንደ ጂን፣ ብራንዲ፣ አረቄ፣... ያለ የመጠጥ አይነት።

**አልጀብራ** ስ በፊደላትና በምልክት ጭምር የሚጠቀም የሂሳብ ትምህርት ዘርፍ።

**አልጉም** "ለጎመ" ስር ተመ.

**አልጋ** ስ 1.በላዩ ላይ ለመተኛት እንዲያመች ተደርጎ ከእንጨት ወይም ከብረት፣ ... የሚሰራ ባለአራት እግር መተኛ። 2.ዙፋን።

**አልጋ ለዩ** ለየብቻ ተኙ (ባልና ሚስት)።

**አልጋ ላይ ዋለ** ከህመም የተነሳ የአልጋ ቁራኛ ሆነ፣ ታመመ።

**አልጋ በአልጋ** ቀና፣ ምቹ (ለመንገድ)።

**አልጋ ነቀነቀ** ሸፈተ፣ አመፀ፣ ንጉስን ተቃወመ።

**አልጋ ያዘ** 1.አልቤርጎ ተከራየ። 2.የአልጋ ቁራኛ ሆነ፣ ታሞ ተኛ።

**አልጋ ፈረሰ** ንጉሱ ከስልጣን በመወገዱ አገሩ መሪ አልባ ሆነ።

**ከአልጋ ወደቀ** በህማማት ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ።

**[የ]አልጋ ልብስ** ስ አልጋን ለማስጌጥ ከብርድ ልብስ በላይ የሚነጠፍ የአልጋ መሸፈኛ።

**አልጋ አንጣፊ** ስ በሆቴል ቤት ውስጥ አልጋ በማንጠፍ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው።

**አልጋ ወራሽ** ስ በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ንጉስ ዙፋኑን በሚለቅበት ጊዜ ንጉሱን ተክቶ መንገስ የሚችል የንጉስ ልጅ ወይም ወገን።

**የአልጋ ቁራኛ** ቅ ለረዥም ጊዜ በመታመሙ ምክንያት ከአልጋ የማይነሳ በሽተኛ።

**አልጌ** ስ በረጋ ውሃ ላይ ተንሳፎ የሚገኝና አረንጓዴ ቀለም ያለው ለስላሳ የእፅዋት አይነት።

**አልጫ** ስ 1.በእርድ ወይም ያለእርድ የተሰራ በርበሬ የሌለው ወጥ። ቅ 2.(ስድብ) ከስታራ ያልሆነ፣ ልፍስፍስ። *የወንድ አልጫ።*

**አሎሎ (አለሎ)** ስ እንደ ቅመማ ቅመም ያሉ ነገሮችን ለመቀጥቀጫ፣ ለመደፍጠጫ፣ ... የሚያገለግል ድብልብልና ከባድ የሆነ ድንጋይ።

**አሎሎ ውርወራ** ስ (ስፖ.) የብረት አሎሎን አርቆ ለመወርወር የሚደረግ ውድድር።

**አመሃኘ** "መከኘ" ስር "አመከኘ"ን ተመ.

**አመለ** ግ ከመቆየት የተነሳ ሽታው ወይም ጣእሙ ተበላሸ፣ እምክ እምክ አለ (ጥራጥሬ፣ ዱቄት)።

**አማላ** ቅ ከመቆየት የተነሳ፣ ሽታው ወይም ጣእሙ የተበላሸ፣ እምክ እምክ የሚል (ጥራጥሬ፣ ዱቄት)።

**አመለመለ** ግ የተነደፈን ጥጥ በትንሽ በትንሹ በመሸብለል ወይም በመጠቅለል ለፈትል አዘጋጀ።

**አመልማሎ** ስ ተነድፎ በትንሽ በትንሹ የተሸበለለ ወይም የተጠቀለለና ለፈትል የተዘጋጀ ጥጥ።

**አመለኛ** "አመል" ስር ተመ.

**አመለጠ** ግ 1.እስረኛ ወይም በቁጥጥር ስር ያለ ወንጀለኛ ከእስሩ ወይም ከቁጥጥሩ ራሱን በህገወጥ መንገድ ነፃ አደረገ፣ ተሰወረ። *እስረኛው አመለጠ።* 2.ጥፋት፣ ወንጀል፣... ሰርቶ ሳይያዝ ወይም ሳይደረስበት ሸሸ፣ ተሰወረ። *ሌባው ሰርቆ አመለጠ።* 3.ተረፈ፣ ዳነ። *ከሞት አመለጠ።* 4.በድንገት ወይም ሳይታሰብ ወደቀ (እቃ)፣ አፈተለከ፣ ወጣ (ወሬ፣ ምስጢር፣ ሽንት፣...)። 5.በወቅቱ ወይም በጊዜው በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ካለመገኘት የተነሳ ተፈላጊው ነገር ሳይገኝ ወይም ሳይደረስበት ቀረ። *አርፍዶ በመሄዱ ባቡሩ አመለጠው።*

**ማምለጫ** ስ መዳኛ፣ መትረፊያ (መንገድ፣ ዘዴ፣ ብልሃት ወይም ቦታ)።

**አመል** ስ 1.ባህርይ፣ ልማድ፣ ጠባይ። 2.ሱስ፣ ሃራራ። *የሲጋራ አመል አለበት።*

**ለአመል (ላመል)** 1.ለልማድ። *ሌባ ለአመሉ ዳቦ ይልሳል።* 2.ትንሽ ወይም ጥቂት። *ወው አታብዝ ፣ ለአመል ያህል ብቻ ወምሪበት።*

**አመል ነሳው** አነጫነጨው፣ ጠባዩን አበላሸው።

**አመል አወጣ** 1.መጥፎ ጠባይ አመጣ:: 2.ደህና የነበረው ይበላሽ ጀመረ (እቃ)::

**አመለ ልስልስ** ቅ ጥሩ ጠባይ ያለው፣ የማያስቸግር::

**አመለ ቢስ** ቅ ጥሩ ጠባይ የሌለው፣ ነጭናጫ::

**አመለ ናጫ** ቅ ጨቅጫቃ፣ አመለቢስ::

**አመለ ወርቅ** ቅ ጥሩ ጠባይ ያለው::

**አመለ ድሃ** ቅ ጥሩ ጠባይ የሌለው፣ ነጭናጫ፣ ከሰው የማይስማማ::

**አመለ ጌታ** ቅ ጥሩ ጠባይ ያለው::

**አመለኛ** ቅ 1.ልማደኛ:: 2.መጥፎ ጠባይ ወይም ባህርይ ያለው፣ አስቸጋሪ::

**አመልማሎ** "**አመለመለ**" ስር ተመ.

**አመመ**[1] ግ የጤና ማጣት ስሜት ተሰማ::

**ህመም** በፊደል ተራው ተመ.

**ህመምተኛ** "**ህመም**" ስር ተመ.

**ህሙማን** ዝ.ከ.

**ታመመ** ግ ህመምተኛ ሆነ፣ ጤና አጣ፣ በሽተኛ ሆነ::

**ታማሚ** ቅ ህመምተኛ፣ በሽተኛ::

**አሳመመ** ግ የህመም ስሜት እንዲሰማ አደረገ::

**አስታመመ** ግ 1.ለበሽተኛ የሚፈለገውን ነገር በማድረግ ረዳ፣ ተንከባከበ:: 2.ታገሰ፣ ቻለ፣ አሳለፈ:: 3.ቀስ አድርጎ ያዘ፣ በጥንቃቄ ተጠቀመ:: *እቃው ጨርሶ ከጥቅም ውጭ እንዳይሆንብኝ እያስታመምኩ ነው የምገለገልበት::*

**አመመ**[2] ግ በመደዳ በአንድ ጊዜ ሊሰራ የሚችለውን ስራ ገምቶና መድቦ መስራት ጀመረ (ለአጨዳ፣ ለአረም፣ ለቁፋሮ)::

**እመም** ስ በአንድ ጊዜ በመደዳ የሚካሄድ ስራ (አጨዳ፣ አረም፣ ቁፋሮ)::

**አመረቃ** ግ አረካ፣ አስደሰተ::

**አመርቂ** ቅ በጣም ጥሩ የሆነ፣ የሚያረካ:: *አመርቂ ውጤት ተገኝቷል::*

**አመራሮ** ስ በደጋ አካባቢ የሚበቅል፣ ቅጠሉ እንደቀላዎ ሰፋ ሰፋ ያለና ሲቀምሱት የሚመር፣ መጠኑ ከግራዋ የማይበልጥ የእፅዋት አይነት::

**አመሰ** ግ 1.ጥራጥሬን፣ ዱቄትን፣ ... በሰማ ምጣድ ላይ በመጠኑ ሞቅ ሞቅ አደረገ:: 2.አወከ፣ በጠበጠ፣ ረበሸ፣ አተራመሰ::

**እምስ** ስ በጣም ሳይበስል በምጣድ ላይ ሞቅ ሞቅ የተደረገ ጥራጥሬ፣ ዱቄት፣ ...::

**አመሰላሳ** ስ የየወሩ የመጨረሻ ቀን::

*ለመስከረም አመሰላሳ እንገናኝ::*

**አመሰኳ** ግ አመነዠከ::

**አመቀ** ግ 1.አንድን ነገር በብዛት እቃ ውስጥ በመጠቅጠቅ ከተተ፣ ጨመረ፣ አጨቀ:: 2.ደብቆ ያዘ፣ ቻለ (ምስጢርን፣ ወሬን፣ ስሜትን)::

**እምቅ** ቅ የታመቀ፣ የታጨቀ::

**አመቀመቀ** ግ አመነታ፣ ወላወለ፣ አቅማማ::

**አመት** ስ 1.አስራ ሁለት ወሮች ወይም ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ቀኖች ወይም ደግሞ በየአራት አመት አንድ ጊዜ ሶስት መቶ ስልሳ ስድስት ቀኖች ያሉት የጊዜ መጠን:: 2.ዘመን፣ ጊዜ::

**አመት አመት ድገመን** ከአመት አመት አድርሰን (ብዙውን ጊዜ የአዲስ አመት እሸት ሲቀመስ የሚባል)::

**አመተ ምህረት** ስ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን መጠሪያ::

**አመተ አለም** ስ 1.አለም ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ዘመን:: 2.ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለው ዘመን መጠሪያ::

**አመት በአል** ስ አውደ አመት፣ በየአመቱ የሚከበር በአል (ገና፣ እንቁጣጣሽ፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ፣ ...)::

**አመነ** ግ 1.ያለጥርጥር ተቀበለ፣ ተስማማ:: 2.ማድረጉን ወይም መፈፀሙን ተቀበለ፣ አረጋገጠ:: *መግደሉን አመነ::* 3.ታዘዘ፣ ገበረ፣ ተገዛ:: *ሽፍቶቹ ለንጉሱ አምነው ገቡ::* 4.አመለከ:: *በእግዚአብሄር ያመነ ይድናል::* 5.እምነት ጣለ::

**ምእመን** (ብ.ቁ. **ምእመናን**) ስ አማኝ (አማኞች)::

**አማኝ** ቅ 1.የአንድ ሃይማኖት ተከታይ:: 2.የሚከተለውን ሃይማኖት አጥብቆ የያዘ::

**እሙን** ቅ 1.ታማኝ፣ የታመነ (ሰው):: 2.የታመነ፣ እውነት ነገር:: *በድርቁ ብዙ ሰው መጎዳቱ እሙን ነው::*

**እማኝ** ስ አንድ ድርጊት ሲፈፀም የነበረ ወይም ያየ ወይም የሰማ ሰው፣ ምስክር::

**እምነት** ስ 1.ሃይማኖት፣ አምልኮ:: 2.እርግጠኝነት:: 3.ሃላፊነት፣ ታማኝነት:: *እምነት የሚጣልበት ሰው አይደለም::*

**እምነት አጎደለ** እንዲጠብቅ፣ እንዲይዝ የተደረገውን አጠፋ፣ አባከነ፣ ሃላፊነቱን ሳይወጣ ቀረ::

**እምነት ጣለ** አመነ፣ ተመካ፣ እርግጠኛ ሆነ::

**የእምነት ክህደት ቃል** ስ የተወነጀሉበትን ወይም የተከሰሱበትን ነገር ማመን ወይም አለማመን፣ አድርጌያለሁ ወይም አላደረግሁም

በማለት የሚሰጥ የአወንታ ወይም የእሉታ ቃል:: *የእምነት ክሀደት ቃሉን ሰጠ::*

**እምነተ ቢስ** ቅ እምነት የማይጣልበት፣ ከሃዲ::

**ታመነ** ግ እምነት ተጣለበት::

**ታማኝ (ተአማኒ)** ቅ የሚታመን፥ እውነተኛ፥ ሃቀኛ፥ የማይጠረጠር፣ ከሃዲ ያልሆነ::

**ተማመነ** ግ 1.ተመካ:: *በጉልበቱ ተማመነ::* 2.እርግጠኛ ሆነ:: *በችሎታው ይተማመናል::*

**ተማመኑ** ግ ተከክደው በነበረው ጉዳይ ላይ ሃቁን አረጋግጠው በመቀበል ተስማሙ::

**መተማመኛ** ስ ማስረጃ፥ ማረጋገጫ፥ ዋስትና::

**አሳመነ** ግ 1. እንዲያምን አደረገ:: 2.(በማስረዳት ወይም በመግለፅ) አንድ ሃሳብ ተቀባይነት እንዲኖረው አደረገ::

**አሳማኝ** ቅ ትክክለኛ፥ እውነተኛ፥ ተገቢ፥ ... ነው በማለት የሚቀበሉት (ሃሳብ፥ ነገር)::

**አስተማመነ** ግ እርግጠኛ፥ የማያጠራጥር ሆነ::

**አስተማማኝ** ቅ እርግጠኛ፥ የማያጠራጥር::

**አመነታ (አመናታ)** ግ ላድርግ አላድርግ አለ፣ ሃሳቡ ለሁለት ተከፈለ፣ አወላወለ::

**አመነዘረ** ግ ከጋብቻ ውጪ የግብረ ስጋ ግንኙነት አደረገ፣ ዝሙት ፈፀመ::

**አመንዝራ** ቅ ከጋብቻ ውጪ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያደርግ፣ ዝሙት የሚፈፅም (ሰው)::

**አመነገከ** ግ እንደ በሬ፥ በግ፥ ... ያለ እንስሳ በደንብ ሳያደቅ የዋጠውን ከሆዱ እያወጣ እንደገና በማኘክ አደቀቀ፣ አመሰኳ::

**ምንገሀ** ስ ከብቶች ያመሰኩት ወይም ያመነገኩት (መኖ)::

**አመንዝራ “አመነዘረ”** ስር ተመ.

**አመክሮ “መከረ”** ስር ተመ.

**አመድ** ስ አንድ ነገር በእሳት ሲቃጠልና እሳቱም ከጠፋ በኋላ የሚቀረው እንደ ዱቄት ያለ ነጣ ያለ ነገር::

**አመዱ ቡን አለ** በጣም ደነገጠ፥ ክው አለ::

**አመድ ነፋበት** አመድ መሰለ፥ ወዝ አጣ (ሰውነት)::

**አመድ አደረገ** ጨርሶ አወደመ፥ እልም አደረገ፣ አጠፋ::

**አመዳም** ቅ (ስድብ) 1.ወዝ የሌለው፥ ነጫጭባ:: 2.ድሃ፥ ያጣ የነጣ::

**አመዳይ** ስ አመድማ መልክ ያለው ውርጭ::

**አመድማ** ቅ አመድ የሚመስል፥ ግራጫ መልክ ያለው::

**አመፀ (አመጠ)** ግ 1.ከዳ፥ ሸፈተ:: 2.አስቸገረ፥ እምቢ አለ፥ አወከ::

**አመፅ** ስ 1.ሁከት፥ ረብሻ:: 2.የተቃውሞ እንቅስቃሴ::

**አመፀኛ (አመጠኛ)** ቅ ረባሽ፥ በጥባጭ፥ ፀጥታ አደፍራሽ::

**አሳመፀ** ግ አመፅ አስነሳ፥ አሳደመ::

**አሚና (ሃሚና)** ስ የ"ሳሊበላ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**አሚን**

**የአሚን ሚስት ወይም ባል** የመጀመሪያ ሚስት ወይም ባል::

**አማ** ግ አንድን ሰው በሌለበት በጥፋቱም ሆነ ያለጥፋቱ በክፉ አነሳ፥ ነቀፈ::

**ሃሜት (አሜት፥ ሃሜታ፥ አሜታ)** ስ 1.አንድን ሰው በሌለበት በመጥፎ ማንሳት:: 2.አንድን ጉዳይ በማስመልከት የተነገረ ያልተረጋገጠ ወሬ:: *የመንግስት ገንዘብ ለጉድሏል የሚል ሃሜት አለ::*

**ሃሜተኛ (አሜተኛ)** ቅ በአጠገቡ የሌለን ሰው በመጥፎ የማንሳት ልማድ ያለው (ሰው)::

**ታማ** ግ አንድ የሆነ ነገር አድርጓል ወይም ፈፅሟል ተብሎ በመጠርጠር ወሬ ተወራበት::

**አሳማ** ግ እንዲታማ አደረገ፥ ምክንያት ሆነ::

**አማላ “አመለ”** ስር ተመ.

**አማረ** ግ 1.ተዋበ፥ ቆነጀ:: 2.ውል አለ ወይም አሰኘ:: *ስጋ ላማረኝ::* 3.ሰመረ፥ ጥሩ ሆነ:: *የዘንድሮው አዝመራ አምሯል::*

**አምሮት** ስ ፍላጎት፥ ምኞት::

**አምሮቱን ቆረጠ** ያማረውን ነገር አግኝቶ ረካ::

**አምሮቱን ተወጣ** የሚፈልገውን ነገር አግኝቶ ወይም አድርጎ ረካ::

**አማሪት** ስ 1.ቀጭን ድምፅ የምትሰጠውና በግራ እጅ በኩል የምትሆነው የከበሮ ቂጥ:: 2.አረሆ:: 3.ቀጭን ድምፅ ከሚሰጡት ከሰስቱ የበገና አውታሮች አንዱ::

**አማተበ** ግ በመስቀል ወይም ሁለት ጣቶቹን በማነባበርና የመስቀል ቅርፅ በመስራት ግንባሩን፥ ደረቱንና ትከሻዎቹን መጀመሪያ ግራውን ቀጥሎ ቀኙን በመንካት የመስቀል ምልክት አሳየ፥ አደረገ (በፀሎት፥ በመሳለም ጊዜ)::

**አማት** ስ 1.የባል ወይም የሚስት እናት ወይም አባት:: 2.የባል እናት::

**አማምቻ** ስ እህትን ከዳሩ በኋላ አማች

የሆነውን ሰው እህት በማግባት የሚመሰረት የጋብቻ ትስስር።

**አማች** ስ የእህት ወይም የልጅ ወይም የዘመድ ባል።

**ያማች ዳሩ** ስ ጨካኝ ወይም ክፉ አማች።

**አምቻ** ስ አማችነት፣ በጋብቻ መተሳሰር።

**አምቻ ጋብቻ** ስ የጋብቻ ዝምድና።

**አማን** ስ ሰላም። *በአማን ላውለኝ*።

**አማኝ** "**አመነ**" ስር ተመ.

**አማጋ** ስ ከመኖሪያ ቤት አካባቢ ርቆ የሚገኝ የከብቶች ማደሪያ ወይም በረት።

**አሜራ** ስ ቀለሙ ለመነቀሻ የሚሆን የእፅዋት አይነት።

**አሜባ** ስ 1.ያለ ማይክሮስኮፕ በአይን ብቻ ሊታይ የማይችልና በአፈር፣ በውሃ ወይም በሰውና በእንስሳት አካል ውስጥ ተገኝ ሆኖ የሚኖር ባለአንድ ህዋስ ነፍሳት። 2.በአሜባ ምክንያት የሚመጣ የተቅማጥ በሽታ።

**አሜተኛ** "**አማ**" ስር "**ሃሜተኛ**"ን ተመ.

**አሜታ** "**አማ**" ስር "**ሃሜት**"ን ተመ.

**አሜት** ዝ.ከ.

**አሜን** ስ እሺ፣ ይሁን፣ ይደረግ ለማለት በፀሎትና በምርቃት ላይ የሚባል ቃል።

**አሜን ብሎ ተቀበለ** እሺ ብሎ ተቀበለ።

**አሜከላ** ስ 1.በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፣ አንጓው አጠር ያለና ቍንቅላቱ እንደ ኳስ የተድበለበለ የእሾህ አይነት። 2.(ዘይ) ምቀኛ፣ ሰላም የሚነሳ ባላጋራ።

**—አም** ቅ —በብዛት ያለበት፣ ያለው ወይም መጠኑ ከሌላው ከፍ ያለ ነው ለማለት የሚያገለግል ምእላድ። *ብርጃም /እከካም/ ወተታም/ ቍንቅላታም*።

**አምላክ** "**መለከ**" ስር ተመ.

**አምልኮ** ዝ.ከ.

**አምልኮኛ** ዝ.ከ.

**አምሮት** "**አማረ**" ስር ተመ.

**አምሳ (ሃምሳ)** ስ 1.በአርባ ዘጠኝና በሃምሳ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፶'፣ '50' ነው። ቅ 2.በአርባ ዘጠኝና በሃምሳ አንድ መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *ሃምሳ ልጆች*።

**አምሳ (ሃምሳ) አለቃ** ስ ከአስር አለቅነት ቀጥሎ ያለ ወታደራዊ ማእረግ ስም።

**አምሳ (ሃምሳ) እግር** ስ ብዙ እግሮች ያሉት፣ በክረምት ጊዜ የሚፈጠር ወይም የሚታይ ትል።



አምሳ (ሃምሳ) እግር

**አምሳል** "**መሰለ**" ስር ተመ.

**አምሳያ** ዝ.ከ.

**አምስት** ስ 1.በአራትና በስድስት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፭'፣ '5' ነው። ቅ 2.በአራትና በስድስት መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ ። *አምስት ጣቶች*።

**አምበል (አንበል)** ስ 1.መሪ፣ አለቃ፣ አባገር፣ አዝማች። *የጦር አምበል*። 2.የእግር ኳስ፣ የመረብ ኳስ፣ ... ጨዋታ የቡድን ተጠሪ ወይም መሪ።

**አምበልጋ** ቅ ፈሪ፣ ቡከን።

**አምበሬ ጭቃ** ስ ለፀጉር የሚያገለግልና ፈሳሽ ያልሆነ የቅባት አይነት።

**አምበሳ** "**አንበሳ**"ን ተመ.

**አምቡላ (አንቡላ)** ስ የጠጅ አተላ።

**አምቡላንስ** ስ ድንገተኛ ህመም ወይም አደጋ ያጋጠማቸውን ወይም በጦር ሜዳ ላይ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች እርዳታ ወደሚያገኙበት (ክሊኒክ፣ ሆስፒታል፣...) የሚያጓጉዝ መኪና።

**አምባ** ስ 1.በአንድ አካባቢ ተቀራርቦ የተሰራ መንደር። 2.በተራራ ወይም በኮረብታ ላይ ያለና ለመኖሪያነት የሚሆን ሰፊ ሜዳ።

**አምባላይ** ስ ነጭ (ፈረስ)።

**አምባራይሌ** ስ መልኩ ቀላ ያለ ዳለቻ ሆኖ ከጀርባው ወደ ሆዱ የሚወርዱ ነጫጭ ሽንትሮች ያሉበት፣ ረጅምና ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ የተጠማዘዙ ቀንዶች ያሉት፣ እሽሃማ ቁጥቋጦች ባሉባቸው ቆላማና ዝቅተኛ ስፍራዎች የሚኖርና አጋዘን የሚመስል የዱር እንስሳ።

**አምባር** ስ ከወርቅ ወይም ከብር፣ ... የሚሰራና ሴቶች በእጃቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ።

**አምባርሚያ** ስ አምባር የሚደረግበት የእጅ ክፍል(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

**አምባሳደር** ስ አገሩን ወክሎ እንዲሰራ በውጭ አገር የሚመደብ ባለስልጣን።

**አምባሻ** ስ ሽልማት ተደርጎበት በወፍራም ቂጣ መልክ የሚጋገር የስንዴ ዳቦ።

**አምባባ** ግ ስርያ የፈለገ ፍየል የእንስቲቱን ፍየል

የሂሳ አካል በእግሩና በአገጩ እየጎነተለ ባባባ የሚል ጨዋታ አሰማ።

**አምባዛ** ስ መልኩ ጠቆር ያለ፥ ቀጫጭንና ረዣዥም ፀጉር መሳይ ነገር አፉ ዳርና ዳር ያለው፥ ሰጋው ውስጥ ጥቃቅን እሾህ መሰል አጥንቶች የሌሉበት የአሳ አይነት፤ ጥቁሬ አሳም ይባላል።

**አምባገነን** ስ በህዝብ ሳይመረጥ በሃይል ስልጣን የያዘ፥ ሁሉን የማድረግና የመወሰን ሙሉ ስልጣን ለራሱ የሰጠና የህዝቡን ፍላጎት አፍኖ የሚገዛ መሪ ወይም መንግስት።

**አምባጓሮ** ስ ጠብ፥ ጥል።

**አምቦ** ስ ጨውነት ያለው ውሃ ወይም አፈር።

**አምቦልክ** "**ኤንቬሎፕ**"ን ተመ.

**አምታሮ** "**መተረ**[1]" ስር "**መተሮ**"ን ተመ.

**አምቻ** "**አማት**" ስር ተመ.

**አምና** ስ አሁን ካለው አመት በፊት ያለው አመት፤ ያለፈው አመት።

**አምኜ** ስ ክረምቱ ካለፈ በሂላ በመስከረም የሚዘራ ስንዴ።

**አምዛ** ስ ተነባብሮ የተጋገረ እንጀራ፥ አነባበሮ።

**አምድ** ስ 1.ምሰሶ። 2.በአርእስትና በህዳግ መካከል ያለ ወይም በተፃፈበት መካከል ለገፅ መከፈያ የሚተው ባዶ ቦታ። 3.በመፅሄት ወይም በጋዜጣ ላይ ሁልጊዜ አንድን ጉዳይ በተመለከተ የሚፃፍበት የመፅሄቱ አንድ ክፍል። *የባህል አምድ።*

**አምደ ወርቅ** ስ በቅኔ ማህሌት ውስጥ በስተቅድስት በኩል በሁለት በሮች መካከል የቆመ አምድ።

**አእማድ** ስ 1.የአምድ ብዙ ቁጥር። 2.እንደ ተደራጊ፥ ተደራራጊ፥ አድራጊ፥ አደራራጊ፥ አስደራጊ፥ ... ያሉ የግስ እርባታ ቅርፆች (ስርአተ እርባታ)።

**አእማደ ምስጢር** ስ ምስጢረ ስላሴን፤ ሚስጢረ ስጋዌን፤... የያዘ መፅሃፍ።

**አምጃ** ስ በደጋና በወይና ደጋ አካባቢ ጥቅጥቅ ብሎ የሚበቅል የቁጥቋጦ አይነት።

**አምፋሮ** "**አንፋሮ**"ን ተመ.

**አምፖል(አምፑል)** ስ በኤሌክትሪክ ሃይል አማካይነት ብርሃን ለመስጠት የሚችሉ ቀጫጭን ሽቦዎች በውስጡ የሚገኙበት፤ የተለያየ ቅርፅና መጠን ያለው የኤሌክትሪክ መብራት ብርጭቆ።

**አምፖል ማቀፊያ** ስ ከኤሌክትሪክ ሽቦ ጋር የሚያያዝና አምፖል የሚሰካበት ቀዳዳ ያለው የኤሌክትሪክ እቃ።

**አሞሌ [ጨው]** ስ ከባህር ውስጥ ሳይሆን መሬት ውስጥ በድንጋይ መልክ የሚገኝ ጨው (በድሮ ጊዜ ለመገበያያ እንደገንዘብ ሆኖ ያገለግል ነበር)።

**አሞራ** ስ 1.እንደጥንብ አንሳ፥ የሎስ፥ ጋጋኖ፥ ... ያሉ ትላልቅ አእዋፍ። 2.(ዘይ.) ፈጣን፥ ቀልጣፋ። *ልጁ አሞራ ነው።* (ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)

**የአሞራ ምሳ** ስ ሲበስል ቀይ የሚሆንና ጣፋጭ ፍሬ ያለው የሃረግ አይነት፤ ፍሬውም የአሞራ ምሳ ይባላል።

**አሞርቲዛተር** ስ በመኪናዎች ጎማ አጠገብ የሚገጠምና መኪናው በመጥፎ መንገድ ላይ እንዳይንገጫገጭ የሚረዳ አረግራጊ መሳሪያ።

**አሞት** "**ሃሞት**"ን ተመ.

**አሞጭ** ስ ስሩ ነጭ ሽንኩርት የሚመስል ፍሬ የሚያፈራና የማይበላ የእፅዋት አይነት።

**አሞጭ የመሰለ** በጣም ነጭ የሆነ።

**አሟረ** የ"**ቀለሰ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**አሟዳ** ቅ አፍንጫ ጎራዳ፤ ደፍጣጣ።

**አረህ** ስ በገደል መካከል ያለ ተዳፋት ቦታ።

**አረሆ** ስ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረች የምትዘፍን ሴት።

**አረመ** ግ 1.ከእህል ጋር የበቀለን አረም ነቀለ። 2.አስተካከለ፤ አቃና፤ እርማት ሰጠ። 3.ስህተት ወይም ልክ መሆኑን እያረጋገጠ ተገቢውን ነጥብ ሰጠ (ለፈተና)። 4.ቀጣ፥ ገራ (ጠባይን)።

**ማረሚያ** ስ ማስተካከያ፥ ማሻሻያ (ፅሁፍ)።

**ማረሚያ ቤት** ስ ወንጀል የሰራ ወይም ህግ ተላልፎ የተፈረደበት ሰው እስከ ቅጣቱ ፍፃሜ ድረስ የሚቆይበት ቦታ፤ እስር ቤት።

**አረም** ስ ከእህል ጋር አብሮ የሚበቅልና አስፈላጊ ባለመሆኑ ተነቅሎ የሚጣል ማንኛውም አይነት እፅዋት።

**አረም ጫኘበት** ተወው፤ ችላ አለው (ለስራ፤ ለጉዳይ፥...)።

**አራሚ** ስ አረም።

**እርማት (እርምት)** ስ 1.የማረም ወይም የማስተካከል ስራ ። 2. ማሻሻያ። *እርማት ተደረገበት።*


**ታረመ** ግ 1.ከአረም ፀዳ፤ አረሙ ተነቀለለት። *ጤፉ ታረመ።* 2.ተስተካከለ፥ ተሻሻለ (ፅሁፍ)። 3.ተሻሻለ፤ ጥሩ ሆነ (ጠባይ)።

**አረመመ** ግ ዝም አለ፤ ከመናገር ተቆጠበ።

**አርምሞ** ስ ዝምታ ወይም ፀጥታ።

**በአርምሞ** በዝምታ፤ በፀጥታ፤ በተመስጦ። *በአርምሞ አዳመጠ።*

**አረመኔ** ቅ 1.ጨካኝ፤ ርህራሄ የሌለው። ስ




1. ጆፌ አሞራ
2. ዳክዬ
3. ጅብሪል
4. የሲጣን ዶሮ
5. ጉጉት
6. ዝዩ
7. ጅግራ
8. ጥንብ አንሳ
9. ሳቢሳ
10. ቆልማማጊት
11. ሲላ
12. ንስር
13. ገዴ
14. ገርጊሶ
15. የወንዝአሙቴ
16. ጋጋኖ

2.ሃይማኖት የሌለው፥ በጣኦት አምላኪ።

**አረመደ** ግ በእንጀራ፥ በዳቦ፥... ብትን በርበሬን ደመደመ ወይም አጠቀሰ።

**ማርመጃ** ስ ድልህ፥ በርበሬ።

**አረማሞ** ስ በአዝመራ ጊዜ ተፈላጊውን መልካም ፍሬ እንዳያፈራ ጥቀርሻ መሰል በሆነ የእህል በሽታ ተጠቅቶ የሚገኝ የስንዴ፣ የገብስ፥... ዛላ።

**አረማዊ** ቅ አረመኔ የሆነ፥ የአረመኔ ወገን።

**አረም "አረመ"** ስር ተመ.

**አረረ** ግ 1.ተቃጠለ፥ ተከነ (ከሚፈለገው በላይ እሳት የበዛበት ምግብ ነክ ነገር)። 2.ተናደደ፥ በገነ። 3.በጣም አዘነ፥ ልቡ በሃዘን ተነካ። 4.ቀጨጨ፥ ማደግ የሚገባውን ያህል ሳያድግ ቀረ።

— **አረረበት** — አጣ፣ ተቸገረ። *ቆሉ አረረበት= ቆሉ እንኳን አጣ።*

**አረረም መረረም** ተወደደም ተጠላም።

**አራራ** ቅ ያረረ፣ የተቃጠለ።

**እርር ምርር አለ** ግ 1.በጣም አለቀሰ፥ ተንሰቀሰቀ። 2.በጣም አማረረ፥ ተማረረ፥ ተንገፈገፈ።

**እርር ብሎ አለቀሰ** ምርር ብሎ አለቀሰ።

**እርር ኩምትር አለ** ግ በጣም አረረ፥ ተናደደ።

**አሳረረ** ግ መታ፥ ሸነቀጠ፣ ገረፈ (በጅራፍ፣ በአርጩሜ)።

**አረር** ስ የጥይት እርሳስ።

**አረሰ**[1] ግ በማረሻ ገመሰ፣ ተለመ፣ ሰነጠቀ (የእርሻ መሬትን)።

**አርሶ በላ** ስ አርሶ አደር፥ ገበሬ።

**አርሶ አደር** ስ ገበሬ፥ በግብርና ስራ የሚተዳደር ሰው።

**ማረሻ** ስ በእርፍ ላይ ተሰክቶ መሬትን ለመትለሚያ፣ ለመሰንጠቂያ፥ ለማረሻ የሚያገለግል ከብረት የሚሰራ የእርሻ መሳሪያ (ስእሉን "**ሞፈር**" ስር ተመ. )።

**አራሽ** ስ ገበሬ፥ አርሶ አደር።

**እራሽ** ስ ማሳ፣ የእርሻ ይዞታ።

**እርሻ** ስ የአዝርእት መዝሪያና ማብቀያ፥ የታረሰ ወይም የሚታረስ መሬት።

**የእርሻ መኪና** ስ ለእርሻ ስራ የሚያገለግልና በሞተር የሚሰራ መኪና፥ ትራክተር።



የእርሻ መኪና

**የእርሻ ውጤት** ስ ከእርሻ የሚገኝ ምርት።

**አሳረሰ** ግ በተለያየ ውለታ (በኪራይ፥ በእርቦ፥...) በመስማማት ሌላ ሰው እንዲያርስለት አደረገ።

**አሳራሽ** ቅ ባለመሬት ሆኖ ሌሎችን በማሳረስ የሚጠቀም።

**አረሰ**[2] ግ አራስን ተንከባከበ (በምግብና በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ)።

**አራስ** ስ 1.ከወለደች ብዙ ቀን ያልሆናት ሴት። 2.ጨቅላ ወይም ከተወለደ ብዙ ጊዜ ያልሆነው ህፃን ልጅ።

**አራስ ነብር ሆነ** በጣም ተቆጣ፥ ተበሳጨ።

**አራስ ልጅ** ስ ጨቅላ ወይም ከተወለደ ብዙ ጊዜ ያልሆነው ህፃን ልጅ።

**አራሽ** ቅ አራስን የሚንከባከብ (ብዙ ጊዜ ሴት)።

**ማረሻ** ስ የወለደች ሴትን ለመንከባከብ የሚዘጋጅ ምግብ።

**ታረሰች** ግ (አራስ ሴት) በጥሩ ሁኔታ እንክብካቤ ተደረገላት።

**አረቀ** ግ 1.እርጥበት ያለውን የጎበጠ እንጨት በእሳት ለብልቦ አቃና፥ ቀጥ አደረገ፤ ወይም ቀጥ ያለውን እርጥብ እንጨት በእሳት ለብልቦ አጎበጠ፥ ለመጠ። 2.በምክር ፣ በተግሳፅ፥... እንዲያስተካክል አደረገ (ጠባይን)። 3.ያጋደለውን የአህያ ወይም የአጋሰስ ጭነት አስተካከለ። 4.መታ። *በዱላ አረቀው።*

***አረቀ**

**እርቅ** ስ ቀድሞ የነበረን ጥል ወይም ቅሬታ በማስወገድ የሚደረግ ስምምነት፣ ፍቅር፥ ሰላም።

**እርቅ ወረደ** ቀደም ሲል የነበረው ጥል ወይም ቅሬታ ተወገደ፣ ሰላም ሆነ፥ ስምምነት ተፈጠረ።

**እርቀ ሰላም** ስ በመካከላቸው ጠብ ወይም ቅሬታ በነበረባቸው ወገኖች መካከል የሚደረግ እርቅ፥ ስምምነት።

**ታረቀ** ግ ከተጣላው ወይም ከተቃቀረው ሰው ጋር ስምምነት፣ ሰላም ፈጠረ።

**አስታረቀ** ግ ጥለኞችን አስማማ፥ በመካከላቸው ሰላም እንዲፈጠር አደረገ።

**አስታራቂ** ቅ በተጣሉ ወገኖች መካከል በመግባት እርቅ ወይም ሰላም እንዲፈጠር የሚያደርግ።

**አስታራቂ [ሽማግሌ]** ዝ.ክ.

**ያስታራቂ** ስ ለአስታራቂ ሽማግሌዎች የሚደረግ ግብዣ።

**አረቄ**[1] ስ የአልኮል መጠጥ አይነት።

**አረቄ**[2]

**አረቄ መርፌ** ስ አጭርና ቀጭን መርፌ፣ ጥልቅ መርፌ።

**አረቄ**[3]

**አረቄ ወገብ** ቅ ወገበ ቀጭን።

**አረበደ** ግ በመቻኮልና በመለፍለፍ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተሯሯጠ።

**አረቦን** ስ ቀብድ፥ዋስትና ወይም መያዣ(ነገር)።

**አረተረተ** ግ በሰምሰማ ሮጠ።

**አረንቋ** ስ ረግረግ፥ ማጥ።

**አረንዛ** ስ 1.ብዙ ድንጋይ ያለበት ቦታ። 2.ጥቁር ድንጋይ የበዛበትና ውስጡ ውሃ የሚሰማው፥ ረግረግነት ያለው መሬት ወይም ቦታ።

**አረንጓዴ** ቅ 1.ለምለም ቅጠልን ወይም ሳርን የመሰለ የቀለም አይነት። 2.አልጌ።

***አረዘ**

**እርዛት** ስ የልብስ እጦት ወይም ችግር።

**ታረዘ** ግ የሚለብሰው አጣ።

**አረደ** ግ 1.የሰውን ወይም የእንስሳትን አንገት ስለት ባለው መሳሪያ ቆረጠ። 2.ቆረጠ። *እጁን በቢላዋ አረደው*። 3.በቦይ ቅርፅ አይነት መሬትን ገመሰ፥ አጎደጎደ፥ ጎደበ። *መሬቱን አረደው*። 4.(ዘይ.) አታለለ፥ ጉድ ሰራ።

**አርዶኝ ሄደ** አታሎኝ፥ ጉድ ሰርቶኝ ሄደ።

**አረድ** ቅ አታላይ፥ ሌባ።

**አራጅ** ስ በሬን፥ ላምን፥ ፍየልን፥ በግን፥ … የማረድ፥ የመግፈፍና ብልት የማውጣት ችሎታ ያለውና ለሚሰጠውም አገልግሎት ገንዘብ ባለሙያ።

**እርድ** ስ 1.ለድግስ፥ ለግብግብ፥… የታረደ እንስሳ (በሬ፥ ላም፥ በግ፥ …)። 2.ምሽግ፥ ጉድባ፥ ጉድጓድ።

**ለእርድ ቀረበ** ለመታረድ ቀረበ።

**ያለእርድ ዋለ** በበአል ቀን በግ፥ ዶሮ፥… እቤቱ ሳያርድ ቀረ።

**ተራረደ** ግ ተገዳደለ፥ ተጨፋጨፈ።

**አረዳ**[1] ስ የአንድ አካባቢ ነዋሪ ህዝብ።

**አረዳ**[2] "ረዳ" ስር ተመ.

**አረዳ**[3] ስ ፍግ ወይም ጥራጊ የሚፈስበት ቦታ።

**አረዳ [መሬት]** ስ የዳበረ መሬት።

**አረጀ** ግ 1.ሸመገለ። 2.አሮጌ ሆነ (ልብስ፥ እቃ፥ …)።

**እርጅና** ስ ሽማግሌ ወይም አሮጊት መሆን።

**አስረጀ** ግ አሮጊት ወይም ሽማግሌ አደረገ።

**አረገ** ግ ከመሬት ወደ ሰማይ ወጣ። *ክርስቶስ ከመቃብር ተነስቶ ወደ ሰማይ አረገ*።

**እርገት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገበትን ቀን ለማስታወስ በየአመቱ በግንቦት ወይም በሰኔ ወር ከፋሲካ በሂላ በአርባኛው ቀን ሃሙስ እለት የሚከበር በአል።

**አሳረገ** ግ የማሳረጊያ ወይም የመደምደሚያ ፀሎት አደረገ።

**ማሳረጊያ** ስ መጨረሻ፥ መደምደሚያ፥ መፈፀሚያ።

**አረጋዊ** (ብቁ.**አረጋውያን**) ቅ ሽማግሌ፥ አዛውንት።

**አረግ ሬሳ** "ሃረግ" ስር "ሃረግ ሬሳ"ን ተመ.

**አረጠረጠ** ግ 1.ቦረቀ፥ ፈነጨ። 2.አዘጠዘጠ፥ ወዲያ ወዲህ አለ።

**አረጥራጭ** ቅ አዘጥዛጭ።

**አረጠች** ግ እድሜዋ በመግፋቱ ምክንያት የወር አበባዋ ቆመ፤ መፅነስ፥ መውለድ አቆመች።

**አረጥራጭ** "**አረጠረጠ**" ስር ተመ.

**አረጭ** ስ ጭሬ።

**አረፈ** ግ 1.እፎይ አለ፥ ድካሙን አስወገደ፥ እረፍት አደረገ። 2.ሞተ። 3.ከመናገር፥ አንድን ነገር ከመስራት፥… ተቆጠበ። 4.ወረደ፥ቦታ ያዘ፤ ተቀመጠ፥ ሰፈረ(ከአየር ወደ መሬት፥ዛፍ፥…)

*ንቡ ላዩ ላይ አረፈ / አውሮፕላኑ አረፈ* ።

5.ተገላገለ፥ ተላቀቀ። *ከጭቅጭቅ አረፈ*። 6.በእንግድነት ተቀመጠ፥ ኖረ። *ከአገሩ ሲመጣ ወንድሙ ዘንድ አረፈ*።

**ማረፊያ** ስ 1.የእንግዳ መቆያ፥ መቀመጫ። 2.ቤት፥ መኖሪያ፥ መጠለያ። *ማረፊያ ሳይኖረው ትዳር ማሰብ የለበትም*።

**ማረፊያ ቤት** ስ እስር ቤት።

**አረፍተ ነገር** ስ አንድ የተሟላ ሃሳብን የሚይዝ የቃላት ስብስብ።

**አረፍት** ስ 1.መቀመጫ፥ ማረፊያ። 2.በገጠር ቤቶች ለእቃ ማስቀመጫነት እንዲያገለግል ከግድግዳ ጋር ተያይዞ የሚሰራ መደርደሪያ፤ ዘለንጋ።

**እረፍ** 1. እረፍ፥ ተው አታድርግ፥…። 2. እረፍት አድርግ።

**እረፍት (እርፈት)** ስ ማረፍ፥ እፎይ ማለት። 2.ለተወሰነ ጊዜ ከስራ፥ ከትምህርት፥ ከስብሰባ፥… ተለይቶ የሚቆይበት ጊዜ፤ ማረፊያ ጊዜ። 3.ሞት።

**እረፍተ ቢስ (እርፈተ ቢስ)** ቅ አርፎ ወይም ተቆጥቦ የማይቀመጥ፤ ቀኅርቃኅ።

**እረፍት የለሽ** ቅ 1. ማረፊያ ጊዜ የሌለው

ባተሌ:: 2. እረፍተ ቢስ::

**አሳረፈ** ግ 1.እረፍት፣ ፋታ እንዲያገኝ አደረገ:: 2.ሸክምን አስቀመጠ:: 3.ገላገለ፥ አዳነ:: 4.ገደለ፥ አሳለፈ:: *በጼላ ማጅራቱን ብሎ ኣሳረፈው::* 5.መሬት አስያዘ፣ አወረደ (አውሮፕላን ላይ)::

**አሳራፊ (አራፊ)** ቅ እንደ እግር ኳስ፥ መረብ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ ... ባሉ ስፖርታዊ ጨዋታዎች ላይ አንድ ተጫዋች በደንብ መጫወት ባይችል ወይም ቢደክመው በምትኩ ገብቶ ሊጫወት የሚችል ተጫዋች::

**አሳርፈው** ተው በለው፥ከልክለው::

**አረፈረፈ** ግ ረጨ፣ አርከፈከፈ::

**አረፋ**[1] ስ እንዶድ፥ ሳሙና፥ አሞ፥ ... በውሃ ሲበጠበጥ የሚፈጥረው ነጭ የሚኩረፈረፍ ነገር፤ ወይም የባህር ውሃ በማእበል ሲጋጭ የሚፈጥረውና ውሃው ላይ ተንሳፎ የሚታየው ነጭ ነገር::

**አረፋ ደፈቀ** በህመም፣ በድካም፥... የተነሳ ከአፉ አረፋ የሚመስል ነገር ወጣ::

**አረፋ**[2] ስ ኢድአል አድሃ::

**አሪማጥ "ረመጠ"** ስር ተመ.

**አሪባሪ** ስ መጠኑ ርግብ የሚያክል፥ የጅራቱ ቀለም ነጭና ጥቁር፥ ሌላው አካሉ ጥቁርና አመድማ የሆነ የወፍ አይነት(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)::

**አሪቲ** ስ አመድማ መልክና ጥሩ ሽታ ያለው የተክል አይነት፣ ናትራን::

**አራ** ግ (ነውር) 1.አይነምድር ከሰውነቱ አስወጣ፣ ተፀዳዳ:: 2.(ዘይ.) ተጨማለቀ፥ ተሞላቀቀ፥ ተንጠባረረ::

**አር** ስ 1. (ነውር) ሰገራ ወይም አይነ ምድር::2. ቆሻሻ ፥ አሰር (የቅቤ)::

**ኣሩን በላ** 1.ክፉኛ ተደበደበ:: 2.ተሰቃየ ወይም ለፋ::

**ኣሩን ይጠፈጥፋል** በጣም አርጅቷል::

**አራም** ቅ (ነውር፥ ስድብ) 1.ጨምላቃ፣ ባለጌ:: 2.ፈሪ::

**አራሙቻ "አረም"** ስር ተመ.

**አራማጅ "*ረመደ"** ስር ተመ.

**አራም "አራ"** ስር ተመ.

**አራራ "አረረ"** ስር ተመ.

**አራራይ** ስ ከሶስቱ ያሬዳዊ የዜማ አይነቶች አንዱ::

**አራስ "አረሰ**[2]**"** ስር ተመ.

**አራሽ "አረሰ**[1]**"** ስር ተመ.

**አ̈ራሽ "አረሰ**[2]**"** ስር ተመ.

**አራባ** ስ የድር፥ የጥለት፣ ... ጥቅል፥ እስር፥ ቱባ::

**አ̈ራ̊ባ "ረባ"** ስር ተመ.

**አራት** ስ 1.በሶስትና በአምስት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፬'፥ '4' ነው:: ቅ 2.በሶስትና በአምስት መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ:: *ኣራት ጫማዎች:*

**በአራቱም ማእዘን** በሁሉም አቅጣጫ::

**አራቱ መደብ** ስ የመደመር፥ የመቀነስ፥ የማባዛትና የማካፈል ስሌት አጠቃላይ መጠሪያ::

**አራት ማእዘን** ስ 1.አራት ገፅ ወይም ጎን ያለው ማንኛውም ነገር:: 2.የሰሜን፥ የደቡብ፥ የምስራቅና የምእራብ አቅጣጫዎች ጥቅል መጠሪያ:: 3. መረባ::

**አራት ነጥብ** ስ በአረፍተ ነገር ማለቂያ ወይም መደምደሚያ ላይ የሚቀመጥ ስርአተ ነጥብ (::) ::

**አራኝ** ስ ጎረዶማን::

**አራዊት**(ነጠ.ቁ. **አርዌ**) ስ 1.በዱር በገደል የሚኖሩ አውሬዎች በጥቅል የሚጠሩበት ስም:: ቅ 2.(ዘይ.) ጨካኝ፥ አረመኔ፥ ክፉ::

**አራዠ** ግ አመመ፥ አሰቃየ፥ እረፍት ነሳ፥ አናወዘ፥ አስጨነቀ (ህመም፥ መድሃኒት፥ ...)::

**አራዳ** ስ 1. በከተማ ወስጥ የሚገኝ የገበያ ቦታ:: 2.ዛሬ ፒያሳ እየተባለ የሚጠራው የአዲስ ኣበባ መሃል ከተማ የድሮ መጠሪያ:: 3.(ዘይ.) ሙሌ፥ ብልጥ፥ ቀልጣፋ::

**የአራዳ ልጅ/ሰው** ንቁ፥ ብልጥ፥ ቀልጣፋ::

**አራጅ**[1] ስ ረጅም ጅራት ያለውና ከአፉ ሞጥሞጥ ያለ፥ ቀፎ ደፍቶ ማር የሚበላ አውሬ፤ ፋደት::

**አራጅ**[2] **"አረደ"** ስር ተመ.

**አራጣ** ስ ከፍተኛ የገንዘብ ብድር ወለድ::

**አራጣ አበዳሪ** ስ በከፍተኛ የወለድ መጠን ገንዘብ የሚያበድር ሰው::

**አሬራ** ስ የረጋ ወተት ተንጦ ቅቤው ከወጣ በሂላ የሚቀረው ቀጭን ወተት::

**አርመን** ስ የጉድጓድ ወይም የግንብ ወይም የካብ የጎን ስፋት::

**አርማ** ስ የአንድ ድርጅት፥ ማህበር፥ ... ህጋዊ መለያ ወይም ምልክት::

**አርምሞ "አረመመ"** ስር ተመ.

**አርበኛ** ስ ለአገሩ፥ ለወገኑ ክብርና ነፃነት ሲል በአገር ወዳድነት ከውጭ ወራሪ ጋር የተዋጋ ጀግና::

**አርቢትር (አልቢትር)** ስ በአንድ ስፖርታዊ ውድድር ወቅት እንደ ውድድሩ አይነት ከሜዳ ውጭ ወይም በሜዳ ውስጥ በመሆን ስፖርታዊ

ህጎችን የሚቆጣጠርና ውሳኔ የሚሰጥ ሰው፤ ዳኛ።

**አርባ** ስ 1.በሰላሳ ዘጠኝና በአርባ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፵'፥ '40'። 2.አንድ ሰው ከሞተ በሂላ በአርባኛው ቀን የሚደረግ ተዝካር። ቅ 3.በሰላሳ ዘጠኝና በአርባ አንድ መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *አርባ ሰዎች*።

**አርብ**[1] ስ በሃሙስና በቅዳሜ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ስድስተኛ ቀን።

**የአርብ ውሃ** ስ አርብ እለት የተቀዳ ውሃ (ለሰንበት አክባሪዎች ተቀድቶ የሚቀመጥ)።

**አርብ**[2] ስ 1.ድር የሚቋጠርበት የሸማኔ እቃ። 2.የማንኛውም ጨርቅ ጎን ወይም ወርድ ወይም ስፋት።

**አርቲስት** ስ 1. ሰአሊ። 2.እንደ ተዋናይ፥ ዘፋኝ ዳንኪረኛ ያለ የመድረክ ሰው።

**አርቲቡርቲ** ስ ፍሬከርስኪ ፥ የማይረባ ነገር።

**አርቲፊሻል** ቅ ተፈጥሯዊ ያልሆነ፥ ሰው ሰራሽ። *አርቲፊሻል ገማገም*።

**አርታኢ** (ብ.ቁ. **አርታእያን**) ስ ብዙውን ጊዜ ሌላው ያቀረበውን ፅሁፍ (መፅሃፍ፥ መፅሄት፥...) ከህትመት በፊት የሚያስተካክልና የሚያቀነባብር ሰራተኛ፤ ኤዲተር።

**አርትኦት** ስ መፅሃፍን፥ መፅሄትን፥... በማረምና በማቃናት ለህትመት የማዘጋጀት ስራ።

**አርነት** ስ ነፃነት።

**አርአያ** ስ 1.ምሳሌ፥ አብነት። 2.ምስል፥ አምሳል፥ መልክ።

**አርእስት** ስ 1.የ "**ርእስ**"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመ. 2. በስተመነሻ በኩል በግሶች ላይ በሚቀጠል ምእላድ("መ-") አማካይነት የሚመሰረት ቃል (ግሱ በ"አ" የሚጀምር ከሆነ "መ-" ወደ "ማ-" ይለወጣል)። ለምሳሌ ብላ→ መብላት/አበላ → ማብላት።

**አርእስተ ነገር** ስ የአንድ ነገር ወይም ሃሳብ መነሻ፤ ጭብጥ።

**አርኬና** ስ የንብ አውራ ወይም የምስጥ ንጉስና ንግስት ወይም የጣዝማ መኖሪያ።

**አርያም** ስ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የእግዚአብሄር ዙፋን የተዘረጋበት ነው ተብሎ የሚታመን ከሰማያት በላይ ያለ የመጨረሻው ሰማይ።

**አርዮስ** ስ ክፉ፥ ጨካኝ፥ አረመኔ (ሰው)።

**አርድእት** ስ 1.የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የነበሩ አስራ ሁለቱ ሃዋርያትና ሰባ ሁለቱ ደቀመዛሙርት። 2.በሰባ ሁለቱ አርድእትና በሃዋርያት ስም የተፃፈ እንደአስማትና እንደ ልብወለድ ያለ መፅሃፍ።

**አርጃኖ** ስ አዞ የሚመስል፥ ቆዳው ሻካራና ጠንካራ የሆነ፥ በውሃ ውስጥና በድንጋይ ስር የሚኖር አውሬ።



አርጃኖ

**አርጩሜ** ስ ለበቅ ወይም ልምጭ።

**አሮጌ** ቅ 1.ሽማግሌ፥ ያረጀ። 2.የቆየ፥ ያረጀ፥ አዲስ ያልሆነ።

**አሮጊት** ስ ያረጀች ሴት፤ ባልቴት።

**አሰላ**[1] ግ አደባ።

**አሰላ**[2] "ሰላ[2]" ስር ተመ.

**አሰላ**[3] "ሰላ[3]" ስር ተመ.

**አሰላ**[4] "*ሰላ" ስር ተመ.

**አሰላሰለ** ግ ስለ አንድ ነገር በተመስጦ ረዘም ላለ ጊዜ አሰበ፥ አወጣ አወረደ።

**አሰረ** ግ 1.እንዳይበተን፥ እንዳይዝረከረክ ወይም አንድ ላይ እንዲሆን በክር፥ በገመድ፥ በሲባጎ፥ ... በማያያዝ ቋጠረ። 2.ጥፋተኛ ወይም ወንጀለኛ ነው ተብሎ የተጠረጠረን ወይም ጥፋተኛ ወይም ወንጀለኛ የሆነን ሰው ያዘ፥ በህግ ቁጥጥር ስር አዋለ። 3.ወዲያ ወዲህ እንዳይንቀሳቀስ አደረገ፥ አንድ ቦታ አስቀመጠ። 4.አረፍተ ነገሩን በማሰሪያ አንቀፅ ደመደመ ወይም ጨረሰ።

**እስር** ስ 1.እስረኛ። 2.ብዛቱ ከአንድ በላይ የሆነና አንድ ላይ የታሰረ ወይም በተወሰነ መጠን ተደርጎ የታሰረ ነገር። *አንድ እስር እንጨት/አንድ እስር ቅጠል*። 3.(ስነ.ል.) ራሱን ችሎ የማይቆም ወይም የማይነገር (ምእላድ)።

**እስር ምእላድ የ"እስር"**ን 3ኛ ፍቺ ተመ.

**እስር ቤት** ስ በጥፋታቸው የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ወይም ወንጀላቸው በመጣራት ላይ ያሉ ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው የሚቀመጡበት ቦታ፤ ወህኒ ቤት።

**እስረኛ** ስ 1.በህግ ቁጥጥር ስር የዋለ ወይም በእስር ቤት ያለ ሰው። 2.በስራ ወይም በተለያየ ምክንያት ከቤት የማይወጣ ወይም ወደ ውጭ ወጥቶ የፈለገውን የማይሰራ ወይም የማይዝናና ሰው።

**እስራት** ስ በህግ ቁጥጥር ስር መዋል ወይም የማዋል ድርጊት።

**ተሳሰረ** ግ 1.ተያያዘ፥ ተቆላለፈ፥ ተተባተበ።

2.ተንተባተበ፡ ተከላተፈ። *ኣንደበቱ ተሳሰረ*። 3.በቅልጥፍና ወይም በደንብ መንቀሳቀስ ኣቃተው። *ሰውነቱ ተሳሰረ*።

**አሰር**[1] ስ 1.በሙቀጫ ወይም በወፍጮ አማካይነት እንደ ገብስ፡ አጃ፡ ባቄላ፡… ካሉ የእህል ፍሬዎች ላይ እየተገለፈፈ የሚወጣ የፍሬዎቹ ሽፋን፡ ገለባ፡ ንፋሽ። 2.እፍታው የተነሳለት ወጥ።

**አሰር ውሃ** ስ የ"**ቅራሪ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**አሰር**[2] ስ ኮቴ፡ ዱካ፡ ፈለግ።

**አሰሰ** ግ 1.የሚፈልገውን ለማግኘት እየተዘዋወረ መረመረ፡ ፈተሸ፡ ፈለገ። 2.በዙሪት አዳረሰ። *ከተማውን ኣሰሰና ተመለሰ*፡ 3.ምጣድን በማሰሻ ወለወለ፡ አለሰለሰ።

**ማሰሻ** ስ 1.ለምጣድ ማለስለሻ ወይም መወልወያ የሚያገለግል የተወቀጠ ጎመን ዘር ወይም ጉሎ ወይም የጥጥ ፍሬ። 2.ለምጣድ መወልወያ የሚያገለግል እራፊ ጨርቅ።

**አሰሳ** ስ የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ መመርመር፡ መፈተሽ፡ መፈለግ።

**አሳሽ** ቅ 1.የተደበቀ ነገርን እየዞረ የሚመረምር ወይም የሚፈትሽ። *ኣሳሽ ቡድን*፡ 2.ዘዋሪ።

**አሰበ** ግ 1.በአእምሮው ውስጥ ስለአንድ ነገር አወጣ አወረደ፡ አሰላሰለ። 2.አሰላ፡ ሂሳብ አደረገ። 3. ተጨነቀ፡ ሰጋ። 4. አስታወሰ፡ ትዝ አለው። *ያለፈውን ሳስበው ይገርመኛል*። 5.አቀደ፡ ቀየሰ፡ ነደፈ። *ነገ ናዝሬት ለመሄድ ኣስቤያለሁ*፡ 6.ፈለገ፡ ፈቀደ። *ለትዳር ኣስቧታል*።7.በአንድ ጉዳይ ላይ ያገባኛል፡ ይመለከተኛል በማለት ተጨነቀ፡ ሃላፊነት ተሰማው። *ለኣገሩ ያስባል /ለቤተሰቡ ያስባል*።

**አሳቡን ጣለ** ማሰብ፡ መጨነቁን ተወ።

**አሳቢ** ቅ ሃላፊነት የሚሰማው፡ የሚጨነቅ፡ የሚቆረቆር።

**አሳብ** "**ሃሳብ**"ን ተመ.

**እሳቤ** ስ ሰንሰ ሃሳብ።

**ታሰበ** ግ 1.ትዝ አለ፡ ታወሰ። 2.ታጨ፡ ተመለመለ። *ለከፍተኛ ስልጣን ታስቧል*።

**ታስቦ ዋለ** አንድ ልዩ ነገር የተፈፀመበትና መታወስ ያለበት እለት፡ ሌሎች በኣላት በሚከበሩበት መልክ ሳይሆን በማስታወስ ብቻ ተከበረ።

**መታሰቢያ** ስ አንድን የተፈፀመ ድርጊት ወይም የሞተ ሰውን ለማስታወስ የሚደረግ ወይም የሚዘጋጅ ወይም የሚቀመጥ፡… ማንኛውም ነገር (ድግስ፡ ሃውልት፡ ህንፃ፡ ወይም ልዩ ልዩ እቃዎች)።

**ታሳቢ** ስ 1.ወደፊት ባንድነት ተጠቃሎ የሚታሰብ፡ ወደፊት የሚደመር ወይም የሚቀነስ የተወሰነ የገንዘብ መጠን። 2.አባል እንዲሆን የታሰበ፡ የታጨ።

**ተሳሰበ** ግ 1.ተሳሳ፡ ተቆጣጠረ። 2.ተረዳዳ፡ ተደጋገፈ። 3.ተፈላለገ፡ ተፈቃቀደ (ለፍቅር፡ ለጓደኝነት፡ ለጋብቻ)።

**አሳሰበ** ግ 1.አስታወቀ፡ አስገነዘበ። 2.አስጨነቀ፡ አሰጋ። 3.አሰላ፡ ሂሳብ አስደረገ። 4.ትዝ እንዲል፡ እንዲታወስ አደረገ።

**ማሳሰቢያ** ስ ማስገንዘቢያ።

**አሳሳቢ** ቅ 1.አስጊ፡ አስፈሪ። 2.አስጨናቂ።

**አስተሳሰበ** ግ 1.አንዱ ለሌላው እንዲያስብ፡ እንዲጨነቅ አደረገ። 2.አገዘ፡ አብሮ አሰላ (ሂሳብን)።

**አስተሳሰብ** ስ አመለካከት።

**አሰንዳቦ** ስ በኮትቻ ወይም በዋልካ መሬት ላይ የሚበቅልና ከብቶች የሚበሉት ፍሬ ያለው የሳር አይነት።

**አሰኘ**[1] ግ አስፈለገ፡ አማረ። *ቡና ኣሰኝቶኛል*።

**አሰኘ**[2] "*ሰኘ" ስር ተመ.

**አሰድ [እሳት]** ስ በሃምሌ ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት፡ በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.


**አሰገረ**[1] ግ አጠመደ (አሳን)።

**አሰገረ**[2] ግ አንድ ቀን አሳለፈ፡ ዘለለ። *በዚህ ወር ሰኞ የዋለችው ልደታ በሚቀጥለው ወር ማክሰኞን ኣሰግራ ረቡእ ትውላለች*፡

**አሲድ** ስ 1.ከተለያዩ ንጥረ ነገሮች የሚገኝ፡ ፈሳሽ የሆነ፡ የመርዝነት ባህሪ ያለውና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ኬሚካላዊ ንጥረ ነገር። 2.እንደ ሎሚ፡ ብርቱካን፡ ኮምጣጤ፡ … ባሉ ፍራፍሬዎች ውስጥ የሚገኝና የሚኮመጥጥ ጣእም ያለው ንጥረ ነገር።

**አሲዳም** ቅ 1.(ስድብ) ቢበላ የማይጠረቃ፡ ሆዳም። 2.ልብስ ጫማ፡ ገንዘብ፡ … ቶሎ የሚያልቅበት ወይም የማይበረክትለት።

**አሳ** ስ በስንጥቡ እየተነፈሰ በውሃ ውስጥ የሚኖርና ከውሃ ውጭ ሊኖር የማይችል፡ ለምግብነት የሚያገለግል ውሃ ውስጥ ከሚኖሩ ፍጥረታት አንዱ።



አሳ

**አሳ ለቃሚ** ስ የወንዝ አሙቴ፥ ምንቃረ ረዥም የሆነችና አሳ እየበላች የምትኖር አሞራ።

**አሳ ነባሪ (አሳ አንበሪ)** ስ በውቅያኖስ ውስጥ የሚኖርና ከአጥቢ እንስሳት ጋር የሚመደብ በጣም ትልቅ የአሳ አይነት።



አሳ ነባሪ

**አሳ አውጪ** ስ አሳ ለቃሚ።


**አሳ አድን** ስ ነጭና ጥቁር መልክ፡ አጭርና ሹል ምንቃር፥ እንዲሁም አጭር ቅልጥም ያለው፡ ብዙውን ጊዜ በሃይቆች አካባቢ የሚገኝና አሳ በመመገብ የሚኖር፡ በመጠን ዋኔን የሚያክል የወፍ አይነት።

**አሳ አጥማጅ** ስ አሳን አጥመዶ በመሸጥ የሚተዳደር ሰው፥ አሳ አስጋሪ።

**አሳ ወርቂት** ስ መካከለኛ መጠንና ወርቃማ መልክ ያለው የአሳ አይነት።

**[የ]አሳ ዘይት** ስ በባህር ውስጥ ከሚገኝና ትልቅ ከሆነ አንድ አይነት የአሳ ጉበት የሚዘጋጅ፥ቫይታሚን "ዲ"ና "ኤ" ያለው፥ ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የዘይት አይነት።

**አሳማ** ስ 1.ሸካራው ድፍን፡ እግሮቹ አጫጭሮች፥ አፉ ሞጥሞጥ ያለ፥ ያገኘውን ነገር የሚመገብ፥ ከአጥቢ እንስሳት ወገን የሚመደብ እንስሳ። 2.(ስድብ፥ ዘይ.) ሆዳም፥ በቃኝ የማይል ።



አሳማ

**አሳማ "ስማ"** ስር ተመ.

**አሳማ "አማ"** ስር ተመ.

**አሳር** ስ መከራ፥ ጭንቅ፥ ስቃይ።

**አሳሩን በላ** ተሰቃየ፥ ተቸገረ፥ መከራውን አየ።

**አሳረኛ** ቅ መከረኛ፥ ጎስቋላ።

**አሳሽ "አሰሰ"** ስር ተመ.

**አሳቢ "አሰበ"** ስር ተመ.

**አሳብ "ሃሳብ"**ን ተመ.

**አሳቻ "ሳተ"** ስር ተመ.

**አሳጣ "አጣ"** ስር ተመ.

**አሳጣ** ግ 1.አጋለጠ፥ አጋፈጠ። 2.ስሞታ አሰማ።

**አሳጭ** ቅ አጋፋጭ።

**አስ—**(ሰዋ.) ከግስ በፊት እየገባ አስደራጊነትን ወይም አድራጊነትን የሚገልፅ እስር ምእላድ። *መጣ → አስመጣ/ተኛ → አስተኛ።*

**አስማት** ስ ለበጎ ወይም ለመጥፎ ነገር ማስፈፀሚያ ይሆናል ተብሎ የሚደረግ ድግምት፥ ምትሃት።

**አስማተኛ** ስ አስማት ማድረግ የሚችል ሰው፥ ምትሃተኛ።

**አስም** ስ የመተንፈስ ችግር የሚያስከትል የበሽታ አይነት።

**አስር** ስ 1.በዘጠኝና በአስራ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፥ በአሃዝ ሲፃፍ '፲'፡ '10' ነው። 2.ቅ በዘጠኝና በአስራ አንድ መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *አስር ተማሪዎች።*

**አስር አለቃ** ስ ከአምሳ አለቅነት በፊት የሚሰጥ ወታደራዊ ማእረግ።

**አስር ጊዜ (አስሬ)** በተደጋጋሚ። *አንዴ ነግሬሀኛል አስር ጊዜ አትጨቅጭቀኝ።*

**አስርቱ ቃላት/ትእዛዛት** ስ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተፃፈው ከእግዚአብሄር በሙሴ በኩል ለሰዎች የተሰጡ አስሩ ትእዛዛት።

**አስራት** ስ ከአስር አንድ የሚከፈል ግብር።

**አስራት በኩራት** ስ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ በታዘዘው መሰረት ለእግዚአብሄር ወይም ለቤተ መቅደስ የሚሰጥ የእህል፡ የወይን፡ የዘይት አስራት፥ እንዲሁም የሰው ወይም የእንስሳ የመጀመሪያ ወይም የበኩር ልጅ።

**አስቤስቶስ** ስ ነጭ ወይም ግራጫ መልክ ያለውና ለስላሳ የሆነ የቃጫ ክር የሚመስል፡ በሰሌዳ ወይም በቆርቆሮ መልክ የሚሰራና እሳት ወይም ሙቀትን መቋቋም የሚችል፡ ከመሬት ውስጥ የሚገኝ ማእድን።

**አስቤዛ** ስ የወር የቤት ወጪ።

**አስብ** ስ ለእረኛ፥ ለቤት ሰራተኛ፡ ... የሚሰጥ የስራ ዋጋ፥ ምንዳ።

**አስተምህሮ "*መሃረ"** ስር ተመ.

**አስተነከረ** ግ አስረገጠ፡ አፅንኦት ሰጠ። *መልእክቱን አስተንክረሀ ንገርልኝ።*

**አስተናበረ** ግ 1.አንድን ስብሰባ ወይም ዝግጅት አቀናበረ፡ አዘጋጀ፥ መራ። 2.አሳለፈ፡ በስርአት እያስቀመጠ አስተናገደ፡ ጋበዘ (በድግስ፡ በግብዣ፡... ጊዜ)።

**አስተናባሪ** ቅ 1.አንድን ስብሰባ ወይም ዝግጅት የሚያቀነባብር፥ የሚመራ:: 2.አስተናጋጅ፡ አሳላፊ (በድግስ፥ በግብዣ፡... ላይ)፡

**አስተናግር (እፀፋርስ)** ስ ቅጠሉ ለስላሳና ሰፋ ሰፋ ያለ፥ ግንዱ ውስጠ ክፍት ሆኖ በእሾህማ ሽፋን ውስጥ የታቀፉ ጥቋቁርና ጠፍጣፋ ፍሬዎች ያሉት አነስተኛ የእፅዋት አይነት::

**አስተኔ** እንደ_ ያለ፥ _መሰል በማለት ብጤን ወይም አይነትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል:: *ቢጫ ኣስተኔ*::

**አስተዋለ** ግ 1. አተኩሮ ተመለከተ፡ በደንብ አየ:: 2. ተገነዘበ፥ አጤነ::

**አስተዋይ** ቅ 1.ብልህ፥ አዋቂ፥ የሚያመዛዝን:: 2.ተመልካች፥ ታዛቢ::

**አስተያየት "አየ"** ስር ተመ.

**አስተጋባ** ግ 1.አንድን የድምፅ አይነት ተቀብሎ እንደገና ጎላ አድርጎ ወይም ጮክ ብሎ አሰማ:: 2.የሌላውን ሰው ሃሳብ ወይም አስተያየት እንደሰውየው ሆኖ ገለፀ ወይም አስታወቀ:: 3.አንድን ሃሳብ ወይም አስተያየት ለሌሎች ገለፀ ወይም አስታወቀ::

**አስታ (አስቴ)** ስ 1.በደጋ አካባቢ ችፍግ ብሎ የሚበቅል፥ ቅጠሉ የጥድ ቅጠል የሚመስል የቁጥቋጦ አይነት (እንጨቱ ሲሰበቅ እሳት ይወጣዋል):: 2.እንጨትን በእንጨት በመሰበቅና በማፋተግ እሳት የማውጣት ድርጊት:: 3.በአስቴ እሳት የተተኮሰ የክንድ ላይ ጠባሳ::

**አስትሮኖሚ** ስ ስለ ፀሃይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብትና ስለመሳሰሉት አካላት የሚያጠና የእውቀት ዘርፍ::

**አስከሬን** ስ ህይወት የሌለው ወይም በድን የሆነ የሰው አካል፡ ሬሳ::

**አስከሬን መስሏል** በጣም ከስቷል::

**አስኳል** ስ 1.በዶሮ፡ በወፍ፡... እንቁላል ውስጥ የሚገኝ ቢጫው ክፍል:: 2. (ዘይ.) ዋና ፍሬ ነገር::

**አስፋልት** ስ ከተፈጨ ድንጋይና ከሬንጅ ድብልቅ ለሙጥ እንዲሆን ተደምጦ የተሰራ መንገድ::

**አሸ** ግ 1.እህልን ወይም ፍሬን ከገለባ ወይም ከሽፋኑ ለመለየት በሁለት እጆቹ መዳፍ መሃል በማስገባት አፍተለተለ:: 2.በደንብ እንዲገናኝ ወይም እንዲዋሃድ አድርጎ አቦካ (ሊጥን፡ ተልባን፡...):: 3.አለፋ፡ አለሰለሰ (ቆዳን):: 4.ወለምታን ለመመለስ፡ ውልቃትን ለማጠም፡ ሙቀትን ለማግኘት ወይም እድፍን ለማውጣት ሰውነትን በእጅ አፍተለተለ:: 5.ቆሻሻው እንዲለቅ በደንብ ፈገፈገ፡ አጠበ (ልብስን፡ሠሌዳን፡...):: 6. በደንብ አድርጎ ደበደበ፡ ረገጠ:: 7.ቀጠቀጠ፡ አኮላሸ (የበሬን፥ የበግን፥... አባለ ዘር):8.አለፋ፥አደከመ፥ደጅ አስጠና::

**ታሸ** ግ 1.ተለጠጠ፡ ተጀነነ:: *ስጠይቀው እየታሸ መለሰልኝ*፡ 2.ለገመ፥ ፈጠን ብሎ ለመስራት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ::

**ተሻሸ** ግ 1.ሰውነት ለሰውነት ተነካካ፡ ተፋተገ:: 2.ሰውነትን እርስ በእርስ ተደባበሰ (ተቃራኒ ፆታ):: 3.ከመታሸት፥ ከመፋተግ የተነሳ ተበላሸ፥ ተጎሳቆለ (ወረቀት፥ ፋይል፥...)::

**አሻሸ** ግ ደባበሰ፥ ዳሰሰ:: *ፀጉሩን ኣሻሸ*:

**አሸለ** ግ 1.ጨመረ፡ አከለ:: 2.ለካ፥ ከነዳ::

**አሻል** ስ በሂላ የተደረ ተጨማሪ ድር::

**እሽል** ቅ ተጨማሪ::

**አሸመ** ግ ወደውስጥ ጎነጎነ፥ ቆነነ፡ ሰራ (ፀጉርን)::

**እሽም** ስ በወፍራሙ የተጎነጎነ የፀጉር አሰራር አይነት::

**አሸቦ (አሻቦ)** ስ ጥሬ ጨው::

**አሸቦ መሰለ** ነጫጭባ፡ አመዳም ሆነ::

**አሸን** ስ መሬት ውስጥ ተፈልፍሎ ከቆየ በሂላ፥ ብዙውን ጊዜ በክረምት መግቢያ አካባቢ ከጉድጓዱ በብዛት እየወጣ የሚርመሰመስና ወደ ሰማይ የሚበር የምስጥ አይነት፥ ክረምት አግቢም ይባላል::


አሸን

**አሸን ነው** ከብዛቱ የተነሳ ቁጥሩን መገመት ያስቸግራል፡ እጅግ ብዙ ነው::

**እንደ አሸን ፈላ** በብዛት ወጣ፥ ታየ::

**አሸንክታብ** ስ በረዥም ማተብ ላይ ከወርቅ ወይም ከብር፥ ... የተሰሩ ትናንሽ ጌጦች የተሰኩበት በአንገትና በአንድ ትከሻ ብቻ የሚጠለቅና በሁለተኛው ትከሻ በኩል ከብብት ስር እስከ ዳሌ የሚደርስ የሴቶች ጌጥ::

**አሸንዳ** ስ 1.ከብረት ወይም ከቆርቆሮ፥... የሚሰራ፥ በቤት ክፈፍ ዙሪያ የሚውል፥ ውስጡ ክፍት የሆነ የውሃ መውረጃ፡ ጎረንዳዮ እየተባለም ይጠራል:: 2.ፈሳሽ ነገር የሚያልፍበት እንደ ቱቦ ያለ ነገር::

**አሸከት "አሸከት"**ን ተመ.

**አሸዋ** ስ በወንዝ፥ በባህር ዳርቻና በበረሃማ አካባቢ የሚገኝ ደቃቅ የድንጋይ አይነት::

**አሸዋ ግርፍ** ስ በአሸዋ፥ በደቃቅ ጠጠርና በሲሚንቶ ድብልቅ የተለሰነ የቤት የውጭኛው

ግድግዳ::

**አሸዋማ** ቅ አሸዋ የበዛበት (ስፍራ)::

**አሸገ** ግ 1.እንዳይገለጥ ወይም እንዳይፈታ ጠቅልሎ በማሸጊያ ኣያያዘ፥ ሸፈነ (እቃን):: 2.በመጣበቅ ወይም በሙጫ ዘጋ (ፖስታን):: 3.ከሚመለከተው ወይም ባለሙበት ከሆነ አካል በስተቀር በሌላ አካል እንዳይከፈት በላዩ ላይ ማህተምና ፊርማ የተደረገበትን ዕሁፍ በመለጠፍ ዘጋ (ለምሳሌ ቤትን፥ ካዝናን፥ ...):: 4.(ምግብን፥ መጠጥን፡ መድሃኒትን፥ ...) በቆርቆሮ ወይም በላስቲክ፥ ... ውስጥ ጨምሮ መረገ፡ ዘጋ፥ ደፈነ::

**እሽግ** ቅ የተጠቀለለ ወይም የታሸገ ማንኛውም እቃ (ብዙውን ጊዜ ገና አገልግሎት ላይ ያልዋለ እቃ)::

**የታሸገ ምግብ** ስ በቆርቆሮ፡ በጠርሙስ፥ በላስቲክ፡... ውስጥ በመታሸግ የተዘጋጀና ለገበያ የሚቀርብ ምግብ::

**አሹ** እሰይ፡ እንኳን፡ ይሁን ለማለት የሚባል ቃል::

**አሹራ** ስ በንብረት ሽያጭ ጊዜ ለመንግስት የሚከፈል ግብር::

**አሹቅ** "ሾቀ" ስር ተመ.

**አሻ[1]** "ሻ[2]" ስር ተመ.

**አሻ[2]** አይ፡ አይሆንም፡ አይደለም::

**አሻል[1]** ስ 1.ቀይነትና ነጭነት ያለው ጨው ወይም አሸቦ:: 2.በመረሬና በቀይ አፈር መካከል ያለ ለስላሳ መሬት፡ አቦልሴ:: 3.በአራት እግሮቹ ጫፍ ላይ ነጭ ያለበት እንስሳ (በሬ፡ ፈረስ፡...):: ቅ 4.ግንባሩ ላይ ነጭ ያለበት (እንስሳ)::

**አሻል[2]** "**አሸለ**" ስር ተመ.

**አሻመደ** ግ በላ (በብዛት)::

**አሻራ** ስ የጣት የውስጠኛ ክፍል እንደ መስታወት ባለ አካል ላይ ሲያርፍ የሚተወው ዱካ ወይም ጣትን ቀለም አስነክቶ ማንኛውም ነገር ላይ ሲጫኑት የሚታየው ምልክት::



አሻራ

**አሻራ ቢስ** ቅ እድለ ቢስ፥ ገደ ቢስ::

**አሻሮ** ስ ለጠላ መጥመቂያ የሚሆንና በመጠኑ አረር እስኪል የተቆላ የገብስ ወይም የስንዴ ወይም የበቆሎ እህል::

**አሻሮ ሆነ** አረረ::

**አሻቦ** "**አሸቦ**"ን ተመ.

**አሻንጉሊት** ስ በልዩ ልዩ ቅርፅና አምሳል (በሰው፡ በእንስሳ፥ ...) ከጨርቅ፡ ከፕላስቲክ፥... የሚሰራ የልጆች መጫወቻ::

**አሻጥረኛ** "**ሻጠረ**" ስር ተመ.

**አሻጥር** ዝ.ክ.

**አሻፈረ**

**አሻፈረኝ አለ** ግ እምቢ፡ አልታዘዝ፥ አልሰራ፡ አልፈፅም፥ ... አለ::

**አሽሙር** ስ አግቦ፡ሽሙጥ፡ ምፀት::

**አሽሙረኛ** ቅ አግቦኛ፥ አሽሟጣጭ::

**አሽሟጣጭ[1]** ስ በጎራዴ አፎት ጫፍ ላይ የሚገኝ ድቡልቡል ጌጥ::

**አሽሟጣጭ[2]** "**ሽሞጠጠ**" ስር ተመ.

**አሽቆመቆመ** "**ሽቆመቆመ**" ስር ተመ.

**አሽከር** ስ 1.ሎሌ፡ አገልጋይ:: 2.እድሜው ከ7-15 አመት የሆነ ልጅ፡ ብላቴና (ጎንደር፥ ጎጃም)::

**አሽኩቲ** ስ እንደ በሶ ብላ ያለ፡ አበባው ቢጫ የሚመስልና ሽታው ጣፋጭ የሆነ የእፅዋት አይነት::

**አሽክላ** ስ 1.ለቀፎ ወይም ለወጥመድ መስሪያ የሚያገለግል፡ ፍሬውን ልጆች ለጌጣጌጥ መስሪያ የሚጠቀሙበት የሃረግ አይነት:: 2.መአዛው ጣፋጭ የሆነና ለጥርስ መፋቂያ የሚሆን የእፅዋት አይነት::

**አሽክት (አሸክት)** ስ መልኩ ጠቆር ያለና መጠኑ ድንብላል የሚያክል፡ ጠጣር ፍሬ ያለው እሾክማ የሆነ ሃረግ መሰል አነስተኛ የእፅዋት አይነት:: ፍሬውም አሽክት ይባላል::

**አሽንበበ** ግ 1. ነገር አጣመመ:: 2.አሽቀበጠ:: 3. ዳርዳሩን ዞረ፡ አስፈራራ::

**አሽንባቢ** ቅ 1.ነገረ ጠማማ:: 2.አሽቃባጭ::

**አሽንበጠ** ግ አሽሟጠጠ::

**አሽንባጭ** ቅ አሽሟጣጭ::

**አሾለቀ** ግ አሾልኮ፡ አጮልቆ አየ::

**አቀረቀረ** ግ አንገቱን ጎንበስ አደረገ፡ መሬት መሬት አየ::

**ኣቀበ** ግ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ለመስዋእት የሚሆነውን ስንዴ በመልቀምና በመፍጨት ቤተክርስቲያንን አገለገለ::

**አቃቢ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) ለመስዋእት የሚሆን ስንዴ በመልቀምና በመፍጨት እንዲሁም ለበዐል የሚሆን ውሃ ቀድቶ በማቅረብ ቤተክርስቲያንን የሚያገለግል ባህታዊ፥ መነኩሴ::

**አቃቢት** ስ የአቃቢነት ስራ የምታከናውን መነኩሲት።
***አቀበ**
**ታቀበ** ግ ተቆጠበ (ከመናገር ወይም ከማድረግ)።
**ተአቅቦ** ስ "ድምፅ" ስር "ድምፀ ተአቅቦ"ን ተመ.
**አቀበት (አቀብ)** ስ ዳገት።
**አቀንቀነ**[1] ግ አቀመቀመ፥ አበቀለ (ቢም)።
**አቀንቀነ**[2] "ቀንቀነ[2]"ን ተመ.
**አቀንጭራ** በፍጥነት የሚስፋፋና በእህል ሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ የአረም አይነት፣ ደሃ ነቀል።
**አቀደ** ግ ወጠነ፥ ነደፈ፥ ቀየሰ።
**አቅድ** ስ 1.እቅድ። 2.ስልት፥ ዘዴ፥ ብልሃት። *የጦር ሰቅድ ያውቃል*። 3.መልክ፥ ስርአት፥ ጥሩ ቅርፅ። *የቤቱ አሰራር አቅድ የለውም*።
**አቅደ ቢስ** ቅ ያልተስተካከለ፥ የማያምር።
**እቅድ** ስ በተወሰነ ጊዜ ሊሰራ የተወጠነ፥ የታሰበ፥ የተቀየሰ ስራ።
**አቀጠለ** ግ 1. ከተቆረጠ ወይም ከተመለመለ በሁላ እንደገና ቅጠል አወጣ፥ አቆጠቆጠ። 2.ጠገነ፥ ዳነ፥ እንደበፊቱ ሆነ (የተሰበረ አጥንት)።
**አቀፈ** ግ 1.በክንዱ ወደ ደረቱ አስጠግቶ ያዘ። 2.ከበበ፥ በዙሪያ ሆነ። *ሲሊንደሩን ሳቅፎ የያዘው ብረት ዝግል*። 3.አስጠጋ፥ በስሩ ያዘ። *ሀዝቡ ሽፈቶቹን አቅፎ ይዟቸዋል/ መስሪያ ቤቱ በስሩ ሶስት ድርጅቶችን ያቅፋል*።
**ማቀፊያ** ስ 1.መታቀፊያ። 2.አንድን ነገር ዙሪያውን አቅፎ የሚይዝ። *ሳምፖል ማቀፊያ /ወረቀት ማቀፊያ*።
**አቃፊ** ቅ የ"ማቀፊያ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.
**እቅፍ** ቅ 1. በአንድ ጊዜ በአንድ ወይም በሁለት ክንድ መሃል ሊያዝ የሚችል መጠን። *ሳንድ እቅፍ እንጨት*። 2.አንድን ነገር አቅፎ ለመያዝ የሚያስችል የክንድና የደረት አካባቢ።
**እቅፍ አበባ** ስ ለስጦታ እንዲሆን በርከት ብሎና በአንድ ላይ ታስሮ የተዘጋጀ አበባ።
**እቅፍ ዶሮ** ስ 1.በሁለት ክንፎቿ ውስጥ ጫጩቶቿን የታቀፈች ዶሮ። 2.ጫጩቶችን ለመፈልፈል እንቁላል ታቅፋ የተቀመጠች ዶሮ።
**እቅፎሽ** ስ እቅፍ።
**ታቀፈ** ግ በክንዱ ወይም በእጁ ወደ ደረቱ ጠጋ አድርጎ ያዘ።
**መታቀፊያ [ጨርቅ]** ስ ህፃን ልጅን ጠቅልሎ ወይም ሸፍኖ ለመያዝ የሚያገለግል ጨርቅ፥ ፎጣ፥...።
**አሳቀፈ (አስታቀፈ)** ግ 1.ጫጩቶች እንድትፈለፍል ዶሮን እንቁላሎቿ ላይ እንድትቀመጥ አደረገ። 2.ደግፎ እንዲይዘው ዙሪያውን አደረገ (አፈርን፥ ድንጋይን በተክል ዙሪያ)።
**አስታቅፎ ሄደ** ለሌላ ሰው ትቶ ወይም ጥሎ ሄደ። *ልጆቹን አስታቅፋው ሄደች/ ሃብቱን ለሚስቱ አስታቅፏት ሄደ*።
**አቁላ** ስ የጅራፉን እጀታና ጅራፉን የምታያይዝ ቀጭን ገመድ(ስእሉን ጅራፍ ስር ተመ.)።
**አቁማዳ** ስ ስልቻ።
**አቁዳማ** ስ በጥንት ጊዜ ጀብዱ የሰራ ሰው ግንባሩ ላይ የሚያንጠለጥለው ጌጥ።
**አቁጣሮ** "ቆጠረ" ስር ተመ.
**አቃሰተ** "ቃሰተ" ስር ተመ.
**አቃቂር** ስ ቁንጥ።
**አቃቂር አወጣ** ቁንጥ አወጣ።
**አቃቂር አውጪ** ቅ ቁንጥ አውጪ።
**አቃቂረኛ** ቅ አቃቂር የሚያወጣ።
**አቃቅማ** ስ በቆላማ አካባቢ መሬት ላይ ተለጥፎ የሚበቅል የእሾህ አይነት፣ ኩርንችት።
**አቃቢ** " አቀበ" ስር ተመ.
**አቃቢት** ዝ.ከ.
**አቃቤ ህግ** ስ ህጎች መከበራቸውንና በትክክል በስራ ላይ መዋላቸውን የሚቆጣጠር፣ ህገወጥ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ የሚከላከልና ከተፈፀሙም ተከታትሎ ለፍርድ የሚያቀርብ የመንግስት ሹም ወይም አካል።
**አቃቤ ስራይ** ስ የባህል መድሃኒት አዋቂ።
**አቃተ** ግ 1.ተሳነ። 2.አስቸገረ፥ አልበገር አለ፥ አሸነፈ።
**አቃፊ** "አቀፈ" ስር ተመ.
**አቅል** ስ አደብ፥ ትእግስት።
**አቅለ ቢስ** ቅ ጠልጧላ፥ ከውካዋ፣ ትእግስት ወይም አደብ የሌለው።
**አቅማማ** ግ አንድን ነገር ላድርግ ላላድርግ ብሎ አሰበ፣ አወላወለ፥ እመንታ።
**አቅም** ስ ችሎታ፥ ጉልበት፥ ሃይል፥ ብርታት። *ይህንን ለማከረዳት አልቻልም ከአቅሜ በላይ ነው /ገንዘብ ከበድ ነው ለመግዛት አቅም የለኝም*።
**ለአቅመ ሄዋን ደረሰች** በእድሜና በአካል ከልጅነት ወደ ኮረዳነት ከፍ አለች፥ ወደ እናትነት ደረጃ ደረሰች፣ ቆነጀች።
**ለአቅመ አዳም ደረሰ** በእድሜና በአካል ከልጅነት ወደ ጉርምስና ደረጃ ከፍ አለ፥ ወደ

አባትነት ደረጃ ደረሰ።

**አቅሙን አያውቅ** ከችሎታው፡ ከጉልበቱ፡... በላይ ለማድረግ የሚሞክር ወይም የሚመኝ።

**ከአቅም በላይ ሆነ** አስቸጋሪ፡ ከባድ ሆነ።

**አቅመ ቢስ** ቅ ጉልበት የሌለው፡ ደካማ።

**አቅራቢያ "ቀረበ"** ስር ተመ.

**አቅራብ [ውሃ]** ስ በጥቅምት ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪ **"ኮከብ ቆጠራ"**ን ተመ.

**አቅርቦት "ቀረበ"** ስር ተመ.

**አቅድ "አቀደ"** ስር ተመ.

**አቅጣጫ** ስ 1.አንፃር፥ መስመር፥ በኩል። *ፀሃይ ሁልጊዜ በስተምስራቅ አቅጣጫ ትወጣለች።* 2.አዝማሚያ፥ ሁኔታ። *የነገሩ አቅጣጫ አላማረኝም።*

**አቆረ** ግ (ጎድጓዳ ቦታ) ውሃ ቋጠረ፥ ያዘ፥ አጠራቀመ። 2.በስራ ወይም በህመም ምክንያት ሰውነት ደም ወይም መግል ያዘ።

**አቆር አለ** ግ በመጠኑ አበጠ፥ እትራት አወጣ።

**አቆስጣ** ስ በብዛት ጠቆር ያለ መልክ ያለው፥ ከቁመቱ ጋር ሲወዳደር ርዝመቱ ትልቅ የሆነ፥ በውሃ ውስጥና ከውሃ ውጪ መኖር የሚችል፥ አጭርና ጥቅጥቅ ያለ ሆኖ እንደሃር የለሰለሰ ፀጉር ያለው፥ እንደ አሳ፥ እንቁራሪት፥... ያሉትን እንስሳት የሚመገብ አውሬ።

**አቋም "ቆመ"** ስር ተመ.

**አበለ** ግ 1.ዋሸ፥ ቀጠፈ። 2.ሸፈጠ። 3.ፍሬ፥ ምርት አልሰጥ አለ። *መሬቱ አበለ።*

**አባይ** ቅ ዋሾ፥ ቀጣፊ።

**አባይ ሚዛን** ስ በትክክል የማይመዝን ወይም ጎደሎውን እንደሙሉ አድርጎ የሚያሳይ ሚዛን።

**አባይ ጠንቋይ** ስ ሊሆን ወይም ሊደረግ የማይችለውን ይሆናል፥ ይደረጋል እያለ ሰዎችን የሚያታልል፥ አዋቂ ነኝ ባይ ጠንቋይ።

**እብለት** ስ ውሸት፥ ቅጥፈት።

**አስተባበለ** ግ የተባለው ነገር ውሸት ነው አለ። *ስለግድያው የተሰራጨውን ወሬ አስተባበለ።*

**አበል "በላ"** ስር ተመ.

**አበልጅ** ስ አንዱ የሌላውን ሰው ልጅ ክርስትና በማንሳቱ ምክንያት በመካከላቸው የሚፈጠር የዝምድና አይነት (አንሺውም ሆነ የልጁ ወላጆች እርስ በርሳቸው አበልጅ በመባባል ይጠራራሉ)።

**አበምኔት "ምኔት"** ስር ተመ.

**አበረ** ግ አንድ ሆነ፥ ተባበረ።

**አብሮ** በአንድ ላይ፥ በአንድነት ሆኖ። *ከእሱ ጋር አብሮ ይሰራል።*

**አብሮ አደግ** ስ በአንድ አካባቢ አብሮ ያደገ የእድሜ እኩያ።

**አባሪ** ስ በተጨማሪ መረጃነት ወይም ማረጋገጫነት ከዋናው ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የፅሁፍ ማስረጃ።

**አባሪ ተባባሪ** ቅ አጋዥ፡ ረዳት (በጠብ፡ በወንጀል ድርጊት ላይ)።

**ተባበረ** ግ ተጋገዘ፡ ተረዳዳ፡ በህብረት ሆነ።

**ተባባሪ** ስ በሃሳብ፡ በስራ፥... አጋዥ፡ ረዳት።

**ትብብር** ስ 1.አንድነት፥ ህብረት። 2.መረዳዳት፥ መተጋገዝ።

**አስተባበረ** ግ አንድ የሆነ ጉዳይን እንዲያከናውኑ የተለያዩ ወገኖች አንድ ላይ እንዲሆኑ አደረገ፥ አሰባሰበ።

**አስተባባሪ** ቅ 1.አንድ የሆነ ጉዳይ እንዲያከናውኑ የተለያዩ ወገኖች አንድ ላይ እንዲሆኑ የሚያደርግ፥ የሚያሰባስብ፡ የሚያቀናጅ። 2.የስራ ሃላፊ፥ ተቆጣጣሪ።

**አበሰ** ግ 1.ጠረገ፥ ወለወለ። *ጠረጴዛውን በጨርቅ አብሰው/ወጡ ስለአለቀ ድስቱን አብስህ ብላ።* 2.ቀባ። *ፊትህ አመድ መስሏል ቅባት አብስ አድርገው።*

**እባሽ** ቅ 1.ጥራጊ፥ ትራፊ (የወጥ)። 2.ወጥ የነካው፥ ትራፊ (እንጀራ)።

**እብስ አደረገ** ግ ሙጥጥ፥ ጥርግ አደረገ።

**ተባበሰ** ግ ተቀባባ (ሰውነትን በቅባት)።

**አበሱዳ** ስ ጥቁር አዝሙድ።

**አበሳ** ስ 1.መከራ፥ ስቃይ፥ ፍዳ። 2.ጥፋት፥ ሃጢአት፥ በደል።

**አበስኩ ገበርኩ** ሰዎች የሚያስደነግጥ ወይም የሚያስፈራ ነገር ባዩ ወይም በሰሙ ጊዜ ከእንደዚህ አይነት ሰውረን፥ አድነን ለማለት የሚጠቀሙበት አባባል።

**አበሻ "ሃበሻ"**ን ተመ.

**አበቀ**[1] ግ እያመቀና እየጠቀጠቀ ከእቃ ውስጥ ከተተ፥ ጨመረ (ለምሳሌ ዱቄትን)።

**አበቀ**[2] ግ ወጋ። *በጦር አበቀው።*

**አበቀ**[3] ግ የቀጠነ ሊጥን ዱቄት በመጨመር እንዲወፍር አደረገ።

**አበቅ** ስ 1.እብቅ። 2.እክክ፥ ደረመን።

**አበበ** ግ 1.አበባ አወጣ። 2.አማረ፥ ደመቀ፥ አሸበረቀ።

**አበባ** ስ 1.ማንኛቸውም የእፅዋት አይነቶች የፍሬ ጊዜያቸው ሲደርስ ፍሬያቸውን የሚመሰርቱበት፥ ከእንቡጥ ውስጥ ተሸልቅቆ የሚወጣና እንደ እፅዋቱ የዝርያ አይነት የተለያየ ቀለም፥ ቅርፅና መጠን ያለው የእፅዋቱ አካል፥

የእፅዋቱ ፍንድ:: 2.አይን የሚስብና ለጌጥ የሚሆን ውብ ቀለም ያለው አበባ የሚያወጣ የተክል አይነት::

**አበባ ምንጣፍ** ስ በአበባ ንድፍ ወይም ምስል የተጌጠ የምንጣፍ አይነት ወይም ስጋጃ::

**አበባ ጎመን** ስ የአበባ ቅርፅ ያለውና ቅጠሉ ጥቅል ጎመን የሚመስል፥ መጠኑ ትንሽ የሆነ የጎመን አይነት::



አበባ ጎመን

**የአበባ ማስቀመጫ** ስ ለጌጥ ሲባል አበባ ተቆርጦ የሚቀመጥበት፥ የተለያየ ቅርፅና መጠን ያለው፥ ከብርጭቆ ወይም ከሸክላ ወይም ከፕላስቲክ፥... የሚሰራ እቃ::

**የአበባ እህል** ስ አበባው ጎላ ብሎ የሚታይ እንደ ባቄላና አተር ያለ የእህል አይነት::

**የአበባ ጉንጉን** ስ ክብ ወይም ሌላ አይነት ቅርፅ ባለው ነገር ላይ ዙሪያውን አበባ በመሰካት የሚዘጋጅና በአንድ ውድድር (ሩጫ፥ ኳስ ጨዋታ፥...) ተወዳድሮ ላሸነፈ ወይም የጀግንነት ስራ ለሰራ፥... የሚበረከት ወይም በቀብር ስነስርአት ጊዜ በመቃብር ላይ የሚደረግ አበባ::

**አበተ** ግ አሰረ::

**ማበቻ** ስ ለማሰሪያነት የሚያገለግል እንደ ገመድ ያለ ማንኛውም ነገር::

**አበኑስ** ስ ትንሽ ጣባ ወይም ቆሬ::

**አበክሮ "*በከረ"** ስር ተመ.

**አበው** (ነጠ.ቁ.**አብ**) ስ የቀድሞ ሰዎች፤ ሽማግሌዎች፥ አባቶች::

**አበይት "አቢይ"**ን ተመ.

**አበደ** ግ 1.አእምሮው ተቃወሰ፥ የአእምሮ ህመምተኛ ሆነ:: 2.በጣም ተናደደ:: 3.ወደደ፥ አፈቀረ:: 4.ከገደብ ያለፈ ወይም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ፈፀመ::

**አበደላት** በጣም አፈቀራት::

**በ—ያበደ** በ—ጥሩ ሆኖ የተሰራ:: (ምግብ፥ መጠጥ፥...):: *በቅመም ያበደ ሻይ::*

**እብድ** ቅ ቀውስ፥ ወፈፌ፥ የአእምሮ ህመምተኛ::

**እብድ ቀን** ስ ያሰቡት ያልሆነበት ወይም ያልተሳካበትና ትርምስ የበዛበት ቀን::

**እብድ ውሻ** ስ አእምሮውን የታመመ ውሻ::

**እብደት** ስ 1.በአእምሮ መታመም ወይም መቃወስ የተነሳ የሚመጣ በሽታ:: 2.ከመጠኑ ያለፈ ወይም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት::

**አሳበደ** ግ በጣም አሳመረ፥ አስጌጠ:: *ስእሉን አሳብዶ ሰራው::*

**አበደም** ስ ጠላት፥ ባላጋራ (በነፍስ ግድያ ምክንያት)::

**አበገደ** ስ ጥንታዊ የግእዝ ቋንቋ ፊደል ተራ::

**አበጋዝ ስ "ጦር"** ስር "የጦር አበጋዝ"ን ተመ.

**አበጠ[1]** ግ 1.ተነፋ፥ ተነረተ (ሰውነት):: 2.ተጀነነ፥ በትእቢት ተወጠረ:: 3-አኮረፈ::

**አባጣ** ቅ አበጥ ያለ ወይም እባጭ ያለበት:: 2-ጉብታ ወይም ከፍታ::

**አባጣ ጎባጣ** ቅ ወጣ ገባ ወይም ያልተስተካከለ::

**እበጥ** ስ እባጭ::

**እባጭ** ስ እንደ እጢ ሆኖ ሰውነት ላይ የሚወጣ የበሽታ አይነት::

**እብጠት** ስ በህመም ወይም በመመታት ምክንያት የሰውነት ማበጥ፥ መነረት::

**አበጠ[2]** ግ አወከ፥ ረበሸ፥ በጠበጠ:: *ልጁ ኣልተኛም ብሎ ሲያብጠን ዋለ::*

**አቡነ ዘለብ** ስ የበቅሎን ወይም የፈረስን የጭራ ስር ከኮርቻ ጋር የሚያያዝ ጠፍር(ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)::

**አቡን** ስ የጳጳስና የኤጲስ ቆጶስ የወል መጠሪያ::

**አቡነ—** የጵጵስና ወይም የኤጲስ ቆጶስነት ስልጣን ካላቸው የቤተክርስቲያን ሰዎች ስም ጋር እየተጣመረ ለመጠሪያነት የሚያገለግል የማእረግ ስም:: *ኣቡነ ሰላማ::*

**አቡጀዲ** ስ በፋብሪካ የሚሰራና ነጣ ያለ ቀለም ያለው የጨርቅ አይነት::

**አቡጊዳ** ስ በቤተክህነት ትምህርት ቤት ከሀሁ ቀጥሎ ከመልእክተ ዮሃንስ በፊት የሚሰጥ የፊደል ትምህርት::

**አቢይ** (ብ.ቁ.**አበይት**) ቅ ትልቅ፥ ዋና::

**አቢይ ሃረግ** ስ (ሰዋ.) የአንድን አረፍተ ነገር ዋና ግስ ወይም ማሰሪያ አንቀፅ የያዘ ሃረግ::

**አቢይ ፆም** ስ ሁዳዴ፥ ፆመ ኢየሱስ፥ ፆመ አርበአ::

**አባ[1]** ስ ከስም ጋር እየተጨመረ ወይም ለብቻው በመሆን ወንድ መነኩሴን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል:: ትርጓሜውም አባት ማለት

ነው።

**አባሆይ** ስ ወንድ መነኩሴን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል።

**አባ²** ግ ሸሸገ፥ ደበቀ። *ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል።*

**አባ—**1.የ– ባለቤት፥ የ–ጌታ እንደ ማለት ሲሆን በአብዛኛው ለፈረስ ከሚወጡና ጀግንነትን ከሚገልፁ ስሞች ጋር በማጣመር የፈረሱን ባለቤት በፈረሱ ስም ለመጥራት የሚያገለግል የቅፅል ስም። *አባታጠቅ /አባበዝብዝ/ አባዳኘው/አባጠቅል* ... ። 2.የአንድን ሰው ጠባይ፥ ስራ፥... ለመግለፅ ከጠባዩ ወይም ከስራው ቀድሞ የሚገባ የቅፅል ስም። *አባመስጠት = ቸር፥ ለጋስ።*

**አባሆይ "አባ¹"** ስር ተመ.

**አባለዘር** ስ 1.የወንድ ብልት ወይም ሃፍረተ ስጋ። 2.የወንድ ወይም የሴት ብልት።

**የአባለዘር በሽታ** ስ አብዛኛውን ጊዜ በግብረ ስጋ ግንኙነት ሳቢያ የሚተላለፍ እንደ ቂጥኝና ጨብጦ ያለ በሽታ።

**አባል** ስ የቡድን፥ የማህበር፥ የድርጅት፥... አካል ወይም ማህበርተኛ። *የፓርቲ አባል።*

**አባሎ** ስ በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፥ ፍሬው ለጠላና ለወተት እቃ ማጠኛ የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

**አባሪ "አበረ"** ስር ተመ.

**አባር** ቅ ድርቅ፥ በና።

**አባሰንጋ** ስ የከብት በሽታ አይነት።

**አባበለ "*ባበለ"** ስር ተመ.

**አባባ "ባባ¹"** ስር ተመ.

**አባባ** ስ 1.አባቴ ለማለት ልጆች አባታቸውን የሚጠሩበት ቃል ወይም የተዘምዶ ስም። 2. ሽማግሌዎች ፥ አባውንቶች የሚጠሩበት የአክብሮት ቃል ወይም ስም።

**አባተ¹** ግ አየለ፥ በረታ፥ የበላይ ሆነ፥ በቁጥጥር ስር አደረገ፥ አሸነፈ።

**አባተ² "ባተ"** ስር ተመ.

**አባት** ስ ያታው ተባእታይ የሆነ ትልቅ ወንድ ወይም ወንድ ወላጅ የሚጠራበት የወል ስም።

**ያባት ነው** ደንብ፥ ወግ፥ ስርአት ነው። *ወላጆችን መርዳት ያባት ነው።*

**አባወራ** ስ የቤተሰብ ሃላፊ፥ አስተዳዳሪ (ወንድ)።

**አባዜ** ስ 1.መጥፎ ቁራኛ፥ ሞገድ፥ እልክ። 2.ችግር፥ እንቅፋት።

**አባያ** ቅ 1.በደንብ የማያርስ፥ የሚለግም (በሬ)። 2.ልግመኛ፥ አልምጥ።

**አባዬ** ስ ልጅ አባቱን የሚጠራበት ቃል ወይም የተዘምዶ ስም።

**አባይ "አበለ"** ስር ተመ.

**አባጀሀኝ** ስ በበጋ ወራት ሳይደርቅ ለአመት ያህል ጥቅም የሚሰጥ የጎመን አይነት።

**አባጎንዳ** ስ አሚናፗ ላሊበላ።

**አባጣ "አበጠ"** ስር ተመ.

**አባጨጓሬ** ስ 1.የሚኮስኩስና ጨፍራራ ፀጉር ያለው ትል። 2.(ዘይ.) ፀባዩ አስቸጋሪ የሆነ (ሰው)።

**አቤት** 1.ወንድ ሲጣራ "አለሁ፥ ምን ልታዘዝ፥.." ለማለት በስም የተጠራው ሰው ለጠሪው የሚያሰማው ትህትናን የተላበሰ የመልስ ቃል። 2.የሚያስደንቅ ወይም የሚያስገርም ነገር ሲታይ ወይም ሲሰማ አድናቆትን ወይም መገረምን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *አቤት! ምን ያህላል።*

**አቤት አለ** ግ አቤቱታ አቀረበ ወይም አሰማ፤ አመለከተ።

**አቤት ባይ** ቅ አቤቱታ የሚያቀርብ።

**አቤቱታ** ስ በደል ደርሶብኛል የሚል ሰው በደሉን ለበላይ ባለስልጣን ወይም ለሚመለከተው ለሌላ ሰው በቃል ወይም በፅሁፍ የሚያቀርበው ፍሬ ሃሳብ፥ ክስ፥ በደል።

**አቤቱታ አቀረበ/አሰማ** አቤት አለ።

**አብላሊት** ስ አለብላቢት።

**አብራክ**

**ከአብራኬ የወጣ/የተከፈለ[ ልጅ]** የወለድኩት ልጅ።

**አብሲት** ስ እንጀራን ለማለስለስና ለማሳመር ሲባል የቦካ ሊጥ ላይ የሚጨመር የፈላ ውሃ ወይም ከቡኮው ተቀንሶ በፈላ ውሃ የሚበጠበጥ ሊጥ።

**አብሲት ጣለ** አብሲት አዘጋጅቶ በሊጥ ላይ ጨመረ።

**አብሽ** ስ ፍሬው አነስ ያለና መልኩ ቢጫ የሆነ፥ በጣም የሚመር፥ ተፈጭቶና ተበጥብጦ የሚጠጣ ወይም በቅመምነት የሚያገለግል የቅመም አይነት። ተክሉም አብሽ ይባላል።

**አብሽሎ** ስ ከዳጉሳ ወይም ከበቆሎ፥... የሚዘጋጅ የጠላ ቂጣ።

**አብሾ** ስ ፍሬውን ወይም ቅጠሉን ሲበሉት ለተወሰነ ጊዜ የሚያሰክር ወይም አእምሮ የሚለውጥ አደንዛዥ እፅ።

**አብሿም** ቅ 1.አብሾ ጠጥቶ አእምሮው የተነካ፥ ወፈፍተኛ። 2.ትንሽ ጠጥቶ የሚሰክር፤ ሰካራም።

**አብነት¹** ስ ምሳሌ፥ አርአያ።

**አብነት²** ስ1. ከተለያዩ ስራስሮችና ቅጠላ ቅጠሎች የሚቀመምና የሚደገምበት የባህል

መድሃኒት:: 2.የጠለቀ ትምህርት ያለውና እውቅ መምህር፣ ምስክር:: *ኣለቃ አገሌ የብሉይና የሃዲስ ኪዳን ትርጉም ኣብነት ነበሩ::*

**አብዛኛው** "በዛ" ስር ተመ.

**አብዬ** ስ ልጅ አባቱን አባዬ፣ አባቴ ለማለት ወይም አንድ ሰው ታላቁን ወይም ሽማግሌዎችን ቍአዛውንቶችን የሚጠራበት የተዘምዶ ወይም የአክብሮት ቃል ወይም ስም::

**አብዮት** ስ በአንድ ነገር ክስተት ወይም ሂደት ውስጥ ያሉ ቅራኔዎች ተካረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚፈጠር መሰረታዊ ለውጥ፤ አዲስ ከፍተኛና የተሻለ ነገር፣ ክስተትና ሂደት ወይም አስተሳሰብና እውቀት የሚከሰትበት::

**አቦል [ቡና]** ስ በአገር ባህል የቡና አፈላል ልማድ በመጀመሪያው ዙር ላይ ተፈልቶ የሚቀዳው ቡና::

**አቦልሴ** ቅ የነጭና የቀይ ቀለም ቅይጥ መልክ ያለው (ጤፍ፡ አፈር፣...):: *ኣቦልሴ መሬት:*

**አቦሬ** ስ አፈ ሰፊ የሆነ ትልቅ ሸክና::

**አቦሬ አፍ** (ስድብ) ቅ 1.አፉ ትልቅ ወይም ሰፊ የሆነ (ሰው):: 2.(ዘይ.) ሳያስብና ሳያመዛዝን እንዳመጣለት የሚናገር (ሰው)::

**አቦስጥ** ስ መላምት፡ ግምት:: *ፈተናውን በኣቦስጥ ሰራሁት:*

**አቧራ (አዋራ)** ስ ደቃቅ አፈር ወይም ትቢያ::

**አቧራማ** ቅ አቧራ የበዛበት (ቦታ)::

**አተላ** ስ 1.ጠላ ተጠጥቶ ካለቀ በሂላ ከስሩ የሚቀረው ዝቃጭ:: 2.የማንኛውም ፈሳሽ ነገር ዝቃጭ::

**አተመ** ግ 1.በማተሚያ መሳሪያ ፃፈ:: 2.በማህተም ረገጠ ወይም ማህተም አደረገ:: 3.አሸገ፣ ዘጋ (ደብዳቤን)::

**ህትመት** ስ በማተሚያ መሳሪያ አማካይነት ፅሁፍን የማተም ስራ::

**ማህተም** ስ 1.በአንድ መስሪያ ቤት፡ ድርጅት ወይም ማህበር ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት እንደ መለያ የሚሆነው የመስሪያ ቤቱ፡ የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ስም ወይም አርማ በላዩ ላይ የተቀረፀበትና ቀለም ላይ እየተረገጠ ምልክቱን በደብዳቤዎች፣ በማስታወቂያዎች፣... ላይ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ከእንጨት ወይም ከብረት፣ ... የሚሰራ ምልክት ማድረጊያ የፅህፈት መሳሪያ:: 2.ከላይ በተጠቀሰው መሳሪያ በመጠቀም በደብዳቤዎች፣ በማስታወቂያዎች፣ ... ላይ የሚቀመጥ ምልክት::

**ማተሚያ** ስ ልዩ ልዩ ፅሁፎችንና ቅርፆችን አትሞ ወይም ቀርፆ የሚያወጣ መሳሪያ::

**ማተሚያ ቤት** ስ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን በመፅሄት፣ በመፅሃፍ፣... መልክ በማተሚያ መሳሪያ እያተመ የሚያወጣ ድርጅት::

**አታሚ** ቅ አሳታሚ::

**እትም** ስ በአንድ ዙር ታትሞ የሚወጣ የአንድ መፅሃፍ፣ መፅሄት፣ ጋዜጣ፣ ... ቅጂ በሙሉ:: *ኣንደኛ እትም፣ ሁለተኛ እትም፣...::*

**ታተመ** ግ 1.ማተሚያ ቤት ገብቶ በማተሚያ መሳሪያ ታትሞ (ተፅፎ) ወጣ (መፅሃፍ፣ መፅሄት፣ ጋዜጣ፣...):: 2.ታሸገ፡ ተዘጋ::

**አሳተመ** ግ መፅሃፍ፣ መፅሄት፣ ጋዜጣ፣... አዘጋጅቶ ለህትመት አበቃ አትሞ አወጣ::

**አሳታሚ [ድርጅት]** ስ በሌላ አካል የሚቀርቡ ረቂቅ መፃህፍትን፣ መፅሄቶችን፣ ጋዜጦችን፣... ሃላፊነት በመውሰድ አዘጋጅቶ እንዲታተሙ የሚያደርግ ድርጅት::

**አተረ** ግ እንደ አተር ድድር ወይም ጥጥር ብሎ አበጠ::

**አተር** ስ ድቡልቡል ፍሬዎቹ በሸፉን ውስጥ ድርድር ብለው የሚገኙና አገዳው እንደ ሃረግ ሆኖ የሚያድግ የአበባ እህል::

**አተሬ [ቂጥኝ]** ስ የአተር ፍሬ መስሎ የሚወጣ የቂጥኝ አይነት::

**እትራት** ስ እንደ አተር ፍሬ ያለ እብጠት::

**አተበ** ግ እትብት ቆረጠ::

**አታቢ** ቅ እትብት የመቁረጥ እውቀት ያለው ሰው::

**እትብት** ስ ህይወት ያለው ፍጡር በእናቱ ማህፀን ውስጥ ባለበት ጊዜ፡ ከእናቱ ምግብ የሚያገኝበት ከእምብርቱ ጋር የተያያዘ የምግብ ማመላለሻ አካል::

**ታተበ** ግ እትብቱ ተቆረጠ::

**አተተ** ግ በዝርዝር አብራራ፡ ተነተነ (በፅሁፍ፣ በቃል)::

**ሃተታ (አተታ)** ስ 1.በአንድ ሃሳብ ላይ በዝርዝር የሚቀርብ ማብራሪያ:: 2.ዝርዝር ወሬ:: *በኣጭሩ ተናገር ሃተታ ኣታብዛ:*

**ታተተ** ግ ተብራራ፡ በዝርዝር ቀረበ::

**አተካሪስ** "ተካሪስ" ን ተመ.

**አተካራ** ስ ንዝንዝ፣ ጭቅጭቅ::

**አቱች** ስ ለባህል መድሃኒትነት የሚጠቀሙበት አነስተኛ የእፅዋት አይነት::

**አታሚ** "አተመ" ስር ተመ.

**አታሞ** ስ አነስተኛ ከበሮ::

**አታቢ** "አተበ" ስር ተመ.

**አታክልት** "ተከለ" ስር "አትክልት"ን ተመ.

**አቴቴ** ስ የዛር አይነት::

**አቴና** ስ ከቀርከሃ ወይም ከሸንበቆ እንደ ቅርጫት

እየተታታ የሚሰራ የቤተ ክርስቲያን ወይም የቤተ መንግስት ወለል ንጣፍ (ይህ ንጣፍ ይሰራ የነበረው የቤት ወለል በሳንቃ፡ በሲሚንቶ፡ … በማይሰራበት ጊዜ ነበር)፡፡

**አትላስ** ስ የተለያዩ የመልክአ ምድር ካርታዎች ብቻ ያሉበት መፅሃፍ፡፡

**አትሌቲክስ** ስ ሩጫ፡ ዝላይና ውርወራን የሚያጠቃልል የስፖርት አይነት፡፡

**አትሌት** ስ በሩጫ፡ በዝላይና በውርወራ የሰለጠነ ስፖርተኛ፡፡

**አትሮንስ** ስ ባለ ሶስት ወይም ባለ አራት እግር ተደርጎ ከእንጨት ወይም ከብረት የሚሰራና መፅሃፍ እላዩ ላይ ተዘርግቶ ለማንበቢያነት የሚያገለግል ብዙ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ እቃ፡፡



አትሮንስ

**አትክልት "ተከለ"** ስር ተመ.

**አትኳር** ስ እንደ አንፋር ያለ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት፡፡

**አቶ** ቅ እንደ ደጃዝማች፡ ዶክተር፡ …ያለ የማእረግ ስም ከሌላቸው ትላልቅ ወንዶች ስም ጋር እየተጣመረ የሚነገር የአክብሮት ስም ወይም መጠሪያ፡፡ *አቶ ታምራት*፡

**አቶሚክ (አውቶሚክ)** ቦንብ ስ ከአቶም የሚሰራ ቦንብ፡፡

**አቶም** ስ የአንድ ቁስ አካል የመጨረሻው ትንሹ ክፍል ወይም ንጥረ ነገር፡፡

**አቶሳል** ስ ጠቆር ያለ የስንዴ አይነት፡፡

**አቻ** ቅ እኩያ፡ በእኩል ደረጃ የሚገኝ፡፡

**አነር** ስ ምድቡ ከድመትና ከነብር ወገን የሆነ፡ አካሉ ወርቅማ ሆኖ ጥቋቁር መቃጠቆና ሽንትሮች ያሉበት፡ እንደአይጥ፡ እንሽላሊት፡ ዶሮ፡ … ያሉትን የሚመገብ የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንሳስ ስር ተመ.)፡፡

**አነሰ** ግ 1.ቀነሰ፡ ጎደለ (መጠን፥ ብዛት)፡፡ 2.ዝቅ አለ (ደረጃ፥ ጥራት)፡፡
ቢያንስ በትንሹ፡፡ *ለልብሱ ቢያንስ መቶ ብር ያስፈልገዋል*፡፡

**አናሳ** ቅ ትንሽ፡፡

**አነስተኛ** ቅ ትንሽ የሆነ፥ ዝቅተኛ (በብዛት፡ በመጠን፥ በደረጃ)፡፡

**ታናሽ** (ብ.ቁ.**ታናናሽ**) ቅ 1.በእድሜ ከሌላው የሚያንስ ወይም ትንሽ የሆነ፡፡ 2.ትንሽ እህት ወይም ወንድም፡፡ *ታናሼ በቁመት ትበልጠኛለች*፡ 3.ከስጋ ብልቶች አንዱ የሆነው የበሬ የፊት እግር፡፡

**ትንሽ (ብ.ቁ.ትንንሽ፥ ትናንሽ)** ቅ 1.ያነሰ፥ ዝቅ ያለ (በእድሜ፡ በመጠን፥ በማእረግ)፡፡ 2. ጥቂት፡፡

**ትንሽ ሰው ነው** ወራዳ፥ ባለጌ ነው፡፡

**ትንሽ ጣት** ስ ከቀለበት ጣት ጎን በዳር በኩል የምትገኝ፡ ከሌሎቹ ጣቶች አጠርና ቀጠን ያለች ጣት(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)፡፡

**አነቀ** ግ 1.ጉሮሮን በመያዝ፥ በማሰር፥ … መተንፈስ ከለከለ፡፡ 2.በጉሮሮ ውስጥ ተወተፈ፥ አልወርድ አለ (ምግብ)፡፡ 3. **አድብቶ ወይም** ተደብቆ በድንገት ያዘ፡፡ *ሌቦቹ በጨለማ ሰው እያነቁ ይዘርፋሉ*፡

**ማነቆ** ስ 1.በተበሳ ቀንበር ውስጥ ገብቶ በበሬው አንገት ግራና ቀኝ የሚውልና በሬው እንደፈለገው ወዲያና ወዲህ እንዳይንቀሳቀስ የሚያግድ የእርሻ እቃ (ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)፡፡ 2.እንቅፋት፡፡ *ስራው እንዳይቀላጠፍ ቢሮክራሲው ትልቅ ማነቆ ሆነብን*፡

**ታነቀ** ግ 1.በገዛ እጁ ራሱን በገመድ ወይም በቀበቶ፡ … አነቀ ወይም ሰቀለ፡፡ 2.በጉሮሮው ውስጥ በተወተፈ ወይም አልወርድ ባለ ምግብ፥ … የተነሳ መተንፈስ አቃተው፡፡

**ተናነቀ** ግ 1.ታገለ፡፡ 2.ሊወጣ ፈለገ (ትውኪያ)፡፡

**ትንቅንቅ** ስ 1.ግፊያ፡ ትርምስ፡፡ 2.ትግል፡፡

**አነበ** ግ ንብ አረባ፡፡

**ንብ** በፊደል ተራው ተመ.

**አነባ** ግ አለቀሰ፥ እንባ አፈሰሰ፡፡

**እንባ (እምባ)** ስ ሲለቀስ ወይም አይን ላይ ጉዳት ሲደርስ ከአይን የሚወጣ ውሃ መሳይ ፈሳሽ፡፡

**በእንባ ተለያዩ** ተላቅሰው ተለያዩ፡፡

**በእንባ ተራጩ** በጣም ተላቀሱ፡፡

**እንባ በእንባ ሆነ** በጣም አለቀሰ፡፡

**እንባ አነቀው (ተናነቀው)** ከውስጥ ፈንቅሎ በወጣ ሃዘን፥ ብስጭት ምክንያት እንባው ተንቀረዘዘ፥ ለማልቀስ ወይም ለማንባት ተቃረበ፡፡

**እንባ እንባ አለ** ጨው በጣም አነሰው፡፡

**እንባ እንባ አለው** እንባው መጣበት፡

አልቅስ የሚል ስሜት ያዘው።

**እንባው ረገፈ** እንባው ፈሰሰ።

**እንባው ቅንዝፍ ቅንዝፍ አለ** እንባው ዱብ ዱብ አለ፥ ፈሰሰ።

**እንባውን አወረደው** አለቀሰ፥ አነባ።

**እንባውን ጠጣ** የመጣበትን እንባ እንደምንም ብሎ እንዳይፈስ አደረገው።

**እንባ አስመጪ ጋዝ** የሚያስለቅስ ወይም እንባ የሚያስመጣ የጋዝ ጭስ(ብዙ ግዜ ስልፍ ወይም ግርግር ለመበተን የሚያገለግል)።

**እንባ አድርቅ** ስ 1.ለቀባሪ የሚቀርብ ንፍሮ። 2.ድምፀ መጥፎ አልቃሽ። 3.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ..) ከሬሳ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን የሚወሰድ እንጀራና ጠላ።

**እንባ ጠባቂ** ስ ፍርድ አስተካካይ፥ እውነተኛ ዳኛ፥ ለድሃ ተቆርቋሪ የሆነ ሹም።

**አነባበሮ "ነበረበረ"** ስር ተመ.

**አነከለ** ግ አነከሰ።

**አንካላ** ቅ አንካሳ።

**አነከሰ** ግ በህመም ወይም በሌላ ጉዳት የተነሳ አንድ እግሩ በደንብ ሳይረግጥ አንደኛው ብቻ በደንብ እየረገጠ ተራመደ።

**አንካሳ** ቅ 1.በህመም ወይም በሌላ ጉዳት የተነሳ በአንድ እግሩ ብቻ በደንብ እየረገጠ የሚሄድ፤ ሽንካላ። 2.ያልተሟላ፥ ያልተስተካከለ (ሃሳብ፥ ስራ፥ ...)።

**የአንካሴ የወላንሴ** አንድ እግርን በማጠፍ በሌላው (በሁለተኛው) እግር እየዘለሉ በመሄድ የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ።

**አስነከሰ** ግ አንካሳ አደረገ።

**አነገረ** ግ ያልበሰለን የኮሽም ወይም የቅሞ ፍሬ መሬት ውስጥ ቀብሮ እላዩ ላይ እሳት በማንደድ እንዲበስል አደረገ።

**አነገበ** ግ 1.ተሸከመ፥ ያዘ። 2. አነገተ።

**አነገተ** ግ የአንድን እቃ ማንገቻ በትከሻ ወይም በአንገት ላይ በማድረግ እቃውን ተሸከመ፥ አነገበ፥ አንጠለጠለ።

**ማንገቻ** ስ 1.አንድን እቃ በትከሻ ወይም በአንገት ላይ ለማንጠልጠል የሚረዳና ከእቃው ጋር የታሰረ ጠፍር ወይም ገመድ ወይም ሌላ ነገር። 2.በጥብጣብ ወይም በቀበቶ መልክ የሚዘጋጅና በሁለቱም ትከሻዎች ላይ አልፎ በወገብጌ ጀርባና ፊት በኩል የሚያያዝ ወይም የሚሰፋ እንደጉርድ ቀሚስና ሱሪ ያሉ የልብስ አይነቶች አካል።

**አንጋች** ስ የጦር መሳሪያ በመታጠቅ እንደ አሽከር ሆኖ ጌታውን የሚያጅብ ወይም የሚጠብቅ ወታደር።

**እንግት** ስ የአንጋች የጦር መሳሪያ ወይም ትጥቅ።

**አነጎጠ** ግ 1.አነቀፈ፥ መታ። 2.በነገር ነካ ወይም ነጎጠ።

**አንጉጥ** ቅ (ስድብ) ነገር ቆስቋሽ፥ በነገር የሚወጋ።

**አነጠነጠ "ነጠነጠ"** ስር ተመ.

**አነፀ (አነጠ)** ግ 1.ጠረበ፥ ላገ። 2.ሰራ፥ ገነባ።

**ህንፃ** በፊደል ተራው ተመ.

**አናፂ (አናጢ)** ስ ከእንጨት የሚሰሩ ቤቶቸንና እቃዎችን የሚሰራና የሚጠግን ባለሙያ።

**ታነፀ** ግ 1.ተጠረበ፥ ተላገ። 2.ተሰራ፥ ተገነባ (ህንፃ፥ ሃውልት፥ ...)።

**አኒሳ** ስ በዳሌ ስጋ አካባቢ የሚገኝና ውስጡ ቅባት ያለው፥ በቀላሉ የሚታኘክ የእንስሳት አጥንት።

**አናት** ስ 1.መሃል ራስ፥ ጭንቅላት። 2.እንጥል። *ልጁ አናት ወረደው።*

**አናቱ (አናቷ) ላይ** በትክክል። *ሁለትሰአት አናቱ ላይ እንገናኝ።*

**አናት ላይ ወጣ** 1.የበላይ ሆነ፥ በቁጥጥር ስር አደረገ። 2.ባለገ፥ አልታዘዝ አለ፥ ከስነ ስርአት ውጪ ሆነ።

**አናናስ** ስ አበቃቀሉ እንደ እሬት ሆኖ አነስ ያለና ስሩ ተገምሶ ውስጡ የሚበላ የፍራፍሬ አይነት።

**አናደለ** ግ 1.ጠገበ፥ ተቤተ። 2.ዘለለ፥ ጨፈረ።

**አናጠረ** ግ 1.ዘለለ፥ ጨፈረ። 2.ተኩራራ፥ ተቤተ። 3.ከበረ፥ በለፀገ።

**አናፂ "አነፀ"** ስር ተመ.

**አናፈለ "ናፈለ"** ስር ተመ.

**አናፈረ "ናፈረ"** ስር ተመ.

**አናፋ** ግ 1.ጮሀ፥ ድምፅ አሰማ (አህያ)። 2.በሃይል ጮሀ፥ ደነፋ።

**አንሲያጠጠ "ሰጠጠ"** ስር ተመ.

**አንስታይ "እንስት"** ስር ተመ.

**አንሶላ** ስ ከጥጥ ወይም ከሌላ ለስላሳ ከሆነ ጨርቅ በብርድ ልብስ ቅርፅ ጥንድ ሆኖ የሚዘጋጅና አንደኛው በፍራሽ ላይ የሚነጠፍ ሌላኛው ደግሞ ከብርድ ልብስ ስር የሚለበስ ሳሳ ያለ የሌሊት ልብስ።

**አንቀላፋ** ግ 1.አንጎላቸ። 2.አሸለበ፥ ተኛ። 3.ፈዘዘ፥ ጀለ፥ ነሆለለ። 4.ሞተ።

**እንቅልፍ** ስ አይንን በመጨፈንና አካልን በማሳረፍ አእምሮና የስሜት ህዋሳት፥ ... ለተወሰነ ጊዜ የሚያገኙት እረፍት።

**እንቅልፋን ለጠጠ** ጥሩ እንቅልፍ ወሰደው፥ በደንብ ተኛ።

**እንቅልፍ አጣ** 1.እንቅልፍ ሳይወስደው፥ ሳይዘው ቀረ። 2.ሃሳብ ገባው፥ በጣም አሰበ።

**እንቅልፍ ወሰደው** አሸለበ፥ ተኛ።

**እንቅልፍ ያዘው** ዝ.ከ.

**እንቅልፋም** ቅ 1.ንቅልፍ የሚያበዛ። 2.ፌዛዛ፥ ነሁላላ ።

**አንቀልባ** ስ ተፍቆ ከተለፋ ቆዳ የሚሰራና ለህፃን ልጅ ማዘያ የሚያገለግል ስስና ለስላሳ ቆዳ።

**አንቀርሻ** ስ በጣም የጠቆረ፥ ጥቀርሻ የሚመስል ነገር።

**አንቀፅ** ስ 1.የአረፍተ ነገር ማሰሪያ፤ ግስ። 2.በፅሁፍ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ በአዲስ መስመር የሚጀምርና ብዙ አረፍተ ነገሮችን ሊይዝ የሚችል አዲስ ሃሳብ ወይም ጭብጥ። 3.በህግና ህግ ነክ በሆኑ ፅሁፎች ውስጥ በተለያዩ ርእሶች ለሚከፋፈሉ ደንቦች ወይም ድንጋጌዎች እንደመክፈያ ሆኖ የሚያገለግል ርእስ ነገር።

**አንቃ (አንቋ)** ስ በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፥ እንጨቱ ከርቻ ለመስራት ወይም በዋና ጊዜ ጀርባ ላይ ታዝሎ ለመንሳፈፍ የሚያስችል፥ እንደ አሱቴ ሲሰበቅ እሳት ሊወጣው የሚችልና ቀላልነት ያለው የእፅዋት አይነት።

**አንቃር** ስ 1. የጉሮሮ የላይኛው ክፍል። 2.እንጥል። 3.የሚዛን ልሳን፥ ውልብልቢት።

**አንቃር መታው** አስታወከው።

**አንቃሩን ቅቤ ያልነካው** ሲጮህ ወይም ሲያለቅስ ድምፁ የሚሰቀጥጥ።

**አንቆላለጨ** ግ ላይስጥ እያሳየ አጓጓ፥ አጎመዠ።

**እንቁልጭልጭህ (እንቁልልጭህ)** እንቁልጭልጮሽ።

**እንቁልጭልጮሽ (እንቁልልጮሽ)** ስ አንድን ነገር እያሳዩ የማጓጓት፥ የማስጎምዠት ድርጊት (የልጆች ድርጊት)።

**አንቋ** "**አንቃ**"ን ተመ.

**አንቋለጠ** (ነውር) ግ 1.ቂጡን ወደፊትና ወደሃላ ወዘወዘ፥ ናጠ (ለወሲብ ድርጊት በሚመስል መልክ)። 2.ነገር ወዲያና ወዲህ ወሰደ፥ አዋሸከ፥ አጣላ።

**አንቋሊት** ስ አይብ።

**አንቋረረ** ግ ለቅሶ በሚመስል ድምፅ ጮሀ፤ እንደ እንቁራሪት ያለ ድምፅ አሰማ።

**አንበል** "**አምበል**"ን ተመ.

**አንበሳ (አምበሳ)** ስ 1.ከድመት ወገን ካሉት እንስሳት ሁሉ የሚበልጥ፥ ፀጉሩ ወርቃማ ቢጫ ሆኖ ሆዱ ላይ ትንሽ ነጣ የሚል፥ ረጅም ጅራትና ጋማ ያለው በደን ውስጥ በረጃጅም ዛፎች ስር የሚኖር ሃይለኛና አስፈሪ የሆነ ስጋ በል የዱር እንስሳ። ሴቷ አንበሳ ጋማ የላትም(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)። 2.(ዘይ.) ጀግና፥ ደፋር።

**አንበሳ መደብ** ስ ሽንት ቤት ወይም ሰገራ ቤት (የንጉስ)።

**አንበጣ** ስ 1.በበረሃ አሸዋ ውስጥ የሚፈለፈልና ሳር፥ ቅጠልና ሰብል የሚበላ፥ በክንፍ የሚበር የነፍሳት አይነት። 2.(ስድብ፥ ዘይ) ሆዳም፥ ከርሳም፥ በልቶ የማይጠግብ።

**አንቡላ** "**አምቡላ**"ን ተመ.

**አንብር** ስ (ኢ.አ.ተ.ቤ) መግቻን ወይም ማቆሚያን የሚያሳይ የዜማ ምልክት ( )።

**አንባባ** "*ባባ" ስር ተመ.

**አንቧቃ** ቅ ፈሪ፥ ቡከን፥ በቅዧቃ።

**አንተ** ተው. ስ በስም ምትክ እየገባ ለሁለተኛ መደብ፥ ነጠላ ቁጥርና ተባእታይ ፆታ የሚያገለግል ቃል፤ ተውላጠ ስም።

**አንቱ** ተው.ስ የሁለተኛ መደብ፥ ነጠላ ቁጥር የአክብሮት መጠሪያ።

**አንቱታ** ስ አንቱ ማለት፥ የአክብሮት አጠራር ወይም አነጋገር።

**አንቴና** ስ ለሬዲዮ ወይም ለቴሌቪዥን ድምፅንና ምስልን ከአየር ተቀብሎ የሚያስተላልፍ ሽቦ መሰል መሳሪያ።

**አንቺ** ተው.ስ በስም ምትክ እየገባ ለሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥርና አንስታይ ፆታ መጥሪያ የሚያገለግል ቃል፤ ተውላጠስም።

**አንከሊስ** ስ 1.ኩፍኝ። 2.ደካማ፥ አቅመቢስ፥ ከሳሳ።

**አንከርት** "**እንክርት**"ን ተመ.

**አንካላ** "**አነከለ**" ስር ተ.መ.

**አንካሳ** "**አነከሰ**" ስር ተመ.

**አንካሴ** ስ ለመቆፈሪያ ወይም ለመውጊያ እንዲያገለግል መጠነኛ ውፍረት ባለው ዘንግ ላይ የተሰካ ሹል ብረት።

**አንካቦ** ስ 1.ትልቅ ዋንጫ። 2. (ዘይ.) ትልቅ ወይም ሰፊ እግር (የሰው)። 3. ከሰሌን ወይም ከገሳ የተሰራ የጨው መያዣ።

**አንኬል** ስ እንደማቶት ያለና ከብረት ወይም ከሃረግ፥... የሚሰራ ክብ የእቃ ማስቀመጫ።

**አንክሮ**

**በአንክሮ** በአድናቆት፥ በመገረም።

**አንኮ** ስ 1.የዝንጀሮ መንጋ፤ ጅር። 2. የዝንጀሮ መጥሪያ ቃል። ቅ 3.(ዘይ.) ቂል፥ ጅል፥ ከርፋፋ።

**አንኮላ** ስ 1.ለውሃ መቅጃ የሚያገለግል ከወደ ቂጡ በኩል ያለው የቅል ጉማጅ:: ቅ 2.(ዘይ.) ሞኝ፥ ቂል፥ እንከፍ::

**አንኳር** ቅ 1.ያልፈራረሰና አንድ ላይ ተያይዞ ያለ የስኳር፥ የጨው፥... ኳል:: 2.ዋና ፍሬ ነገር:: *ዝርዝር ውስጥ ሳትገባ የጉዳዩን አንኳር ብቻ ንገረኝ:*

**አንኳኳ** "ኳ[1]" ስር ተመ.

**አንዠት** "**አንጀት**"ን ተመ.

**አንደርቢ (አንደርብ)** ስ አንድ ሰው የጠላቱ ቤት እንዲቃጠል ወይም የሚበላው ምግብ ቆሻሻ እንዲነዛበት፥... ያደርጋል ተብሎ የሚታመንበት ድግምት፥ አስማት::

**አንደበት** ስ ለመናገር የሚያስችል የሰውነት ክፍል፤ ልሳን::

**አንደበቱ ተዘጋ** ዝም አለ፤ መናገር ተሳነው::

**አንደበቱ ተፈታ** መናገር ጀመረ (በሆነ ምክንያት ሳይናገር የቆየ)::

**አንደበቱን ቆለፈው** መናገር ተሳነው ወይም አቃተው (በህመም ምክንያት)::

**አንደበተ ልቅም** ቅ ቁጥብ::

**አንደበተ ርቱእ** ቅ ጥሩ ተናጋሪ፥ ንግግር አዋቂ::

**አንደበቱ የረታ** ቅ ንግግር አዋቂ::

**አንድ** ስ 1.የመቁጠሪያ ቁጥሮች መጀመሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፩'፥ '1' ነው:: 2.ነጠላ፥ ብቻውን የሆነ:: ቅ 3.ማንኛውም:: *አንድ ሃገር የራሱን ዳር ድንበር ማስከበር አለበት:*

**አንድ ሁለት ተባባሉ** 1.ክፉና በጎ ተነጋገሩ፤ ተሰዳደቡ:: 2.ተገባበዙ (ለመጠጥ)::

**አንድ ሁለት ሲሉ** 1.በትንሹ ወይም በጥቂቱ ጀምረው:: 2.ቀስ በቀስ፥ ሳይቸኩሉ::

**አንድ ሁለት ያህል** ጥቂት ወይም አነስተኛ የሆነ::

**አንድ ሃሙስ የቀረው** የተጎሳቆለ፤ የከሳ፥ የተጎዳ፥ ለሞት የደረሰ የሚመስል::

**አንድ ሆነ** 1.ተባበረ፥ ተስማማ:: 2.ተመሳሰለ፥ ተቀራረበ (በመልክ፥ በቅርፅ፥...)::

**አንድ በለኝ** 1.አንድ መልስ ስጠኝ:: 2.ጋብዘኝ (መጠጥ):: 3.ገላግለኝ:: *ይህን ሰው አንድ በለኝ:*

**አንድ በለው** 1.ዝም አትበለው፥ መልስ ስጠው፥ አናግረው፤ ጉዳዩን ፈፅምለት:: 2.ተው በለው:: 3.ምከረው::

**አንድስ ያህላል** አንዳች ያህላል::

**አንድና ሁለት የለውም** አያጠራጥርም፥ የተረጋገጠ ነው::

**በአንድ ልብ** 1.ባለማመንታት፥ ባልተበታተነ ሃሳብ:: 2.በአንድነት፥ በህብረት፤ በአንድ አይነት ሃሳብና ፍላጎት:: *ለአገራችን በአንድ ልብ መስራት አለብን:*

**በአንድ ቃል/ድምፅ** በተመሳሰለና አንድ አይነት በሆነ አቋም፥ አስተሳሰብ::

**በአንድ አፍታ** በፍጥነት፥ በቅፅበት::

**አንዱ በቃኝ** 1.በጣም ሃይለኛና አስካሪ የሆነ (መጠጥ):: 2.(ሽሙጥ) ጥራቱ መናኛ የሆነና ተፈላጊነት የሌለው::

**አንድ ለአንድ** 1.(ስፖ) በውድድር ጊዜ አንድ አንድ ነጥብ በማግኘት እኩል ለእኩል መሆን:: *ጎይሸናነፉ አንድ ለአንድ ተለያዩ:* 2.ብቻ ለብቻ::

**አንድ ላይ** በጅምላ፥ በጥቅል::

**አንድ በአንድ** 1.በየተራ፥ በተናጠል:: 2.በጠቅላላ፥ አንድ ሳይቀር፥ ሁሉም::

**አንድ ቀን** 1.ወደፊት ከሚመጡት ቀኖች በአንዱ:: *አንድ ቀን እመጣለሁ:* 2.ካለፉት ቀናት መካከል በአንደኛው ቀን:: *ባለፈው ወር አንድ ቀን ተገናኝተን ነበር:*

**አንድ በቀል** መንትያ የሌለው፥ አንድ ቅንጣት ብቻ የሆነ::

**አንድ ነገር** ያልተገለፀ ወይም ያልታወቀ ነገር::

**አንድ አገር** አያሌ፥ ብዙ:: *ምሳዬን አንድ አገር እንጀራ በልቻለሁ:*

**አንድ እግር** ስ አንዲ ነጠላ ተክል ወይም ችግኝ (የበርበሬ፥ የጌሾ)::

**አንድ ወርዶ** ስ አንዱ አጎንብሶ ሳለ ሌላው ከሃላ እየሮጠ መጥቶ የጎነበሰውን በመዝለል የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ::

**አንድ ጊዜ (አንዴ)** ተው.ግ 1.ሳይደጋገም፥ ብዙ ጊዜ ሳይሆን:: *ደብዳቤ የፃፈልኝ አንድ ጊዜ ብቻ ነው::* 2.ለተወሰነ አጭር ጊዜ ለማለት የሚያገለግል ቃል:: *አንዴ ይህን መፅሃፍ ያዝልኝ:*

**በአንድ ጊዜ** 1.ሳይደጋገም:: 2.በፍጥነት፥ ቶሎ:: *በአንድ ጊዜ አደገ:*

**አንድ ፍሬ** ትንሽ:: *አንድ ፍሬ ቆሎ::*

**አንደኛ** ቅ 1.ቀዳሚ፥ ፊተኛ፥ መጀመሪያ:: 2.በደረጃ ወይም በማእረግ ወይም በጥራት ከፍ ያለ፥ የበለጠ::

**አንደኛ ደረጃ ት/ቤት** ስ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ ያለው ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት::

**አንዲት** ቅ በሴቴ ፆታ የሚጠሩ ስሞችን ተከትሎ የሚገባና አንድ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *አንዲት ሴት*።

**አንዳች** ቅ ምንነቱ ያልታወቀ፥ ያልተለየ፥ ያልተገለጠ (አንድ ነገር)። *አንዳች ነገር በዚህ አለፈ*።

**አንዳች አይፈታሽ** ምንም ነገር የማይበግረው።

**አንዳች (አንድስ) ያህላል** ትልቅ ወይም ግዙፍ ነው።

**አንዳንድ** 1.ጥቂት፥ መጠነኛ፥ የተወሰነ። 2.በነፍስ ወከፍ አንድ። *ለሁሉም አንዳንድ ሰጣቸው*።

**አንዳንድ ጊዜ** ተው.ግ አልፎ አልፎ፥ ሁልጊዜ ሳይሆን።

**እያንዳንዱ** ቅ 1.አንዱ፥ ነጠላው። *የእያንዳንዱ ማንኪያ ዋጋ አንድ ብር ነው*። 2.ማንኛውም። *እያንዳንዱ ሰው ምግብ ማግኘት አለበት*።

**አንድም** 1.ምንም፥ ማንም። 2.አለዚያ፥ ወይም።


**አንድምታ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አንድ መፅሃፍ ሲተረጎም አባባሉን በተለያየ መንገድ አጉልቶና ዘርዝሮ ሚስጢሩን የመተርጎሚያ ስልት።

**አንድነት** ስ 1.ህብረት። 2.ተመሳሳይነት።

**አንድዬ** ስ እግዚአብሄር ወይም አምላክ ለማለት የሚነገር ቃል ።

**አንዷዷ** "ዷ" ስር ተመ.

**አንጀት (አንገ'ት)** ስ በጨጓራ ውስጥ የተፈጨ ምግብ የሚተላለፍበት ቀጭን ቱቦ መሳይ የሰው ወይም የእንስሳ ውስጣዊ አካል።




**አንጀቱ ራስ /ቅቤ ጠጣ** የልቡ ደረሰ፥ የፈለገው ነገር ስለሆነለት ተደሰተ።

**አንጀቱ ቆሰለ /ከሰለ** በጣም ተናደደ።

**አንጀቱ ቆረጠ** "ሆድ" ስር "ሆዱ ቆረጠ"ን ተመ.

**አንጀቱ ቡጭ ቡጭ አለ** "ሆድ" ስር "ሆዱ ቡጭ ቡጭ አለ"ን ተመ.

**አንጀቱ (ሆዱ) ተቆለፈ** 1.ምግብ አልበላህ አለው ወይም አስጠላው። 2.ተቀየመ።

**አንጀቱ ተበጠሰ** ተስፋ ቆረጠ።

**አንጀቱ ነፈረ** "ሆድ" ስር "ሆዱ ነፈረ"ን ተመ.

**አንጀቱን ቋጥሮ** ተርቦና ተጠምቶ፥ ተቸግሮ።

**አንጀቱን አለበው** ሃይለኛ ተቅማጥ ያዘው።

**አንጀቴን በላኝ** አሳዘነኝ።

**አንጀቴን አራሰው** አስደሰተኝ፥ አረካኝ።

**አንጀት ራቀው** በምግብ እጦት ወይም በበሽታ ምክንያት ደከመ፥ መናገር አቃተው።

**ከአንጀት—** ከውስጥ በመነጨ ስሜት፥ ከልቡ። *ከአንጀቱ ሳቀ*።

**አንጀት የለሽ** ቅ ጨካኝ፥ አረመኔ።

**የአንጀት ወዳጅ** ስ ችግርንም ሆነ ደስታን የሚያካፍሉት የቅርብ ጓደኛ፥ ምስጢረኛ።

**አንጃ** ስ ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ተገንጥሎ የወጣ የፖለቲካ ቡድን።

**አንጃ ግራንጃ** ቅ 1.ዝባዝንኪ፥ ትርኪምርኪ። 2.ጭቅጭቅ፥ ንትርክ።

**አንጆ (አኞ)** ቅ 1.የከሳ፥ ያረጀ (ከብት)። 2.ለማኝክ የሚያስቸግር ጠንካራ ስጋ። 3.(ዘይ.) ሊያገኙትና ሊያነጋግሩት የማይፈልጉት መንቻካ ሰው።

**አንገት** ስ ጭንቅላትንና ትከሻን የሚያያይዝ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**አንገቱን ደፋ** ተከዘ፥ አዘነ፥ ቅስሙ ተሰበረ።

**አንገቱን የደፋ** ትሁት፥ ታዛዥ፥ ልታይ ልታይ የማይል።

**አንገቷን የደፋች** 1.ጨዋ፥ አይናፋር። 2. ትሁት፥ ታዛዥ፥ ልታይ፥ ልታይ የማትል።

**አንገት የለውም** 1.የነበረበትን ወይም የደረሰበትን ችግር አያስታውስም። 2. የተዋለለትን ውለታ የማይመልስ፥ ውለታ የማይከብደው፥ ውለታ ቢስ ነው።

**አንገተ መቃ** ረዥም አንገት ያለው።

**አንገተ ሰባራ** አይን አፋር፥ ትሁት፥ ጭምት።

**አንገተ ደንዳና** ምክር የማይሰማ፥ ደንታ ቢስ፥ ግድ የለሽ።

**ከአንገት በላይ** ለይምሰል፥ ከልብ ወይም ከአንጀት ያልሆነ።

**የአንገት ልብስ** ስ ከመቀነት አጠርና ሰፋ ብላ ከጥጥ በሸማኔ የምትሰራ፥ በጫፍና በጫፍ

በኩል ጥለት ያላትና ሴቶች ራሳቸውንና ትከሻቸውን የሚሸፍኑባት ልብስ።

**የአንገት ማስገቢያ** ትንሽ ቤት ወይም ጎጆ። *የአንገት ማስገቢያ ካለህ በቂ ነው።*

**የአንገት ወርቅ** ስ ከወርቅ የተሰራና በአንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ።

**አንገትጌ** ስ እንደ ሸሚዝ፥ እጀጠባብ፥ ኮት፥ ... ባሉ ልብሶች ላይ በአንገት በኩል የሚውለው የልብሱ ክፍል፤ ክሳድ፤ ኮሌታ።

**አንጉዝ** ስ ቆስሎ የዳነ ወይም የሻረ ጠባሳ።

**አንጉጥ** "**አነጎጠ**" ስር ተመ.

**አንጋሬ** ስ የደረቀ የፍየል ወይም የበግ ቆዳ።

**አንጋች** "**አነገተ**" ስር ተመ.

**አንጋፋ** ቅ 1.ታዋቂነትና ቀደምትነት ያለው። 2.ታላቅ፥ የበኩር (ለልጅ)። 3.በእድሜ የገፋ፥ አዛውንት።

**አንጎል** ስ 1.የነርቭ ማእከል በመሆን አስተሳሰብንና ስሜትን የሚቆጣጠር፥ በራስ ቅል ውስጥ የሚገኝና በጣም ለስላሳ የሆነ የሰውነት ክፍል። 2. (ዘይ.) ንፍጥ።

**አንጎሉ ዞረ** 1.በትክክል መስራት አቃተው ወይም ተሳነው። 2.በጣም ተበሳጨ።

**አንጎል ነው** ቀውስ፥ እብድ፥ ወፈፌ ነው።

**አንጎለ ቢስ** ማስተዋል ወይም ማመዛዘን የማይችል፥ ይሉኝታ ቢስ።

**አንጎላም** (ስድብ፥ ዘይ.) 1.ጅል፥ 2.ንፍጣም።

**አንጎራጎረ** ግ 1.ለስለስ ባለ ድምፅ ዘፈነ ወይም አዜመ። 2.ሃዘኑን፥ ብሶቱን የሚመለከት እንጉርጉሮ አሰማ።

**እንጉርጉሮ** ስ አንድ ሰው ብቻውን የሚያዜመው የደስታን ወይም የሃዘንን ስሜት የሚገልፅ ለስላሳ ዜማ።

**አንጎርባ** ስ ሆድ የሚነፋና ቆብር የሚያስደፍቅ የከብት በሽታ።

**አንጓ** ስ 1.የጣት ወይም የቅልጥም ወይም የአገዳ ክርክራት። 2.በክርክራቱ መካከል ያለ አካል።

**አንጡራ ሃብት/ንብረት** ስ የጠራ ሃብት፤ አንድ ሰው ጥሮ ግሮ፥ ወዙን አፍስሶ በግሉ ያገኘው ሃብት።

**አንጣሪያ** ስ እራሱን ችሎ ወደ ላይ መቆም የማይችል የእፅዋት አይነት። *አንጣሪያ ለአንጣሪያ ቢደጋገፍ ተያይዞ ዘፍ።*

**አንጣቆ** "**እንጣቆ**"ን ተመ.

**አንጥረኛ** "**ነጠረ**[1]" ስር ተመ.

**አንጪጪ** "**ጪ**[2]" ስር ተመ.

**አንፃር** "***ነፀረ**" ስር ተመ.

**አንፊላ** ስ ተቀቅሎ የሞከከ ንፍሮ ወይም ስጋ ወይም ከእነእንቡጡ የተቀቀለ የአተር ወይም የባቄላ እሸት።

**አንፋሮ** ስ 1.የአንበሳ ጋማ። 2.ዙሪያውን እንደቆብ በራስ ላይ የሚደረግ የአንበሳ ጋማ።

**አንፎርሻ** ቅ ያልጠራ ወይም የደፈረሰ (ውሃ)።

**አንፏሸረ** "**ፏሸረ**" ስር ተመ.

**አንፏሻሪ** ዝ.ከ.

**አኘከ** ግ አላመጠ፥ አመነገከ (ምግብን)።

**አይታኘክም** ሲበሉት ለጥርስ ያስቸግራል፥ ጠንካራ ነው።

**እኛኪ** ቅ ተበልቶና ተመጦ የተተፋ፤ ብላቶ።

**አኝ—**

**አኝ አደረገ** ግ ቀረጨጨ፥ ነከሰ።

**አኞ** "**አንጆ**"ን ተመ.

**አእላፍ** "**እልፍ**[1]" ስር ተመ.

**አእማድ** "**አምድ**" ስር ተመ.

**አእምሮ** ስ ህሊና፤ ናላ።

**አእምሮው ላሸቀ** ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ወረደ፥ ዝቅ አለ (በአስተሳሰብ፥ በችሎታ)።

**አእምሮው ዛገ** አእምሮው ደነዘ፤ ደደበ።

**አእምሮ ቢስ** 1. ይሉኝታ ቢስ። 2. የማያመዛዝን። 3.የማያስታውስ።

**አከለ**[1] ግ ከ—ጋር እኩል፥ ትክክል ሆነ። *ልጁ አባቱን አከለ።*

**እኩሌታ** ቅ ግማሽ።

**እኩል** ቅ 1.ግማሽ፥ እኩሌታ። 2.አቻ፥ የማይበላለጥ።

**እኩሉ** ግማሹ። *እኩሉ ሲዘፍን እኩሉ ያለቅሳል።*

**እኩል ለእኩል** 1.መሳ ለመሳ። 2.እኩል ነጥብ ወይም ውጤት ያለው።

**እኩል በእኩል** ግማሽ በግማሽ።

**የእኩል** የጋራ።

**ያህል (ያክል)** 1.መጠንን፥ ብዛትን፥ ልክን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል ። *ስምንት ያህል መፅሃፍ አለኝ።* 2. የአንድን ነገር ድርጊት ወይም መጠን ወይም ክብደት፥ ... በማነፃፀር ለመግለፅ የሚገባ ቃል። *ዘመድ የምተበት ያህል አዘነ።*

**ለ—ያህል (ያክል)** 1.በብዛት ሳይሆን በመጠኑ ለማለት የሚነገር ቃል። *ለመቅመስ ያህል።* 2.ከልብ ሳይፈልጉ የሚያደርጉትን ነገር ለመግለፅ የሚነገር ቃል።*ለወጉ ያህል።*

**—አሳከለ** መጠኑ—ን እንዲያክል (እንዲያህል) አደረገ። *በሬ አሳከለ /ጤፍ አሳከለ።*

**እኩለ ሌሊት** ስ የሌሊት አጋማሽ፤ መንፈቀ ሌሊት።

**እኩለ ቀን** ስ ቀትር፤ ከቀኑ ስድስት ሰአት፤ ተሲአት።

**እኩሌታ** ቅ ግማሽ፥ እኩል።

**እኩያ** ቅ እቻ፥ ተመጣጣኝ ጓደኛ።

**ተካከለ** ግ እኩል ሆነ፥ ተስተካከለ።

**ትክክል** ቅ 1.ልክ፥ እውነት፥ ሃቅ፥ እርግጥ። 2.እኩል የሆነ። *ሁለቱ በቁመት ትክክል ናቸው*። 3.አኳያ፥ አንፃር። *በዛፉ ትክክል ቆም*። 4.ቀጥ ያለ፥ አባጣ ጎባጣ የሌለው።

**ትክክለኛ** ቅ እውነተኛ፥ እርግጠኛ።

**ተስተካከለ** ግ 1.እኩል ሆነ፥ ተመጣጠነ። 2.ተጠረገ፥ ተደለደለ። *መንገዱ ተስተካከለ*። 3.ተቆረጠ፥ ተቀመቀመ (ፀጉር፥ ፅድ)። 4.ትክክለኛውን መስመር ያዘ ወይም ተከተለ። 5.ተገቢውን ደረጃ ወይም መጠን እንዲይዝ ተደረገ። *ደመወዜ ተስተካከሉልኛል*። 6.ስርአት ያዘ፥ ልክ ወይም ትክክል ሆነ። 7.ታረመ።*ፅሁፉ ተስተካከለ*።8.ተዘጋጀ፥ ተበጀጀ። *ፎቶ ለመነሳት ተስተካከለ*። 9.በአንድ ነገር ትይዩ ወይም አንፃር ሆነ።

**አስተካከለ** ግ 1.እኩል አደረገ። 2.ትክክል አደረገ፥ አረመ። 3.አነጣጠረ። 4.ቀመቀመ፥ ቆረጠ (ፀጉርን፥ ፅድን)። 5.ተገቢውን ደረጃ ወይም መጠን እንዲያገኝ አደረገ። 6.ጠረገ፥ ደለደለ። *መንገዱን አስተካከለ*።

**አከለ**[2] ግ ጨመረ፥ ደረበ። *በሃብት ላይ ሃብት አከለበት*።

**አከመ** ግ በሽተኛን አይቶና መርምሮ መድሃኒት በመስጠት፥ በመጠገን፥... ጤናው እንዲመለስለት እርዳታ አደረገ።

**ሃኪም** በፊደል ተራው ተመ.

**ሃኪም ቤት "ሃኪም"** ስር ተመ.

**ህክምና** በፊደል ተራው ተመ.

**ታከመ** ግ ከበሽታው ለመፈወስ ወይም ለመዳን በሃኪም ታይቶና ተመርምሮ የህክምና እርዳታ አገኘ።

**ታካሚ** ቅ የህክምና እርዳታ ለማግኘት ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ የሚገኝ ህመምተኛ።

**አሳከመ** ግ የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ አደረገ።

**አከረ**[1] ግ አንድ የእርሻ መሬት በተደጋጋሚ ይዘራበት የነበረውን የእህል አይነት በመተውና ሌላ እህል በመዝራት ወይም ምንም ሳይዘራበት ቢያንስ ለአንድ አመት ያህል በዝና እንዲከርም በማድረግ የራሱን የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲያዘጋጅ አደረገ።

**እክር** ስ በተደጋጋሚ ታርሶ በማርጀቱ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት እንዲረዳው የአበባ እህል ተዘርቶበት የቆየ የእርሻ መሬት (በተደጋጋሚ የታረሰ መሬት)። *የባቄላ፥ የአተር፥ ... እክር*።

**ታከረ** ግ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ዘር እየተፈራረቀ ተዘራበት (ማሳ፥ እርሻ)።

**አከረ**[2] ግ ጠጠረ፥ ደደረ።

**አከርካሪ** ስ የጀርባ አጥንት።

**አከበ** ግ ሰበሰበ፥ አጠራቀመ፥ አከማቸ።

**አከተ** ግ 1.ኮተቱን ጠቀለለ፥ ሰበሰበ። 2.በተወሰነ ቦታ አከማቸ ወይም ሰበሰበ።

**እክት** ስ ኮተት፥ ቅራቅንቦ።

**እክታም** ቅ ኮተታም፥ ቅራቅንቧም።

**አከቴ (አከት)** ስ የጥርስ እድፍ፥ ልማም።

**አከከ** ግ 1.ደረመን ወይም እከክ የያዘው ሰው በጥፍሮቹ ሰውነቱን ፎከተ፥ ፈገፈገ። 2. (ዘይ.) ተጎሳቆለ፥ ተቆራመደ (በችግር)።

**እከክ** ስ ደረመን፥ ፎከት።

**እከክ ለበሰ** እከክ ያዘው ወይም ወረሰው።

**እከካም** ቅ 1.እከክ፥ ደረመን የወረሰው ወይም የያዘው። 2.(ዘይ፥ ስድብ) ቆርማዳ፥ ድሃ፥ ችጋራም።

**ታከከ** ግ 1.አካሉን ከሌላ ነገር ጋር በማነካካት ተሻሸ፥ ተፈጋፈገ። 2.ተጠጋ፥ ነካ። *ጓዷ የጎሉን እንጨት ታካ ሳለፈች*።3. ተሳበበ ተመካኘ።

**አሳከከ** ግ በላ፥ አስፎከተ፥ እከኩን እከኩኝ አለ (ገላ)።

**አሳከከው** እከክ ያዘው፥ በላው።

**አስታከከ**ግ 1.አስነካ፥ አስጠጋ። 2.አመካኘ፥ አሳበበ።

**አኩፋዳ (አቁፋዳ) "አኮፋዳ"**ን ተመ.

**አካል** (ብ.ቁ. **አካላት**) ስ 1.ሰውነት፥ ገላ። 2.ክፍል። *የበላይ አካል*።

**ለአካለ መጠን ደረሰ** ለጋብቻ ደረሰ።

**አካሌ** ፍቅሬ፥ ወዳጄ ለማለት የሚጠቀሙበት ቃል።

**አካለ ስንኩል** (ብ.ቁ.**አካለ ስንኩላን**) ቅ በተፈጥሮ ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ የጎደለ (ሰው)።

**አካለ ጎዶሎ** ቅ ከመወለዱ በፊት ወይም ከተወለደ በሂላ በደረሰበት ጉዳት አካሉ የጎደለ፥ ሙሉ አካል የሌለው።

**አካል ማሰልጠኛ** ስ ለአካል ብቃት የሚደረግ እንቅስቃሴ፣ስፖርት።

**የአካል ጉዳተኛ** ስ በተፈጥሮ ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ የጎደለ ሰው።

**አካርሚኝ "ከረመ"** ስር ተመ.

**አካኪ ዘራፍ** ቀጣን በተላበሰና ከፍ ባለ ድምፅ የሚባል የጀግንነት፥ የወኔ፥... መግለጫ የሆነ የፉከራ ቃል።

**አካይስት** ቅ ክፉ፥ ከይሲ።

**አካዴሚ** ስ 1.በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሰዎችን የሚያሰለጥን ከፍተኛ የትምህርት ተቋም። *ጦር አካዴሚ*። 2.በተለያዩ የእውቀት መስኮች ላይ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድና የተገኙትን

ውጤቶች ጥቅም ላይ ለማዋል፡ ለማስተዋወቅ፥ ለማበልፀግና የእውቀት መስኮቹን በሚመለከት ማንኛውንም ሃላፊነት የሚወስድ ተቋም።
*የቋንቋዎች አካዴሚ /ሳይንስ አካዴሚ፡*

**አካፋ** ስ የብረት ወይም የእንጨት እጀታ የተዋደደበት፥ የላይዳ ወይም የማንኪያ ቅርፅ እንዲኖረው ተደርጎ ከብረት የተሰራና ለአፈር፥ ... መዛቂያ የሚያገለግል መሳሪያ።



አካፋ


**አካፋ** "*ካፋ" ስር ተመ.

**አክ**

**አክታ** ስ በጉንፋን፥በሳል፥... ምክንያት ከጉሮሮ የሚወጣ እንደ ንፍጥ ያለ ዝልግልግ ምራቅ።

**አክ አለ** ግ አክታውን ከጉሮሮው አወጣ፥ አክ አንትፍ ብሎ ተፋ።

**አክሊል** ስ የቤተክርስቲያን ሰዎች ወይም የነገስታት ወገኖች በበአል ቀን በራሳቸው ላይ እንደቆብ የሚደፉት ከብር ወይም ከወርቅ፥ ... የሚሰራ የክብር ወይም የማእረግ ምልክት።



አክሊል

**አክሊል ደፋ** በራሱ ላይ አክሊል አደረገ።

**አክላላ** "ከለለ[2]" ስር ተመ.

**አክምባሎ** "አክንባሎ"ን ተመ.

**አክርማ** ስ ለሰፌድ፥ ለቁና፥ ለወንፊት መስሪያ የሚያገለግል የሳር አይነት።

**አክስት** ስ የአባት ወይም የእናት እህት።

**አክታ** "አክ" ስር ተመ.

**አክንባሎ (አክምባሎ)** ስ ከጭቃ ወይም ከቀርከሃ ተሰርቶ እበት የተለቀለቀ የምጣድ መክደኛ፤ ሙግድ።



አክንባሎ

**አክንባሎ ሰበራ** የአራስነት ጊዜዋን ከጨረሰች ሴት ጋር ለመጀመሪያ ቀን የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት።

**አክፋይ** "*ከፈለ" ስር ተመ.

**አክፌሎት** ዝ.ከ.

**አኮሌ (አሆሌ)** ስ ከቅል የሚሰራ የወተት ማለቢያ፤ ግሬራ።

**አኮረተ** ግ አፈራ፥ ፍሬው ትልልቅ ሆነ (ሽንኩርት፥ ድንች፥...)።

**አኮርባጅ** ስ ከጉማሬ ቆዳ የሚሰራ ወፈር ያለ አለንጋ።

**አኮርዲዮን** ስ ሙዚቀኛው በየተራ በጣቱ የሚነካካቸው ከአምስት እስከ ሃምሳ የሚደርሱ የድምፅ መስጫ ቁልፎች ያሉትና በነፋስ ሃይል የሚሰራ ሳጥን መሰል አነስተኛ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**አኮቴት** ስ ለቁርባን የተዘጋጀ ህብስት።

**አኮኮ** "እንኮኮ"ን ተመ.

**አኮፋዳ (አኩፋዳ፥ አቁፋዳ)** ስ ከቆዳ ወይም ከሰሌን የሚሰራና የቆሎ ተማሪ ምግቡን ወይም እቃውን የሚይዝበት ኮረጆ።

**አኳሃን** "ሆነ" ስር ተመ.

**አኳስ** "*ኳስ" ስር ተመ.

**አኳሽ** "ኳሸ" ስር ተመ.

**አኳያ** ስ 1.ትይዩ፥ አፍላግ፥ ፊት ለፊት። ቅ 2. አቻ፥ እኩያ።

**አወረ** ግ እውር አደረገ።

**እውር** ቅ 1.አይኑ የጠፋ፥ ማየት የማይችል፤ አይነ ስውር። 2.(ስድብ፥ ዘይ) ደንባራ፥ ጠምባራ።

**እውር እከክ** ስ በጣም የሚያሳክክ ሃይለኛ የሆነ ደረመን ወይም እከክ።

**እውር የዘራው** በየአቅጣጫው የተዝረከረከ፥ የተመሰቃቀለ፥ በወግና በስርአት ያልተቀመጠ።

**ታወረ** ግ እውር ሆነ።

**አወቀ** ግ 1.ተረዳ፥ ተገነዘበ፥ አስተዋለ። 2.ለየ። *ገና ከሩቁ ሳየው እሱ እንደሆነ አወቅሁ።* 3.ተማረ፥ አጠና። *የአማርኛ ቋንቋ ጠንቅቆ አወቀ።* 4.በግብረ ስጋ ተገናኘ። *አዳም ሄዋንን አወቃት።*

**አውቆ** ሆን ብሎ:: *ላውቆ ነው የጠፋው*::

**አዋቂ** ስ 1.በእድሜ የበሰለ፥ ጎልማሳ:: 2.ብልህ:: 3.ጠንቋይ:: 4.ምሁር፥ ሊቅ::

**የአዋቂ አጥፊ** ቅ ጥፋትነቱን እያወቀ ጥፋት የሚፈፅም::

**እውቀት** ስ የሰው ልጅ በትምህርት ወይም በልማድ የሚያገኘውና ለማሰብ፥ ለማስተዋል፥ ለመመራመር የሚያበቃው አእምሮአዊ ችሎታ::

**በእውቀት በለፀገ** አእምሮው በእውቀት ዳበረ::

**እውቅ** ቅ ዝነኛ፥ ስመጥር::

**እውቂያ** ስ ትውውቅ::

**ታወቀ** ግ 1.ዝነኛ ሆነ፥ ስሙ ገነነ:: 2.ተለየ:: *ሌባው እሱ መሆኑ ታወቀ*:: 3.ተገለጠ፥ ይፋ ወጣ፥ ገሃድ ሆነ::

**መታወቂያ[ወረቀት]** ስ ለቀበሌ ነዋሪዎች፥ ለመንግስት መስሪያ ቤት፥ ለድርጅት፥ ... ሰራተኞች መለያ እንዲሆን የባለቤቱ ፎቶና አስፈላጊው መረጃ ተፅፎበት የሚሰጥ ካርድ ወይም ወረቀት::

**ታዋቂ** ቅ ስመጥር::

**ተዋወቀ** ግ በፊት ከማያውቀው ሰው ጋር ስምና አድራሻ ተገላለፀ፥ ተጨዋወተ፥ ሃሳብ ተለዋወጠ::

**ትውውቅ** ስ ቀደም ብለው ከማያውቁት ሰው ጋር ስም፥ አድራሻ፥... መለዋወጥ፥ ግንኙነት፥ ጭውውት ማድረግ::

**አሳወቀ** ግ 1.ገለፀ፥ አስረዳ:: *ጉዳዩን ለበላይ ባለስልጣን አሳወቀ*:: 2. ይፋ አደረገ:: *ወራሽ መሆኑን በጋዜጣ አሳወቀ*::

**አስታወቀ** ግ 1.አሳወቀ:: 2.ታየ፥ ግልፅ፥ ጉልህ ሆነ:: *ተደጋግሞ ቢታጠብም ቀለም ነክቶት እንደነበረ አስታወቀ*::

**ማስታወቂያ** ስ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ለመግለፅ ወይም ለማስተላለፍ የፈለገውን ነገር ፅፎ በሚታይ ቦታ ላይ የሚለጥፈው ወይም በዜና ማሰራጫ የሚያስተላልፈው መግለጫ::

**ማስታወቂያ አወጣ** በማስታወቂያ ገለፀ ወይም ነገረ::

**የማስታወቂያ ሰሌዳ** ስ የተለያዩ ማስታወቂያዎች የሚለጠፉበት ሰሌዳ::

**አስተዋወቀ** ግ 1.በፊት ትውውቅ ያልነበራቸውን ሰዎች አገናኘ፥ አነጋገረ:: 2.ከዚህ በፊት ያልታየን ወይም ያልተሰማን እንግዳ ነገር እንዲታይ፥ እንዲሰማ ወይም እንዲታወቅ አደረገ::

**አስተዋዋቂ** ቅ አንድን ጉዳይ በተመለከተ ለአድማጮች ወይም ለተመልካቾች የሚገልፅ ወይም የሚያስረዳ::

**አወን** "አዎ"ን ተመ.

**አወንታ** "አዎ" ስር ተመ.

**አወከ** ግ በጠበጠ፥ ረበሸ፥ አስቸገረ::

**ሁከት (ህውከት፥ እውከት)** ስ ረብሻ፥ ብጥብጥ፥ ግርግር::

**ሁከተኛ (ህውከተኛ፥ እውከተኛ)** ቅ ረብሸኛ፥ በጥባጭ::

**አዋኪ** ቅ በጥባጭ፥ ረባሽ፥ አስቸጋሪ::

**ታወከ** ግ ተበጠበጠ፥ ተረበሸ፥ ተሸበረ፥ ተቸገረ::

***አወከ**

**ትውከት** ስ ከተበላና ከተጠጣ በኋላ በህመም ወይም ባለመስማማት ከሆድ ተመልሶ በአፍ የሚወጣ ምግብና መጠጥ፥ ትፋት::

**አስታወከ** ግ አስመለሰ፥ ለበቀ፥ ቋቅ አለ::

**አወደ**[1] ግ 1.ጥሩ ጥሩ ሸተተ:: 2.ቤተክርስቲያንን አጠነ::

**አወደ**[2] ግ የቤተክርስቲያንን ዙሪያ ዞረ::

**ኡደት** ስ 1.በክብረ በአል ቀን ታቦትን አጅቦ ቤተክርስቲያንን የመዞር ስነ ስርአት:: 2.በድግግሞሽ የሚካሄድ የአንድ ድርጊት ክንዋኔ ወይም ሂደት፥ ዙረት::

**ታወደ** ግ ታቦትን አጅቦ ቤተክርስቲያንን በመዞር የሚከናወነው ስነ ስርአት ተካሄደ ወይም ተፈፀመ::

**አሳወደ** ግ ታቦት ሲነግስ በስነ ስርአቱ ላይ ተገኝቶ በአሉን አከበረ::

**አወደወደ** ግ አውደለደለ፥ አደሸደሸ፥ አዘጠዘጠ::

**አወጀ** ግ አዋጅ አወጣ ወይም ተናገረ::

**አዋጅ** ስ በመንግስት የሚወጣና በይፋ የሚገለጥ ማናቸውም አቢይ ህግ፥ ደንብ፥ ውሳኔ::

**አዋጅ አወጣ/ነገረ** አወጀ::

**አዋጅ ነጋሪ** ስ ዘመናዊ የዜና ማሰራጫ ድርጅቶች ባልተስፋፉበት ወቅት በገበያ ቦታ ወይም በአደባባይ እየተገኘ መንግስት ያወጣውን አዋጅ ለህዝብ ያሰማ የነበረ ባለስልጣን ወይም የመንግስት ወኪል::

**ታወጀ** ግ አዋጅ ወጣ ወይም ተነገረ::

**አሳወጀ** ግ አንድን ጉዳይ (ውርስን፥...) በተመለከተ ያገባኛል የሚል ተቃዋሚ ወይም ተከራካሪ ካለ በተወሰነ ጊዜ እንዲቀርብ በጋዜጣ አሳወቀ::

**አው** ስ የጅብ ጩሀት::

**አው አለ** ግ ጮሀ (ጅብ)።

**አውላ** ስ ንቦች የሚያዘጋጁት የማር እንጀራ ውጥን ወይም ጅምር።

**—አዊ** "ዊ"ን ተመ.

**አዋልድ** ስ ቀጥራቸው ከሰማንያ አሃዱ መፃህፍት ውስጥ ያልሆነና እንደ ገድል፣ ድርሳን፣ ታምር የመሳሰሉ በሃይማኖት ሰዎች የተዘጋጁ መፃህፍት።

**አዋልድጌሳ** ስ ፈካ ያለ ቡናማ መልክ ያለው፣ ጀርባው እንደደጋን የጎበጠ፣ አፉና አፍንጫው በረጅሙ ሞጥሞጥ ያሉ፣ ጆሮቹ ረጃጅም፣ ጅራቱ ከስሩ ደንደን ብሎ ከወደጫፉ ሾል ያለ፣ በቀላማ ስፍራዎች የሚኖርና በጣም ረጅም ምላስ ያለው ጉንዳንና ምስጥ የሚመገብ አሳማ የሚመስል የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**አዋራ** "አቧራ"ን ተመ.

**አዋሽ** ቅ (ዘይ.) ትልቅ፣ ሰፊ። *ላዋሽ በርሜል*።

**አዋቂ** "አወቀ" ስር ተመ.

**አዋኪ** "አወከ" ስር ተመ.

**አዋዜ** ስ 1. ከቅመም ጋር የተደቆሰና በውሃ የታሸ በርበሬ ወይም ልቁጥ ድልህ። 2.በጠጅ ወይም በጠላ፣... ታሽቶ የሚዘጋጅ የበርበሬ ዱቄት ብጥብጥ ወይም ድልህ።

**አዋጅ** "አወጀ" ስር ተመ.

**አውሊያ** ስ ዛር።

**አውላላ** ቅ ግልፅና ሰፊ የሆነ (ስፍራ፣ ሜዳ፣...)።

**አውላላ ሜዳ** ስ ዛፍ፣ ጉብታ፣... የሌለበት ሰፊና የተንጣለለ ሜዳ።

**አውሎ ንፋስ** ስ በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ሃይለኛ ነፋስ።

**አውራ** ስ 1.ኮርማ፣ ወይፈን። 2.ያልተቀጠቀጠ ወይም ያልተኮላሸና እንስትን ማጥቃት የሚችል ተባእት እንስሳ። 3.ዋና፣ አይነተኛ።

**አውራ መንገድ** ስ ሰፊ፣ ትልቅ መንገድ፣ አውራ ጎዳና።

**አውራ ንብ** ስ ንግስቷን ንብ የሚጠቃ ንብ።

**አውራ አዘል** ቅ ለመጠቃት የደረሰች (ጊደር)።

**አውራ ዶሮ** ስ ትልቅ ወንድ ዶሮ።



አውራ ዶሮ

**አውራ ጎዳና** ስ አውራ መንገድ።

**አውራ ጣት** ስ ከአመልካች ጣት ጎን የሚገኝ አጭርና ወፍራም ጣት(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

**የአውራ እራት** ስ ማር ሲቆረጥ ለንቡ አውራ ተብሎ የሚተው ትንሽ ማር።

**አውራሪስ** ስ ከጭንቅላቱ አሳማ መስሎ አፍንጫው ላይ አንድ ትልቅና አንድ ትንሽ ቀንድ ያሉት፣ ብዙውን ጊዜ ቀላማ በሆነ ስፍራ የሚኖርና የዛፍ ቅጠል፣ ቅርፊትና ስራስሮች የሚመገብ ቁጡና ሃይለኛ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**አውራጅ** "ወረደ" ስር ተመ.

**አውሬ** ስ 1.በዱር፣ በጫካ፣ በባህር የሚኖር እንደ አንበሳ፣ ጊንጥ፣ ጅብ፣ አዞ፣ ... ያለ ፍጥረት። ቅ 2.(ዘይ.) ክፉ፣ ጨካኝ፣ አረመኔ። 3.ከሰው የማይጠጋ፣ ከሰው ርቆ ወይም ሸሽቶ ለብቻው የሚኖር።

**አውሮፕላን** "አይሮፕላን"ን ተመ.

**የአውሬ እራት ሆነ** በአውሬ ተበላ።

**አውታር** "*ወተረ" ስር ተመ.

**አውታንቲ** ስ እንደ ጭነት መኪና፣ አውቶቡስ፣... ባሉ የንግድ መኪናዎች ውስጥ ቲኬት ነክ የሆነ ወይም ያልሆነ አገልግሎት የሚሰጥ የሾፌር ረዳት።

**አውቶማቲክ** ስ 1.በውስጣዊ ባህርዩ ምክንያት በራሱ ሃይል በመንቀሳቀስ የተወሰነ ተግባር የማከናወን ችሎታ ያለው መሳሪያ። 2. (ዘይ.) ፈጣን፣ ቀልጣፋ። *ጎጊ ሲሰራ አውቶማቲክ ነው*።

**አውቶሞቢል** ስ ለሰው መጓጓዣ የሚያገለግል አነስተኛ መኪና፣ የቤት መኪና።

**አውቶቡስ** ስ ከክፍለ ሃገር ወደ ክፍለ ሃገር ወይም በከተማ ውስጥ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ማጓጓዝ የሚችል ትልቅ መኪና።

**አውቶቡስ ማቆሚያ** ስ የከተማ አውቶቡስ በተወሰነ ርቀት እየቆመ ሰዎችን የሚያሳፍርበትና የሚያወርድበት ቦታ፣ ፌርማታ።

**አውዛ (ሃውዛ)** ስ የተቀቀለ የጫት ውሃ።

**አውድ** ስ አደባባይ፣ ሸንጎ፣ የህዝብ መሰብሰቢያ።

**አውደ አመት** ስ የዘመን መለወጫ በአል ወይም በየአመቱ የሚከበር እንደ ገና፣ ፋሲካ ያለ አቢይ በአል።

**አውድማ (ውድማ)** ስ እህል የሚወቃበት የተስተካከለና የለሰለሰ ቦታ።

**አውጥ** ስ ከፈፍ ባለ ለስላሳ ሽፋን ውስጥ የሚገኝና ሲበስል ሊበላ የሚችል ፍሬ ያለው የተክል አይነት። ፍሬውም አውጥ ይባላል።

**አዎ (አወን÷ አዎን)** ግ አንድን ነገር ወይም ድርጊት ልክ ነው÷ እውነት ነው ወይም ነው ለማለት የሚያገለግል ቃል። *ድመት ጥርስ አላት? አዎን አላት።*

**አወንታ** ስ እሽታ÷ ይሁንታ።

**አዘለ** ግ 1.በጀርባ ተሸከመ (ልጅን ወይም ሌላን)። 2. በጎኑ ፍሬ ያዘ፤ ሸጎጠ (በቆሎ)። 3. ያዘ÷ አካተተ። *ቋም ነገር የአዘለ ንግግር።*

**አዛዬን ነካሽ** በችግር ጊዜ በደረሰለት ወይም ውለታ በዋለለት ሰው ላይ ተንኮል የሚፈፅም ሰው።

**ማዘያ** ስ 1.ልጅን በጀርባ መሸከሚያ ጨርቅ፤ አንቀልባ። 2.እቃን በጀርባ ለመያዝ ወይም ለመሸከም የሚያስችል ጨርቅ።

**—አዘል** ቅ —የያዘ÷—ያካተተ። *ቁም ነገር አዘል።*

**እዝል** ስ 1.ሸክም። 2.ተጨማሪ ወይም አባሪ የሆነ ነገር (ዕሁፍ÷ መረጃ÷ ...)።

**ታዘለ** ግ 1.በጀርባ ተያዘ። 2.እራሱን መቻል አቃተው፡ የሌላ ሰው ሸክም ወይም ጥገኛ ሆነ።

**ተዛዛለ** ግ 1.አንዱ በአንዱ ላይ ሆነ÷ ተነባበረ÷ ተደራረበ። 2.አንዱ ሌላውን በጀርባው ተሸከመ።

**አስተዛዘለ** ግ 1.አንዱን በአንዱ ላይ አደረገ÷ አነባበረ÷ አደራረበ። 2.አንዱ ሌላውን እንዲሸከም አደረገ።

**አዘመረ**[1] ግ 1.እንደ ማረስና መዝራት ያለ የእርሻ ስራ ሰራ። 2.አመረተ።

**አዝመራ** ስ ሰብል÷ የእርሻ ውጤት።

**አዝመራው ሰጥቷል** ብዙ ሰብል ወይም ምርት ተገኝቷል።

**አዘመረ**[2] **"ዘመረ"** ስር ተመ.

**አዘረጠ** ግ 1.በሃይል መታ፤ ደበደበ። *በዱላ አዘረጠው።* 2.ጨፈጨፈ÷ ሞሸለቀ÷ አዋረደ። *በስድብ አዘረጠው።*

**አዘራ**[1] ግ ክፉኛ መታ ወይም ሰደበ።

**አዘራ**[2] **"ዘራ"** ስር ተመ.

**አዘቅት** ስ ጥልቅ ጉድጓድ።

**አዘበዘበ** ግ 1.ተንጠለጠለ÷ ለመፍረስ ወይም ለመውደቅ ተቃረበ (ያረጀ ካብ÷ የግድግዳ ምርጊት)። 2.ያለ ቅጥ ወፈረ (ከምችት የተነሳ)።

**አዘቦት [ቀን]** ስ በአል ያልሆነ ተራ የስራ ቀን።

**አዘነ** ግ 1.ተፀፀተ÷ ተከፋ÷ ተቆረቆረ÷ ተከዘ። 2.ራራ።

**አዘኔታ (ሃዘኔታ)** ስ ደግነት÷ ርህራሄ።

**አዘን "ሃዘን"**ን ተመ.

**አዛኝ** ቅ ደግ÷ ሩህሩህ።

**አዛኝ ቅቤ አንጓች** ተቆርቋሪ መሳይ÷ አልኩ ባይ።

**አዛኝቱ** ቅ የድንግል ማሪያም የቅዕል ስም።

**[የ]እዝን** ስ ሃዘን ወይም ለቅሶ ቤት የሚወሰድ ምግብ÷ መጠጥ÷...።

**ተዛዘነ** ግ ተሳሰበ÷ ተረዳዳ÷ አንተ ትብስ አንተ ትብስ ተባባለ።

**አሳዘነ** ግ 1.አስከፋ÷ አስቀየመ÷ ቅር አሰኘ። 2.አራራ÷ አባባ።

**አስተዛዘነ** ግ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበትን ሰው አዋየ÷ አፅናና÷ አረጋጋ።

**ማስተዛዘኛ** ስ 1.የእዝን። 2.የተገዛበትን ዋጋ ብቻ ሊያስገኝ የሚችል የሎተሪ እጣ።

**አዘዘ** ግ አንድ ነገር እንዲሰራ ትዕዛዝ ሰጠ።

**አዘዘበት** ፈረደበት፤ መጥፎ እድል ወይም መጥፎ አጋጣሚ አገኘው።

**ማዘዣ** ስ 1.አንድ ነገር እንዲደረግ ወይም እንዲከበር የተፃፈ ትእዛዝ÷ ደብዳቤ። 2.ከላይ በኩል አድራሻና አርማ ያለውና ልዩ ልዩ ጉዳዮች የሚፃፉበት የመንግስት ወይም የግል መስሪያ ቤት ወረቀት።

**አዛዥ** ስ 1.የቤተ መንግስት ወይም የታላላቅ መኳንንት የንብረት ሹም ወይም አስተዳዳሪ። 2.የበላይ ሃላፊ÷ አለቃ። *የጦር ሃይሎች አዛዥ።*

**እዝ** ስ በአንድ ማእከል ስር አመራርን የሚቀበል ምድብ÷ ቀጣና÷ ...።

**[የ] እዝ ኢኮኖሚ** ስ በኢኮኖሚው ዘርፍ ከግል ባለሃብቶች ተሳትፎ ይልቅ መንግስት ኢኮኖሚውን በብቸኝነት የሚቆጣጠርበት ሁኔታ።

**ታዘዘ** ግ 1. እሺ አለ÷ ትእዛዝ ተቀበለ። 2.አንድ ስራ በተወሰነ ጊዜ እንዲሰራ ተነገረ÷ ትእዛዝ ተሰጠ። 3.ከተጠቃሚው ወይም ከተገልጋዩ ትእዛዝ ተቀበለ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ጠየቀ፡ አስተናገደ (ቡና ቤት÷ ምግብ ቤት÷...)።

**ታዛዥ** ቅ 1.ትሁት÷ ሰው አክባሪ÷ እሺ ባይ። 2.አሽከር÷ አገልጋይ÷ ሎሌ።

**ትእዛዝ** ስ 1.አንድ ነገር መሰራት ያለበት መሆኑን የሚገልፅ የበላይ ውሳኔ። 2.ፍርጃ÷ ድንገተኛ አደጋ።

**ትእዛዝ አንቀፅ** አንድ ነገር መደረግ ወይም መከናወን ያለበት መሆኑን ለመግለፅ የሚነገር ግስ (ለምሳሌ ሂድ÷ እንድትሄድ)።

**አዘገበ** ግ አለመ፤ አነጣጠረ።

**አዙሪት "ዞረ"** ስር ተመ.

**አዚም** ስ የሚያፈዝ ወይም የሚያደነግዝ መተት፤ አስማት።

**አዚመኛ** ቅ የሚያፈዝ ወይም የሚያደነግዝ መተት ወይም አስማት በሰው ላይ የሚያደርግ::

**አዚማም** ቅ. 1.አዚም የተደረገበት (ቦታ፡ ነገር):: 2.የሚቀፍ፡ የሚከብድ::

**አዚፋ** ስ የተቀቀለ ምስር ከተደቆሰ በሃላ ከቃሪያ፥ ከሽንኩርት፥... ጋር ተዋህዶና ተደባልቆ የሚሰራ የፆም ምግብ አይነት::

**አዛመ** ቅ አንቀጠቀጠ፥ አንዘፈዘፈ (ወባ፥ ብርድ፥...)::

**አዛመረ** ግ አወላዳ፥ አላወሰ፥ አሰናዘረ::

**አያዛምርም** አያሰናዝርም፥ አያወላዳም::

**አዛምር** ስ የእፅዋት አይነት::

**አዛቆነ**[1] ግ አደቆነ::

**አዛቆነ**[2] **"ዛቆነ"** ስር ተመ.

**አዛባ** ስ 1.የላቆጠ የከብቶች እበት:: 2.(ዘይ፡ ስድብ) ረሀጥ፡ ሰነፍ፡ ገልቱ::

**አዛኝ "አዘነ"** ስር ተመ.

**አዛኝቱ** ዝ.ከ.

**አዛውንት** ስ ሽማግሌ ወይም አሮጊት::

**አዛዥ "አዘዘ"** ስር ተመ.

**አዟጋ** ግ አፋሸገ፡ አፉን አላቀቀ::

**አዜብ** ስ በደቡብና ብምስራቅ መካከል ያለ የአለም ማእዘን አቅጣጫ (በተጨማሪ ማእዘን ስር ተመ.)::

**አዝመራ "አዘመረ**[1]**"** ስር ተመ.

**አዝማሚያ "ዘመመ**[1]**"** ስር ተመ.

**አዝራር** ስ ከተለያየ ነገር (ከቀንድ፥ ከእንጨት፥...) በተለያየ ቅርፅ የሚሰራ የልብስ ቁልፍ::

**አዞ** ስ በደረት ከሚሳቡት አራዊት ሁሉ የመጨረሻው ትልቅ የሆነ፥ ርዝመቱ እስከ 6 ሜትር የሚደርስ፥ አካሉ ከወደላይ ደንዳና ሆኖ እንደ ጥፍር በጠነከረ ቅርፊት የተሸፈነ፥ ከወደሰፋ ቆዳው ለሰላላ የሆነ፥ መጋዝ ጥርሶችና ረጅም አፍ ያለው፥ በብዛት በሞቃት አካባቢ በሚገኙ ትልልቅ ጅረቶችና ሃይቆች ውስጥ የሚኖር የውሃ ውስጥ አውሬ::

**አዞ ሃረግ** ስ ቅጠሉ ሰውነትን ሊያቃጥልና ሊያቆስል የሚችልና እንደ ልጥ ለማሰሪያ ወይም ለቀፎ መስሪያ፥... የሚያገለግል ጠንካራና ረጅም የሆነ የሃረግ አይነት::

**አዞጠ** ግ በሃይል መታ፥ ገረፈ፥ ደበደበ::

**አገ** ግ 1.አመረቀዘ፥ መገለ:: 2.በትንሹ ማፍሰስ ጀመረ:: *እንስራው ኣገ*::

**አየ** ግ 1-ተመለከተ፥ አተኩረ፡ ተረዳ፥መረመረ፥ አስተዋለ:: 2.ጎበኘ፥ ጠየቀ:: 3.ታዘበ::

**አየሁህ** 1.ታዘብኩህ:: 2.ልጆች የሚጫወቱት የድብብቆሽ ጨዋታ አይነት::

**አላየሁም** 1. አላጋጠመኝም፡ አላገኘሁም:: *እንደ እገሌ ያለ ሰው አላየሁም*: 2.አልወሰድኩም፡ አልነካሁም:: *የእሱን ገንዘብ ኣላየሁም*:

**እዩኝ ባይ** 1.በማያገባው ቦታ ወይም ነገር ውስጥ ጥልቅ የሚል:: 2.ያልሆነውን መስሎ መታየት የሚሻ::

**ታየ** ግ ታወቀ፡ ተገለፀ፡ ተከሰተ::

**ታይቶ ጠፋ** ሞተ፥ ተቀጨ::

**ታየበት** ተፈረደበት::

**ታየው** 1.ተረዳው፥ ተገነዘበው:: 2.ተገለፀለት::

**መታያ (መተያያ)** ስ ገፀበረከት፥ ስጦታ፥ እጅ መንሻ::

**ተያየ** ግ በአካል ተገናኘ::

**ትይዩ** ስ ፊት ለፊት፥ ማዶ ለማዶ::

**አሳየ** ግ 1.አመለከተ፥ ጠቆመ፥ መራ:: 2.አስረዳ፥ አሳወቀ:: 3-አቀመሰ (በዱላ፥ በስድብ፥...)::

**አሳይቶ መለሰው** በጠና ታሞ ዳነ ወይም ከከባድ አደጋ ተረፈ::

**ያሳየኝ** 1.እግዚአብሄር ይፍረደኝ:: 2.(ርግማን) ችግር፥ ስቃይ ገጥሞት ለማየት ያብቃኝ:: *የእርሱን ነገር ያሳየኝ*:

**አስተያየ** ግ 1.አመሳከረ፥ አገናዘበ:: 2.አወዳደረ፥ አነፃፀረ::

**አስተያየት** ስ 1.አመለካከት:: 2.ሃሳብ:: *ጥሩ አስተያየት ሰጠኝ*:

**አስተያየት አደረገ** 1.ዋጋ ቀነሰ:: *እቃውን አስተያየት አድርጎ ሸጠለት*:: 2.ራራ፥ አዘነ:: *ለእስረኞቹ አስተያየት አደረገላቸው*:

**አየለ** ግ በረታ፥ ጠነከረ፥ ጠና::

**ሃይል** በፊደል ተራው ተመ.

**ሃይለቃል "ሃይል"** ስር ተመ.

**ሃያል** ዝ.ከ.

**አየመ** ግ በድጋሚ አረሰ፥ አለሰለሰ (ማሳን)::

**አየር** ስ 1.መሬትን የከበበና ህይወት ለአላቸው ነገሮች አስፈላጊ የሆነ የብዙ ጋዞች ጥርቅም:: 2.ከምድር በላይ ከጠፈር በታች ያለ ቦታ:: 3.አይሮፕላን::

**አየር ለወጠ** ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ሄደ (ለእረፍት ወይም በጤና ምክንያት)::

**አየር ማረፊያ** ስ የአይሮፕላን ማረፊያ::

**አየር ተቀበለ "ነፋስ"** ስር "ነፋስ

ተቀበለ"ን ተመ.

**አየር ወሰደ** 1.አየር ወደ ሳምባው አስገባ፥ ወደ ውስጥ ተነፈሰ::2.አየር ተቀበለ::

**አየር ሃይል** ስ 1.በተዋጊ አይሮፕላኖች የአየር ላይ ውጊያ ማስልጠኛ ተቋም:: 2.በዚሁ ተቋም የሰለጠነ ወታደር::

**አየር መቃወሚያ** ስ የጠላትን ተዋጊ አውሮፕላን መትቶ ለመጣል የሚያገለግል የጦር መሳሪያ::

**አየር መንገድ** ስ ሰውን ወይም እቃን በአየር የሚያጓጉዝ የንግድ ድርጅት::

**አየር ትራንስፖርት** ስ በአየር ላይ የሚ ደረግ ጉዞን በበላይነት የሚቆጣጠር የበላይ ሃላፊ ወይም ተጠሪ የሆነ መስሪያ ቤት::

**አየር ወለድ** ስ 1.ከአውሮፕላን ላይ በፓራሹት እየወረዱ የሚዋጉ ወታደሮች የሚሰለጥኑበት ተቋም:: 2. በዚሁ ተቋም የሰለጠነ ወታደር::

**የአየር መልእክት** ስ በአውሮፕላን የሚላክ መልእክት ወይም ደብዳቤ::

**የአየር ጠባይ** ስ አንድ የተወሰነ ቦታ በተ ወሰነ ጊዜ የሚኖረው የዝናም፥ የነፋስ፥ የሙቀት፥... ሁኔታ::

**አያ (አይያ፥ አይዋ)** ስ ታናሽ ታላቅ ወንድሙን ወይም ዘመዱን ለመጥራት የሚጠቀምበት የአክብሮት መጥሪያ ወይም ስምን ተከትሎ እየገባ ተባእታይ ፆታን በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል:: *አያ ከበደ*:

**አያሌ (አያል)** ቅ ብዙ፥ በርካታ::

**አያት** ስ የአባት ወይም የእናት አባት ወይም እናት::

**አያያዘ "ያዘ"** ስር ተመ.

**አዬ** (ቃ.አ.) ቅሬታን፥ ጥርጣሬን፥... ለመግለፅ የሚነገር ቃል::

**አዬ ጉድ** ቃ.አ. ማዘንን፥ መገረምን፥ መደነቅን፥... ለመግለፅ የሚነገር ቃል:: *አዬ ጉድ! ጨክነህ ከአገር ልትወጣ ነው?*

**አይ** 1.አይደለም ወይም አይሆንም ለማለት የሚያገለግል አፍራሽ ቃል:: 2.ቁጣን ለመግለፅ የሚነገር ቃል:: *አይ! እንግዲህ አትጨሀብኝ*:

**አይሁድ** ስ (ዘይ.) እርጉም፥ ክፉ፥ ከሃዲ::

**አይሮፕላን(አውሮፕላን)** ስ ሰውንና እቃን በሰማይ ላይ ለማጓጓዝ የሚችል ሰው ሰራሽ በራሪ አካል፤ አየር::

**አይሮፕላን ማረፊያ** ስ አይሮፕላን የሚያርፈበት ቦታ ወይም ጣቢያ፤ አየር ማረፊያ::

**አይበሉባ (አይበሉብሽ)** ስ የእጅ መዳፍና ጣት ጀርባ የሆነው የሰውነት ክፍል(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)::

**አይበሉብሽ ጥፊ** ስ በጣት ጀርባ የሚመታ ጥፊ ፤ ቃሪያ ጥፊ::

**አይበት** ስ ከወይፈን ቆዳ የሚሰራ ስልቻ::

**አይብ** ስ ቅቤው የወጣለት ወተት (ወገሚት) ከተፈላ በሂላ ዘቅጦ ከአጓት ስር የሚቀረው የምግብ አይነት::

**አይት** ስ የባል እህት ወይም የወንድም ሚስት::

**አይነምድር** ስ ሰገራ፥ አር::


**አይነት**[1] ስ 1.ቀለምን፥ መልክን፥ ጠባይን፥ ተፈጥሮን፥ ሁኔታን፥ ... ለመግለፅ ወይም ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል:: *ልብስ ይሉሃል የዚህ አይነት ነው፣ምን አይነት ሰው ነው ፈልጎኝ የነበር?* 2.ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ልዩ ልዩ ምግቦች::

**የአይነት ለውጥ** ስ (ፍል.) በአንድ ነገር ላይ (ቀድሞ በነበረው ጠቅላላ ባህርይ፥ መልክ፥ ምንነት ላይ) ፈጣን በሆነ መንገድ ወይም በቅፅበት የሚመጣ መሰረታዊ ለውጥ::

**አይነተኛ** ቅ ዋነኛ፥ አቢይ::

**አይነት**[2] ስ እከክ የሚመስል ቁስል::

**አይን** ስ 1.የማያ ወይም የመመልከቻ አካል:: 2.በእንጀራ፥ በማር ከዳ፥... ላይ አይን መስሎ የሚታይ ጠቃጠቆ:: 3.ብስ፥ ቀዳዳ (የመርፌ፥ የመዋጥ፥...):: 4.በእንጨት ግንድ ላይ ቅርንጫፍ ከመውጣቱ በፊት የምትወጣ ጉጥ:: 5.በእጅ ባትሪ ወይም በተሽከርካሪዎች መብራት ውስጥ የምትገኝ ትንሽ አምፑል::




አይን1ኛ ፍቺ

**ለአይን አይሞላም** በጣም ትንሽ ወይም ጥቂት ነው::

**ለአይን ያዘ** ጨለም አለ::

**በአይነ ስጋ** በአካል፥ ፊት ለፊት:: *በአይነ ስጋ ለመገናኘት ያብቃን*:

**በአይነ ቁራኛ** በሰውር ክትትል:: *ተካባቢው በአይነቁራኛ እየተጠበቀ ነው::*

**በአይኑ ላይ ዞረ/ሄደ** 1.ናፈቀ፥ ትዝታው መጣበት:: 2.አማረ፥ አሰኘ::

**በአይኔ መጣህ** በጣም የምወደውንና

እንዲነካብኝ የማልፈልገውን ነገር ነካህ፥ ጠየቅህ፥ አነሳህ፥ ...።

**አይኑ ላይ ጣለበት** አይኑ ብረት ላይ ነጭ ነገር በመውጣት የማየት ሃይሉን በመጠኑ ጋረደው።

**አይኑ ሰከረ** የሚያየው ነገር ከመብዛቱ የተነሳ የሚመርጠውን አጣ።

**አይኑ ቀላ /ደም ለበሰ** ተመቀኘ፥ ቀና።

**አይኑ በራ** እውር የነበረው አይኑ ዳነ።

**አይኑ ባከነ** አይኑ አንድ ነገር ለማየት ተንከራተተ፥ ተቅበዘበዘ፥ ወዲያና ወዲህ አየ።

**አይኑ ብር አለ** 1. ከህመም፥ ከድካም፥... የተነሳ አይኑ ፈዘዘ። 2.ናፈቀ፥ ለማየት ጓጓ።

**አይኑ ተመረገ** አይኑ አልገለጥ አለ፥ ተደፈነ።

**አይኑ ተንከራተተ** አንድን ነገር ለማግኘት ጎምጅቶ ወይም ጓጉቶ ወዲያ ወዲህ ተመለከተ።

**አይኑ ተከፈተ/ተገለጠ** ማስተዋልና ማመዛዘን ቻለ፤ ክፉና ደጉን ወይም ጠቃሚና ጎጂውን ለየ፤ ብልህ ሆነ።

**አይኑ አረፈበት/ወደቀበት** ወደደው፥ አይኑን ጣለበት።

**አይኑ እንባ አቀረረ** እንባው በአይኑ ሞላ።

**አይኑ ደም ጎረሰ** 1.ተበሳጨ፥ ተናደደ። 2.ተመቀኘ፥ ቀና።

**አይኑ ደገደገ** አይኑ ፈዘዘ ወይም ደከመ (በእድሜ መግፋት)።

**አይኑ ደፈረሰ** 1.አይኑ ቀላ፥ ደም መሰለ። 2.ተቆጣ። ተመቀኘ፥ ቀና።

**አይኑ ጠገበ** የሚፈልገውን ነገር በብዛት በማግኘቱ በማየት ብቻ ረካ ወይም ጠገበ።

**አይኑ ፈሰሰ** አይኑ ፈረጠ፥ ጠፋ፥ ታወረ።

**አይኑ ፈጠጠ** 1.ተጨነቀ። 2.ክው አለ፥ ደነገጠ።

**አይኑን ሰበረ** ከማፈር፥ ከመሽኮርመም የተነሳ ወደ መሬት ተመለከተ።

**አይኑን ሰካ/ተከለ** 1.ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ተመለከተ (በህመም ምክንያት)። 2.አተኩሮ ተመለከተ፥ ትክ ብሎ አየ።

**አይኑን ቁልጭ አደረገ** 1.አይኑን ገለጠ፥ ተመለከተ። 2.ከእንቅልፉ ነቃ።

**አይኑን ቁልጭ ቁልጭ አደረገ** 1.ጓጓ፥ በጉጉት አየ። 2.ከመደንገጥ፥ ከመገረም፥... የተነሳ ሁኔታዎችን በአርምሞ ተመለከተ።

**አይኑን በአይኑ አየ** ልጅ ወለደ።

**አይኑን በጨው አጥቦ** እፍረቱን፥ ይሉኝታውን ትቶ።

**አይኑን አያሳየኝ አለ** ጠላው፥ አራቀው።

**አይኑን አጎረጠ/ጎለጎለ** አይኑን አፈጠጠ፥ አጉረጠረጠ።

**አይኑን ከደነ** 1.አይኑን ጨፈነ። 2.እንቅልፍ ያዘው፥ አሸለበው።

**አይኑን ወረወረ** አሻግሮ አየ።

**አይኑን ገለጠ** 1.ፊደል ቆጠረ፥ ተማረ። 2. ነቃ፥ አወቀ።

**አይኑን ጋረደው /ከለለው** ማየት ተሳነው።

**አይኑን ጣለበት** ወደደው፥ ፈለገው፥ መረጠው።

**አይኔን ግንባር ያድርገው አለ** አላየሁም፥ አልሰማሁም፥ አላውቅም አለ።

**አይን ለአይን ተያየ** ከተለየው ወይም ከናፈቀው ሰው ጋር ተገናኘ፥ ለመተያየት በቃ።

**አይን ለአይን ተጋጨ** አንዱ ሌላውን በስርቆት ለማየት ሲል ወይም ባጋጣሚ ሁለቱም ተያዩ።

**አይን በላው** 1.ቡዳ በላው። 2.ተስፋ ተጥሎበት ሳለ እንደተጠበቀው ሳይሆን ቀረ፥ ተበላሸ።

**አይን በአይን** በገሃድ ወይም በግልፅ።

**አይን ነው** ዋና፥ አይነተኛ፥ ብቃት ያለው ነው። *ሰውየው ለተመደበበት ስራ አይን ነው።*

**አይን አወጣ** ከመጠን በላይ ደፈረ፥ እፍረተ ቢስ ሆነ።

**አይን አውጣ** ቅ የማያፍር፥ ይሉኝታ ቢስ።

**አይን አዋጅ ሆነበት** ሁሉም ስለአማረው ምርጫውን ለመወሰን ተቸገረ።

**አይን ገባ** 1.ቡዳ በላው። 2.ሁሉም አተኮረበት፥ የሁሉንም ስሜት ሳበ።

**አይንህን ለአፈር አለ** ፈፅሞ ጠላ።

**አይንና ናጫ / አፈር** የማይስማማ፥ የማይጣጣም።

**አይነ ሌባ** ቅ የአመንዝራነት ጠባይ ያለው፥ አይኑ የሚቃብዝ፥ በአይኑ የሚጠቅስ።

**አይነ ማዝ** ስ ትራኮማ የሚባል የአይን በሽታ።

**አይነ ስብ** ስ 1. ከአይን በታች በኩል ያለ ስስ ቆዳ። 2.የአይን ጉድጓድ።

**አይነ ስውር** ስ አይኑ ለማየት የማይችል፤ እውር።

**አይነ ቀላዋጭ** ቅ ሁሉንም ለማየት አይኑ የሚራወጥ፥ የሚቃበዝ።

**አይነ ቆሎ** ቅ አይነ ትልልቅ::
**አይነ በላ** ቅ (ስድብ) እፍረተ ቢስ፥ አይን አውጣ::
**አይነ በጎ** ስ ከጨጓራ ጋር ተያይዞ የሚገኝ የማር እንጀራ የመሰለ አይን ያለው ከእንስሳት የሆድ እቃ አንዱ::
**አይን አፋር** ስ እንግዳ ሰውን ትክ ብሎ ማየት ወይም ማነጋገር የሚፈራና የሚያፍር ሰው::
**የአይን መቃድ** ስ የአይን የቅዱ ቅርፅ::
**የአይን ማሚቶ** ስ የአይን ብሌን::
**የአይን ምስክር** ስ አንድ ድርጊት ሲፈፀም በቦታው የነበረና የተመለከተ እማኝ::
**የአይን ቆብ** ስ ከቅንድብ በታች ያለው የአይን መከደኛ፥ ሽፋን (ስእሱን አይን ስር ተመ.)::
**የአይን ብረት/ብሌን** ስ ጥቁሩ የአይን ክፍል::
**የአይን አባት** ስ ህፃን ወንድ ሲገረዝ አይኑን የሚይዝለትና በዚህም የተነሳ ዘመድ የሚሆን ሰው::
**የአይን እናት** ህፃን ሴት ስትገረዝ አይኗን የምትይዝላትና በዚህም የተነሳ ዘመድ የምትሆን ሴት::
**አይናማ** ቅ ጎላ ጎላ ያለ አይን ያለው፤ አይነ ትልልቅ::
**አይናማ ድንጋይ** ስ እንደ ብስ ያለ ጠቃጠቆ ያለበት ድንጋይ::
**አይዋ** "አያ"ን ተመ.
**አይያ** ዝ.ከ.
**አይደለም** የ"ነው" ተቃራኒ::
**አይደርቄ** "ደረቀ" ስር ተመ.
**አይጥ**[1] ስ በቤት አካባቢ ወይም በዱር የሚኖርና በስብልም ሆነ በቤት ውስጥ የተለያዩ ምግቦችንና ነገሮችን በመብላት ጥፋት የሚያደርስ ጅራተ ረጅም ትንሽ አውሬ::
**አይጠ መጎጥ** ስ አፉ ሾል ያለና የአይጥ መልክ ያለው አነስተኛ አውሬ::
**[የ]አይጥ ሃረግ** ስ የተንገርረገገ ድቡልቡል ፍሬ ያለው ቀጭን ሃረግ፤ እንሳቺት::
**[የ]አይጥ ምስር** ስ ፍሬው ምስር የሚመስል የእፅዋት አይነት::
**[የ]አይጥ አተር** ስ እንደ አተር ያለ ፍሬና ሃረግ ያለው የእፅዋት አይነት::
**አይጥ**[2] ስ የክንድ ጡንቻ::
**አደለ** ግ ሰጠ፥ አከፋፈለ::
**ማደያ** ስ ማከፋፈያ::
**አዳይ** ቅ 1.አሳዳፊ፥ አስተናባሪ::2.አከፋፋይ::
**እደላ** ስ የማዳረስ፥ የማከፋፈል ስራ፤ ስርጭት::
**እድል** ስ 1.እጣ ክፍል፥ ግንባር:: 2.ድርሻ::
**እድሉ ተሰበረ** እድሉ ተሰናከለ፥ ኑሮ ሳይሳካለት ቀረ::
**እድለ ሰባራ** ቅ እድለ ቢስ፥ ያልታደለ፥ መልካም ወይም ጥሩ ነገር የማይገጥመው::
**እድሉ ተዘጋ** 1.በእድሉ እንዳይጠቀምበት ሆነ:: 2. በነበረው እድል መጠቀም ተከለከለ፥ ታገደ::
**እድሉ ጠባብ ነው** የነገሩ የመሆን ወይም የመፈፀም ተስፋው ያነሰ ነው::
**እድለ ቢስ** ቅ መልካም ነገር የማይገጥመው፥ ያልታደለ::
**እድል ፈንታ** ስ እጣ ፋንታ፥ድርሻ::
**እድለኛ** ቅ መልካም ወይም ጥሩ ነገር የገጠመው ወይም የሚገጥመው::
**እድላም** ዝ.ከ.
**ታደለ** ግ ጥሩ ነገር አገኘ፥ መልካም እድል ገጠመው::
**የታደለ** ቅ እድለኛ::
**አደመ**[1] ግ አሴረ፥ ዶለተ::
**አድማ** ስ ሴራ፥ ዱለታ::
**አድማ መታ** አሴረ::
**አድመኛ** ቅ ለተንኮል ስራ ሌሎችን የሚያስተባብር፤ ሴረኛ::
**አሳደመ** ግ ለተንኮል ስራ ሌሎችን አስተባበረ፥ ሴራ ቀረጠ ወይም አድማ መታ::
**አደመ**[2] ግ ጠራ፥ ጋበዘ (ለሰርግ፥ ለግብዣ ፥...)::
**እድምተኛ(እድመኛ)** ስ ለሰርግ ወይም ለግብዣ፥... የተጠራ ሰው፥ ተጋባዥ::
**ታደመ** ግ ተጠራ፥ ተጋበዘ (ለሰርግ፥ ለግብዣ)::
**ታዳሚ** ስ ተጋባዥ፥ ተጠሪ::
**አደረ** ግ 1.በቤት ውስጥ ወይም ሌላ ስፍራ ሆኖ ሌሊቱን አሳለፈ ወይም አነጋ:: 2.(ዘይ.) ተስማምቶና መስሎ ኖረ:: *ከሰው ማደር ይቻላል*:: 3. ለሌላ ጊዜ ተላለፈ:: *ውሳኔው በእለቱ ሳይሰጥ አደረ::*
**—አደረበት** ያዘው:: *ቅናት አደረበት/በሽታ አደረበት::*
**አድሮ ልጅ** ከርሞ ጥጃ፤ እድገት ወይም መሻሻል የማያሳይ::
**እያደር** ተው.ግ ቀስ በቀስ፥ እየሰነበተ፥

እየቆየ::

**ማደሪያ** ስ 1.ሌሊቱን ማሳለፊያ፥ መኝታ ቦታ ወይም ቤት:: 2.መተዳደሪያ (ስራ፥.. )::

**አዳሪ** ቅ 1.የሌሊት ተረኛ (የተወሰነ ተግባር ለማከናወን):: 2.በሚማርበት ቦታ የሚኖር (ተማሪ ወይም ሰልጣኝ)::

**አዳሪ ትምህርት ቤት** ስ ተማሪዎች የምግብ፥ የመኝታ፥... አገልግሎት እያገኙ የሚማሩበት ት/ቤት::

**አዳር** ስ 1.ትዳር:: 2-ኑሮ:: 3.የአንድ ሌሊት ጊዜ:: 4.ማደሪያ::

**አዳሩ ሞቀ** ትዳሩ ሰመረ፥ ሃብት ንብረት አገኘ::

**አዳሩን ሄደ ወይም መጣ** ለማደር ሄደ ወይም መጣ::

**አድርባይ** ቅ ለጥቅሙ ሲል የሚያጎበድድ፥ ተለማማጭ::

**ተዳደረ** ግ 1. በተወሰነ ደንብ ተመራ 2. ተኳኋነ፥ ተስማማ፥ ተመሳስሎ ኖረ:: 2.ኖረ:: *በእርሻ ስራ ነው የሚተዳደረው:*

**መተዳደሪያ** ስ 1.ስራ:: 2.ደንብ፥ ስርአት::

**ተዳደሪ** ቅ ከሌላው ጋር ተስማምቶ መኖር የሚችል::

**መስተዳድር** ስ የአንድን ሃገር የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮችን በሃላፊነት የሚመራ ከፍተኛው የመንግስት ስልጣን አካል::

**አሳደረ** ግ 1. በሃላፊነት ያዘ፥ ተንከባከበ (ቤተሰብን):: 2.ለሌላ ጊዜ አስተላለፈ (ጉዳይን ፥ስራን፥...)::

**አሳዳሪ** ስ 1. የቤተሰብ ሃላፊ፥ ተንከባካቢ:: *አሳዳሪሽ ማነው?* 2.በሴት ሙሽራ ቤት የወንድን ሙሽራ ተቀብሎ የሚያስተናግድና የሚጋብዝ ሰው:: 3.የአሽከር፥ የሎሌ፥ የገረድ ጌታ::

**አስተዳደረ** ግ 1.ተቆጣጠረ፥ መራ፥ አኖረ (ህዝብን፥ ቤተሰብን፥ ሰራተኛን):: 2.አብሮ አደረ::

**አስተዳደር** ስ 1.የስራ አመራርና የሃላፊነት ተግባር:: 2.የሰው ሃይልንና የስራን አመራር በተመለከተ ስልጣንና ሃላፊነት ያለው አካል:: 3.የሌሊቱ አጠቃላይ ሁኔታ ወይም አኳሃን:: *የዛሬ ሌሊት አስተዳደርህ እንዴት ነበር? አልተሻለህም?* 4.የቤተሰብ አኗኗር ሁኔታ::

**አስተዳዳሪ** ስ መሪ፥ ሃላፊ (የድርጅት፥ የተወሰነ ሃገር ክፍል፥...)::ቅ 2.አብሮ የሚያድር::

**አደራ** እንደ አድርጉልኝ፥ ጠብቁልኝ፥ አስቀምጡልኝ፥... የመሳሰሉት ቃላት የሚያስተላልፉትን መልእክት በተመለከተ የሚነገር የጠበቀ ተማፅኖ፥ ልመና፥ማሳሰቢያ፥... ቃል:: *አደራ ይህንን እቃ አስቀምጥልኝ /አደራ ነገ እንድትመጣ:*

**ባለአደራ** አንድን ነገር ለማከናወን፥ ለማስቀመጥ፥... በፈቃደኝነት ሃላፊነትን የተቀበለ ሰው::

**አደራ በላ** ግ 1.አስቀምጥልኝ፥ ያዝልኝ፥... የተባለውን እቃ ወይም ገንዘብ፥... አጠፋ፥ ተጠቀመበት:: ቅ 2.እንዲጠብቅ፥ እንዲይዝ፥... የተሰጠውን እቃ ወይም ገንዘብ፥ ... ያጠፋ፥ የበላ (ሰው)::

**አደራ አለ** ግ አንድ ነገር እንዲደረግለት አጥበቆ አሳሰበ፥ ተማፀነ::

**አደራ ከታች** ቅ እንዲይዝ ወይም እንዲያስቀምጥ የተሰጠውን እቃ ወይም ገንዘብ፥... በጥንቃቄ የሚይዝ ወይም የሚጠብቅ፤ ታማኝ::

**የአደራ—** አስቀምጡልኝ፥ ጠብቁልኝ የተባለ (እቃ፥ ገንዘብ፥ ...)::

**የአደራ ደብዳቤ** ስ ከተራ መልእክት በተለየ ብልጫ የተከፈለበት፥ ደረሰኝ የሚሰጠውና ልዩ ጥንቃቄ ተደርጎለት ለተላከለት ሰው በእጁ የሚሰጥ ደብዳቤ::

**አደሰ** ግ 1.ጠገነ፥ አሮጌውን አዲስ እንዲሆን ወይም እንዲመስል አድርጎ ሰራ:: 2.አፀዳ፥ አሳመረ:: 3.እንደገና ተስማማ ወይም ተዋዋለ:: *ኮንትራቱን አደሱ:* 4-አስደሰተ ወይም አዝናና:: *ሙዚቃው መንፈሴን አደሰው:*

**አዲስ** (ብ.ቁ.**አዳዲስ**) ቅ 1.ከተሰራ ወይም ከተገዛ ያልቆየና አሮጌ ያልሆነ ወይም ያላገለገለ:: 2.እንግዳ፤ ከመጣ ያልቆየ (ሰው):: 3.ከዚህ በፊት ያልተሰማ ወይም ያልተባለ ወይም ከሌላው የተለየ (ሃሳብ)::

**አዲስ የመጣ** ቅ ከበፊቱ የተለየ፥ አዲስ ተሰርቶ የቀረበ:: *ያረገችው ጫማ አዲስ የመጣ ፋሽን ነው:*

**አዲስ መስመር** ስ በፅሁፍ ላይ አዲስ አንቀፅ የሚጀመርበትና ብዙውን ጊዜ ወደ ውስጥ ገባ ያለ ቦታ፤ የአንቀፅ መጀመሪያ::

**አዲስ [ሃዲስ] ኪዳን** ስ አራቱን ወንጌሎች፥ የሃዋርያት ስራን እንዲሁም የሃዋርያት መልእክቶችንና የዮሃንስ ራእይን የሚያጠቃልል የመፅሃፍ ቅዱስ ክፍል::

**እድሳት** ስ 1.ጥገና:: 2.ውልን፥ ፈቃድን፥ ... የማራዘም ሁኔታ::

**ታደሰ** ግ አገረሸ:: *ህመሙ ታደሰበት:*

**አደስ** ስ ቅጠሉ ደርቆ ከተወቀጠ በሂላ ሴቶች ከቅቤ ጋር ለውሰው ፀጉራቸውን የሚቀቡት ጥሩ ሽታ ያለው የእፅዋት አይነት::

**አደበ** ግ ዝም አለ፥ ጨመተ፥ ረጋ::

**አደብ** ስ ዝምታ፥ እርጋታ፥ ትእግስት::

**አደብ ገዛ** ጨዋ፥ ጭምት ሆነ።

**አደባባይ** ስ 1.ብዙ ህዝብ የሚሰበሰብበት ወይም የሚገኝበት ቦታ። 2.ሸንጎ ወይም ችሎት የሚካሄድበት ቦታ።3. አብዛኛውን ጊዜ በከተማ መንገዶች መጋጠሚያ መሃል ላይ በክፍትነት ተትቶ አትክልት፥ ሳር...የሚተከልበት ወይም ሃውልት የሚቆምበት ቦታ።

**የአደባባይ ልብስ** ስ የስራ ልብስ ያልሆነ፤ የክት ልብስ።

**የአደባባይ ሚስጢር**ሁሉም የሚያውቀው።

**አደብ** "አደበ" ስር ተመ.

**አደነ** ግ 1.አድብቶ ወይም አሳዶ ያዘ ወይም ገደለ። 2.ከዚያም ከዚህም እያለ ሰበሰበ፥ ቃረመ። *ወሬ ሲያድን ይውላል*። 3.አሰሰ፥ ፈለገ፥ አሳደደ፥ ተከተለ። *ሌት ሲያድን ይውላል*።

**አደን** ስ አውሬን አሳዶ ወይም አድብቶ የመያዝ ወይም የመግደል ድርጊት።

**አዳኝ** ቅ 1.እንደ አንበሳ፥ ነብር፥ ... ያሉ ሃይለኛ አውሬዎችን በመግደል የሚታወቅ ሰው። 2.ፈላጊ፥ አሳሽ። *ሌባ አዳኝ*።

**አዳኝ ውሻ** ስ አንድን የሚፈለግ ነገር (ለምሳሌ አውሬን፥ ወንጀለኛን፥...) በጠረን ወይም በሽታ ተከታትሎ የሚይዝ ወይም ምልክት የሚሰጥ የሰለጠነ ውሻ፤ ሰላግ ውሻም ይባላል።

**ታደነ** ግ 1. ተፈለገ፥ ክትትል ተደረገበት። 2.ተፈልጎ እንዲያዝና በቁጥጥር ስር እንዲውል ተደረገ (ሰው)።

**አደንጓሬ** ስ ቅርፁ ባቄላ የሚመስል ነገር ግን ጠፍጣፋ ያለና የተለያየ ቀለም ያለው ባለሃረግ የአበባ እህል።

**አደይ [አበባ]** ስ በመስከረም ወር የሚፈነዳ ብጫ ቀለም አበባ።

**አደገ** ግ 1.ቁመቱ ጨመረ፥ ተለቀ፥ተመነደገ። 2. ጨመረ፥ በረከተ፥ በዛ። 3. ላቀ፥ ከፍ አለ (በደረጃ፥ በሃብት፥በስልጣኔ ...)።

**ማደጎ** ቅ በተለያየ ምክንያት ከወላጆቹ ተነጥሎ ባእድ ወይም ዘመድ ቤት ያደገ።

**አዳጋ** ቅ ከፍ ያለ፥ ዳገታማ። *አዳጋ ቦታ*።

**እድገት** ስ 1.ከፍ ወይም ላቅ ያለ ደረጃ። 2.ብልፅግና ወይም ሃብት። 3.የቁመት መጨመር።

**ታዳጊ** ቅ 1.ቶሎ ቶሎ የሚያድግ። 2. ከ7-14 አመት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ወጣት (ልጅ)።

**ታዳጊ አገሮች** ስ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች።

**አሳደገ** ግ ተንከባክቦ ለትልቅነት አበቃ ወይም አደረሰ።

**አሳዳጊ** ቅ ልጆችን በመንከባከብ የሚያሳድግ፥ ወላጅ፤ ሞግዚት።

**አሳዳጊ የበደለው** (ስድብ) ያልተቀጣ፥ መረን አደግ፥ ባለጌ (ልጅ)።

**አስተዳደግ** ስ የእድገት ሁኔታ። *የልጁ አስተዳደግ ምቾት ያለው ነበር*።

**አደጋ** ስ ድንገት ሳይታሰብ የሚደርስ መጥፎ አጋጣሚ ወይም ጉዳት።

**አደጋ ላይ ጣለ** አደጋ እንዲደርስበት አደረገ።

**አደጋ ወደቀበት** አደጋ አጋጠመው።

**አደጋ ጣለ** አድፍጦ በሌላው ላይ አደጋ ወይም ድንገተኛ ጉዳት አደረሰ።

**አደገኛ** ቅ 1.ጉዳት የሚያስከትል ወይም የሚያደርስ። 2.ሃይለኛ፥ ብርቱ፥ ጠንካራ። 3.ተንኮለኛ፥ ክፉ።

**አደፈ** ግ ቆሸሸ፥ እድፍ ያዘ።

**አዳፋ** ቅ የቆሸሸ።

**እድፍ** ስ ቆሻሻ፥ ጭቅቅት።

**እድፋም** ቅ (ስድብ) ቆሻሻ፥ ጭቅቅት ያለበት ወይም የበዛበት።

**አደፍ** ስ የሴቶች የወር አበባ።

**አዱኛ** ስ ሃብት፥ ብልፅግና።

**አዲስ** "አደሰ" ስር ተመ.

**አዳል በግ** ስ በጣም ቆላ በሆነ አካባቢ የሚረባና ላቱ ሰፊ የሆነ የበግ አይነት።

**አዳሜ**(የን.አነ.) ስ ህዝብ፤ የአዳም ዘር። *አዳሜን ስቀልብ ልኖር ነው እንዴ?*

**አዳም ሃሙስ** ስ ከፋሲካ በሂላ ለሚመጣው የመጀመሪያው ሃሙስ የተሰጠ ስም።

**አዳሪ** "አደረ" ስር ተመ.

**አዳራሽ** ስ 1.ለስብሰባ፥ ለትርኢት ማሳያ፥ ... የሚያገለግልና ብዙ ሰው የሚይዝ ሰፊ ቤት። 2.ሰፊ፥ ትልቅ (ለቤት)።

**አዳር** "አደረ" ስር ተመ.

**አደሴቁኒ** ስ ጥቁር መልክ ያለው፥ ከአይጥ በለጥ የሚልና አይጥ መሰል የዱር አውሬ።

**አዳኝ** "ዳነ" ስር ተመ.

**አዳኝ** "አደነ" ስር ተመ.

**አዳይ** "አደለ" ስር ተመ.

**አዳጋ** "አደገ" ስር ተመ.

**አዳፋ** "አደፈ" ስር ተመ.

**አዳፍኔ** "ደፈነ" ስር ተመ.

**አድለቀለቀ** ግ አናወጠ፥ አንቀጠቀጠ።

**አድልዎ** "***ደላ**" ስር ተመ.

**አድመኛ** "**አደመ**[1]" ስር ተመ.

**አድማ** ዝ.ከ.

**አድማስ** ስ ሰማይና ምድር የተገናኙበትና የምድር ዳር ድንበር መስሉ የሚታይ ቦታ::

**አድራሻ** "**ደረሰ**" ስር ተመ.

**አድርባይ** "**አደረ**" ስር ተመ.

**አድባር** "**ደበረ**[1]" ስር ተመ.

**አድናቆት** "**ደነቀ**" ስር ተመ.

**አዶ** ስ እንደዝሆንና አንበሳ ያሉ ሃይለኛ አውሬዎችን የገደለ አዳኝ ያደርገው የነበረ ከዝሆን ኮቴ የሚሰራ አምባር ወይም ሎቲ::

**አዶቀረ** ገ ሲጠራ ጆሮው እየሰማ እንዳልሰማ በመምሰል ዝም አለ ወይም መልስ ሳይሰጥ ቀረ፤ አዶበረ::

**አዶወሸባዬ** ስ አውሬ (አንበሳ÷ ዝሆን÷...) ሲገደል አዳኝ ይዘፈን የነበረ ዘፈን::

**አጀለ** ገ 1.የደረቀ ወይም የገረረ ቆዳን ቅባት ቀብቶ በቅጠል በመጠቅለልና ድንጋይ ጭኖ በማሰንበት እንዲለዝብ ወይም እንዲለሰልስ አደረገ:: 2.የተሰበረ ወይም ቦታውን የለቀቀ አጥንትን ለማስተካከል ወይም ለመጠገን እንዲያመች አብሽ ቀብቶና በጨርቅ ጠቅልሎ አሰነበተ:: 3.ረዘም ላለ ጊዜ አንድ ቦታ ላይ አስቀመጠ÷ ወዘፈ::

**እጅላት** የአስተጃጀል ሁኔታ ወይም መንገድ::

**ታጀለ** ገ ከአንድ ቦታ ሳይንቀሳቀስ ለረጅም ጊዜ ቆየ:: *ስንት ሰአት ሙሉ እዚህ ታጅዬ እቀመጣለሁ?*

**አጀረ** ገ ነፋ፡ ቀበተተ (ሆድን)::

**አጀበ** ገ 1.ከበበ፡ ከግራ ከቀኝ፡ ከፊት ከሃላ በመሆን አብሮ ሄደ፤ ተከተለ:: 2.አንድ ቦታ ላይ ሰበሰበ ወይም አከማቸ::

**አጀብ** ስ 1.የማጀብ ስራ:: 2.አጃቢ::

**አጃቢ** ስ 1.ከንጉስ፡ ከባለስልጣን÷ ... ጋር ወደ ተለያየ ቦታ አብሮ የሚሄድ፤ ጠባቂ:: 2.የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመያዝ ድምፃዊውን (ዘፋኙን) የሚያዳምቅ የኪነት ጓድ::

**አጀብ** ግሩም÷ድንቅ÷ጉድ ለማለት የሚነገር ቃል::

**አጀንዳ** ስ 1.አድራሻና ከእለት እስከ አመት የተከናወኑ ወይም የሚከናወኑ ጉዳዮች የሚመዘገቡበት የቀን መቁጠሪያ ያለበት ማስታወሻ ደብተር:: 2.ለስብሰባ ወይም ለውይይት የሚቀርቡና በተራ ቁጥር የተዘረዘሩ ርእስ ጉዳዮች::

**አጃ** ስ የተነባበረ ሽፋንና ምርቅ ያለው ስንዴ የሚመስል እህል::

**አጃቢ** "**አጀበ**" ስር ተመ.

**አጅሬ** ቅ ጎበዙ÷ የማይሳነው÷ የታወቀው (በጥሩም በመጥፎም):: *አጅሬ ስራውን በጠዋት ጨርሶ ሄደ/ቤቱ ክፍት ከሆነ አጅሬ ገብቶ ይሰርቃል::*

**አገለ**[1] ገ ኮተኮተ÷ አፈር አስታቀፈ (ተክልን)::

**እግል** ስ የተኮተኮተና ስሩ አፈር የታቀፈ (አትክልት)::

**አገለ**[2] ገ አገረሸ÷ መልሶ አመመ (ቂጥኝ)::

**እግል** ስ የአገረሸ የቂጥኝ በሽታ::

**አገልግል** ስ በውስጡ ምግብ ወይም የተለያየ እቃ ለመያዝ የሚያገለግል ባለመክደኛ የስፌት እቃ::(ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)

**አገልግሎት** "***ገለገለ**" ስር ተመ.

**አገመ** ገ የታመመን ሰው ገላ በጥቶ የተበከለውን ደም በዋግምት ስቦ አወጣ::

**አገም ጠቀም አደረገ** 1.በአንድ በኩል የጠቀመ አስመስሎ በሌላ በኩል ጎዳ :: 2.ጥሩ ወይም መጥፎ የማይባል ስራ ሰራ::

**ዋገምት** በፊደል ተራው ተመ.

**አገመደደ** ግ አኮሳተረ÷ አጨማደደ÷ አጠቆረ (ፊትን)::

**አገር** "**ሃገር**"ን ተመ.

**አገተ** ገ 1.የተከለከለ ቦታ የገባና አትክልት÷ ሳር÷ አዝመራ÷... የበላን÷ ያበላሸን ከብት ይዞ አሰረ ወይም አጎረ:: 2.የዋስን ንብረት በእዳ ያዘ ወይም ወሰደ::3. አንድን ጉዳይ በማስገደድ ለማስፈፀምሰዎችን በመያዣነት ያዘ::

**አጋች** ቅ1. በተከለከለ ክልል ውስጥ የገቡ ከብቶችን ወይም ዋስ ሆኖ ግዴታውን ያልተወጣ ሰውን በመያዝ ወይም በማሰር አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ ወይም ለማስወሰድ የሚችል (ሰው):: 2. አንድን ጉዳይ አስገድዶ ለማስፈጸም ሰዎችን በማያዣነት የያዘ::

**እግት** ስ በህግ የተያዘ (ከብት÷ እቃ÷ ንብረት÷...)::

**ታገተ** ገ 1. በህግ ተያዘ (ዋስ÷ ንበረት÷...):: 2.በመያዣነት ተያዘ::

**ታጋች** ቅ በዋስትና ምክንያት ወይም በለውጡ ጥቅም ለማግኘት ሲባል በህግ ወይም በህገወጥ መንገድ በቁጥጥር ስር እንዲውል የተደረገ ሰው÷ ንብረት÷...::

**አገነደረ** "***ገነደረ**" ስር ተመ.

**አገና (አጋና)** ስ በሻጭና በገዢ መካከል የሚደረግ ስምምነት÷ ውል::

**አገና ተማታ** ሻጭና ገዢ ተስማማ፤ ተሻኮተ::

**አገና አማታ** ሻጭና ገዢን አስማማ፤አሻኮተ::

**አገዘ** ግ ረዳ፥ ደገፈ፥ ተባበረ።
**አጋዥ** ቅ ረዳት፥ ደጋፊ።
**አጋዥ ግንድ** ስ ከፊት ግንድ ቀጥሎ የሚገኝና የፊት ግንድ ረዳት የሆነ የሽማኔ እቃ።
**እገዛ** ስ እርዳታ።
**ታገዘ** ግ ተረዳ፥ ተደገፈ።
**ተጋገዘ** ተረዳዳ፥ ተባበረ (እርስ በእርስ)።
**አገደ** ግ 1.ከለከለ፥ አቆመ። 2.ገደበ፥ ከተረ። 3.ከብትን ጠበቀ።
**አጋጅ** ቅ እረኛ ወይም ጠባቂ።
**እገዳ** ስ 1.ከብት ጥበቃ። 2.ማእቀብ።
**እግድ** ቅ 1.ክልክል፡ ዝግ። 2.ክትር፥ ግድብ።
**አገደደ** ግ 1.አዞረ፥ ጠመዘዘ። *አንገቱን አገደደ*። 2.ጠመመ፥ ወለገደ።
**አገዳ** ስ 1.እንደ በቆሎ፥ ማሽላ፥ ... ያሉ የአዝርእት እህሎች ግንድ። 2.ሸንኮራ አገዳ። 3.ከጉልበት እስከ ቁርጭምጭሚት ወይም ከክርን እስከ አምባር መዋያ ያለው የእግርና የእጅ ክፍል።
**አገዳ ሰበር** ስ የአሞራ አይነት፥ ወድቆ የሚያገኘውን የበሬ ቅልጥም መቅን ለመብላት ሲል ወደ ሰማይ አውጥቶ ድንጋይ ላይ በመጣል ስለሚሰብር ቅልጥም ሰባሪ እየተባለም ይጠራል።
**የአገዳ እህል** ስ እንደ ማሽላ፥ በቆሎ፥... ሁሉ አገዳ ያለው የእህል አይነት።
**አገጭ** ስ በታችኛው ከንፈር አካባቢ የሚገኝ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።
**አገጫም** ቅ (ስድብ) አገጩ ትልቅ የሆነ ሰው፥ግንጭላም።
**አጉል** "**አጎለ**" ስር ተመ.
**አጉመተመተ** "**አጉተመተመ**"ን ተመ.
**አጉራ** "**አጎረ**" ስር ተመ.
**አጉራዶ** "**ጎረዶ**" ስር ተመ.
**አጉተመተመ(አጉመተመተ)** ግ አጉረመረመ።
**አጉተምታሚ (አጉመትማች)** ቅ አጉረምራሚ።
**አጋ**
**አጋ ለየ** በጥል ጊዜ ወገን፥ አጋር፥ አንጃ ለየ፥ የአንዱ ወገን ከሌላው ተለይቶ በመተባበር በአንድ በኩል ሆነ።
**አጋሙዳ** ቅ (ስድብ) ሆዳም፥ ከርሳም።
**አጋሚዶ** ስ በህዝብና በመንግስት ላይ ያመፀ፥ ዱር የገባ ወንበዴ፥ ሽፍታ።
**አጋም** ስ ፍሬው የሚበላ እሾሃም የእፅዋት አይነት።
**አጋም መሰለ** 1.ቀላ ያለ መልክ ያዘ። 2.በሰለ፥ ጎመራ።
**አጋም አዙርበት** በአጋም ተነቀስ (ጥርስህን)።
**አጋራ** ስ ገበሎ።
**አጋር** ስ ረዳት፥ ተባባሪ፥ ግብረ አበር።
**አጋሰስ** ስ 1.ለእቃ መጫኛ የሚያገለግል በቅሎ ወይም ፈረስ። 2.(ስድብ ዘይ) ሀ. ሆዳም፥ በልቶ የማይጠግብ።ለ. ገልቱ፥ ሙያ የሌለው።
**አጋች** "**አገተ**" ስር ተመ.
**አጋንንት** "**ጋኔን**"ን ተመ.
**አጋዘን** ስ ምድቡ በከብት ዘር ውስጥ የሆነ፥ ጠምዛዛና ረጃጅም ቀንዶች ያሉት ቅጠላ ቅጠል የሚመገብ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።
**አጋዥ** "**አገዘ**" ስር ተመ.
**አጋይ** '**ሃጋይ**"ን ተመ.
**አጋደደ** ግ አበደረ፥ አዋሰ።
**አጋጅ** "**አገደ**" ስር ተመ.
**አጋፈረ** ግ በቤተመንግስት፥ በግብር ቦታ፥... በር ላይ ቆሞ የሚገባውንና የሚወጣውን ሰው አስተናበረ፥ አስተናገደ።
**አጋፋሪ** ቅ አስተናባሪ (ብዙውን ጊዜ በግብር ወይም በቤተመንግስት በር ላይ በመቆም ስርአት የሚያስከብር)።
**አጋፌተ** ግ 1.ተረከዞቹ ላይ ቁጢጥ ብሎ በመቀመጥና በውስጥ በእግሮቹ ጣቶች መሬት በመርገጥ እጆቹን እጉልበቶቹ ላይ አድርጎ እፍ እፍ የሚል ድምፅ እያሰማ ወደ ላይ እንጣጥ እንጣጥ በማለት እየዘለለ ተጫወተ። 2.ያለ ስራ ከወዲያ ወዲህ ሮጠ፥ አደሸደሸ።
**አጋፋሪ** "**አጋፈረ**" ስር ተመ.
**አግራፍ** ስ ወረቀቶችን በአንድነት አጣብቆ ለመያዝ የሚያገለግል መንታ ጫፍ ያለው ሽቦ ወይም ብረት።



**አግራፍ**

**አግባብ** "**ገባ**" ስር ተመ.
**አግቦ** ስ አሽሙር፥ ሽሙጥ።
**አግቦኛ** ቅ አሽሟጣጭ፥ አሽሙረኛ።
**አግድመት** "**ገደመ**" ስር ተመ.
**አግድም** ዝ.ከ.
**አግድሞሽ** ዝ.ከ.
**አጎለ** ግ አወከ፥ አስቸገረ፥ መሰናከል ሆነ።
**አጉል (አንጉል)** ቅ የማይመች፥ መጥፎ።
**ታጎለ** ግ ተጓፈነ፥ ተቋረጠ(ግብር፥ቅዳሴ፥ ...)።

**ተጓጎለ** ግ ተሰናከለ፥ መደረግ የሚገባው ሳይደረግ ወይም ሳይከናወን ቀረ።

**አስታጎለ** ግ አዳፈነ፥ አቋረጠ (ቅዳሴን፥ ግብርን፥ ...)።

**አጎመ** ግ አነቀለ፥ አጎመጎመ።

**አጎረ** ግ 1.ከብቶችን ወደ በረት አስገብቶ በሩን ዘጋ። 2.አከማቸ፥ ሰበሰበ፥ አከተ።

**አጉራ** ስ ከብቶች እንዳይወጡ በበረት በር ላይ የሚጋደም እንጨት።

**አጉራህ ጠናኝ አለ** ተረታሁ፥ ተሸነፍኩ አለ (በሙግት ጊዜ)።

**አጉራ ዘለል** ቅ (ስድብ) ባለጌ፥ ስድ፥ ስነ ስርአት የጎደለው፤ ጋጠ ወጥ።

**አጎበር** ስ 1.አቧራን ወይም ነፍሳትን ለመከላከል በአልጋ ወይም በዙፋን ዙሪያ ላይ እንደ ድንኳን የሚዘረጋ መጋረጃ። 2.በአልጋ ቅርፅ የተሰራ፥ በላዩ ላይ እንደ ጣሪያ የሚያገለግሉ ቅስቶች የተደረጉበትና በግምጃ ወይም በጨርቅ የተሸፈነ የሬሳ ወይም የበሽተኛ ማጓጓዣ። 3.ግድግዳውና ጣሪያው ወጥነት ባላቸው እንጨቶች በቅስት መልክ የሚሰራ ጎጆ፤ ቅልስ።

**አጎበጎበ** ግ አሽቃበጠ፥ አቃለጠ።

**አጎብጋቢ** ቅ (ስድብ) አሽቃባጭ፥ አቃላጭ፥ አጨብጫቢ።

**አጎዛ** ስ 1.ተለፍቶ ለልብስነት ወይም ለንጣፍ የሚያገለግል የበግ ወይም የፍየል ቆዳ። 2.(ስድብ ዘይ.) ሞኝ፥ ጅል።

**አጎዳ** ስ የከብት ኩቱ። *ከብቱ ሲነዳ አጎዳው ከሩቅ ይሰማ ነበር።*

**አጎዶ**[1] ስ 1.እንደ ከሰል፥ ወርቅ፥... ያለ ማእድን የሚወጣበት ጉድጓድ። ቅ (ስድብ) መልከ ጥፉ።

**አጎዶ**[2] ስ የላም በረት (ጎንደር)።

**አጎት** ስ የአባት ወይም የእናት ወንድም።

**አጎጠጎጤ** "*ጎጠጎጠ" ስር ተመ.

**አጎጤ** ዝ.ከ.

**አጓመጠ** "ጓመጠ" ስር ተመ.

**አጓራ** ግ ተደጋጋሚ ጩሀት አሰማ (ዛር የሰፈረበት ሰው)።

**አጓት** ስ አሬራ ወይም ወገሚት ከተፈላ በሗላ አይቡ ሲዘቅጥ ከላይ ጠልሎ የሚቀረው ውሃ መሰል ወተት ወይም ነጭ ፈሳሽ።

**አጓጉል** "አጎለ" ስር ተመ.

**አጓጎት (ጓጎት)** ስ ብዙውን ጊዜ በፊት ወይም በእጅ ላይ የሚታይ እንደ ጭርት ያለ የቆዳ በሽታ።

**አጠረ**[1] ግ 1.ቁመቱ ወይም ርዝመቱ ተቀነሰ፥ አጭር ሆነ፤ አነሰ። 2.አጠጠ፥ ቸገረ (ገንዘብ፥ ጊዜ፥ ...)።

**አጣራ** ቅ አጭር ወይም ቁመቱ ዘለግ ያላለ።

**አጭር** (ብ.ቁ.**አጫጭር**) ቅ 1. ርዝመቱ ወይም ቁመቱ ያነሰ። 2.ድንክ፥ ድውይ። 3.የተወሰነ፥ ጥቂት (ጊዜ፥... )።

**በአጭር ቀረ** 1.ያለ እድሜው በቶሎ ሞተ። 2.እድገቱ ተደናቀፈ ፥ ተቀጨ።

**በአጭር ቅር** (እር.) አትደግ፥ ያለእድሜህ ቶሎ ይግደልህ።

**በአጭር ታጠቀ** ከልብ ተዘጋጀ (ለስራ፥ ለጉዞ፥...)።

**አጭር ልቦለድ** ስ በጥቂት ገፀ ባህርያትና በአጠረ ጊዜ ተመጥኖ በአንድ ታሪክና በዚያ ታሪክ ነጠላ ውጤት ላይ የሚያተኩር፥ በስድ ንባብ የተቀነባበረ የስነፅሁፍ አይነት።

**አጭር ቃል** ስ ሃተታ የሌለበት ንግግር፥ ፍሬ ነገሩ ብቻ።

**አጭሬ** ስ 1.ቁመተ አጭር የዘንጋዳ አይነት። 2.ከዶሮ ስጋ ብልት የጭኑ ክፍል።

**እጥረት** ስ የአንድ ነገር ማነስ፥ በበቂ ሁኔታ ወይም በብዛት አለመገኘት።

**እጥር ምጥን ያለ** ሳያጥር ሳይረዝም፥ ሳይበዛ ሳያንስ በልክ የሆነ፥ የተመጠነ።

**አጠረ**[2] ግ1. በእንጨት፥ በድንጋይ፥ በእሾሁ፥ ... የቤትን የአዝርእትን፥ ... ዙሪያ ከለለ ወይም ጋረደ።2. ከለከለ፥ዘጋ፥አላሳልፍ አለ።

**አጥር** ስ በእንጨት ወይም በድንጋይ ወይም በእሾህ፥... በቤት፥ በአዝርእት፥... ዙሪያ የሚደረግ ከለላ፤ ገረገራ፤ ቅጥር።

**አጥር ቅጥር** ስ የቤት አጥርና ግቢ።

**አጥር ግቢ** ስ ከአጥር በውስጥ በኩል ያለ የቤት አካባቢ፥ ግቢ።

**አጠበ** ግ 1. እፀዳ፥ አጠራ፥ አነፃ፥ ቆሻሻን አስለቀቀ ወይም አስወገደ (በውሃ፥ በሳሙና፥...)። 2.ሙጥጥ አድርጎ ወሰደ ወይም ሰረቀ (ንብረትን)። 3. ከፎቶግራፍ ፊልም ላይ ምስልን በወረቀት ላይ አወጣ፥ አተመ።

**ቢያጥቡት አይጠራ** 1.ቂመኛ፥ ነገር በሆዱ የሚይዝ (ሰው)። 2.እንከን፥ ጉድለት፥... የማያጣው።

**እጣቢ** ስ ከሚታጠብ ነገር ላይ የሚወጣ እድፍ ወይም ቆሻሻ።

**እጥብጣቢ** ዝ.ከ.

**እጥብጥብ አለ** ግ 1.ተጣጠበ፥ ፀዳ። 2.ለቀቀ፥ ተሟጠጠ፥ ባዶ ሆነ።

**እጥብጥብ አድርጎ ወሰደ** ምንም ሳያስቀር ሙጥጥ አድርጎ ወሰደ።

**ታጠበ** ግ 1. ከቆሻሻ ጠራ፥ ፀዳ፥ ነፃ።

2. በኬሚካል አማካይነት በፎቶግራፍ ፊልም ላይ ያለ ምስል እንዲታይ ማድረግ፡ ማጥቆር።

**ታጥቦ ጭቃ** ስ አንድን እጉል ልማድ ወይም አታድርግ፡ አይሆንም የተባሉትን ነገር ለጊዜው ከተው በሂላ እንደገና ወደዚያው የመመለስ ድርጊት።

**መታጠቢያ** ስ ገላን (ሰውነትን) ለመታጠብ የሚያገለግል (ውሃ፡ ሳሙና፡ ቦታ)።

**መታጠቢያ ቤት** ስ ገላን (ሰውነትን) ለመታጠቢያ የሚያገለግል ቤት ወይም ክፍል።

**ተጣጠበ** ግ ተለቃለቀ፡ ታጠበ።

**አስታጠበ** ግ እጅ ላይ ውሃ በመጨመር እንዲታጠብ አደረገ።

**አጠነ** ግ 1. እንደ እጣን፡ ስራስር፥ ቅጠላ ቅጠል፡ ... ያሉ ነገሮችን እሳት ላይ አድርጎ በማጤስ መአዛው እንዲሸት ወይም እንዲያውድ አደረገ። 2.የታጠበ ልብስ ወይም የጠላ እቃ ጥሩ መአዛ እንዲያገኝ የማእጠንት ጢስ እንዲጤስበት አደረገ።

**አጣኝ** ስ ቤተ ክርስቲያንን ወይም ቤተ ፀሎትን የሚያጥን ቄስ።

**ያጣኝ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) ዋናው ተዝካር በተበላ በሰለተኛው ቀን ለተወሰኑ ካህናት ብቻ ይደረግ የነበረ መጠነኛ ግብዣ።

**እጣን** ስ ጢሱ ጥሩ መአዛ ያለው የእንጨት ሙጫ።

**እጣን ሞገር** ስ ከቅዳሴ መጨረሻ ገደማ ላይ የሚባል የግእዝ ቅኔ።

**ማእጠንት (ማጠንት)** ስ እንደ ሰንቡል፥ ኡድ፥ ጥንዡት፥ ... ያለና ጥሩ መአዛ ያለው የጢስ እንጨት።

**አሳጠነ** ግ እንዲታጠን አደረገ ወይም አስደረገ።

**አጠናቀረ** "*ጠነቀረ" ስር ተመ.

**አጠናገረ** "*ጠነገረ" ስር ተመ.

**አጠድ** "አፀድ"ን ተመ.

**አጠገብ** ተው.ግ አቅራቢያ።

**አጠገብ ለአጠገብ** ቅርብ ለቅርብ፥ ያልተ ራራቀ።

**አጠጠ** ግ አነሰ፥ ጎደለ።

**እጥጥ ሙጥጥ አለ** ግ አለቀ፥ ተሟጠጠ።

**አጠፈ** ግ 1.ስፋት ወይም እርዝመት ያለውን ነገር (ጋቢ፥ ነጠላ፥ ...) ደጋግሞ በመቀልበስ መጠኑ አነስ እንዲል አደረገ። 2.ቆለመመ፥ አስጎነበሰ። *ምስማሩን አጠፈው*። 3.ዘጋ፥ ከደነ (መፅሃፍን)። 4.ያለውን ቁጥር ያህል መጠኑ ጨመረ፤ አጠፌታ አደረገ።

**ማጠፊያ** ስ መዝጊያንና መስኮትን ከመቃን ጋር ለማያያዝና ወዲያና ወዲህ ለማንቀሳቀስ (ለመዝጋትና ለመክፈት) የሚያገለግል ብረት።

**አጠፌታ** ስ እጥፍ።

**እጥፍ** ቅ ድርብ፥ ጥንድ ፤ ነጠላ ያልሆነ።

**እጥፍ ድርብ** ቅ አያሌ፡ ብዙ።

**እጥፋት** ስ ቅልብሳት፤ ስብራት (የልብስ)።

**ታጠፈ** ግ 1.ቀጥታውን መንገድ ትቶ ወደ ጎን አመራ። 2.ተቀነፈ፡ ተቀለሰ። 3.ተጎነበሰ፥ ተቆለመመ።

**ታጣፊ** ቅ ሊያጥር ወይም ሊተጣጠፍ፥ ሊቆለመም የሚችል (አልጋ፥ ወንበር፥ ብረት፥...)።

**ተጣጠፈ** ግ ተከራመተ፥ ተጨባበጠ።

**አጣ** ግ 1.ተቸገረ፡ ደሀየ። 2.የፈለገውን ወይም የተመኘውን ሳያገኝ ቀረ። 3.ረሳ፡ ጠፋበት፥ ሳያውቀው ቀረ። *የጥያቄውን መልስ አጣው*።

**አጣ ነጣ** በጣም ተቸገረ፡ ደሀየ።

**እጦት** ስ ችግር፡ ድህነት።

**እጦተኛ** ቅ ችግረኛ፡ ደሃ።

**ታጣ** ግ 1.ጠፋ፡ ሳይገኝ ቀረ። 2.ተረሳ፡ ተዘነጋ።

**ተጣጣ(ተጣጡ)** ግ 1. ተረሳሳ፡ አንዱ ሌላውን ማስታወስ ተሳነው፡ ተጠፋፋ። 2.ሳይገናኙ ቀሩ።

**አሳጣ** ግ ከለከለ፡ ነሳ።

**አጣሪ** "ጠራ[2]" ስር ተመ.

**አጣራ** ዝ .ከ.

**አጣራ** "አጠረ[1]" ስር ተመ.

**አጣቀሰ** ግ አሳበቀ፥ አዋሸከ።

**አጣቢ** "አጠበ" ስር ተመ.

**አጣና** ስ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጥ፥ መጠነኛ ውፍረት ያለውና መለል ብሎ ዘለግ ያለ ድፍን እንጨት(ብዙውን ጊዜ ባህርዛፍ)።

**አጣኝ** "አጠነ" ስር ተመ.

**አጣጥ** ስ ትንንሽ እሾህ ያለው የቁጥቋጦ ዛፍ አይነት።

**አጣፋ** ግ 1.ጋቢን፥ ነጠላን፥ ኩታን፥... ከአንደኛው ትከሻው እስከ ሁለተኛው ትከሻው በመዘርጋት ሰውነቱን ሸፈነ፥ አለበሰ። 2.መካፈል የሚችሉ ቁጥሮችን አካፈለ (ሂሳብ)።

**ማጣፊያ** ስ የኩታ፥ የጃኖ ቁመት ወይም ርዝመት።

**ማጣፊያ አጠረው** የሚናገረውን ወይም የሚያደርገውን ወይም የሚሆነውን እጣ፥ ተቸገረ፤ ዘዴ፥ ተብልሃት ጠፋው፥ አጠረው።

**አጣፊኝ** ስ በአንገት ላይ የሚለበስ ባለ አንድ ፈርጅ ነጠላ።
**አጤ** "**አፄ**"ን ተመ.
**አጥሚት** ስ በአብዛኛው የአጃ ወይም የገብስ ወይም የስንዴ ዱቄትን በውሃ በጥብጦ እሳት ላይ በማንተክተክ (በማብሰል) በፈሳሽ መልክ የሚዘጋጅ ምግብ፤ ሙቅ፤ እንትክትክ።
**አጥር** "**አጠረ**²" ስር ተመ.
**አጥቅ** "**አፅቅ**" ን ተመ.
**አጥቢያ**¹ ስ አካባቢ፥ ሰበካ፥ ቀበሌ።
**አጥቢያ ዳኛ** ስ በአንድ በተወሰነ አካባቢ በዳኝነት እንዲያገለግል ከህዝብ መካከል ተመርጦ የተሰየመ ዳኛ።
**አጥቢያ**² "**ጠባ**²" ስር ተመ.
**አጥናፍ** "**ጠንፍ**" ስር ተመ.
**አጥንት** ስ በስጋና በቆዳ የተሸፈነውና ጠንካራ የሆነው የአካል ክፍል።
**አጥንተ ሰባራ** ቅ ዘሩ ወይም ትውልዱ ከሃብታም፥ ከባላባት፥ ከጨዋ ዘር ያልሆነ ለማለት በቀድሞ ጊዜ ይነገር የነበረ ቃል።
**አጥንት የሚሰብር** ስሜት የሚጎዳ፥ ዘርን የሚነካ መጥፎ ስድብ ወይም ንግግር ።
**አጥንቱ የወጣ** በጣም የከሳ፤ አጥንቱ የገጠጠ።
**የአጥንት ልጅ** መደበኛ የመወለጃ ጊዜውን አሳልፎ የተወለደ ልጅ።
**የአጥንት ፍላጭ የስጋ ቁራጭ** ከአብራክ የወጣ የገዛ ልጅ።
**አጥግቢኝ** "**ጠገበ**" ስር ተመ.
**አጥፍ** "**አፅፍ**"ን ተመ.
**አጩ** ግ 1.መለመለ፥ መረጠ (ለሹመት፥ ለእድገት)። 2.ቃል ኪዳን አሰረ፥ ለትዳር መረጠ፥ ተዋዋለ።
**ማጫ** ስ ለሚስትነት ለተመረጠችው ልጅ የሚ ሰጥ ገንዘብ፥ ከብት፥ ...።
**እጭታ** ስ አንድን ሴት ልጅ ለትዳር መርጦ ወይም መልምሎ በቃል ኪዳን ያስቀመጠ ሰው።
**እጩ** ቅ ለአንድ ጉዳይ (ለሹመት፥ ለስራ፥ ...) የተመለመለ ወይም የታሰበ (ሰው)።
**እጮኛ** ስ ቃል ኪዳን የገባ ወይም ቀለበት ያሰረ የወደፊት የትዳር ጓደኛ።
**አጨለገ** ግ 1.በአንድ አይኑ በቀዳዳ ተመለከተ፥ አጮለቀ፥ አንጣጠረ። 2. አታልሎ ወሰደ፥ ሰረቀ።
**አጭልግ (አጭላጊ)** ቅ አታላይ፥ ሌባ።
**አጨቀ** ግ በብዛት አመቀ፥ ከተተ፥ ጨመረ።
**ታጨቀ** ግ በብዛት ተከተተ፥ ታመቀ።
**አጨናፈረ** "**ጨነፈረ**" ስር ተመ.
**አጨደ** ግ በብዛት በመያዝ ከስር ቆረጠ (ሳርን፥ ሰብልን፥...)።
**አጨደው** ጨረሰው፥ ፈጀው። *ረሃብ ህዝቡን ላጨደው*።
**ማጭድ** ስ ከብረት የሚሰራ፥ እንደ ደጋን ጎበጥ ብሎ በአንድ በኩል ከስር እስከ ጫፍ ስለት ያለው ና ሳርን፥ ሰብልን፥... ለማጨድ የሚያገለግል ባለእጀታ የግብርና መሳሪያ።



ማጭድ

**አጨዳ** ስ የማጨድ ተግባር።
**አጫዳ** ስ (ዘይ፥ ስድብ) እግረ ሽፋፋ።
**አጭልግ** "**አጨለገ**" ስር ተመ.
**አጭሬ** "**አጠረ**¹" ስር ተመ.
**አጭር** ዝ.ከ.
**አጭታ** "**አጨ**" ስር ተመ.
**አጮለ** "***ጮለ**" ስር ተመ.
**አጮለቀ** ግ አዩኝ አላዩኝ እያለ ቀስ ብሎ በስርቆት ተመለከተ።
**አጮልቆ አየ** ዝ.ከ.
**አፀድ (አጠድ)** ስ 1.የአትክልት ወይም የዛፍ ቦታ። 2.በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ያለ አትክልት ወይም ዛፍ።
**አፀደ ህፃናት** ስ ህፃናትን ለመደበኛ ትምህርት የሚያዘጋጅ ትምህርት ቤት።
**አፀደ ነፍስ** ስ ሰው ከሞተ በሂላ ነፍሱ በሰማይ ትኖርበታለች ተብሎ የሚታመንበት ቦታ።
**አፀፋ** ስ ምላሽ።
**አፄ (አጤ)** ቅ በንጉስ የተፀውኦ ስም ላይ ተደርቦ በመነገር ንጉሳዊ ማእረግን የሚገልፅ ቃል። *አፄ ዮሃንስ፥ አፄ ሚኒልክ፥ አፄ ሃይለ ስላሴ*።
**አፅም** ስ አጥንት።
**አፅሙ የረገፈበት** የተቀበረበት።
**አፅመ ርስት** የ"ርስት"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.
**አፅቅ (አጥቅ)** ስ 1. የዛፍ



አፅም

ወይም የተክል ቅርንጫፍ አናት፥ ጫፍጫፉ:: 2.ከአንጓ እስከ አንጓ ያለ የጣት ክፍል፣ ቅልጥም::

**አፅናፍ "ጠንፍ"** ስር **"አጥናፍ"**ን ተመ.

**አፅፍ (አጥፍ)** ስ ከአጋዘን ወይም ከበሬ ቆዳ የሚሰራ የመነኩሴ ልብስ::

**አፈለ** ግ 1.ጎለመሰ፥ ጎረመሰ:: 2.ጠነከረ፥ በረታ፥ ጎበዘ::

**አፍላ** ቅ 1.ጎረምሳ፥ ወጣት:: 2.ያልዘገየ፥ ያል ቆየ፥ ትኩስ::

**አፍላ እንቅልፍ** ከጀመረ ብዙም ያልቆየ ሃይለኛ እንቅልፍ::

**አፍለኛ** ቅ 1.ጎረምሳ፥ ወጣት:: 2.አፍለኝ::

**አፍለኝ (አፍለኛ)** ቅ ከአልቦካ ሊጥ የተጋገረ እንጀራ::

**አፈላማ** ስ አትክልቱ ወይም ሰብሉ በከብት የተበላበት ሰው ከባለከብቱ የሚቀበለው ገንዘብ::

**አፈሙዝ** ስ የጠመንጃ፥ የሽጉጥ፥ ... አፍ::

**አፈረ** ግ 1.በአሳፋሪ ድርጊቱ ተዋረደ፥ ቀለለ:: 2.ፈራ፥ ተሽኮረመመ:: 3.ጠወለገ፥ ደረቀ:: 4.ሽፈጠ፥ ከዳ፥ አሌ አለ፥ ቃሉን ለወጠ:: 5.እያነሰ ወይም እየጎደለ ሄደ (ምንጭ)::

**ማፈሪያ** ስ አሳፋሪ፥ አዋራጅ::

**እፍረት (ሃፍረት፥ ህፍረት)** ስ 1.ውርደት፥ ቅሌት፥ ነውር:: 2.ፍርሃት፥ መሽኮርመም:: 3.ሽፍጥ::

**እፍረቱን ጣለ** 1.እርቃኑን ሆነ:: 2.ማፈር መፍራቱን ተወ፣ አይነ ደረቅ ሆነ::

**ሃፍረት የሌለው (እፍረት የሌለው)** 1.(በድብ) የማያፍር፥ ቅሌታም፥ ወራዳ፥ ነውረኛ:: 2.ይሉኝታ የለሽ፥ የማይፈራ::

**እፍረተ ስጋ** ስ የሴት ወይም የወንድ ብልት::

**እፍረተ ቢስ** ቅ ሃፍረት የሌለው::

**ታፈረ** ግ ተፈራ፥ ተከበረ::

**ተፋፈረ(ሩ)** ግ ተፈራራ::

**አሳፈረ** ግ 1.አዋረደ፥ አቃለለ:: 2.አስከበረ፥ አስጠበቀ::

**አሳፋሪ** ቅ አዋራጅ፥ ዝቅ የሚያደርግ፥ ቅሌት ላይ የሚጥል::

**አፈር** ስ 1.የተፈረፈረ ወይም የተቆፈረ የመሬት አካል:: 2.አቧራ፥ ትቢያ::

**አፈሩን ገለባ ያድርግለት** የሞተን ሰው ስም በማንሳት ሃሳቡን ለመግለፅ የሚፈልግ ሰው የሟችን ስም ከመጥራቱ በፊት "መከራው ይቅለልለት" ለማለት የሚጠቀምበት የበጎ ምኞት መግለጫ ቃል::

**አፈር ሆነ** 1.ሞተ፥ ተቀበረ:: 2.በሰበሰ፥ ወደአፈርነት ተለወጠ፥ ትቢያ ሆነ::

**አፈር ስሆንልህ** አንድ ነገር እንዲደረግ፥ እንዲሰራ ለመለመን የሚያገለግል የልምምጥ ወይም የማግባቢያ ቃል:: *አፈር ስሆንልህ ይቾን ጉረስልኝ::*

**አፈር ለበሰ** ተቀበረ::

**አፈር አለበሰ** ቀበረ::

**አፈር አልባሽ** 1.ቀባሪ (ዘመድ፥ ቤተሰብ፥ ወገን):: 2.ጧሪ ቀባሪ::

**አፈር መለሰ** ቀበረ፥ በአፈር ሸፈነ::

**አፈረ መሰለ** ፊቱ በጣም ጠቆረ፥ ጠወለገ፥ ተጎሳቆለ::

**አፈር ቀመሰ** 1.ሞተ:: 2.ተቀበረ::

**አፈር ቃመ** 1.አፈር በላ:: 2.በአፈር ተለወሰ፥ ተበላሸ::

**አፈር በላ** 1.ሞተ:: 2.ተበላሸ፥ ከጥቅም ውጭ ሆነ::

**አፈር በላው** ሞተ::

**አፈር ብላ/ቃም** (እር.) ሙት፥ አፈር ሁን፥ ተቀበር::

**አፈር ይብላኝ** ማዘንን ወይም መፀፀትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል:: *አፈር ይብላኝ ከቤቱ እንደወጣ በዚያው ድፍት ብሎ ቀረ::*

**አፈር ጋጠ** ብዙ ለፋ፥ ደከመ::

**አፈር [ድቤ] አስጋጠ** 1.በሃይል ደበደበ፥ መታ:: 2.አለፋ፥ አደከመ::

**አፈር ጠራው** ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንደ ሄደ በድንገት ሞቶ እዚያው ተቀበረ::

**እንደ አፈር ነው** ብዙ፥ ኣያሌ ነው::

**አፈር ገፊ** ስ ገበሬ፥ አርሶ አደር::

**አፈርማ** ቅ አፈር የሚመስል::

**አፈርሳታ** ስ አንድን ወንጀል በድብቅ የፈፀመን ሰው ለማውጣት ወይም ለማጋለጥ የሚደረግ የሰፈር ስብሰባ፣ አውጫጭኝ::

**አፈሰ** ግ 1.ዘገነ፥ ዛቀ፥ ተረፈሰ (እህልን፥ አፈርን፥...):: 2.ሰውን ያለፍላጎቱ በማስገደድ ወሰደ::

**አፋሽ አጎንባሽ** ማንኛውም ተራ ሰው፥ ትንሽ ትልቁ::

**አፈሳ** ስ 1.ለተወሰነ አላማ ሰዎችን አለፍላጎታቸው ይዞ የመውሰድ ድርጊት:: 2.ዝቆሽ፥ ርካሽ:: *የዘንድሮው ዝሪ አፈሳ ነው::*

**ታፈሰ** ግ 1. ተያዘ፥ ተወሰደ:: 2. በብዛት ተገኘ፥ በረከተ (ምርት)::3. ተዛቀ፥ተተረፈሰ::

**አፊቀላጤ "አፍ"** ስር ተመ.

**አፈተተ**

**እንደ አፈተተው** እንደአሻው፥ እንደፈለገው:: *እንደ አፈተተው ያድርግ*::

**አፈቸለ** ግ ለፈለፈ::

**አፈነ**[1] ግ 1.ትንፋሽ ከለከለ፥ ዘጋ:: 2.አጨለመ፥ ሸፈነ (ጉም፥ ጭጋግ):: 3.ወሬን እንዳይሰራጭ ወይም እንዳይሰማ አደረገ:: 4.የመናገር ወይም ሃሳብ የመግለፅ እድል አሳጣ:: 5.በቤት አስሮ ቀለበ (እንስሳትን):: 6.አስገድዶ ወይም አንቆ ወሰደ:: 7.አውድማ ላይ የሚያበራየውን የበሬ አፍ አሰረ ወይም ሸበበ:: 8.እጅብ እጅብ አደረገ፥ ከበበ::

**ማፈኛ** ስ የጆሮ ጌጥ፥ ጆሮ ላይ ከተሰካ በሂላ እንዳይወልቅ ከበስተሂላ በኩል ዘንጉ ላይ የሚሰካ ነገር::

**አፈና** ስ 1.አስገድዶ ወይም አፍኖ መውሰድ:: 2.ጭጋግ፥ ጉምና ዝናብ የሆነበት ቀን::

**አፋኝ [ቡድን]** ስ ሰውን እያስገደደ የሚወስድ፥ የሚያስር፥ የሚሰውር ቡድን::

**እፍንፍን** ስ ትፍግፍግ፥ ጭንቅንቅ::

**እፍንፍን አለ** ግ ተጣበበ፥ ተጨናነቀ::

**ታፈነ** ግ 1.አየሩ በጢስ፥ በጭጋግ፥... ተበከለ፥ ተሞላ፤ ንፁህ አየር ታጣ:: 2.ትንፋሹ ተቋረጠ፥ ተዘጋ::

**ተፋፈነ** ግ ተፋፈገ፥ እፍንፍን አለ::

**አፈነ**[2] ግ በእፍኝ ዘገነ፥ ቆነጠረ::

**እፍኝ** ስ 1.ጥራጥሬ፥ ውሃ፥...መያዝ የሚያስችል የተገጣጠሙና ጣቶች ወደ ላይ ቀና ያሉበት የሁለት እጆች የውስጥ ክፍል:: 2.በእፍኝ የተያዘ ወይም የተለካ ጠጣር ወይም ፈሳሽ ነገር:: 3.ጥርኝ፥ ጭብጥ::

**አፈነገጠ "*ፈነገጠ"** ስር ተመ.

**አፈንጋጭ** ዝ.ከ.

**አፈና "አፈነ[1]"** ስር ተመ.

**አፈኛ "አፍ"** ስር ተመ.

**አፈከፈከ** ግ በህመም ምክንያት የሰውነት ቆዳ ሊገለፈፍ ወይም ሊቀረፍ ደረሰ፤ አሸቀሸቀ::

**አፈገ** ግ አመገ፥ አፈነ:: 2-መሰገ፥ አከተ፥ አጎረ (ከብትን)::

**እፍግ** ቅ በመተፋፈን ወይም በመታፈግ የሚፈጠር መጥፎ ሽታ፥ እምክ::

**ታፈገ** ግ ታመገ፥ ታመከ፥ ታፈነ::

**ተፋፈገ** ግ ተጣበበ፥ ተጨናነቀ::

**አፈገፈገ** ግ ወደ ሂላ ሸሸ::

**አፈጠረ** ግ (እስል.) የረመዳን ፆም ሲፆም ውሉ ማታ ላይ ምግብ በላ፥ ፈሰከ::

**አፈጠፈጠ** ግ አቆጠቆጠ፥ ቅጠል አወጣ::

**አፈፈ** ግ ከረከመ፥ አስተካከለ::

**እፉፊ** ቅ ቅራፊ፥ ቁራጭ::

***አፈፈ**

**አፈፍ አለ** ግ በፍጥነት ተነሳ፥ ብድግ አለ::

**አፈፍ አፈፍ አለ** ግ ፈጠን ፈጠን፥ ቸኮል ቸኮል ብሉ ተራመደ::

**አፈፍ አደረገ** ግ ለቀም አደረገ፥ በፍጥነት ያዘ ወይም ጨበጠ::


**አፉ** ስ እንደሰይፍ ያለ ትልቅ ቢላዋ፤ ካራ::

**አፋኝ [ቡድን] "አፈነ[1]"** ስር ተመ.

**አፋዊ "አፍ"** ስር ተመ.

**አፋፍ** ስ 1.የገደል አፍ ወይም ጠርዝ:: 2.የተራራ ወይም የኮረብታ ጫፍ::

**አፍ** ስ 1.በውስጡ ምላስንና ጥርስን የያዘና ለምግብ መብያ፥ ለመተንፈሻና ለመናገሪያ የሚያገለግል፥ የሚዘጋና የሚከፈት የሰውነት ክፍል:: 2.ስለት:: *ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ*:: 3.ቋንቋ፥ ልሳን:: *የፈረንጅ አፍ ያውቃል*:: 4.ለማስገቢያና ለማስወጫ የሚያገለግል በአንድ በኩል ብቻ ያለ ክፍፍተት:: *የጠርሙሱ አፍ ጠባብ ነው*:: 5.ፊርጅ፥ ጠርዝ (የነጠላ፥ የጋቢ፥ ...):: *ሌላውን ቋጭቼ አንድ አፍ ይቀረኛል*:: 6.(ዘይ.) ነገር፥ ጭቅጭቅ፥ ንትርክ:: *አፍ ያበዛል*::




አፍ 1ኛ ፍቺ

**ለአፉ ገደብ (ለከት) የለውም** እንደልቡ፥ እንደመጣለት ይናገራል::

**በአፌ** በጠበቃዬ::

**በአፍ በአፉ አጎረሰው** በላይ በላዩ ቶሎ ቶሎ አጎረሰው::

**አፉ ተዘጋ** ዝም አለ::

**አፉ ላይ ተንቀዋለለ** የምግብ ፍላጎት ከማጣት የተነሳ የጎረሰው ምግብ አልዋጥ አለው::

**'አፉን ለጎመ** ዝም ወይም ፀጥ አለ፥ አልናገር አለ::

**አፉን ሞልቶ ተናገረ** በድፍረት፥ በሙሉ እምነት፥ ሳያመነታ፥ ሳይጠራጠር ተናገረ::

**አፉን ነጠቅ ነጠቅ ያደርገዋል** 1.ሲናገር አንደበቱ በጣም ይፈጥናል:: 2.ሲናገር ጠንቃቃ አይደለም፤ መናገር የማይገባውን ሁሉ ይናገራል::

**አፉን ነጠበው** ሳያስበው፥ መናገር የማይገባውን ነገር በድንገት ተናገረ::

**አፉን አሟሸ** እህል ውሃ ቀመሰ::

**አፍ ማሟሻ** ስ ቁርስ::

**አፉን አሾለ** ለነገር፥ ለስድብ አቆበቆበ::

**አፉን አበላሸ /አጠፋ** የለመነውን ወይም የጠየቀውን ሳያገኝ ቀረ::

**አፉን አዳለጠው /አዳጠው** መናገር የማይገባውን ነገር ተሳስቶ ተናገረ፤ ነገር አመለጠው::

**አፉን ከፈተ** 1.ጮሀ፥ ቀባጠረ፥ ለፈለፈ:: 2.በጣም ተሰነጠቀ::

**አፉን ያዘ** ዝም ወይም ፀጥ አለ::

**አፉን አስያዘው** ዝም ወይም ፀጥ አሰኘው፤ አሳፈረው::

**አፉን ይበላዋል** ለመናገር ይቸኩላል፥ ዝም ማለት አይችልም፤ እንዲናገር የሚገፋፋው ስሜት አለ::

**አፉን ይይዘዋል** በትክክል መናገር ይሳነዋል፤ ይነተባተባል፥ ይኮላተፋል (ለትልቅ ሰው)::

**አፉን ጠበቀ** የማይገባ ነገር እንዳይናገር ጥንቃቄ አደረገ::

**አፉን ፈታ** መናገር ጀመረ (ህፃን)::

**አፌ ላይ ነው** ትውስታው አእምሮዬ ውስጥ እያለ በአንደበቴ ነገሩን መጥራት አቃተኝ::

**አፍ ለቀቀበት** "ላሰ" ስር "ምላስ ለቀቀበት"ን ተመ.

**አፍ ለአፍ** ፊት ለፊት፥ ትይዩ::

**አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ** ተቀራርበው በሹክሹክታ ሲያወሩ::

**አፍ ቂጡ ሳቀ** (ተራ.አነ.) በጣም ተደሰተ፥ ተፍነከነከ::

**አፍ ቂጡ ሸበተ** (ተራ.አነ.) በጣም አረጀ፥ አፈጀ::

**አፍ ተካፈተ** ተሰዳደበ፤ ከፉና ደግ ተነጋገረ::

**አፍ አትስጠው** አትመልስለት፥ አታናግረው::

**አፍ አወጣ** ተናጋሪ፥ ለፍላፊ ሆነ::

**አፍ ያለው** አስመስሎ መናገር የሚችል፥ ነገር አሳማሪ::

**የአፍሽ የቂጥሽ ወሬ** (ተራ.አነ.) ዝሙት ነክ ወሬ::

**የአፍ አመል አለበት** 1.ይዋሻል:: 2.ወሬ ያሳብቃል ወይም ያመላልሳል::

**አፈ ልስልስ** መጥፎ ወይም ክፉ ነገር የማይናገር::

**አፈ ምላጭ** "ላጨ" ስር "ምላጭ አፍ"ን ተመ.

**አፈ ሾሌ** ቅ ከንፈሩ የበሰለ ሾላ የሚመስል (ፈረስ)::

**አፈ ቀላጤ** ስ 1.አንድን ሰው ወይም ቡድን ወይም ድርጅት ወክሎ መግለጫ የሚሰጥ ሰው:: 2.ለአንድ ሰው ወይም ቡድን ወይም ድርጅት ወግኖ የሚከራከር::

**አፈ ቅቤ /ጮማ** ነገር አሳማሪ፤ አለስልሶና አሳምሮ የመናገር ችሎታ ያለው::

**አፈ ቅይድ /እስር** ኮልታፋ፥ ተብታባ፥ ለፍዳዳ::

**አፈ ብልጥ** 1.ጮሌ፥ ንግግር አሳማሪ:: 2.በአነጋገሩ ጮሌ ወይም ብልጥ የሚመስልና በተግባር ሲታይ ግን ያልሆነ::

**አፈ ታሪክ** ስ በፅሁፍ ሳይሆን በቃል ብቻ ሲወርድ ሲዋረድ፥ ሲነገር የቆየ ታሪክ::

**አፈ ንጉስ** ስ 1.በንጉስ ቦታ ሆኖ ማንኛውንም ነገር የሚፈፅም የንጉስ ባለሟል:: 2.የዳኞች የበላይ ሹም፤ አለቃ::

**አፈ ለቃቃ** ቅ ሰፊ አፍ ያለው (እቃ)::

**አፈ ወሪሳ** ቅ አፉ እንዳመጣለት የሚቀባጥር፥ የሚያወራ::

**አፈ ዋሾ** ውሸታም፥ ሃሰተኛ::

**አፈ ዘርጣ /ግም** አፉ እንዳመጣለት የሚቀባጥር፥ አስተውሎ የማይናገር::

**አፈ ዝናም** ንግግር ከጀመረ የማያቋርጥ ወይም ብዙ የሚናገር::

**አፈ ድስት** ስ ከሆዱ ዘርጠጥ፥ ከአፉ ጠበብ ብሎ ከንፈሩ እንደ ድስት ወደውጪ ቀልበስ ያለ ብርሌ(ስእሉን ብርሌ ስር ተመ.)::

**አፈ ጉባኤ** ስ ጉባኤውን ወክሎ የሚናገር የጉባኤ አለቃ፥ ተጠሪ፥ መሪ::

**አፈ ጨዋ** 1.እውነትነት የሌለው፥ ያለአዋቂ ሰው የሚናገረው ወግ፥ ታሪክ:: 2.መጥፎ ነገር የማይናገር::

**አፈ ጭቃ** አነጋገረ ጅል::

**አፈ ፀያፍ** መጥፎ፥ ነውር፥ ባለጌ ነገር የሚናገር::

**አፈ ፃድቅ** እውነተኛ ወይም ጥሩ ሰው በመምሰል በአፉ ጥሩ ነገር እየተናገረ መጥፎ ነገር የሚፈፅም::

**አፍ ሳቻ** ሳይታሰብ የተነገረ የአፍ ስህተት::

**አፍ ተጅ** ቅርብ፥ አጠገብ::

**አፍ እላፊ** ሊያስቀይም ወይም ሊያስቆጣ የሚችልና ተገቢ ያልሆነ ንግግር።

**የአፍ ወለምታ** ሌላውን የሚያስቀይም ወይም የሚያስከፋ ፀያፍ ንግግር።

**አፈኛ** ቅ ነገረኛ፥ ምላሰኛ፥ ለፍላፊ።

**አፉዊ** ቅ 1.በቃል ብቻ የሚነገርና በፅሁፍ የሌለ። 2.ከልብ+ ከአንጀት ያልሆነ፤ ከአንገት በላይ የሆነ። 3.ውጫዊ፤ የላይን ቅርፅ ብቻ የሚያመለክት።

**አፍለኛ "አፈለ"** ስር ተመ.

**አፍለኝ** ዝ.ከ.

**አፍላ** ዝ.ከ.

**አፍላል** ስ ከማሰሮ የሚበልጥና ከእንስራ የሚያንስ ትልቅ ድስት።

**አፍርንጅ** ስ ለጥሬ ስጋ መብያ የሚያገለግል የተደቆሰና የተቀመመ የበርበሬ ፍሬ።

**አፍሮ አይገባ** ስ እንደ ጥንብ አንሳ ያለ ሆኖ ግን መጠኑ ከጥንብ አንሳ አነስ የሚል የአሞራ አይነት (ካልቀረቡት የማይሸሽ)።

**አፍታ** ተው.ግ. አጭር ጊዜ።

**አፍን** ስ ነብርማ መልክ ያለውና እንደ በግ፥ ፍየል፥... ያሉትን የሚበላ የዱር አውሬ።

**አፍንጫ** ስ ከአፍ በላይ ከግንባር በታች የሚገኝ፥ ለማሽተቻና ለመተንፈሻ የሚያገለግሉ ሁለት ቀዳዳዎች ያሉት የሰውነት ክፍል(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

**አፍንጮ** አፍንጫው ትልቅ ወይም ትንሽ ወይም ጎራዳ ወይም ደፍጣጣ የሆነ ሰው (በቀልድ የሚነገር)።

**አፍንጫውን ነፋ** ተቆጣ፥ አኩረፈ።

**አፍንጫውን ይዞ ተቀበለው** አስገድዶ፥ አስጨንቆ ተቀበለው።

**አፍንጫ ጎራዳ** ቅ አፍንጫው ትንሽና አጭር የሆነ፤ ቶንጋ።

**አፎቄ** ስ ትልቅ ስለታም ጦር።

**አፎት** ስ የሰይፍ ወይም የጎራዴ ቤት፤ ሰገባ።

**ኤ** የ "አ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ኤሊ** ስ ገላዋ በጣም ጠንካራ በሆነ ቅርፊት መሰል አካል (ዛጎል) የተሸፈነና አረማመዷ በጣም ዝግ ያለ+ አስፈሪ ነገር ስታይ ጭንቅላቷንና እግሮቿን ከጠንካራው ሽፋኗ ውስጥ የምትደብቅ እንስሳ።



ኤሊ

**ኤሌክትሪክ** ስ ሙቀትን፥ ብርሃንን የሚሰጥ እንዲሁም ማሽኖችን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ኤሌክትሮንና ፕሮቶን ከተባሉ ነገሮች በተለያየ መንገድ የሚገኝ ሃይል።

**ኤሌክትሪክ ማሞቂያ** ስ በቅዝቃዜ ጊዜ አንድን ክፍል በኤሌክትሪክ ሃይል ለማሞቅ የሚያገለግል መሳሪያ።

**ኤሌክትሪክ ሽቦ** ስ ለኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ተብሎ የተሰራ የመዳብ ሽቦ።

**ኤሌክትሪክ ገመድ** ስ የኤሌክትሪክ ሃይል በውስጡ ለማስተላለፍ የሚችል የፕላስቲክ ሽፋን ያለው ሽቦ።

**ኤሌክትሪክ ጋን** ስ የኤሌክትሪክ ሃይልን ከጣቢያው ተቀብሎ በተፈለገው መጠን (ጉልበት በመጨመር ወይም በመቀነስ) ለተጠቃሚው አካባቢ የሚያሰራጭ ትልቅ የኤሌክትሪክ እቃ፤ ትራንስፎርመር።

**የኤሌክትሪክ ሃይል** ስ የኤሌክትሪክ ጉልበት፤ የመብራት ሃይል።

**የኤሌክትሪክ መስመር** ስ የኤሌክትሪክ ሃይል የሚተላለፍበት ሽቦ።

**የኤሌክትሪክ ምድጃ** ስ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምድጃ።

**የኤሌክትሪክ ጉልበት** ስ የኤሌክትሪክ ሃይል።

**ኤምባሲ** ስ የአንድ አገር አምባሳደር ተልእኮና ተግባር የሚከናወንበት መስሪያ ቤት።

**ኤሮግራም** ስ ተጣጥፎ እንደ ፖስታ ሊታሸግ የሚችልና ሌላ ፖስታ እንዲሁም ቴምብር የማያስፈልገው በአየር የሚላክ የደብዳቤ መፃፊያ ወረቀት።

**ኤንቬሎፕ** ስ ደብዳቤ አሽጎ ለመላክ የሚያገለግል የወረቀት ከረጢት፤ ፖስታ። አልፎ አልፎ አምቦልክም ይባላል።

**ኤክስሬይ** ስ በአጭር ርቀት ወደ አንድ አካል ውስጥ ዘልቆ በመግባት ተፈላጊውን የሰውነት ወይም የአካል ክፍል ለማሳየትና በፊልም ለመቅረፅ የሚያስችል ሃይለኛ የብርሃን ጨረር። አልፎ አልፎ ፊልሙም ሆነ መሳሪያው ኤክስሬይ ይባላል።

**ኤክስሬይ አነበበ** ኤክስሬዩ (ፊልሙ) ላይ የተነሳውን ወይም የተቀረፀውን ምስል በማየት ምን እንደሆነ ተናገረ፥ ተረጎመ።

**ኤክስፐርት** ስ በአንድ የሙያ መስክ የተለየና ጠለቅ ያለ እውቀት ያለው ባለሙያ።

**ኤዲተር** ስ አርታኢ።

**ኤዲያ** ቃ.አ. 1.ወዲያ! እጭ! ለማለትና ጥላቻን፥ ንቀትን፥... ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ኤዲያ! አትጨቅጭቂኝ*። 2.አንድን ነገር

በማጋነን ለማድነቅ የሚነገር ቃል:: *ኤዲያ/እንዲህ ነው እንጂ ስራ::*

**ኤድስ** ስ በሽታን የመቋቋም ተፈጥሮአዊ ሃይልን በማዳከም ሰውነት በቀላሉ በበሽታ እንዲጠቃና ለሞት እንዲበቃ የሚያደርግ፥ ብዙውን ጊዜ በግብረ ስጋ ግንኙነት አማካኝነት በሚተላለፍ ቫይረስ የሚመጣ በሽታ::

**ኤግዚቢሽን** ስ 1. የስእል፥ የምርት ውጤቶች፥...ትርኢት:: 2. ህዝብ እንዲያያቸው የተፈለጉ ነገሮች ተሰባስበው የሚታዩበት ቦታ ወይም አዳራሽ፤ መካነ ትርኢት::

**ኤጲስ ቆጶስ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ማእረጉ ከቆሞስ በላይ፥ ከጳጳስ በታች የሆነ መንፈሳዊ አባት::

**እ** የ "አ" ፊደል ሳድስ ዘር::

**እ—** ሃሳቤ ካልሆነ ግስ ጋር እየተጣመረ የሚገባ የአንደኛ መደብ አመልካች ምእላድ:: *እመጣለሁ::*

**እሁድ** ስ በቅዳሜና በሰኞ መካከል ያለው ቀን ስም፤ የሳምንቱ መጀመሪያ ቀን::

**እህ**

**እህ አለ** ግ ወሬ ጠየቀ፥ ሰበሰበ፥ አዳመጠ::

**እህህ** የሃዘን፥ የህመም ስሜት የሚገለፅበት ድምፅ::

**እህል** ስ 1.ለምግብ የሚያገለግል የአዝርእት ውጤት:: 2.ምግብ::

**እህል ቀመሰ** ተመገበ፤ በጥቂቱ በላ::

**እህል በእህል** ማባያው ስጋ የሌለበት ምግብ::

**እህል ውሃ** 1.አንዱ ከሌላው ጋር በመኖር የሚያሳልፈው ጊዜ:: 2. እድል ወይም እጣ ፈንታ:: *እህል ውሃዬ ሆኖ እዚሁ ቤት ኣረጀሁ::* 3.ኑሮ፥ ህይወት:: 4.ምግብና መጠጥ::

**እህል ውሃ አያሰኝም** ትልቅ ወይም ከባድ ነው፤ ቢመታ ሊገድል ይችላል:: *ዱላው እህል ውሃ ኣያሰኝም::*

**እህል ውሃው አለቀ** ካለበት ቦታ ለቀቀ፤ ሞተ፤ ተለያየ (አብሮት ከነበረው ሰው ጋር)::

**እህት** ስ 1.ከአንድ እናትና አባት ወይም ከሁለቱ በአንደኛው ከተወለዱት ልጆች መካከል ሴቷ ልጅ ለወንዱ ልጅ ወይም ለሌላይቱ ሴት ልጅ ያላት የስጋ ዝምድና መጠሪያ:: 2.ባላት ቀረቤታ (በዝምድና፥ በቤተሰብነት) እንደ እህት የምትቆጠር የሴት ዘመድ:: 3. የማያውቋትን ሴት በትህትና ለመጥራትና ለማናገር የሚያገለግል ቃል::

**እህትማማች (እትማማች)** ስ ከአንድ እናትና አባት ወይም ከሁለቱ በአንዱ የተወለዱ ሴት ልጆች::

**እለት** ስ ቀንና ሌሊትን ጨምሮ ያለው ሃያ አራት ሰአት፤ ቀን::

**የእለቱ እለት (የለቱለት)** በዚያኑ ቀን፥በዚያው እለት::

**የእለት እራት/እንጀራ** ስ የእለት ምግብ::

**እላቂ "አለቀ"** ስር ተመ.

**እላፊ "አለፈ"** ስር ተመ.

**እሌት** ስ ዱቄት ከተነፋ በሗላ በወንፊት ላይ የሚቀረው ቅጥቃጭ፥ ንፋሽ፥ ጥራጊ ዱቄት::

**እልህ (እልክ)** ስ እንዴት ተደፈርኩ፥.ተነካሁ የሚያሰኝ የእምቢታ፥ የሞገደኛነት ስሜት::

**እልህ አስጨራሽ** እጅግ በጣም አድካሚ፥ አስቸጋሪ፥ አሰልቺ::

**እልህ ያዘው** የእልህ ስሜት አደረበት::

**እልሀኛ (እልከኛ)** ቅ የእልህ ስሜት ያለበት፤ ሞገደኛ::

**እልል**

**እልል (እልልታ)** ስ እልል እልል በማለት የሚገለፅ የደስታ ጩሀት::

**እልል አለ** ግ 1.እልልታ አሰማ:: 2.ተደሰተ::

**እልም**[1]

**እልም እልም አለ** ግ በጣም በጥቂቱ፥ በትንሹ ተሰማ (ለማጣፈጫ የሚጨመር ጨው፥ ስኳር፥...):: *ጨው ሊታብዛ እልም እልም ካለ ይበቃል::*

**እልም**[2] "ህልም"ን ተመ.

**እልም**

**እልም አለ** ግ 1.ጠፋ፥ ጨለመ (መብራት):: 2.ጠፋ፥ አልገኝ አለ፥ ትዝ አልል አለ። 3.ጠፋ፥ ተሰወረ:: 4.ተደመሰሰ (ፅሁፍ):: 5.ሄደ፥ ነጎደ::

**እልም ድርግም አለ** ግ ፈፅሞ ጠፋ::

**እልምልም አለ** ግ 1.ጠፋ፥ ጭልምልም አለ (መብራት):: 2.ተበላሸ፥ ተደመሰሰ፥ ወደመ::

**እልምልም አደረገ** ግ 1.አጠፋ፥ አጨለመ (መብራትን):: 2.አበላሸ፥ አወደመ፥ ደመሰሰ:: 3.አባከነ፥ አጠፋ (ገንዘብን፥...)::

**እልቀት "አለቀ"** ስር **"እልቂት"**ን ተመ.

**እልቂት "አለቀ"** ስር ተመ.

**እልቅት** ስ በአንገትና በደረት መጋጠሚያ ላይ ጎድጎድ ብላ የምትገኝ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::

**እልቅና "አለቃ"** ስር ተመ.

**እልቆ መሳፍርት "ሁልቆ መሳፍርት"ን** ተመ.

**እልበት (ህልበት)** ስ ጎንቆሉ የደረቀ ኣብሽ ከተከካ ባቄላ ጋር በማስፈጨት እንደ ገንፎ

ተዘጋጅቶ በደንብ ከቀዘቀዘ በኋላ በማንኪያ ወይም በእጅ እስኪቀጥን ድረስ ተመትቶ ብዙውን ጊዜ ከስጎ ጋር እየተቀላቀለ በእንጀራ የሚበላ የምግብ አይነት።

**እልባት** "አለበ[2]" ስር ተመ.

**እልከኛ** "እልህ" ስር "እልሀኛ"ን ተመ.

**እልክ** "እልህ"ን ተመ.

**እልፈት** "አለፈ" ስር ተመ.

**እልፌት** ዝ.ከ.

**እልፍ[1]** ስ 1.አስር ሺህ። 2.(ዘይ.) ብዙ፥ አያሌ።

**አእላፍ** ስ መቶ ሺህ።

**እልፍ አእላፍ/አእላፋት** ቅ እጅግ ብዙ፥ አያሌ።

**እልፍ[2]** ስ የሰንሰለ ወይም የገብስ እሸት ዛላ፤ አንድ ራስ እህል።

**እልፍኝ** ስ ቀደም ባለው ጊዜ ነገስታቱና መኳንንቱ ታላላቅ እንግዶችን ለመቀበያና ለማስተናገጃ ይገለገሉበት የነበረና ከዋናው ቤት በስተሂላ በኩል የሚገኝ ትንሽ ቤት።

**እልፍኝ አስከልካይ** ስ የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ።

**[የ]እልፍኝ አሽከር** ስ 1.በቤተ መንግስት ውስጥ ያልተፈቀደለት ሰው ወደ ቤተ መንግስት እንዳይገባ የሚጠብቅ በእልፍኝ አስከልካይ የሚታዘዝ አሽከር። 2. ቀደም ባለው ስርአት የቤተ መንግስት አንጣፊ፥ ጋራጅ፥ አስታጣቢ፥ አልባሽ የነበረ ሰራተኛ ይጠራበት የነበረ ስም።

**እልፍ አእላፍ** "እልፍ[1]" ስር ተመ.

**እመም[1]** "ህመም"ን ተመ.

**እመም[2]** "አመመ[2]" ስር ተመ.

**እመምኔት** "ምኔት" ስር ተመ.

**እምር**

**እምርታ** ስ 1.ዝላይ። 2.እድገት፥ እርምጃ።

**እምር አለ (መር አለ)** ግ እንጣጥ ብሎ ተራመደ።

**እምር እምር አለ** ግ ፈጠን ፈጠን እያለ በረጅሙ ተራመደ።

**እመበለት (መበለት)** ስ 1.መነኩሲት። 2.ባሏ የሞተባት ወይም በብቸኝነት የምትኖር ጠና ያለች ሴት።

**እመቤት** ስ 1.ባለፀጋ ወይም ሃብታም ሴት። 2.ቆንጆ፥ ውብ፥ ደርባባ ሴት።3. ሃላፊ፥አዛዥ፥ አስተዳዳሪ ሴት(በመኖሪያ ቤት)።

**እመብርሃን** ስ የቅድስት ድንግል ማርያም ሌላ መጠሪያ።

**እመት[1] (እምነት)** ስ በውሃ በጥብጦ ቢጠጡት ወይም ሰውነትን ቢቀቡት ከህመም ይፈውሳል ተብሎ የሚታመንበት በቤተ ክርስቲያን የሚጨስ እጣን አመድ።

**እመት[2]** ስ 1. ሴት ስትጣራ "አለሁ፥ ምን ልታዘዝ፥..." ለማለት በስም የተጠራው ሰው ለጠሪዋ የሚያሰማው የትህትና መልስ ። 2.ትልልቅ ሴቶችን እመቤቴ ወይም እሜቴ ለማለትና አክብሮትን ለመግለፅ ስምን ቀድሞ የሚገባ ቃል። *እመት አገሊት*።

**እመጫት** ስ 1.ከወለደች ብዙ ያልቆየች ወይም አራስ ሴት። 2.ከዛፍ ላይ የሚበቅል የሌላ እፅዋት ችግኝ። 3.በፅሀፊት ወቅት ተዘልሎ የነበረና መፃፍ በነበረበት ቦታ ትክክል ወደላይ ከፍ ብሎ የሚፃፍ ወይም የሚገባ ቃል፤ ስርዋፅ።

**እሙን** "አመነ" ስር ተመ.

**እማ** "እማ ሃ"ን ተመ.

**እሚታ** ስ ሴት አያት።

**እማሆይ** ስ የመነኩሲት መጠሪያ።

**እማማ (እማ፥ እማዬ)** ስ 1.ልጆች እናታቸውን የሚጠሩበት ቃል ወይም የተዘምዶ ስም። 2.በእድሜ የገፉች ታላቅ ሴትን በአክብሮት ለመጥራት ስምን ቀድሞ ወይም ብቻውን የሚነገር ቃል።

**እማኝ** ስ ምስክር።

**እማኝ አነሳ** ምስክር ቆጠረ ወይም ጠራ።

**እማዬ** "እማማ"ን ተመ.

**እሜቴ** ስ በእድሜም ሆነ በደረጃ ከፍ ብላ የምትገኝን ሴት በክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል።

**እምር**

**እምር ታህል** በጣም ትንሽ።

**እምስ** ስ (ነውር) የሴት ብልት ወይም ሃፍረተ ስጋ(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**እምስ አንቀጥቅጥ/ፊሪ** ስ በአብዛኛው በገደል አካባቢ የሚበቅል አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

**እምስ** "አመሰ" ስር ተመ.

**እምቅ** "አመቀ" ስ . ተመ.

**እምቡር** "እንቡር"ን ተመ.

**እምቡስ (እንቡስ)** ስ አብዛኛውን ጊዜ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**እምቡሽቡሽ** ስ ጉሽ ጠላ።

**እምቡጣ** "እንቡጣ"ን ተመ.

**እምቡጣጢያ** "እንቡጣጥያ"ን ተመ.

**እምቡጥ** "እንቡጥ"ን ተመ

**እምቡፍና** "እንቡፍና"ን ተመ.

**እምቢ** "እንቢ"ን ተመ.

እምቢልታ "እንቢልታ"ን ተመ.
እምባ "አነባ" ስር "እንባ"ን ተመ.
እምብርት "እንብርት"ን ተመ.
እምብርክክ "*በረከከ" ስር "እንብርክክ"ን ተመ.
እምብዛም (እምብዛ) አፍራሽ አንቀፆችን እያስከተለ ብዙም፥እስከዚህም፥... የሚለውን አሉታዊ ስሜት ለመግለፅ የሚነገር ተውሳከ ግሳዊ ቃል ። *ወረቀቱ እምብዛም አይፈለግም/ እዚህ ሰፈር እምብዛም አይመጣም*።
እምቦሳ "እንቦሳ"ን ተመ.
እምቦጭ አለ "ነቦጨ" ስር ተመ.
እምቦፍ አለ "ቦፍ" ስር ተመ.
እምቧይ "እንቧይ"ን ተመ.
እምቧ "እንቧ"ን ተመ.
እምቧጮ "እንቧጮ"ን ተመ.
እምነት[1] "አመነ" ስር ተመ.
እምነት[2] "እመት[1]"ን ተመ.
እረብ አለ "ረብ[1]" ስር ተመ.
እረኛ ስ 1.ጠባቂ፥ አጋጅ (ከብትን)። 2.(ስድብ፥ ዘይ.) ባለጌ፥ ስድ።
እረፍት "አረፈ" ስር ተመ.
እሩምታ ስ ለተወሰነ ጊዜ ያለማቋረጥ የሚሰማና ተከታታይነት ያለው የጥይት ተኩስ።
እሩር "ሩር"ን ተመ.
እሪ
እሪታ ስ አደጋ በደረሰ ጊዜ እርዳታ ለመጠየቅ የሚደረግ የጩሀት ማስሚያ ቃል፤ ኡኡታ።
እሪ አለ ግ ለደረሰበት አደጋ እርዳታ ለማግኘት ጮሀ፤ ኡኡ አለ።
እራሽ "አረሰ[1]" ስር ተመ.
እራት "ራት"ን ተመ.
እራቻ "ራቻ"ን ተመ.
እራፊ ፣ የጨርቅ ቁራጭ።
እሬት "ሬት"ን ተመ.
እሬንሳ "ሬንሳ"ን ተመ.
እርማት "አረመ" ስር ተመ.
እርም ስ ክልክል፥ ውጉዝ፥ ሃራም። *የሰው ስጋ መብላት እርም ነው*።
እርሙን በላ ከነእርሙ በላ።
ከነእርሙ በላ የዘመዱን ሞት ሳይሰማ ቀረ ወይም አልቅሶ እርሙን ሳያወጣ ቀረ።
እርመ በላ ዘመዱ መሞቱን ሰምቶ ያላለቀሰ ወይም ለቅሶ ያልደረሰ።
እርሙን አወጣ 1.የዘመዱን ሞት ሰምቶ አለቀሰ። 2.አንድ ነገር ተመልሶ እንደማይመጣ፥ እንደማይደረግ፥... ወይም ይሆናል ብሎ ያሰበው ወይም የተመኘው ነገር እንደማይሆን በመረዳት ተስፋ ቆረጠ።
እርም ታህል በጣም ትንሽ።
እርም አለ ፊፅሞ ተወ፥ አቋረጠ፥ አቆመ።
እርም ይሁንብኝ ድጋሚ አላደርገውም። *እርም ይሁንብኝ ሁለተኛ መጠጥ አልጠጣም*።
እርምት "አረመ" ስር "እርማት"ን ተመ.
እርምጃ "*ረመደ" ስር ተመ.
እርምጥምጥ "ረመጠ" ስር ተመ.
እርርት ስ 1.በሰውና በከብት አይን ላይ የሚወጣ ጭራ መሳይ ነገር። 2.በከብት ጭራ ላይ የሚወጣ ቁስል።
እርስዎ ተው.ስ. በሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የ ፒነገር ተባእታይም ሆነ አንስታይ ፆታን በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ተውላጠ ስም።
እርሱ "እሱ"ን ተመ.
እርሳስ "ረሰሰ" ስር ተመ.
እርሳቸው "እሳቸው"ን ተመ.
እርሷ "እሷ"ን ተመ.
እርሻ "አረሰ[1]" ስር ተመ.
እርሾ ስ 1.ያልቦካን ሊጥ እንዲቦካ የሚያደርግ ቀደም ብሎ የቦካ ሊጥ፤ የሰነበተ የሊጥ ቅሪት። 2.ባይካርቦኔት ሶዳ የሚባልና ሊጥ እንዲቦካ የሚያደርግ፥ በዱቄት መልክ የተዘጋጀ ኬሚካል። 3.አንድን ተግባር ለማከናወን እንደመነሻ ሆኖ የሚያገለግል መጠነኛ ገንዘብ ወይም ጥሪት።
እርቃን ስ ራቁት፥ መለመላ።
እርቃኑን ቀረ 1.ራቁቱን ሆነ። 2.አጣ፥ ደሀየ። 3.ተጋለጠ፥ መጥፎ ስራው ታወቀ።
እርቃኑን አስቀረው 1.ያለውን ሁሉ ወሰደበት፥ ሰረቀው። 2.ራቁቱን አስቀረው። 3.አጋለጠው።
እርቃነ ስጋ ስ ያልለበሰ ወይም ራቁቱን የሆነ አካል፥ ሰውነት።
እርቅ "*አረቀ" ስር ተመ.
እርባታ "ረባ" ስር ተመ.
እርባና ቢስ ዝ.ክ.
እርባን[1] ስ የተለያየ ጥቃቅን ቅርፃ ቅርፅ ያለበትና በረቀቀ ዘዴ በጥበብ የተሰራ የቀለበት፥ የኮርቻ፥ የመስቀል፥ ... ንቅስ ወይም ንድፍ።

**እርባን ስራ** ስ በላዩ ቀጭን ሽቦ የተጠመጠመበትና ረቂቅ ንቅስ ያለበት፥ የረቀቀ አሰራርን የተከተለና ውበት ያለው የወርቅ ወይም የብር ጌጥ ስራ።

**እርባን**[2] "ረባ" ስር "እርባና"ን ተመ.

**እርብትብት** "*ረበተበተ" ስር ተመ.

**እርብድብድ** "*ረበደበደ" ስር ተመ.

**እርቦ** ስ 1.የቁና አንድ አራተኛ የሆነ የእህል መስፈሪያ። 2.ከስፌት የተሰራ የቁርስ ወይም የቆሎ ማቅረቢያ። 3.ጢሰኛ ለባለርስት ይሰጠው የነበረ አንድ አራተኛ የምርት ውጤት።

**እርቦ አራሽ** ስ የባለርስትን መሬት እያረሰ ከሚያገኘው ምርት አንድ አራተኛውን ለባለርስቱ የሚሰጥ ገበሬ።

**እርቦ አፍሳሽ** ዝ.ከ.

**እርከን** ስ 1.ደረጃ፥ መውጫ መውረጃ። 2.መሬት እንዳይሸረሸርና በጎርፍ እየተጠረገ እንዳይወሰድ ደግፎ የሚይዝ የድንጋይ ካብ። 3.ለመንግስት ሰራተኛ በየተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ የደመወዝ ጭማሪ።

**እርኩም** ስ ሙሉ በሙሉ ጥቁር ሆኖ ከፊቱ በኩል አንገቱ አካባቢ ቀይ ያለበትና መንቁረ ረዥም የሆነ ከጥንብ አንሳ ከፍ የሚል ትልቅ የአሞራ አይነት።

**እርኩም አፍ** (ስድብ) ያሞጠሞጠ ወይም የሾለ አፍ ያለው።

**እርኩስ** "ረከሰ" ስር ተመ.

**እርካብ** "ርካብ"ን ተመ.

**እርካታ** "ረካ" ስር ተመ.

**እርክፍካፎ** "*ረከፈከፈ" ስር ተመ.

**እርኮት** ስ ከበሬ ወይም ከጎማሬ፥... ቆዳ የሚሰራ የውሃ መያዣ።

**እርዛት** "*አረዘ" ስር ተመ.

**እርዳታ** "ረዳ" ስር ተመ.

**እርድ**[1] ስ ቢጫ ቀለም ያለው የቅመም አይነት።

**እርድ**[2] "አረደ" ስር ተመ.

**እርጅና** "አረጀ" ስር ተመ.

**እርገት** "አረገ" ስር ተመ.

**እርጉም** "ረገመ" ስር ተመ.

**እርጉዝ** "*ረገዘ" ስር ተመ.

**እርጋታ** "ረጋ" ስር ተመ.

**እርጋጭ** "ረገጠ" ስር ተመ.

**እርግማን** "ረገመ" ስር ተመ.

**እርግብ** "ርግብ"ን ተመ.

**እርግብግቢት** "*ረገበ" ስር ተመ.

**እርግብግብ** ዝ.ከ.

**እርግዝና** "*ረገዘ" ስር ተመ.

**እርግጠኛ** "*ረገጠ" ስር ተመ.

**እርግጥ** ዝ.ከ.

**እርግጫ** "ረገጠ" ስር ተመ.

**እርግፍግፍ አለ** "*ረገፈገፈ" ስር ተመ.

**እርጎ** "ረጋ" ስር ተመ.

**እርጓ** ስ መወርወሪያ ውስጥ በሚጋደም ቀሰም ውስጥ ተሰክታ፥ ቀሰሙ (ድውሩ) እንዲሽከረከርና ማጉ በድሩ መካከል እንዲዘረጋ የምትረዳ እንደሰንበሌጥ አገዳ ያለች ቀጭን ሽመል።

**እርጥባን** "ረጠበ[2]" ስር ተመ.

**እርጥብ** "ረጠበ[1]" ስር ተመ.

**እርጥጥ** "ረጠጠ" ስር ተመ.

**እርጭ**

**እርጭ (ረጭ) አለ** ግ ፀጥ፥ ዝም አለ።

**እርፌት** "አረፈ" ስር "እረፍት"ን ተመ.

**እርፍ** ስ በአንድ በኩል ከማረሻና ከሞፈር ጋር የሚዋደድ፥ በሌላ በኩል ገበሬ ሲያርስ የሚጨብጠውና የማረሻውን ጥልቀትና ሂደት የሚቆጣጠርበት የበሬ እቃ(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)።

**እርፈ መስቀል** ስ ከመያዣው በኩል የመስቀል ቅርፅ ያለበት የስጋ ወደሙ ማቀበያ ወይም መስጫ ማንኪያ።

**እርፍ መጣያ** ስ ገበሬ የእርሻ ስራውን በነሃሴ ወር ከጨረሰ በሂላ የግብርና እቃውን የሚያስቀምጥበት ወቅት።

**እሮሮ** "ሮሮ"ን ተመ.

**እሰይ** ደግ፥ ማለፊያ ለማለት የሚነገር የደስታ መግለጫ ቃል።

**እሱ (እርሱ)** ሶስተኛ መደብ ተባእታይ ፆታ፥ ነጠላ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

**እሳቤ** "አሰበ" ስር ተመ.

**እሳት** ስ 1.ብርሃንና ሙቀት የሚሰጥና የማቃጠል፥የማፍላት፥የማብሰል፥ የማንደድ፥... ሃይል ያለው ነዲድ ወይም ፍም። 2.(ዘይ.) ጎበዝ፥ ቀልጣፋ፥ ንቁ፥ ሎሌ። *በትምህርቱ እሳት ነው።*

**እሳት ሆነ** 1.በጣም ተናደደ፥ በሸቀ። 2.እጅግ ተወደደ፥ ውድ ሆነ። *ቡና ባሁኑ ጊዜ እሳት ሆኗል።*

**እሳት መታው** በእሳት በጣም በሰለ።

**እሳት ሰደደበት** ቃጠሎ አስነሳ፥ በእሳት አያያዘ፥ ለኮሰ።

**እሳት በላው** እሳት ፈጀው፥ አቃጠለው።

**እሳት ተነሳ** የእሳት ቃጠሎ ወይም አደጋ ተፈጠረ።
**እሳት አፍ** (ስድብ) ለፍላፊ፣ ነገረኛ፣ ምላሰኛ።
**እሳት ገባው** ከሚያስፈልገው በላይ በሰለ።
**እሳትና ጭድ** የማይስማሙ፣ አጥፊና ጠፊ።
**እሳተ ገሞራ** ስ ከመሬት ከርስ ውስጥ የቀለጠ ድንጋይና ሌሎች ነገሮችን በመያዝ ፈንድቶ የሚወጣ እሳት።
**እሳት አደጋ** ስ 1.በእሳት ምክንያት በቤት ወይም በንብረት ላይ የሚደርስ አደጋ፣ ቃጠሎ። 2.በእሳት ምክንያት በቤት ወይም በንብረት ላይ ቃጠሎ ሲነሳ ጥሪ እየተደረገለት አደጋውን የሚከላከል ድርጅት(ሙሉ መጠሪያው የእሳት አደጋ መከላከያ ነው መኪናውም እሳት አደጋ ይባላል) ።
**የእሳት ላንቃ** ስ የእሳት ነበልባል።
**የእሳት ራት** ስ ማታ ማታ በእሳት ወይም በመብራት ዙሪያ የምትበር ቢራቢሮ።



የእሳት ራት

**የእሳት ክፋይ** ላ ጫፉ በእሳት የፋመ የእንጨት ጉማጅ።
**እሳቸው (እርሳቸው)** እሱ ወይም እሷ በሚባሉት ተውላጠ ስሞች ፈንታ የሚገባ የአክብሮት ተውላጠ ስም።
**እስላም** "ሰለመ" ስር ተመ.
**እስልምና** ዝ.ከ.
**እስረኛ** "አሰረ" ስር ተመ.
**እስራት** ዝ.ከ.
**እስር** ዝ.ከ.
**እስስት**[1] ስ 1.የመልኳን ቀለም ከአካባቢዋ ቀለም ጋር የምታመሳስል፣ዝርያዋ ከገበሎ ወገን የሆነ፣ረዥም ምላስ ያላት አነስተኛ ፍጡር። 2.(ዘይ.) ባህሪው የሚለዋወጥ፣ ጠባዩ የማይታወቅ ሰው።



እስስት 1ኛ ፍቺ

**እስስት**[2] ስ ማንቁርት። *እስስቱን አንቆ ገንዘቡን ተቀበለው።*
**እስቱኮ** "ስቱኮ"ን ተመ.
**እስቲ** "እስኪ" ን ተመ.
**እስታዲየም** "ስታድየም"ን ተመ.
**እስቴንስል** "ስቴንስል"ን ተመ.
**እስቴፕለር** "ስቴፕለር"ን ተመ.
**እስትንፋስ** ስ ትንፋሽ።
**እስትንፋስ ዘራበት** ህይወት ሰጠው።
**እስከ** መዋ. መድረሻን አመልካች ቃል። *እስከ ድሬዳዋ እሄዳለሁ/ እስከ ነገ እቆያለሁ።*
**እስኩታ** ስ በጠላ ላይ የሚንሳፈፍ የጊሾ፣ የብቅልና የአሻሮ አሰር፤ ገፈት።
**እስኪ(እስቲ)** (አንድን ድርጊት)ፈልም/አትፈልም፣ አድርግ/አታድርግ ለማለት ከግስ ቀድሞ የሚነገር ቃል። *እስኪ ሂደው/ እስኪ ስጠኝ/ እስኪ ንካኝ።*
**እስክሪቢቶ** "ስክሪቢቶ"ን ተመ.
**እስክስታ (እስክስ)** ስ በዘፈን ጊዜ ምትን ጠብቆ የሚደረግ የትከሻና የአንገት እንቅስቃሴ።
**እስክስታ ወረደ (እስክስ አለ)** በዘፈን ጊዜ ምትን ጠብቆ በትከሻና በአንገቱ እንቅስቃሴ አደረገ።
**እስኮላርሽፕ** "ስኮላርሽፕ"ን ተመ.
**እስኮችቴፕ** "ስኮችቴፕ"ን ተመ.
**እስኳድራ**"ብረት" ስር "ብረት ማእዘን"ን ተመ.
**እስፒል** "ስፒል"ን ተመ.
**እሷ (እርሷ)** በሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር፣ አንስታይ ፆታን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።
**እሸት** "ሸተ" ስር ተመ.
**እሺ** 1. ለአንድ ድርጊት፣ ስራ፣... መስማማትን፣ ፈቃደኛነትን ለመግለፅ የሚባል ቃል።2. በጋራ ወዋታ ወይም ንግግር ጊዜ አድማጭ አውራውን ቀጥል፣ ከዚያስ፣... ለማለት የሚጠቀምበት የወሬ ማራዘሚያ ቃል።
**እሺታ** ስ ፈቃደኛነት፣ መስማማት፣ ይሁንታ።
**እሺ አለ** ግ ተስማማ፣ ፈቃደኛ ሆነ።
**እሺ ባይ** ቅ ታዛዥ፣ ይሁን ባይ።
**እሽ** 1.ዝንብን፣ ወፍን፣ ዶሮን ለማባረር የሚነገር ቃል። 2.ዝም በል ወይም ፀጥ በል ለማለት የሚነገር ቃል።
**እሽ አለ** ግ 1.ዝንብን፣ ወፍን፣ ዶሮን አባረረ፣ ተከላከለ። 2.ዝም በል ወይም ፀጥ በል አለ።
**እሽል** "አሸለ" ስር ተመ.

**እሽም** "አሸመ" ስር ተመ.

**እሽሩሩ** የታዘለ ወይም በእቅፍ የተያዘ ህፃን ሲያለቅስ ዝም እንዲል እየተዋዛወዙ በዜማ የሚባል የማባበያ ቃል::

**እሽሩሩ አለ** ግ 1.የሚያለቅስ ህፃን ልጅ ዝም እንዲል በዜማ እሽሩሩ እያለ አባበለ፥ ዝም እንዲል አደረገ:: 2.(ዘይ.)ተለማመጠ፥አሽበለበለ::

**እሽቅድድም (እሽቅድምድም) "ቀደመ"** ስር ተመ.

**እሽኮለሌ** ስ የስድብ ምልልስ::

**እሽኮኮ "እንኮኮ"**ን ተመ.

**እሽግ "አሸገ"** ስር ተመ.

**እሾህ (እሾክ፥ ሾክ)** ስ እንደ ኢጋም፥ግራር፥ ... ባሉ እፅዋት ላይ የሚገኝ እንደመርፌ ሹል የሆነና የሚዋጋ የእፅዋት አካል::

**እሾህ ነው** ክፉ፥ ነገረኛ ነው::

**እሾህ አፍ** ቅ (ስድብ) ተሳዳቢ፥ ነገረኛ (ሰው)::

**እቁባት "ቁባት"**ን ተመ.

**እቁብ** ስ 1.ሰዎች በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ክፍያ እየከፈሉና ገንዘቡ አንድ ላይ ተሰብስቦ ገቢ እየሆነ በየተራ ወይም በእጣ ለእያንዳንዳቸው እንዲደርስ ለማድረግ የሚያቋቁሙት ማህበር:: 2.ለዚሁ ማህበር የሚከፈል ገንዘብ:: *በየሳምንቱ እቁብ ይጥላል::*

**እቁብ ደረሰው** ተራው ደርሶ (እጣ ወጥቶለት) የተሰበሰበውን ገንዘብ ወሰደ::

**እቁብ ጠጣ** የእቁብ ማህበር አባል ሆነ::

**እቁብ ጣለ** በእቁብ ውስጥ ለሚሰበሰበው ገንዘብ የራሱን ድርሻ ከፈለ::

**እቁብተኛ** ቅ የእቁብ ማህበርተኛ ወይም አባል::

**እቃ** ስ 1.ተንቀሳቃሽ የመገልገያ መሳሪያ፥ ቁሳቁስ:: 2.ጓዝ:: 3.(ዘይ.) በራሱ አስተሳሰብ መሰረት የማይንቀሳቀስ፥ ደካማ፥ እንደፈለጉ ወዲያ ወዲህ የሚያደርጉት ሰው::4.(ዘይ.) የወንድንም ሆነ የሴትን አባለዘር በስሙ ላለመጥራት ተተክቶ የሚባል የማለዘቢያ ቃል::

**እቃ ቤት** ስ የእቃ ማስቀመጫ ወይም ማጠራቀሚያ ክፍል::

**እቃ ግምጃ ቤት** ስ 1.በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ለአገልግሎት እንዲውሉ የተገዙ እቃዎች የሚቀመጡበት ቤት ወይም ክፍል:: 2.በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በሃላፊነት የሚሰራ ሰራተኛ::

**እቅድ "አቀደ"** ስር ተመ.

**እቅጩን** እርግጡን፥ እውነቱን::

**እቅጩን ተናገረ** እውነቱን፥ ትክክለኛውን ተናገረ::

**እቅፍ "አቀፈ"** ስር ተመ.

**እቅፎሽ** ዝ.ከ.

**እበት** ስ 1.የቀንድ ከብት እዳሪ፥ ፍግ:: 2.(ስድብ፥ ዘይ.) ሰነፍ፥ ጅል፥ የማይረባ::

**እበት ጣለ** ኩሳ (የቀንድ ከብት)::

**እበጥ "አበጠ"** ስር ተመ.

**እቡይ** ቅ ክፉ፥ ትእቢተኛ::

**እባሽ "አበሰ"** ስር ተመ.

**እባብ** ስ 1.እግር የሌለው፥ በልቡ እየተሳበ ወይም እየተንሻለለ የሚሄድ መርዘኛ አውሬ፥ ከይሲ:: 2.(ዘይ.) ክፉ፥ ምቀኛ፥ ተንኮለኛ::

**እባብ ዋጭ [አሞራ]** ስ አንገቱ ረዥም፥ መልኩ ገብስማ የሆነና ብዙ ጊዜ እባብና ትላትል የሚመገብ የአሞራ አይነት::

**እባክህ** አንድ ነገር እንዲሆን፥ እንዲደረግ ለመጠየቅ ወይም ለመለመን ሲፈለግ ከሚጠየቀው ነገር ቀድሞ የሚነገር የልመና ማቅረቢያ ቃል:: *እባክህ ስራውን ቶሎ ቶሎ ጨርስልኝ::*

**እባጭ "አበጠ"** ስር ተመ.

**እብለት "አበለ"** ስር ተመ.

**እብሪት** ስ ጥጋብ፥ ትእቢት፥ ማን አለብኝነት::

**እብሪተኛ** ቅ ጥጋበኛ፥ ትእቢተኛ::

**እብቅ** ስ ከእህል ላይ ተለይቶ የሚወጣ የደቀቀ ገለባ፥ ንፉሽ::

**እብነበረድ** ስ በተፈለገው ቅርፅና መጠን እየተስተካከለ ለተለያየ አገልግሎት (ለቤት፥ለሃውልት፥ ... ግንባታ) የሚውል፥ የተለያየ መልክ ያለውና ዋጋው ከፍተኛ የሆነ የድንጋይ አይነት::

**እብደት "አበደ"** ስር ተመ.

**እብድ** ዝ.ከ.

**እብጠት "አበጠ"** ስር ተመ.

**እቦኛ** ቅ ክፉ፥ ጨካኝ፥ እቡይ::

**እቴቴ** ስ ታላቅ እህትን፥አክስትን፥...በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል::

**እቴጌ** ስ የንጉስ ሚስት የማእረግ ስም::

**እትማማች "እህት"** ስር "እህትማማች"ን ተመ.

**እትም "አተመ"** ስር ተመ.

**እትራት "አተረ"** ስር ተመ.

**እትብት "አተበ"** ስር ተመ.

**እትት**

**እትትት አለ** ግ ብርድ፡ ቆፈን የያዘው መሆኑን እትትት በማለት ገለፀ።

**እትዬ** ስ ዘመድ ወይም ቅርብ የሆነችን ሴት በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል፤ ማንኛዋንም ሴት ለመጥራት ያገለግላል።

**እቶን** ስ የእንጨት እሳት የሚነድበት ጎድጎድ ያለ ትልቅ ምድጃ።

**እችክ እችክ** ቀዝቃዛ ውሃ ወይም ብርድ የነካው ሰው የሚያሰማው የመሳቀቅ ድምፅ።

**እነ—** ከነጠላ ስም ጋር ተጣምሮ በመነገር ከነጠላው ስም ጋር ሊጎዳኝ የሚችለውን ስም ሁሉ አጠቃሎ ለመጥራት የሚያገለግል ምእላድ። *እነከበደ መጡ።*

**እነሆ** ይህው፥ ይህውና።

**እነርሱ (እነሱ)** በሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

**እነዚህ (እነኚህ፥ እኚህ)** በሁለተኛ መደብ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅፅል ወይም ተውላጠ ስም። (አመ.ቅ.) *እነዚህ መፃህፍት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ናቸው።* (አመ.ተ.ስ.) *የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ መፃህፍት እነዚህ ናቸው።*

**እነዚያ (እነኚያ፥ እኚያ)** በሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅፅል ወይም ተውላጠ ስም።

**እና** "-ና"ን ተመ.

**እናት** ስ 1.የወለደች ሴት ከወለደችው ጋር ባላት የተዛምዶ ግንኙነት የምትጠራበት ቃል፤ ወላጅ ። 2.ሴት ሞግዚት ወይም አሳዳጊ። 3.(ዘይ.) ደግ፥ ሩህሩህ።

**እናት አልባ** እናት የሌለው ወይም እናቱ የሞተችበት።

**እናት አገር** ስ የአንድ ሰው የትውልድ አገር።

**እናንተ** ተው.ስ. በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

**እኔ** ተው.ስ. በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

**የእኔ ብጤ** ደሃ፥ ለምኖ አዳሪ።

**እንሰሳ** "**እንስሳ**"ን ተመ.

**እንሰት** ስ ስሩ ቆጮ የሚባለውን ምግብ ለማዘጋጀት የሚያገለግል፥ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ የተክል አይነት፤ ኮባ።

**እንሰላል** ስ እንጨቱ ውስጠ ክፍት የሆነና ቅጠሉ አረቄ አረቄ (የፈረንጅ) የሚሸት የተክል አይነት።

**እንስራ** ስ ከሸክላ አፈር የሚሰራ የጠላ መጥመቂያ ወይም የውሃ መቅጃና ማስቀመጫ እቃ(ስእሉን "ሸክላ እቃ" ስር ተመ.)።

**እንስሳ (እንሰሳ)** ስ 1.ማንኛውም ህይወት ያለውና በራሱ ሃይል ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀስ ፍጥረት። 2.እንደ ላም፥ በግ፥ ድኩላ፥... ያለ የቤትና የዱር ፍጥረት። 3.(ስድብ፥ ዘይ.) ሞኝ፥ ጅል፥ ቂል፤ የዋህ ።

**የቤት እንስሳ** ስ በቤት ውስጥና በቤት አካባቢ የሚኖር፥ ለሰው ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጥ እንደ ዶሮ፥በግ፥ፈረስ፥...ያለ ማንኛውም እንሰሳ።

**የእንስሳት ሃኪም** ስ የቤት እንስሳትን በማከም ሙያ የሰለጠነ ሃኪም።

**የዱር እንስሳ[አውሬ]**ስ በዱር በጫካ የሚኖር እንደ አንበሳ፥ቀጭኔ፥ዝንጀሮ፥...ያለ ማንኛውም እንሰሳ።

**እንስት** ስ የተባእት ተቃራኒ፤ ሴት።

**አንስታይ** ቅ ሴቴ።

**እንሶስላ** ስ ሴቶች እጅና እግራቸውን የሚያቀሉበት የእፅዋት አይነት።

**እንሻፎ** ስ ብርድ ወይም ውርጭ የመታው እህል።

**እንሽላሊት (መንሽላሊት)** ስ ጅራቷና ጭንቅላቷ እባብ የሚመስልና አራት እግር ያላት ትንሽ አውሬ።



እንሽላሊት

**እንሽርት [ውሃ]** ስ ለመውለድ በምጥ ላይ ካለች የሴት ብልት የሚፈስ እንደ ውሃ ያለ ፈሳሽ ነገር፤ "**ሽንት ውሃ**"ም ይባላል።

**እንቀት** ስ 1.የስንዴ ወይም የገብስ ክክ፤ ቅንጬ። 2.የእህል እንቅጥቃጭ።

**እንቁ** ስ በጣም ውድ የሆነና ለጌጥነት የሚያገለግል በባህር ውስጥ የሚገኝ የከበረ ድንጋይ፤ ሉል።


**እንቁላል** ስ 1.በአብዛኛው ከአእዋፍ ወገን የሆኑ እንሰሳት የሚወልዱት፥ በስስና ጠንካራ ቅርፊት የተሸፈነ፥ ውስጡ በነጭ ፈሳሽ የተከበበ አስኳል ያለው እንክብል። 2.ፅንስ ሊሆን የሚችል ሴቴ ዘር።

**እንቁላል መስሏል** በጣም አምሮበታል።

**እንቁላል ጣለች** እንቁላል ወለደች (ዶሮ፥ ወፍ፥ ...)።

**የእንቁላል ውሃ** ስ በእንቁላል ውስጥ የሚገኝ ውሃ መሳይ ፈሳሽ ነገር፤ ዞፍ።

## የቤት እንስሳት






1.አውራ ዶሮ
2.ፈረስ
3.ውሻ
4.ላም
5.ዶሮ
6.በቅሎ
7.ድመት
8.በግ
9. አህያ
10.ፍየል
11.ግመል
12.በሬ

## የዱር እንስሳት





1.ዝሆን
2.አንበሳ
3.ነብር
4.ድብ
5.ካንጋሩ
6. ጥንቸል





1.ነጭ ዝንጀር
2.ጥርኝ
3.ጭላዳ
4.ኢንሹ
5.ጅብ

6.ጎሽ
7.ጦጣ
8.ፌቆ
9.የሜዳ ፍየል
10.ሳላ

11.ገረኑክ
12.አዋልድጌሳ
13.ፋደት
14ሌች.ዌ
15.ቶራ ፈረስ

16.አጋዘን
17.ሸለምጥማጥ




1.ጉሬዛ
2.ዋልያ
3.እቆስጣ
4.ድኩላ
5.ቀበሮ
6.ሽኮኮ
7.ሚዳቋ
8.ቀጭኔ
9.ዱልጋ አንበሳ
10.አነር
11. ሜዳ አህያ
12. አውራሪስ
13. ኒያላ
14. ወቦ ሸማኔ
15. ቆርኬ

**እንቁልጭልጮሽ (እንቁልልጮሽ)** ስ ልጆች አንድ ነገር ይዘው፥ ላይሰጡ እያሳዩና እያጓጉ የሚናገሩት የጨዋታ ቃል።

**እንቁራሪት** ስ ጅራት የሌላት፥ በውሃ ውስጥና በየብስ መኖር የምትችል፥ ጡብ ጡብ እያለች የምትሄድ ትንሽ አውሬ፤ ጓጉንቸር።



እንቁራሪት

**እንቁር** ስ ከጠፍር ወይም ከእንጨት የተበጀ እሩር፤ ጥንግ።

**እንቁርባ** ስ የአተር፥ የባቄላ፥ የሽንብራ፥... ፍሬ ልብስ፥ ገለባ፥ ገለፈት።

**እንቁሽቁሽ "ቆሽቆሽ"** ን ተመ.

**እንቁጣጣሽ** ስ 1.መስከረም አንድ ቀን የሚውል የዘመን መለወጫ በአል፤ ቅዱስ ዮሃንስ፤ የአዲስ አመት የመጀመሪያ ቀን። 2.በአዲስ አመት መጀመሪያ ቀን ልጆች ለወዳጅ፥ ለዘመድና ለጎረቤት እንደ ገፀበረከት የሚያቀርቡት እንግጫና አደይ አበባ፤ የአዲስ አመት የበጎ ምኞት መግለጫ ስጦታ።

**እንቁጥቁጥ "*ቆጠቆጠ²"** ስር ተመ.

**እንቃሪ "*ነቀረ"** ስር ተመ.

**እንቃቅላ¹** ስ አራስ ልጅ።

**እንቃቅላ²** ስ እንደ እንሽላሊት ያለ የገበሎ አይነት።

**እንቅልፋም "አንቀላፋ"** ስር ተመ.

**እንቅልፍ** ዝ.ከ.

**እንቅርት** ስ በሰው አንገት ላይ ብዙውን ጊዜ በፊት ለፊት በኩል በጉሮሮ ላይ የሚወጣ እባጭ መሰል በሽታ።

**እንቅርታም** ቅ እንቅርት ያለበት ሰው።

**እንቅሽ አለ "ነቀሸ"** ስር ተመ.

**እንቅሽ አደረገ** ዝ.ከ.

**እንቅብ** ስ አስር ቁና ያህል የሚይዝ ከአክርማ ወይም ከስንደዶ የሚሰራ ሰፊና ጎድጓዳ የስፌት እቃ (መጠኑ እንደየአካባቢው ይለያያል)(ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

**እንቅብ ሆድ** (ስድብ) ቦርጫም።

**እንቅጥቃጭ "ቀጠቀጠ"** ስር ተመ.

**እንቅፋት "*ነቀፈ"** ስር ተመ.

**እንቅፍድ "*ቀፈደደ"** ስር ተመ.

**እንቆቅልሽ** ስ ድፍን ያለና ምስጢር አዘል ነገር (ጭውውት) በጥያቄ መልክ የሚቀርብበት የስነ ቃል አይነት።

**እንቆቅልሽ ሆነ** ምስጢሩ አልታወቅ አለ፥ ድፍን ያለ ነገር ሆነ።

**እንቆቆ** ስ ፍሬው ለኮሶ መድሃኒት የሚሆን፥ አብዛኛውን ጊዜ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**እንቡር (እምቡር)**

**እንቡር አለ** ግ ዘለለ፥ እመር አለ።

**እንቡር እንቡር አለ** ግ ዘለለ፥ እንጣጥ እንጣጥ አለ።

**እንቡርጧይ** ስ **"በረበረ"** ስር ተመ.

**እንቡስ "እምቡስ"**ን ተመ.

**እንቡሽቡሽ [ጠላ]** ስ ቢጠጡት የማያሰክር ጉሽ ጠላ።

**እንቡቅቡቅ "*ቦቀቦቀ"** ስር ተመ.

**እንቡቡ**

**እንቡቡ አለ** ግ ልጅን በጀርባ ላይ በአንቀልባ ወይም በልብስ አዘለ ወይም ተሸከመ።

**እንቡጣ (እምቡጣ)** ስ ጥጃዋ ሲሞት ላሟ ወተት መስጠቷን እንዳታቋርጥ የጥጃውን ቆዳ ጭድ ወይም ሳር ሞልተው በላሟ ፊት የሚያቆሙት የጥጃ ምስል፤ ጎፍላ።

**እንቡጣጢያ (እምቡጣጢያ)** ስ ለጋ፥ ጨቅላ።

**እንቡጥ (እምቡጥ)** ስ 1.እንደ ባቄላ፥ አተር፥ ሽንብራ፥... ያሉ የአበባ እህሎች አበባቸው ከረገፈ በሂላ በአበባው ቦታ የሚተካው የፍሬ አያያዝ ጅምር፥ ውጥን። 2.እንደ ባቄላ፤ አተር፥ ... ያሉ የአበባ እህሎች በእሽትነታቸው ጊዜ ፍሬውን ሸፍኖ ወይም ጠቅልሎ የሚይዘው ገለፈት። 3.ለጋ ፥ ጮርቃ።

**እንቡጥ ያህላል** በጣም ትንሽ ነው።

**እንቡጥ ጣለ** ተክሉ አበባውን አራግፎ ፍሬ ማፍራት ጀመረ።

**እንቡጭቡጭ "*ቦጨቦጨ"** ስር ተመ.

**እንቡፍና (እምቡፍና) ጠላ** ስ ያልጠራና ያልፈላ ጉሽ ጠላ።

**እንቢ (እምቢ)** ተው.ግ. አይሆንም፥ አሻፈረኝ ወይም አላደርግም ለማለት የሚያገለግል ቃል ።

**እንቢዮ** ዝ.ከ.

**እንቢታ** ስ እሺ ወይም ይሁን አለማለት።

**እምቢተኛ** ቅ አልቀበልም፥ አላደርግም፥

አይሆንም ባይ።

**እንቢ አለ** ግ 1.አልቀበልም፥ አሻፈረኝ፥ አልታዘዝም፥ ... አለ። 2.አልሰራ፥ አልሆን አለ (እቃ፥ መሳሪያ፥...)።

**እንቢ ነገር** ስ የለሰለሰ ቁርበት እንደ ከረጢት ተሰፍቶ በውስጡ ገለባና ሳር ከተሞላበት በሂላ በአጋሰስና በአህያ ጀርባ ላይ ከጭነት በታች የሚውል የጀርባ መከላከያ፤ መደላድል።

**እንቢልታ (እምቢልታ)** ስ በአፍ የሚነፋ፥ ወፍራምና ቀጭን ድምፅ ማውጣት የሚችል፥ ከቀርከሃና ከብረት የሚሰራ እንደ ዋሽንት ያለ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**እንቢልታ ነፊ** ስ በእንቢልታ መጫወት የሚችል ሙዚቀኛ።

**እንቢልተኛ** ዝ.ከ.

**እንቢያጉስ** ስ በጭነት በቅሎ ወይም በፈረስ ደረት ላይ የሚውል ከቀደማይና ከቅናት ጋር የሚያያዝ የበቅሎ እቃ(ስእሉን "ኮርቻ" ስር ተመ.)።

**እንባ** "**እነባ**" ስር ተመ.

**እንብርቢጣ** ስ ብብት።

**እንብርት (እምብርት)** ስ 1.በሆድ መካከል የሚገኝ እትብት የሚቆረጥበት፥ ወደ ውስጥ ሰርጎድ ያለ ክብና ትንሽ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2.መሃል። *ቤቴ ከከተማው እንብርት ብዙም አይርቅ*።

**እንብርት የለሽ** በልቶ የማይጠግብ፤ ሆዳም።

**እንብርክክ (እንብርክ)** "***በረከከ**" ስር ተመ.

**እንብድብድ** "***በደበደ**" ስር ተመ.

**እንቦሳ (እምቦሳ)** ስ ከወተት በቀር ውሃ የማይጠጣና ሳር የማይበላ ያልጠነከረ ትንሽ ጥጃ።

**እንቦሳ እሰሩ** ወደ አዲስ ቤት ሲገባ "ቤት ለእንቦሳ" በማለት መልካም ምኞትን ለሚገልፅ እንግዳ በምላሹ የሚቀርብ የመልካም ምኞት መግለጫ።

**እንቦቀቅላ (እንቦቃቅላ)** ስ 1.አበባው ቅላት ያለው በወይናደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት። 2.ያልጠና፥ ለጋ (ልጅ፥ ቀንበጥ፥...)።

**እንቧ (እምቧ)**

**እንቧ አለ** ግ ጮሀ፥ ድምፅ አሰማ (በሬ፥ ላም)።

**እንቧይ (እምቧይ)** ስ ፍሬው ድቡልቡል የሆነና ሲበስል ሎሚ የሚመስል፥ እሾሃማና የማይበላ የእፅዋት አይነት፤ ፍሬውም እንቧይ ይባላል ።

**እንቧጮ (እምቧጮ)** ስ ቅጠሉ ለስላሳ፥ አገዳው ውስጠ ክፍት የሆነና ሲቀምሱት ጨው ጨው የሚል ጣእም ያለው የእፅዋት አይነት።

**እንተን** "**እንትና**"ን ተመ.

**እንትብትብ** "***ተበተበ**[2]" ስር ተመ.

**እንትና (እንተን፥ እንተኔ፥ እንቶኔ)** የአንድን ሰው ስም በረሱ ጊዜ ለስሙ ምትክ ወይም ልዋጭ ሆኖ የሚያገለግል ተውላጠ ስም። *እንትና መጣ።*

**እንትን** የአንድ ነገር ወይንም እቃ ስም በረሱ ጊዜ ለስሙ ምትክ ወይም ልዋጭ ሆኖ የሚያገለግል ተውላጠ ስም። *እንትን ስጠኝ*።

**እንትክትክ** "***ተከተከ**" ስር ተመ.

**እንትፍ**

**እንትፍታ** ስ የተተፋ ምራቅ፥ አክታ።

**እንትፍ አለ** ግ አክ አለ፥ ተፋ (ምራቅን፥ አክታን)።

**እንትፍ እንትፍ አለ** ግ ምራቅን በጥቂት በጥቂቱ በሚመረቀው ነገር ላይ በመትፋት ምርቃት ሰጠ፤ መረቀ።

**እንትፍትፍ አለ** ዝ.ከ.

**እንቶ** "**ኢንቶ**"ን ተመ.

**እንቶ ፈንቶ** የማይረባ፥ የማይጠቅም፥ ምናምን፥ ቅራቅንቦ ነገር።

**እንቶኔ** "**እንትና**"ን ተመ.

**እንችፍ** ስ የስንዴ ወይም የገብስ እንግውላይ፥ ግርድ።

**እንከን** ስ ጉድለት፥ ነውር፥ ፀያፍ፥ ሳንካ።

**እንከፍ (መንከፍ)** ቅ ቂል፥ ጅል፥ ሞኝ፥ ከርፋፋ።

**እንከፍ እንከፍ አለ** ግ ሲሄድ ጎፈፍ ጎፈፍ ዘርፈፍ ዘርፈፍ አለ።

**እንኩሮ** "**ነከረ**" ስር ተመ.

**እንኩቶ** "**ነኮተ**" ስር ተመ.

**እንኪያስ** ቃ.አ. ታዲያ፥ እንግዲያማ፥ እንግዲያውስ።

**እንካ** አንድን ነገር በእጅ ይዞ ለሌላው ለመስጠት ሲፈልግ ተቀበል፥ ውሰድ፥ያዝ ለማለት የሚያገለግል ቃል።

**እንካ ሰላንቲያ** ስ 1.በአብዛኛው እረኞች ልጆች በጥያቄ መልክ እየተጠያየቁ የሚጫወቱት የቀልድ ጨዋታ። 2.ጭቅጭቅ፥ንትርክ፥...፤የስድብ ልውውጥ።


**እንካ በእንካ** መጠቃቀም፥ ሰጥቶ መቀበል።

**እንካ አለ** ግ ለመስጠት እጁን ዘረጋ፥ ውሰድ አለ።

**እንክል**

**እንክል አለ** ግ አንከስ አለ፥ ሽመድ ሽመድ አለ።

**እንክርት (አንክርት)** ስ 1.ክበታ በታ ሊዘዋወር የሚችል ከሸክላ ወይም ከብረት የተሰራ ምድጃ። 2.የድርን አራባ ለማጠንጠን ወይም ለማድራት አራባው የሚወጠርበት መቃ፤ ዋግንበ።



እንክርት 1ኛ ፍቺ

**እንክርዳድ** ስ1.ከስንዴ ጋር አብሮ የሚበቅልና የፍሬው መጠን ከስንዴ የሚያንስ፥ ሲበሉት ወይም ጠላውን ሲጠጡት ራስ የሚያዞር ወይም የሚያሰክር የአረም አይነት። 2.(ዘይ.) መጥፎ፥ ተፈላጊነት የሌለው (ሰው)።

**እንክርፍ "*ከረፈፈ"** ስር ተመ.

**እንክብል "*ከበለለ"** ስር ተመ.

**እንክብካቤ "*ከበከበ[1]"** ስር ተመ.

**እንክብክብ[1]** ዝ.ክ.

**እንክብክብ[2] "*ከበከበ[2]"** ስር ተመ.

**እንክፍር "ከፈረረ"** ስር ተመ.

**እንኮኮ (እሽኮኮ)** ስ ልጅን ማጅራት ላይ በማስቀመጥ ሁለት እግሮቹ በሁለት ትከሻ በኩል ደረት ላይ እንዲንጠለጠሉ ተደርጎ የሚያዝበት የአሸካከም አይነት (አኮኮ ወይም ኮኮ ይባላል)።

**እንኮኮ (እሽኮኮ) አለ** ግ ልጅን ማጅራት ላይ በማስቀመጥና ሁለት እግሮቹ በደረት ላይ እንዲንጠለጠሉ በማድረግ ተሸከመ።

**እንኮይ** ስ በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል፥ ፍሬው እንደወይን ሆኖ ከፍ ከፍ የሚልና የሚበላ የእፅዋት አይነት።

**እንኳን** 1.በአንድ ድርጊት ላይ የመደሰትና የመስማማትን ሁኔታ ለመግለፅና ደግ፥ እሰይ፥ አሹ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *እንኳን አተረፈህ!* 2.አንዱን ከሌላው ለማነፃፀር የሚነገር ቃል። *እንኳን እሱ አንተም አታልፍ።*

**እንኳን ማርያም ማረችሽ** (ምር.) አራስ ሴትን እሰይ በደህና ወለድሽ፥ ተገላገልሽ ለማለት የሚነገር።

**እንዘረዘይ** ስ አበቃቀሉ እንደ ፌላ፥ ስሩ እንደ ሽንኩርት ያለና አበባው ቀይ የሆነ የእፅዋት አይነት።

**እንዘጥ (እንዘጭ)**

**እንዘጥ አለ** ግ ድንገት ወደቀ፥ እንበፍ አለ(ብዙውን ጊዜ በቂጥ)።

**እንዚራ** ስ 1.ማንኛውም የሙዚቃ መሳሪያ የሚጠራበት የጥቅል ስም። 2.በገና የሚመስልና የሚነዘር አውታር ያለው የሙዚቃ መሳሪያ።

**እንዛዝላ** ስ 1.ወይፈንን ለማቅናት ወይም ለመግራት ሲባል በጫንቃው እንዲጎትተው የሚደረግ ረዥም ግንድ፤ ጅንግላ። 2.ስድ፥ ባለጌ። 3.አልቃሻ።

**እንዝህላል (ንዝህላል)** ቅ 1.ግዴለሽ፥ ሃሳብ ቢስ። 2.ዝንጉ፥ ተላላ። 3.ስራ ፈት አውታታ።

**እንዝርት** ስ 1.እጀታው ከቀጭን ቀርከሃ ወይም ሽመል የሚሰራ፥ በራሱ ላይ ክብ የሆነ የቅል ስባሪ የተገጠመበትና ጫፉ ላይ የሚሰካ አነስተኛ ቆልማማ ሽቦ ያለበት የፈትል መሳሪያ። 2.ለስፌት መኪና በውስጥ በኩል የሚያስፈልገው ክር የሚጠነጠንበት የስፌት መኪና እቃ።




እንዝርት 1ኛ ፍቺ

**እንዝዝ[1]** ስ ጢንዚዛ።

**እንዝዝ[2]** ስ እበት እያድበለበለ የሚያንከባልል ከጥንዚዛ አነስ የሚል ነፍሳት።

**እንጉርባን (እንጁባን)** ስ ጣፋጭ ሽታ ያለው በሶብላ መሰል የእፅዋት አይነት።

**እንጅቦ (እንጆቦ፥ እንጆሞ)** ስ ሳይቀቀል ከእንጀራ ጋር የሚበላ ወተታም የእፅዋት አይነት።

**እንደ-** 1. ከ-በሂላ፥ወዲያው።*እንደመጣ ይምጣ።* 2.መሆኑን፥-መደረጉን፥- መፈፀሙን፥..። *እንደሞተ አውቃለሁ/እሱ እንደወሰደው ገብቶኛል።* 3. ለማድረግ፥ ለመፈፀም፥... መሞከሩን ለማሳየት የሚገባ ምእላድ። *እንደመተኛት አለ።* 4.የ-ያህል። *እንደአባት ያየዋል።* 5.ከ-ጋር ተመሳሳይ ነው፥-አይነት ነው፥...።*እንደ ወንድሙ ቀይ ነው/እንደ ሰማይ ይርቃል*፡6. ከመደብ፥ከፆታና ከቁጥር መቀያየር ጋር መጠነኛ የቅርፅ ለውጥ እያደረገ ይሆን፥ይፈፀም፥...ዘንድ ለማለት በግስ ላይ የሚቀጠል ምእላድ። *እንዲመጣ ንገረው/እንድንራብ አንፈልግም።*

**እንደሂሁላ (እንድሆህላ፥ እንዳሁላ)** ስ ቁመቱ በአማካይ እስከ አንድ ክንድ ሊረዝም የሚችል፥ ግንዱ አቅመቢስ የሆነ፥ በጣም ወፍራምና ለስላሳ ቅጠል ያለው፥ በወይና ደጋ የሚበቅል አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

**እንዱሽዱሽ "*ዶሸዶሸ"** ስር ተመ.

**እንዲያው** ተው.ግ. 1.ምንም ጥቅም ለሌለው፥ በባዶ፥ በከንቱ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *እንዲያው ነው የለፋሽው።* 2.በነፃ፥ በብላሽ። *ባለሱቁ ወረቀቱን እንዲያው ሰጠኝ።* 3.አረ። *እንዲያው ምን ይሻልሃል?*

**እንዲያውም** ተው.ግ. 1.በጭራሽ፥ ፈፅሞ።

*እንዲያውም መጥቶ ላያውቅም*። 2.አማራጭ ሃሳብ ለማቅረቢያነት የሚያገለግል ቃል። *እንዲያውም ነገ እንሄዳለን*፡

**እንዳለ** "አለ" ስር ተመ.

**እንዳለ** "አለ" ስር ተመ.

**እንዴ** የጥያቄን፥ የመገረምን ሃሳብ ለማስተሳለፍ ከሌሎች ቃላት ጋር በመጣመር ሃሳቡን፥ ጥያቄውን፥... ለማጉላት የሚያገለግል ቃል። *እንዴ! ከየት መጣህ? /ትሄዳለህ እንዴ?*

**እንዴታ** አዎ፥ ነው ለማለት እርግጠኛነትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *እንዴታ! መሄድ እፈልጋለሁ*።

**እንዴት** የአንድን ነገር ኣሰራር፥ ሁኔታ፥ አኳሏን ወይም ምክንያት ለማወቅ፥ እንዲሁም በሰላምታ አሰጣጥ ጊዜ የጤንነትን ሁኔታ ለመረዳት ጥያቄ የሚቀርብበት ቃል። *እንዴት ተሰራ? /እንዴት መጣህ? እንዴት ሳደርክ?*፡

**እንድርማሚት** ስ ትልቅ ቀንሙና ረዥም ምንቃር ያላት ዥንጉርጉር የወፍ አይነት(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

**እንዶድ** ስ ቀጥ ብሎ መቆም የማይችልና እንደ ሃረግ የሚሳብ፥ ፍሬው ለልብስ ማጠቢያ የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

**እንጀራ** ስ 1.የቦካ የጤፍ ወይም የስንዴ፥ የገብስ፥... ሊጥ ኣብሲት ከተጨመረበት በኋላ በሚፈለገው መጠን ቀጥኖ ምጣድ ላይ በሰፊውና በስሱ ክብ ሆኖ የሚጋገር (የሚሰፋ) ብዙ አይን ያለው ምግብ። 2.(ዘይ.) መተዳደሪያ፥ መኖሪያ።

**እንጀራ ነሳ** ኣደሀየ፥ ለችግር ዳረገ።

**እንጀራ ወጣለት** ሃብት አገኘ ወይም ባለፀጋ ሆነ።

**[የ]እንጀራ ልጅ** ስ ባል ወይም ሚስት ከውጭ ወይም ከሌላ ሰው የወለዱት ልጅ።

**እንጀራ ቤት** ስ 1.ቀደም ባለው ግዜ በነገስታትና መኳንንት ግቢ ውስጥ በተለይ እንጀራ የሚቀመጥበት ቤት ወይም የእንጀራ ቤት ሃላፊ። 2.በድግስ ወይም በግብዣ ጊዜ እንጀራ ለማቅረብ ወይም ለማደል የተመደበ አስተናጋጅ።

**[የ]እንጀራ አባት** ስ ሚስቱ ከሌላ ወንድ ለወለደችው ልጅ እንደሁለተኛ አባት የሚቆጠር ወንድ።

**[የ]እንጀራ እናት** ስ ባሏ ከሌላ ሴት ለወለደው ልጅ እንደሁለተኛ እናት የምትቆጠር ሴት።

**[የ]እንጀራ እናት ጡጦ** ስ ህፃናትን ለማባበል ኣፋቸው ላይ የሚደረግ ወተት መያዣ የሌለው ጡጦ።


የእንጀራ እናት ጡጦ

**እንጀራ ጋጋሪ** ስ ስራዋ እንጀራ መጋገር የሆነና በዚሁ የምትተዳደር ሴት።

**እንጆባን** "እንጉዳባን"ን ተመ.

**እንጂ** ብዙውን ጊዜ አፍራሽ ሃሳብን የሚያስከትል አነጋገር ምእላድ። *እሱ ጥቁር እንጂ ነጭ አይደለም/ይሞታል እንጂ ገንዘብ አይወጣውም/ መጣልህ እንጂ መች ቀረብህ*።

**እንጃ** ቃ.አ. ስለ ኣንድ ነገር አለማወቅን፥ ጥርጣሬን፥ እንቢታን ለመግለፅ የሚነገር ኣሉታዊ ቃል። *መምጣቱን እንጃ*።

**እንጅላት** ስ የምዝላት አባት ወይም እናት፤ 6ኛ ኣያት።

**እንጅልሽ** ስ እጅግ በጣም ብዙ፥ እያሌ፤ ከብዛቱ የተነሳ ስፍር ቁጥሩ የማይታወቅ የቁጥር መጠን።

**እንጆሪ** ስ 1.ግንዱ እንደ ሃረግ ያለ፥ ክብ ቅርፅ ያለውና ሲበስል ወይም በጣም ቀይ ሲሆን የሚበላ ፍሬ የሚያፈራ እሾሃማ የእፅዋት አይነት፤ ፍሬውም እንጆሪ ይባላል። 2. ቀጫጭንና ረዣዥም ቅርንጫፎች ያሉት፥ ሲበስሉ ቀያይ የሚሆኑና የሚበሉ ሞላላ ቅርፅ ያላቸው ትናንሽ ፍሬዎች የሚያፈራ የእፅዋት ኣይነት። ፍሬውም እንጆሪ ይባላል። 3.እንደቁጥቋጦ ሆኖ የሚበቅልና የሶስት ማእዘን ቅርፅ ያለው ሞላላ የሆነ ጣፋጭ ውሃ ያዘለ፥ ሲበስል በጣም የሚቀላና የሚበላ ፍሬ የሚያፈራ ተክል። የፈረንጅ እንጆሪም ይባላል።

**እንገር** ስ ላም፥ ፍየል፥... እንደወለደች የምትታለበው የመጀመሪያው ወፍራም ወተት።

**እንጉርጉሮ** "እንጎራጎረ" ስር ተመ.

**እንጉዳይ** ስ በክረምት የሚበቅልና ዣንጥላ የሚመስል ቅርፅ ያለው የእፅዋት አይነት።


እንጉዳይ

**እንግሊላ (እንግላል)** "*ጋለለ"ስር ተመ.

**እንግሊዝ** (ዘይ.) መሰሪ፥ ማሸንክ።

**እንግርግብ** "*ገረገበ" ስር ተመ.

**እንግት** "እነገተ" ስር ተመ.

**እንግውላይ** "ገወለለ" ስር ተመ.

**እንግዲህ (እንግዴህ)** መ. 1.ታዲያ፥ እንኪያ። *እንግዲህ ምን ይሻላል ሁሉም ነገር ሳልገባ ሳለ*። 2.እነሆ፥ ይህው። *ተመልከቱ! እንግዲህ በሽታው ተነሳበት*። 3.አሁን። *ምግብ*

*ተርጇል፤ እንግዲህ እንብላ*፡ 4.ካሁን በሂላ፥ ካሁን ጀምሮ፡፡ *እንግዲህ ወደየቤታችሁ ሂዱ*፡፡ 5.ዳግመኛ፥ ሌላ ጊዜ፡፡ *ደህና ሰንብቱ፤ እንግዲህ የምመጣ አይመስለኝም*፡

**እንግዲህማ** 1.አሁንማ፡፡ 2.ካሁን በሂላ፡፡

**እንግዲህም** 1.አሁንም፡፡ 2.ካሁን በሂላም፥ እንደገና፡፡

**እንግዲህስ** ለ 1.አሁንስ፡፡ 2.ካሁን በሂላ፡፡

**ከእንግዲህ [ወዲህ]** ካሁን ጀምሮ፥ ከዚህ በሂላ፡፡

**እንግዲያ (እንግዲያማ፥ እንግዲያስ፥ እንግዲያውስ)** 1-እንደዚያ ከሆነ፡፡ *እንግዲያ ወደቤቴ እሄዳለሁ*፡ 2-ታዲያ፡፡ *እንግዲያ ለምን ቶሎ ብለን አንጫወትም*፡

**እንግዳ** "*ነገደ" ስር ተመ.

**እንግዴ ልጅ** ለ በእርግዝና ወቅት ከሽል ጋር በማህፀን የሚፈጠር፥ ፅንሱ በእትብት አማካይነት እየተመገበ የሚዳብርበትና ህፃኑ ከተወለደ በሂላ የሚወጣ አካል፡፡

**እንግጫ (ግጫ)** ለ የዘመን መለወጫ ጊዜ ልጃገረዶች ከአበባ ጋር እየጎነጎኑ የመልካም ምኞት ስጦታ የሚያደርጉበት የሳር አይነት፡፡

**እንግፍጥ** "*ገፈጠጠ" ስር ተመ.

**እንጎቻ** "*ነጎተ" ስር ተመ.

**እንጎችት** ዝ.ከ.

**እንጣቆ (አንጣቆ)** ለ በአገዳ እህል ቡቃያና በጎመን ላይ የሚገኝ መርዛማ ትል፡፡

**እንጣጢት** ለ ተልባ፡፡

**እንጣጥ**

**እንጣጥ አለ** ግ 1.ድንገት ዘለለ፥ እመር አለ፡፡ 2.(ዘይ.) ከአቅም በላይ ተንጠራራ፡፡

**እንጥል** ለ በጉሮሮ ውስጥ ከላይኛው ጫፍ የተንጠለጠለችና ምላስ የምትመስል የሰውነት ክፍል፡፡(ስእሉን "አፍ" ስር ተመ.)

**እንጥል ወረደው** እንጥሉ አበጠ፥ ታመመ፡፡

**እንጥልጥል** "*ጠለጠለ" ስር ተመ.

**እንጥርጣሪ** "ጠረጠረ[2]" ስር ተመ.

**እንጥስታ** "*ነጠሰ" ስር ተመ.

**እንጥብጣቢ** "ነጠበ" ስር ተመ.

**እንጥፍጣፊ** "*ጠፈጠፈ" ስር ተመ.

**እንጦ[1] (ህንጦ)** ለ ገና አዲስ የተወለደ አራስ ልጅ፡፡

**እንጦ[2]** ለ 1.እንደቀስም ያለ ውስጠ ክፍት ነገር፡፡ 2.የሚያመነዥኩ እንስሳት ሁለተኛ ጉሮ ሮ+ የምንግቢ መተላለፊያ፡፡

**እንጦርጦስ** ለ መቀመቅ፥ ጥልቀቱ የማይታወቅ የጨለማ ጉድጓድ፡፡

**እንጨት** ለ 1.የዛፍ ወይም የተክል ጠንካራው አካል፡፡ 2.ከዛፍ ላይ ተቆርጦ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል የዛፍ ወይም የተክል ጠንካራው ክፍል፡፡

**እንጨት ሰበረ** ጫካ ሄዶ የማገዶ እንጨት ለቀመ ወይም ሰበሰበ፡፡

**የእንጨት ሽበት** (ስድብ) ቅሌታም፥ ወራዳ (ምግባረ ብልሹ ለሆነ አዛውንት የሚነገር)፡፡

**እንጨት ፈላጭ** ለ እንጨት በመፍለጥ ስራ የሚተዳደር ሰው፡፡

**እንጫጮላ** ቅ እምቦቃቅላ፥ ለጋ፥ ያልጠና፡፡

**እንጭብሬ** "*ጨበረረ" ስር ተመ.

**እንጭብር** ለ ቅጠለ ሻካራ የሆነ አነስተኛ የሃረግ አይነት፡፡

**እንጭጭ** ቅ ለጋ፥ ጮርቃ፡፡

**እንፊፍ** ቅ ጅላጅል፥ ሞኝ፥ ቂል፡፡

**እንፉቅቅ** "ፉቀቀ[1]" ስር ተመ.

**እንፉጭ** ለ 1.ውርጭ የመታውና ፍሬው የተጨራመተ እህል፡፡ ቅ 2.(ዘይ.) ጅል፥ ሞኝ (ሰው)፡፡

**እንፋሎት** ለ ከፈላ ውሃ ወይም እርጥበት ካለው መሬት ላይ በፀሃይ ሙቀት ምክንያት የሚነሳ ጭስ፤ ተን፡፡

**እንፍሌ** ለ 1.የተቀቀለ ስጋ፡፡ 2.ከነእንቡጡ የተቀቀለ የባቄላ ወይም የአተር እሸት፡፡

**እኚያ** "እነዚያ"ን ተመ.

**እኛ** በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም፡፡

**እኛን ምሰል** እኛ የምናደርገውን አድርግ ለማለት የሚነገር፡፡

**እኝ[1]** ለ ወንፊል፡፡

**እኝ[2]**

**እኝ አለ** ግ ጥርሱን አገጠጠ፥ ከንፈሩን ገልጦ ጥርሱንና ድዱን አሳየ፡፡

**እኝህ** "እነዚህ"ን ተመ.

**እኝኝ**

**እኝኝ አለ** ግ 1.ዝናቡ ያለማቋረጥ ለረዥም ጊዜ ዘነበ፡፡ 2.ተነዛነዘ፥ ተጨቃጨቀ፡፡

**እኝኝ ብላ** ለ ከነሃሴ 28-30 ድረስ አፍኖና ካፊያ ሆኖ የሚሰነብትበት ሰሞን፡፡

**እኝያ** "እኚያ" ን ተመ.

**እከሌ** "እገሌ"ን ተመ.

**እከካም** "አከከ" ስር ተመ.

**እከክ** ዝ.ከ.

**እከየኛ** ቅ እኩይ፥ ትእቢተኛ።

**እከደከ (እከድእከድዬ፥ እከድዬ)** መደነቅን፥ መገረምን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *እከደከ! ምነው ጉድ ሰራህኝ?*

**እኩሌታ "አከለ"** ስር ተመ.

**እኩል** ዝ.ከ.

**እኩያ** ዝ.ከ.

**እክል** ስ 1.ድንገተኛ ችግር። 2.ሃዘን፥ ለቅሶ።

**እክር "አከረ[1]"** ስር ተመ.

**እክታም "አከተ"** ስር ተመ.

**እክት** ዝ.ከ.

**እኮ (እኮን)** ተው.ግ. 1.ከተለያዩ ቃላት ጋር በመጎዳኘት የሚነገር አጎላማሽ ምእላድ።*እኮ ስጠኝ /ከበደ እኮ ጎበዝ ነው።* 2.እንጂ። *ተው እኮ።* 3.ነውና፥ ነው እንጂ። *እንደነገርከኝ እቃው እወነትም ጥሩ ነው። እኮ!*

**እውር "አወረ"** ስር ተመ.

**እውቀት "አወቀ"** ስር ተመ.

**እውቂያ** ዝ.ከ.

**እውቅ** ዝ.ከ.

**እውን** እውነት፥ እርግጥ።

**እውነታ** ስ 1.ሃቅ፥ እርግጥ፥ ትክክል። 2.በተጨባጭ ያለው ነገር ወይም ሁኔታ።

**እውነት** ዝ.ከ.

**እውነተኛ** ቅ 1.ሃቀኛ፥ የማይዋሽ። 2.ትክክለኛ፥ የሃሰት ያልሆነ። *እውነተኛ የብር ኖት።*

**እውከተኛ "አወከ"** ስር ተመ.

**እዚህ** ቅ ቅርብ ወይም አጠገብ የሆነ ቦታን ወይም ተናጋሪው ያለበትን ስፍራ ለማመልከት የሚያገለግል ቃል። *እዚህ አገር ከገባሁ አስር አመት ሆነኝ/ ቤቱ ሩቅ አይደለም፥ እዚህ ጋ ነው።*

**ለዚህ ለዚህ** ለውጥ ለሌለው፥ ለማያረካ። *በጣም ውድ ነው ለዚህ ለዚህ ፒያሳ መግዛት ይሻላል።*

**እዚሁ ለዚህ** ቅርብ።*ቤታችን እዚሁ ለዚህ ሆኖ ብዙ አንገናኝም።*

**እዚሁ በዚሁ** አሁን በአሁን፥ በአንድ አፍታ።*እዚሁ በዚሁ ብሬን ሰረቁኝ።*

**እዚያና እዚያ** ሩቅ ለሩቅ።

**ያለዚያ(ያለዛ)** የተባለው፥የተነገረው ካልሆነ።

**በዚህ** 1. የቅርብ አቅጣጫን ወይም ቀደም ሲል የተጠቀሰን ወይም የታወቀን ጉዳይ የሚያመለክት ቃል። *በዚህ በኩል እለፍ። በዚህ ምክንያት /በዚህ መሰረት/በዚህ ሁኔታ/እዚህ ነገር ውስጥ አታስገቡኝ...።*2.አንድን፥ተግባር፥ድርጊት፥ ...ለመፈፀሚያ የሚያገለግል እቃን፥ነገርን፥... የሚያመለክት ተውሳጠስም። *በዚህ ገመድ እሰረው።*

**በዚህ ላይ** በተጨማሪ።

**በዚህም በዚያም** 1.በሁሉም በኩል፥ በሁሉም አቅጣጫ። 2.በማንኛውም አይነት፥ ምክንያት፥ ሁኔታ።

**ከዚህ** አሁን ካለንበት ቦታ፥ ሁኔታ፥ ነገር፥ ጊዜ፥... ለማለት የሚያገለግል ቃል።

**ከዚህ ሌላ** 1.ሌላ። 2.በተጨማሪ።

**ከዚህ ቀደም** ባለፈው ጊዜ፥ አሁን ካለንበት ጊዜ በፊት።

**ከዚህ በኋላ** አሁን ካለበት ቦታ፥ ሁኔታ፥ ነገር፥... ቀጥሎ።

**ከዚህ ውጭ** ከተባለው ወይም ከተጠቀሰው ሌላ።

**ከዚህም በላይ** በተጨማሪ።

**እዚያ** ሩቅ ቦታን ወይም አቅጣጫን ወይምአንድ የታወቀ ሁኔታን፥ጉዳይን፥... ለማመልከት የሚያገለግል ቃል። *እዚያ ብትጠይቅ ታገኘዋለህ/ እዚያ ጉዳይ ውስጥ አንገባ።*

**በዚያ** ሩቅ ቦታን ወይም አቅጣጫን ወይም የታወቀ ጉዳይን፥ ሁኔታን፥ጊዜን፥ ... አመልካች ቃል። *በዚያ ሂድ/ በዚያ ዘመን/በዚያ ጭቅጭቅ።*

**እዚያ ላይ ወጣ** 1.(ለዋጋ) ተወደደ። 2.ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነ፥ ደረሰ።

**በዚያ በዚህ ብሎ** እንደምንም።

**ከዚያ** 1.ከአንድ ነገር፥ ሁኔታ፥ ቦታ፥... ቀጥሎ። *ምሳ እንብላና ከዚያ ወደ ት/ቤት እንሄዳለን/በመጀመሪያ አዲስ አበባ ሄደን ከዚያ ናዝሬት እንሄዳለን።* 2.ወዲያ፥ እዚያ። *ከዚያ ማዶ ከሚታየው ቤት ውስጥ ነው የሚኖረው።*

**ከዚያ በኋላ** ከአንድ ነገር፥ ሁኔታ፥ ቦታ፥... ቀጥሎ።

**ከዚያ በላይ** በተጨማሪ።

**እዝ "አዘዘ"** ስር ተመ.

**እዝል[1]** ስ ከሶስቱ ያሬዳዊ የዜማ አይነቶች አንዱ።

**እዝል[2] "አዘለ"** ስር ተመ.

**እዝን "አዘነ"** ስር ተመ.

**እየ—[1]** ከግስ ጋር በመጣመር አንድ ድርጊት በመካሄድ ላይ መሆኑን የሚገልፅ እስር ምእላድ። *እየገባ ነው።*

**እየ—[2]**

**እያንዳንዱ "አንድ"** ስር ተመ.

**እዬዬ**

**እዬዬ አለ** አለቀሰ፥ አነባ።

**እይታ** ስ 1.አስተያየት፥ አመለካከት። 2.ገፅታ።

**እደላ** "አደለ" ስር ተመ.

**እዳ** ስ 1.ብድርን፥ ቅጣትን፥ ካሳን፥… የሚመለከት ክፍያ። 2.(ዘይ.) ችግር፥ ስቃይ። *እዳዬን አየሁ።*

**ምን እዳዬ/ተዳዬ** ምን ቸገረኝ፥ ምን እዳ አለብኝ፥ እኔን ምን አገባኝ።

**በእዳ ተነከረ** እዳ ውስጥ ገባ፥ ባለእዳ ሆነ።

**በእዳ ያዘ** እዳ ያለበትን ሰው ወይም ንብረቱን በመያዝ እዳውን እንዲከፍል ጠየቀ፥ አስገደደ።

**እዳ በእዳ ሆነ** እዳ በዛበት ወይም እዳ ተጨማመረበት።

**እዳ ከሜዳ** ያልታሰበ ያልተጠበቀና ይመለከተኛል የማይሉት ችግር ወይም እዳ።

**እዳ ሰርጉ** እዳ የማይከብደው ወይም የማያስጨንቀው።

**እዳሪ** ስ 1.ከዚህ በፊት ታርሶ የማያውቅ ወይም በርከት ላሉ አመታት ሳይታረስ የቆየ መሬት። 2.ሰገራ፥ ኩስ። 3. ከቤት፥ ከግቢ ውጪ፤ ሜዳ፤ ደጅ።

**እዳሪ ወጣ** ተፀዳዳ።

**እዳሪ አወጣ** ለእርሻ ስራ ውሉ የማያውቀውን ወይም ረዘም ላሉ አመታት ሳይታረስ የቆየውን መሬት አረሰ፥ አለማ።

**እዳሪ መሬት** የ"እዳሪ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**እዳይት (እድያት)** ስ በነጠላ፥ በጋቢ፥ በቀሚስ፥… ጠርዝ ወይም ከፈፍ ላይ ለጌጥ የሚሰራ የተለያየ ቀለም ያለው ጥለት።

**እድለኛ** "አደለ" ስር ተመ

**እድላም** ዝ.ከ.

**እድል** ዝ.ከ.

**እድመኛ** "አደመ[2]" ስር "እድምተኛ"ን ተመ.

**እድሜ** ስ ከተወለዱበት እለት ጀምሮ ያለ ዘመን ወይም ጊዜ።

**በእድሜ ገፋ** አረጀ፥ ሸመገለ።

**እድሜ አገኘ** ብዙ ዘመን ኖረ፥ ቆየ።

**እድሜ የለውም** ብዙ አይቆይም፥ ቶሎ ያልቃል፤ ይሞታል።

**እድሜው በሰለ** ነፍስ አወቀ፤ አደገ።

**እድሜው አጠረ** ያለጊዜው ቶሎ ሞተ፤ ተሰበረ (ለሰው፥ ለእቃ፥…)።

**እድሜ ልክ** 1.እስከ እለተ ሞት። 2.ሁልጊዜ።

**እድሜ ይፍታህ** ስ እስከ እለተ ሞት ድረስ በእስር የሚያቆይ ፍርድ።

**እድምተኛ** "አደመ[2]" ስር ተመ.

**እድሞ** ስ 1.የካብ ወይም የግምብ አጥር። 2.በአጥር በር ላይ የተሰራ ቤት። 3.ለአጥር በር የተሰራ ጣሪያ።

**እድር** ስ 1.የአንድ አካባቢ ሰዎች ችግራቸውን በህብረት ለመወጣት የሚያቋቁሙት የመረዳጃ ማህበር (በአብዛኛው ለሞት ጊዜ)። 2.ልማድ። 3.ማህበር፥ ቡድን።

**እድር ለፋፊ** ስ ለቅሶ ባለ ጊዜ እድርተኞች እንዲሰበሰቡ ጥሩንባ በመንፋት እየዞረ የሚናገር ሰው።

**እድርተኛ** ስ የእድር አባል።

**እድሳት** "አደሰ" ስር ተመ.

**እድያት** "እዳይት"ን ተመ.

**እድገት** "አደገ" ስር ተመ.

**እድፋም** "አደፈ" ስር ተመ.

**እድፍ** ዝ.ከ.

**እጀታ** "እጅ" ስር ተመ.

**እጀኛ** ዝ.ከ.

**እጅ** ስ 1.ከትከሻ እስከ እጅ ጣት ድረስ ያለው የሰውነት ክፍል። 2.ከእጅ መዳፍ እስከ ጣት ድረስ ያለው አካል። 3.ከአንድ ሙሉ ነገር ውስጥ የተወሰነው ክፍል። *ሃብቴን ሁለት ቦታ ከፍላችሁ ላንዱን እጅ ለድሆች ስጡልኝ።*




እጅ 2ኛ ፍቺ

**እጁ ሰባራ አደረገ** ጥራት የሌለው ወይም ሰሪውን የማያስመሰግን ሆነ (የተሰራው ስራ)።

**እጁ ረጠበ** ገንዘብ አገኘ።

**እጁ እርጥብ** ቅ ገንዘብ የማያጣ።

**እጁ ቀዳዳ ነው** ገንዘብ አይበረክትለትም።

**እጁ አመድ አፋሽ ነው** ውለታው አይቆጠርለትም፥ አይመሰገንም።

**እጁ አቆመ** መስጠቱን ተወ፥ አቋረጠ (ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር)።

**እጁ አጠረ** 1. ገንዘብ አጣ፥ ተቸገረ።

ገንዘብ አነሰው (አንድ ነገር ለማከናወን)::

**እጀ አጭር** ቅ ድሃ፥ ችግረኛ::

**እጁ ወርቅ ነው** ጥሩ የእጅ ሞያ አለው::

**እጁ ጣለው** ውለታ ለዋለለት ወይም ጥሩ ስራ ለሰራለት ሰው መጥፎ በመስራቱ መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት አጋጠመው::

**እጁን ሰበሰበ** መጥፎ ነገር ከመስራት ተቆጠበ፥ አደብ ገዛ::

**እጁን በእጁ ቆረጠ** በገዛ ወገኑ ላይ ጉዳት አደረሰ::

**እጁን በደም ነከረ** በግፍ የሰው ህይወት አጠፋ::

**እጁን አነሳ** 1.ተወ፥ ለቀቀ:: 2.ተሸነፈ፥ የመሸነፍ ምልክት አሳየ::

**እጁን አወጣ** 1.ራሱን ቻለ:: 2.አመለጠ (ከችግር)::

**እጁን ከብብቱ አገባ** ሰነፈ፥ ያለ ስራ ተቀመጠ::

**እጁን ዘረጋ** ሰጠ፥ ቸረ፥ ለገሰ::

**እጁን ጫነበት** ያዘው፥ ለመውሰድ ወይም የግሉ ለማድረግ ፈለገው::

**እጅ መታ** የሌላን ሰው የውስጥ እጅ በመምታት ማለ::

**እጅ ሰጠ** 1.ተማረከ፥ በቁጥጥር ስር ዋለ:: 2.ተሸነፈ፥ ተጸከመ (በበሽታ፥ በችግር፥...)::

**እጅ በዛበት** ወሳጁ ወይም ተካፋዩ በዛ፤ በብዙ ሰው ተነካካ::

**እጅ ተጣፋ** ተማማለ::

**እጅ ነሳ** ሰላምታ አቀረበ::

**እጅ አስነሳ** 1.የአክብሮት ሰላምታ ተቀበለ:: 2.ከባለስልጣን ዘንድ ቀርበው እጅ እንዲነሱ ወይም ሰላምታ እንዲሰጡ አደረገ:: 3.ሰዎች እሱን እንዲለማመጡት ወይም እንዲያከብሩት አደረገ::

**እጅ አስገባ** 1.ተባበረ፥ ተሳተፈ:: 2.ያዘ፥ ወሰደ::

**እጅ አላስገባም አለ** ለማረም ወይም ለማጨድ አስቸገረ (አረም)::

**እጅ አዛወረ** አንድን ይዞታ ከአንዱ ወደ ሌላው አስተላለፈ::

**እጅ አደረገ** ያዘ፥ ወሰደ፥ ተረከበ::

**እጅ እጅ አለ** 1.ጣእሙ ተበላሸ (ምግብ):: 2.ሰለቸ፥ አስጠላ (ነገር)::

**እጅህን አውሰኝ** ስለእኔ ሆነህ ምታልኝ፥ በልልኝ::

**እጅ ያስቆረጥማል** በጣም ይጣፍጣል::

**የእጁን ሰጠው** እንደ መጥፎ ስራው መጥፎ ነገር አጋጠመው::

**የእጅ አመል አለበት** ሌባ ነው፤ የመስረቅ ልምድ አለበት::

**በእጁ ሄደ** ጉቦ ሰጠ::

**በእጅ አለ** ዝ.ከ.

**በእጅ አደር** በእጅ ያለ፥ የተያዘ::

**በእጁ አደሪ** ቅ ባለው የእጅ ሙያ (እውቀት) እየሰራ የሚተዳደር::

**እጅ በእጅ** ተው.ግ. 1.በአንድነት፥ በህብረት፥ በመረዳዳት(ለስራ):: 2.ከፍያው ወዲያውኑ የሚፈፀምና ዱቤ ያልሆነ::

**እጅ ከፍንጅ** ተው.ግ. አንድን ወንጀለኛ ወንጀል በመፈፀም ላይ እንዳለ የመያዝ ሁኔታ::

**እጀ መርዝ** ቅ የመታው ወይም ያቆሰለው ቶሎ የማይድን::

**እጀ መናኛ** ቅ የሰው ንብረት የሚወስድ::

**በእጀ መናኛ** በጉቦ ወይም በእጅ አዙርና በገንዘብ የሚፈፀም (ህገ ወጥ ድርጊት)::

**እጀ ሙሉ** ቅ 1. ቸር፥ ለጋስ:: 2.ባለረጅም እጅጌ (ለልብስ)::

**እጀ ሰብ (እጀ ሰብእ)** ስ መተት፥ ድግምት፥ ስራይ::

**እጀ ሰፊ** ቅ ቸር፥ ለጋስ::

**እጀ ብልህ** ቅ ጥበበኛ፥ የእጅ ስራ አዋቂ::

**እጀ ደረቅ** ቅ የቆረጠው ተክል መልሶ የማያቆጠቁጥለት ወይም የሚደርቅበት::

**እጀ ጠባብ** ስ እጅጌው ጠባብና ረጅም፥ ቁመቱ ከጉልበት በታች የሚወርድ፥ ከጎንና ከጎኑ ከላይ እስከታች ድረስ ስንጥቃት ወይም ክፍተት ያለው ልብስ።

[የ]**እጀ ጠብቅ ዋስ** ስ እገሌ ለህይወቱ ያስጋኛል ብሎ ለዳኛ ያመለከተ ሰው ባላጋራው ለአመልካቹ የሚጠራለት ዋስ::

**እጅ መንሻ** ስ አንድ ነገር እንዲደረግለት የፈለገ ሰው ለባለስልጣን የሚሰጠው ስጦታ ወይም ገፀበረከት::

**እጅ ማሟሻ** ስ በጾግም ትንሳኤ ማግስት የሚውለው ቀን (ሰኞ) የሚጠራበት ስም (ስራ የሚጀመርበት ቀን)::

**እጅ አዙር** ስ አንድን ድርጊት በስውር በሌላ ሰው እንዲፈፀም ማድረግ::

**እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ** ስ አንድን አገር በፖለቲካ ስልጣን በኩል ነፃ አድርጎ በኢኮኖሚው በኩል ጥገኛ የሚያደርግ የቀድሞ ቅኝ ገዢዎች አዲሱ የብዝበዛ ፖሊሲ::

**እጅ ጥበብ** የእጅ ሙያ+ እውቀት::

**የእጅ መብራት** ስ ባትሪ::

**የእጅ ሙያ** ስ እንደ ጥልፍ+ሸክላ ስራ+ አናጢነት+... ያለ በእጅ የሚሰራ ስራ ችሎታ+ እውቀት::

**የእጅ ስራ** ስ 1.የእጅ ጥበብን የሚጠይቅ እንደ ስፌት+ ሸክላ+ ጥልፍ+... ያለ ስራ:: 2.በጨርቅና በክር የሚሰሩ እንደ ጥልፍ+ ዳንቴል የመሳሰሉ ስራዎች::

**የእጅ ሰአት** ስ አምባር መዋያ ላይ የሚታሰር ሰአት::

**የእጅ ሹራብ** ስ 1. ከጥጥ ወይም ከሱፍ የሚሰራ የእጅ መሸፈኛ፤ ጓንት:: 2.በፋብሪካ ሳይሆን ሰዎች በቤት ውስጥ በእጃቸው የሚሰሩት ሹራብ::

**የእጅ ባትሪ** "ባትሪ[2]" ን ተመ.

**የእጅ ቦምብ** ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በእጅ የሚወረወር ቦምብ::

**የእጅ ኳስ** ስ ኳስን በእጅ በመቀባበልና በመሬት ላይ በማንጠር ብቻ ግብ ለማግባት የሚደረግ የውድድር ስፖርት::

**የእጅ ውሃ** ስ ለእጅ መታጠቢያ የሚቀርብ ውሃ::

**የእጅ ፅሁፍ** ስ በፅህፈት መሳሪያ (በቀለም+ በብእር+...) አማካይነት በእጅ የተዘጋጀ ፅሁፍ::

**እጀታ** ስ የመጥረቢያ+ የጎራዴ+... መያዣ::

**እጀኛ** ቅ ሌባ+ ቀማኛ+ ዘራፊ::

**እጅጌ** ስ በእጅ በኩል ያለና እጅ የሚገባበት የልብስ ክፍል::

**ባለእጅጌ** ቅ አጭር ወይም ረጅም እጅጌ ያለው፤ `ሿፖኒ ወይም እጀጌ ጉርድ ያልሆነ (ልብስ)::

**እጅጌ ሙሉ** ቅ ከትከሻ አንስቶ አምባር መዋያ ድረስ የሚጠለቅ እጅጌ ያለው(ልብስ)::

**እጅጌ ጉርድ** ቅ እጅጌው ከትከሻ እስከ ክርን አካባቢ ድረስ ብቻ የሆነ(ልብስ)::

**እጅሳት** "አጀለ" ስር ተመ.

**እጅጌ** "እጅ" ስር ተመ.

**እጅግ** ቅ 1.ብዙ፥ አያሌ:: 2.በጣም:: *እጅግ ትልቅ ነው::*

**እጅጉን** ተው.ግ. በጣሙን፥ በአያሌው (ለሰላምታ የሚነገር)::

**እጅግም ነው** ብዙም አይደለም፥ በጥቂቱ ነው::

**እገሌ (እከሌ)** ተው.ስ. ስሙ በተዘነጋ፥ ባልታወቀ ወይም ስሙን ለመጥራት ባልተፈለገ ሰው ስም ምትክ እየገባ የሚነገር::

**እገዛ** "አገዘ" ስር ተመ.

**እገዳ** "አገደ" ስር ተመ.

**እግል[1]** "አገለ[1]" ስር ተመ.

**እግል[2]** "አገለ[2]" ስር ተመ.

**እግር** ስ 1.ለመሄጃ + ለመራመጃ፥ ለመቆሚያ የሚያገለግል የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.):: 2.ከብረት+ ከእንጨት+... የሚሰራ የወንበር+ የአልጋ+... መቆሚያ::

**በእገሌ እግር** በእገሌ ምትክ፥ ቦታ::

**በእግር በፈረስ** በብዙ አቅጣጫ በመሄድና በመልፋት፤ በጉጉት+ በጥብቅ በፍለጋ :: *በእግር በፈረስ ስለምትፈለግ ቶሎ ድረስ::*

**እግሩን ዘረጋ** ሰነፈ+ ቦዘነ::

**እግሬ አውጪኝ አለ** ተፈተለከ፥ ሮጠ (ከአንድ ነገር ለማምለጥ)::

**እግር ሳሰ/ ሳመ** ተለማመጠ::

**እግር በእግር** ወዲያው እንደሄደ+ እንደወጣ+ ሳይቆይ+ ተከታትሎ::

**እግር አወጣ** ዘዋሪ ሆነ::

**እግር እስኪነቃ ቢኬድ** ቢዞር+ ቢለፋ::

**እግር ከወርች ታሰረ** ሁለት እግሩ ከአንድ እጁ ጋር ታሰረ::

**እግር ጣለው** ሳይታሰብ ድንገት ደረሰ::

**እግረ መልስ** ስ የኮበለለን ሰው ወይም የጠፋን ከብት ወደ ቤቱ እንዲመለስ ያደርጋል ተብሎ የሚታመንበት ድግምት ወይም መተት::

**እግረ መንገድ** ተው.ግ. በዚያው:: *እግረ መንገድህን ያንን እቃ ይዘህልኝ ና /እግረ መንገዴን አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎት::*

**እግረ ሙቅ** ስ እግር ብረት::

**እግረ ቀላል** ቅ ፈጣን+ ችኩል (ለአካሄድ)::

**እግረ እርጥብ** ቅ እድለኛ+ ገዳም::

**እግረ ደረቅ** ቅ በሄደበት ወይም በደረሰበት የማይቀናው+ እድለ ቢስ::

**እግረ ጭራሮ** ቅ በጣም ቀጭን እግር ያለው (ሰው)::

**እግረ ፀሃይ** ስ የፀሃይ ጨረር ወይም አውታር::

**እግር ብረት** ስ ጥፋት ያጠፋ ወይም ወንጀል የፈፀመ ሰው እግሩን የሚታሰርበት ብረት፤ እግረ ሙቅም ይባላል::

**እግር ተከል** ቅ መቆም የጀመረ (ህፃን ልጅ)::

**የእግር መንገድ** ስ 1. ለእግረኞች ብቻ የተፈቀደ መንገድ:: 2.መኪና የማይገባውና በእግር ብቻ የሚያስኬድ መንገድ::

**የእግር ኳስ** ስ አስራአንድ አስራ አንድ

ተጫዋቾች በያዙ ሁለት ቡድኖች መካከል ኳስን በእግር እየመቱና እየተቀባበሉ ወደ ተቃራኒ ቡድን ግብ (ጎል) ለማግባት የሚደረግ ጨዋታ፤ ኳሱም የእግር ኳስ ይባላል።

**የእግር ውሃ** ስ ለእግር መታጠቢያ የተዘጋጀ ውሃ።

**እግረኛ** ቅ 1.በመጓጓዣ አገልግሎት የማይጠቀም፥ በእግሩ የሚጓጓዝ። 2.ዘዋሪ፥ ከውካዋ።

**እግረኛ [ወታደር]** ስ የነፍስ ወከፍ መሳሪያ በመያዝ የምድር ላይ ውጊያ የሚያካሂድ ወታደራዊ ክፍል።

**እግረኛ [ጦር]** ዝ.ከ.

**እግት** "አገተ" ስር ተመ.

**እግዚአብሄር (እግዜር)** ስ አለማትን የፈጠረና የሚቆጣጠር፥ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፥ የሁሉ በላይ የሆነ አምላክ።

**እግዜር ይስጥልኝ** (ምር.) አንድ ነገር ለሰጠ ወይም ላደረገ ሰው የሚቀርብለት የምስጋና ቃል።

**እግዜር ይይለት** (እር.) እግዜር ይፍረድበት።

**የእግዚአብሄር ሰላምታ** ስ ሰዎች በሚገናኙበት ጊዜ እንደምን አደርክ፥ እንደምን ሰነበትክ፥ እግዚአብሄር ይመስገን፥... በማለት የሚለዋወጡት ሰላምታ።

**እግዚእ** ቃ.አ. 1.አቤቱ ጌታዬ ብሎ ለፈጣሪ የሚቀርብ የልመና ወይም የመማፀኛ ቃል። 2.አድናቆትን፥ መገረምን ለመግለፅ የሚነገር ቃል።

**እግዚኦታ** ስ ለፈጣሪ የሚቀርብ አቤቱታ፥ ፀሎተ ምህላ።

**እግዜር** "እግዚአብሄር"ን ተመ.

**እግድ** "አገደ" ስር ተመ.

**እጓለማውታ**(ብ.ቁ **እጓለማውታን**) ስ እናት አባት የሞቱበት ልጅ፤ ድሃ አደግ።

**እጢ**[1] ስ እንደ እበጥ ወይም እንደ ኳስ ድቡልቡል የሆነ ቅርፅ ይዞ በሰውነት ላይ የሚወጣ የህመም አይነት።

**እጢ**[2] ስ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ተግባራቸውን በጥሩ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የሚረዳ ፈሳሽን በማመንጨት ወደየክፍሎቹ በደም አማካኝነት የሚያስተላልፍ ውስጣዊ የሰውነት አካል።

**እጢው ዱብ አለ** ደነገጠ፥ ክው አለ።

**እጣ** ስ 1.እድል። 2.ድርሻ፥ ፈንታ። 3.ከአንድ በላይ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱን ከሌላው ለመምረጥ ሲያስቸግር ስምን በቁራጭ ወረቀት ፅፎ በመጠቅለል ወይም ቁርጥራጭ እንጨቶችን ለምርጫ በቀረቡት ነገሮች በመተካትና ከነዚህ መሃከል በመላ አንዱን በማንሳት ተመራጩን ለመለየት፥ ለመምረጥ የሚጠቀሙበት የምርጫ ዘዴ።

**እጣ አወጣ** ከተሰበሰቡት እጣዎች ወስጥ አንዱን አነሳ ወይም ባለእጣውን ለየ፥ አሳወቀ።

**እጣ ጣለ** 1.እጣዎች እንዲወጡ አደረገ። 2.እጣ አወጣ።

**እጣ ተጣለ /ወጣ/ወደቀ** በእጣ አንዱ ከሌላው ተለየ፥ ተመረጠ፤ የያንዳንዱ ድርሻ ተለይቶ ታወቀ።

**እጣቢ** "አጠበ" ስር ተመ.

**እጣን ሞገር** ስ በቅዳሴ መጨረሻ አካባቢ የሚባል የግእዝ ቅኔ አይነት።

**እጣን** "አጠነ" ስር ተመ.

**እጥረት** "አጠረ[1]" ስር ተመ.

**እጥብጣቢ** "አጠበ" ስር ተመ.

**እጥፋት** "አጠፈ" ስር ተመ.

**እጥፍ** ዝ.ከ.

**እጦተኛ** "አጣ" ስር ተመ.

**እጦት** ዝ.ከ.

**እጨጌ** ስ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ የማእረግ ስም።

**እጩ** "አጨ" ስር ተመ.

**እጭ** ስ ገና አዲስ የተፈለፈለና መንቀሳቀስ ያልጀመረ ንብ ወይም መሰል ነፍሳት።

**እጮኛ** "አጨ" ስር ተመ.

**እፁብ** ቅ አስገራሚ፥ አስደናቂ የሆነ።

**እፅ(ብ.ቁ. እፀዋት)** ስ በሳር፥ በቁጥቋጦ፥... መልክ የሚገኝ ማንኛውም ተክል።

**እፀ መሰውር** ስ አንድ ሰው እሱን ከያዘ ሰዎች ሊያዩት አይችሉም ተብሎ የሚታመንበት እፅ፤ መድሃኒት።

**እፀ ምናሄ** ስ ለተለያዩ በሽታዎች መድሃኒት ይሆናል የሚባልና በቆላ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**እፀ በለስ** ስ የ"በለስ"ን አንደኛ ፍቺ ተመ.

**እፀ ጳጦስ** ስ ረዣዥም ቅጠል ያለውና በደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**እፀፋርስ (እጠፋሪስ)** ስ የትምህርት አብነት ይሆናል በማለት የቆሎ ተማሪዎች የሚቀምሱት የእፅዋት አይነት።

**እፉኝት** ስ ትንፋሹ ሰውን፥ ከብትን፥... በማሳበጥ ጉዳት የሚያደርስ የእባብ አይነት።

**እፊያ** ስ የመሰብ፥ የድስት፥... መክደኛ።

**እፍ**

**እፍ አለ** ግ ሃይለኛ ግፊት ያለው ትንፋሽ በአፉ በኩል ተነፈሰ (እሳትን ለማንደድ ወይም ለማጥፋት፥ የሻማ ብርሃንን ለማጥፋት፥ አቧራን ወይም ጉድፉን ለማስወገድ፥ ...)።

**እፍ አሉ** በጣም ተዋደዱ፥ ተቀራረቡ፥ ተፋቀሩ።

**እፍ ያለ** 1.የወጣለት፥ የታወቀ (ሸርሙጣ)። 2.በጣም ስስ የሆነ (ለምሳሌ ጨርቅ)።

**እፍ ያለ ሜዳ** አባጣ ጎርባጣ ያልሆነ፥ ለጥ ያለ ሜዳ።

**እፍ እፍ አለ** በወረት ወደደ፥ አፈቀረ።

**እፍረት "አፈረ"** ስር ተመ.

**እፍንፍን "አፈነ[1]"** ስር ተመ.

**እፍኝ "አፈነ[2]"** ስር ተመ.

**እፍግ "አፈገ"** ስር ተመ.

**እፎይ**

**እፎይታ** ስ እረፍት፣ ከሃሳብ፥ ከድካም ግልግል።

**እፎይ አለ** ግ 1.አረፈ፣ ከድካም፥ ከሃሳብ ተገላገለ። 2-ተነፈሰ።

**ኦ የ"አ"** ፊደል ሳብእ ዘር።

**ኦሞ** ስ ለልብስ፥ ለእቃ፥... ማጠቢያ የሚያገለግል በዱቄት መልክ የተዘጋጀ ሳሙና (ስያሜው ለማንኛውምየዱቄት ሳሙና ቢያገለግልም "ኦሞ" የአንድ አምራች ድርጅት የንግድ ምልክት ነው።

**ኦሪት** ስ 1.በሙሴ የተፃፈ የእስራኤላውያን ወይም የእብራውያን ሃይማኖት ህግ። 2. በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝና ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም ያለው አምስቱ የሙሴ መፅሃፍት።

**ኦሪታዊ** ቅ 1.የኦሪት ወይም የኦሪት ጊዜ። 2.በአስተሳሰቡ ሂላ ቀር የሆነ።

**ኦርቶዶክስ** ስ ከኒቂያ ጉባኤ በሂላ በክርስቶስ አምላክነት እምነታቸውን ሳፀኑት ወገኖች የተሰጠ ተጨማሪ መጠሪያ።

**ኦርቶዶክስ ተዋህዶ** ስ ቃልና ስጋ በተዋህዶ አንድ አካል፥ አንድ ባህርይ፥ አንድ ልጅ፥ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ሆነ የሚል ትምህርተ ሃይማኖት።

**ኦርኬስትራ** ስ የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የሚጫወቱ ሰዎችንና ድምፃውያንን የያዘ የሙዚቃ ቡድን።

**ኦርጋን** ስ በጣት የሚነኩ ቁልፎችና በአየር ግፊት አማካይነት ድምፅ የሚሰጡ ብዙ ቧንቧዎች ያሉት የሙዚቃ መሳሪያ።

**ኦቶሞቢል "አውቶሞቢል"** ን ተመ.

**-ኦች (-ዎች)** ብዛትን አመልካች ምእላድ። (ለምሳሌ አንበሳ→አንበሶች/በሬ→በሬዎች)።

**ኦዞን** ስ የፀሃይ ጨረር በቀጥታ መሬት ላይ እንዳያርፍና ጉዳት እንዳያስከትል የሚከላከል፥ ምድርን ከሸፈናት ከባቢ አየር በላይ የሚገኝና ሃይለኛ ሽታ ያለው የኦክስጅን ንብርብር የሆነ ልባስ።

**ኦፊ ያሬድ** ስ ድምፀ መልካም ወፍ።

**ኦፔራ** ስ በሙዚቃና በዜማ በመታጀብ የሚቀርብ ድራማ።